## ተስፋ ዐቃብያነ ክርስትና ማኅበር

የሚከተሉትን መጻሕፍት ገዝተው እንዲያነቡ ያበረታታል

1. የይሖዋ ምስክሮችና አስተምህሮአቸው በቃለ እግዚአብሔር ሲመዘን—ከተስፋዬ ሮበሌ
2. የሥነ ምግባር መርሖ—ከተስፋዬ ሮበሌ
3. ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር—ርእሰ ጕዳዮችና ተግዳሮቶች —ከምኒልክ አስፋው
4. ዐበይት መናፍቃን—ከተስፋዬ ሮበሌ
5. ሰባልዮሳውያን:—“የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን” የሥላሴ አስተምህሮ በቃለ እግዚአብሔር ሲመዘን (ቅጽ 1)—ከተስፋዬ ሮበሌ
6. ውሃውና ስሙ:—“የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን” የድነት አስተምህሮ በቃለ እግዚአብሔር ሲመዘን (ቅጽ 2)—ከተስፋዬ ሮበሌ
7. ቅድስት ሥላሴ:—የአስተምህሮተ ሥላሴ መጽሐፍ ቅዱሳዊ፣ ታሪካዊና ሥነ አመክንዮአዊ ትንታኔ —ከአማረ መስፍንና ከተስፋዬ ሮበሌ
8. የዳ ቪንቺ ኮድ:—ድርሳነ ጠቢብ ወይስ ድርሳነ ባልቴት? —ከተስፋዬ ሮበሌ
9. በውኑ እግዚአብሔር አለን? ፍልስፍናዊ ጥናት —ከሪቻርድ ስዊንበርን (ፕሮፌሰር)
10. ይድረስ ለሐያስያን—በውኑ መጽሐፍ ቅዱስ እርስ በርስ ይቃረናልን?—ከተስፋዬ ሮበሌና ከአማረ መስፍን
11. የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያንና ትምህርተ ሥላሴ—ከተስፋዬ ሮበሌ
12. በቅዱሳት መጻሕፍት ዘገባ በርግጥ ኢየሱስ ክርስቶስ ማነው? — ከተስፋዬ ሮበሌ
13. የአስተምህሮተ ሥላሴ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት—ከተስፋዬ ሮበሌ
14. በእምነት መኖር—ከተስፋዬ ሮበሌ
15. እግዚአብሔርን በተመለከተ ልጆች የሚጠይቋቸው 101 ጥያቄዎች—ከተስፋዬ ሮበሌ
16. መጽሐፍ ቅዱስን በተመለከተ ልጆች የሚጠይቋቸው 102 ጥያቄዎች—ከተስፋዬ ሮበሌ
17. ትክክልና ስሕተትን በተመለከተ ልጆች የሚጠይቋቸው 103 ጥያቄዎች—ከተስፋዬ ሮበሌ

# የሺህ ዓመት ጕረቤታሞች

## ሙስሊሞችና ክርስቲያኖች

ዴቪድ ደብሊው ሼንክ

# የሺህ ዓመት ጐረቤታሞች

## ሙስሊሞችና ክርስቲያኖች

ዴቪድ ደብሊው ሼንክ

ተስፋ ዐቃብያነ ክርስትና ማኅበር
የመልእክት ሣጥን ቁጥር 23045፣ ኮድ 1000
አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

የሺህ ዓመት ጉረቤታሞች—ሙስሊሞችና ክርስቲያኖች
—ዴቪድ ደብሊው ሼንክ
ተርጓሚና አሳታሚ—ተስፋ ዐቃብያነ ክርስትና ማኀበር
መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው © 2000 ዓ.ም

ያለ አሳታሚው ፈቃድ አባዝቶ ማሳተምም ሆነ የተወሰነን ክፍል በተለያዩ መንገዶች ማራባት/ማባዛት በጥብቅ የተከለከለ ነው። በማንኛውም መልኩ መረጃ ለመውሰድ ከተፈለገ፣ በትክክል ሥርዐቱን ጠብቆ ሲጠቀስ፣ በግርጌ ማስታወሻ ሲመላከት ይገባዋል።

የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች የተወሰዱት የኢትዮጵያ የመጽሐፍ ቅዱስ ማኀበር በጁሊያን የዘመን አቈጣጠር በ1954 ዓ.ም ካሳተመው መጽሐፍ ቅዱስ ትርጒም እንዲሁም የኢንተርናሽናል የመጽሐፍ ቅዱስ ማኀበር በጁሊያን የዘመን አቈጣጠር በ1993 ዓ.ም ካሳተመው የአዲሱ መደበኛ ትርጒም ነው። የቁርአን ጥቅሶች የተወሰዱት፣ ሸኽ ሰይድ ሙሐመድ ሳዲቅና ሐጂ ሙሐመድ ሳኒ ሐቢብ ወደ አማርኛ ተርጒመውት ነጃሺ አሳታሚ ድርጅት በጁሊያን የዘመን አቈጣጠር 1961 ዓ.ም እንዲሁም ወርኀ ሚያዝያ 1997 ዓ.ም ካሳተመው የቁርአን ቅጅ ነው።

በእንግሊዝኛው ቅጅ ላይ የሌሉ አንዳንድ አስፈላጊ መረጃዎችን በግርጌ ማስታወሻ ላይ አቅርበናል። ልዩ መግለጫ ካልቀረበ በስተቀር፣ የተከተልነው የጎርጎርሳውያኑን የዘመን አቈጣጠር ነው።

መጽሐፉን ማግኘት የሚፈልጉ ከሆነ ወይም በርእሰ ጒዳዩ ላይ ጥያቄ፣
አስተያየትም ሆነ ሒስ ካልዎ በሚከተለው አድራሻ ይጻፉ:—
ተስፋ ዐቃብያነ ክርስትና ማኀበር
የመልእክት ሣጥን ቍጥር 23045፤ ኮድ 1000
አዲስ አበባ፤ ኢትዮጵያ

Journeys of the Muslim Nation and the Christian Church: Exploring the Mission of Two Communities
Author—David W. Shenk
Translator and Publisher —TESFA Evangelical Society For Apologetics
Copyright © 2007—TESFA Evangelical Society For Apologetics

All rights reserved. No part of this publication may be reproduced, stored in a retrieval system, or transmitted in any form or by any means-electronic, mechanical, photocopying, or other wise-without the prior written permission of the publisher and copyright owner.
If you need the book write us in our address. Comments, questions, corrections, and criticisms of this book are welcome. Please address all correspondence to the publisher on the following address:
***The Evangelical Society For Apologetics (TESFA)***
***Post Office Box 23045, Code 1000***
***Addis Ababa, Ethiopia.***
**E-mails:** <apologetics@ethionet.et>, <tesfa_apologetics@yahoo.com>

# Dedication

*In loving memory of our beloved*
*brother and co-labourer,*

Rev. Luke Paul Wilson

Who is away from the body
and at home with the Lord
(Corinthians 5:8)

# Acknowledgments

THERE ARE MANY WHO HAVE GIVEN BOTH THEIR encouragement and support to this work. We would especially like to thank the following persons and institutions, all of whom contributed to making this book not only possible but actual.

We wish to earnestly express our gratitude for to our friend and fellow worker the late Rev. Luke P. Wilson. He supported the idea to translate this material into the Amharic language and approached Dr. David Shenk and led him to our office. We would like to give thanks to the staff and board of the Institute for Religious Research, the organization which Rev. Wilson directed for their constant encouragement and generosity. We are grateful beyond words.

We would like to give special thanks to Dr. David W. Shenk, Tobias Messner and Waldemar Pritzkau for helping us in so many ways.

We are grateful to Professor Eleonore Stump, Mr. Paul Carden, and Dr. Brian Holt for sharing our passion for this ministry. We are also grateful to the translators, editors, pagemakers, and cover designers. We thank our members who critically read the book manuscript prior to publication.

It is our sincerest hope that this book will glorify God, and, instruct and edify the people of God. May God be pleased to use this book to those ends, and may He richly bless you as you read the fruits of our labour.


# ማውጫ


መቅድም 1

1. ምዕራፍ አንድ—የተለያዩ ጉዞዎች 15
2. ምዕራፍ ሁለት—ዐረባዊ ጅማሬ 41
3. ምዕራፍ ሦስት—በኤደን ገነት 57
4. ምዕራፍ አራት—የአብርሃም ልጆች—እስማኤልና ይስሐቅ 74
5. ምዕራፍ አምስት—መሪዎች—የነቢያት መደምደሚያና መሲሑ 91
6. ምዕራፍ ስድስት—ቅዱሳት መጻሕፍት—ቁርአንና መጽሐፍ ቅዱስ 115
7. ምዕራፍ ሰባት—መገለጥ—ታንዚልና ተሰግዎ 141
8. ምዕራፍ ስምንት—ኀይል—ሒጅራና መስቀል 163
9. ምዕራፍ ዘጠኝ—ቅድስቲቱ ከተማ—መዲናና ኢየሩሳሌም 181
10. ምዕራፍ ዐሥር—አሐዱ አምላክ—ተውሒድና ሥላሴ 203
11. ምዕራፍ ዐሥር አንድ—ሃይማኖታዊ ጉዞ—ሃጂና የጌታ ራት 223
12. ምዕራፍ ዐሥራ ሁለት—ሁለት መንገዶች—ሸሪዓና መንፈስ ቅዱስ 241
13. ምዕራፍ ዐሥራ ሦስት—ጸሎት—ሰላት—ኅብረት 263
14. ምዕራፍ ዐሥራ አራት—ምድራዊ ተልእኮ—ኡማና ቤተ ክርስቲያን 281
15. ምዕራፍ ዐሥራ አምስት—ማጠቃለያ ሐሳብ—303
16. ሙዳየ ቃላት—305

ዋቢ መጻሕፍት—ከአጫጭር ማብራሪያዎች ጋር 317

# መቅድም

ከሙስሊሙ ማኅበረሰብ ጋር ለመጀመሪያ ጊዜ የተዋወቅሁት ሶማሊያ በኖርሁባቸው ዓመታት ነው። አብዛኛው ሕዝቧ ግመል እያረባ በሚኖርባት በዚህች ሙስሊም አገር፣ ከጎርጎሮሳውያኑ የዘመን አቈጣጠር 1963 ዓ.ም ጀምሮ ለዐሥር ተከታታይ ዓመት ኖሬያለሁ። ወደዚህች አገር የላከንም፣ ምሥራቅ ሜኖናይት ሚስዮን ነበር። ወደ ሶማሊያ ከመሄዴ በፊት ዕድገቴ በታንጋኒካ (በታንዛኒያ) ሲሆን፣ ከዚያ በኋላ በአሜሪካን አገር ዐሥር ዓመት ተቀምጫለሁ።

ከባለቤቴ ግሬስና ከሁለቱ ሴት ልጆቼ (ከሁለት ዓመቷ ካረንና ከሁለት ወር ጨቅላ ሕፃኗ ዶሪስ) ጋር በመሆን፣ ሞቃዲሾ አውሮፕላን ማረፊያ ስንደርስ የሰማሁት ጩኸት፣ ከዚህ በፊት ከማውቀው ፍጹም የተለየ ነበር። ከዚያ በፊት በዚህ መልኩ የእግዚአብሔርን ስም የሚገልጹ ንግግሮች የሚሰሙት በአብዛኛው በአምልኮ ቦታዎች እንዲሁም ዐልፎ ዐልፎ፣ አያፍ በሆኑ ንግግሮች ውስጥ ነው።

ምንም እንኳ ሥራችንን የምንሠራው በሶማሊያ ሜኖናይት ሚስዮን የትምህርት ፕሮግራም ውስጥ ቢሆንም፣ በዐሥር ዓመት ቆይታችን ያስተዋልነው ነገር ቢኖር፣ የሶማሊያ ማኅበረሰብ የእግዚአብሔር ጒዳይ እጅግ ግድ እንደሚለው ነው። የሶማሊያውያኑ ሕይወት የተሞላው፣ ስለእግዚአብሔር መናገርና እግዚአብሔርን ማወቅ በሚሉት ርእስ ጒዳዮች ነው። እስልምና በሶማሊያውያን ሕይወትና ባህል ውስጥ ትልቅ ቦታ አለው።

የእምነትን ጒዳይ በተመለከተ ከሶማሊያውያን ጓደኞቼ ጋር በየሻይ መጠጫ ስፍራም ሆነ በየቤታችን ውስጥ፣ በርፍልና በኢል የተቀመመውን ሻያችንን ፉት እያልን ለረጅም ሰዓት እንወያያለን።

እንደ ጎርጎርሳውያኑ የዘመን አቈጣጠር 1973 ዓ.ም የማርክሳዊው አብዮት ከአገር ሲያስወጣን፣ መቀመጫችንን ያደረግነው፣ የሶማሊያ ደቡባዊ ጎረቤት አገር በሆነችው በኬንያ ነበር። በዚህ ጊዜ ከሙስሊሙ ማኅበረሰብ ርቀን መኖር ስላልፈለግን ነበር፣ መኖሪያችንን በናይሮቢ ምሥራቃዊ ክፍል ያደረግነው። ከምንኖርበት ቤት ፊት ለፊት ካለው መንገድ ባሻገር ቃድርያ ሱፊ የሚባል መስጊድ ነበር። በቤታችን ውስጥም ከሙስሊሞችና ቀኣልፍ ከሚባሉ የሃይማኖቱ

መሪዎች ጋር ውይይት እናካሂድ ነበር። በእንዲህ ዐይነቱ ውይይት ጊዜም፣ የቤታችንን ወንበሮች ሁሉ አውጥተን ምንጣፍ በማንጠፍ፣ ክብ ሠርተን ምንጣፉ ላይ በመቀመጥ ሻያችንን እየጠጣን ስለአምላክ፣ ስለእምነት፣ ስለእውነት፣ ስለቁርአን፣ ስለመሐመድ፣ ስለክርስቶስ እንዲሁም ስለድነት እንወያያለን።

በኬንያ ቆይታዬ፣ ሙስሊሞችና ክርስቲያኖች ሲገናኙ ለውይይት የሚያነሡአቸው የነገረ መለኮት ርእስ ጉዳዮች፣ ለነገረ መለኮት ያለኝን ፍላጎት አሳድጎታል። በሙስሊሙ ማኅበረሰብ መካከል በመኖር የምሰጠውን የፍቅር አገልግሎትና ምስክርነት በክርስቲያኖችና በሙስሊሞች መካከል ያለውን ልዩነት በመጠኑም ቢሆን ሊቀንሰው እንዲሁም ያለመተማመኑንም ሊያረግብ አልቻለም። "የሙስሊም ክርስቲያን ግንኙነት በአፍሪካ ፕሮጀክት" (Program for Christian-Muslim Relation in Africa [Procmura]) በመባል የሚታወቀው ድርጅት፣ በሙስሊሞች መካከል ከሌሉች መሰል ክርስቲያኖች ጋር በታማኝነትና በጥምረት እንድንሠራ መልካም የሆነን አጋጣሚ ፈጥሮልኛል። እኔም ከፕሮክሙራ (Procmura) ቡድን ጋር በመሆን ለሙስሊሞች ወንጌል ለሚመሠክሩና ውይይት ለሚያደርጉ አገልጋዮችና መሪዎች ሥልጠና እሰጣለሁ፤ በዐውደ ጥናቶችም ላይ አስተምራለሁ።

ከእኔ ጋር የሚሠራውም ቡድን እስላማዊ በሆነው ንጽርአተ ዓለም ውስጥ ሙስሊሞች ክርስቲያኖችን አስመልክቶ ያላቸውን የተሳሳተ ግንዛቤና ተቃውሞ ሊያስወግድ የሚችል፣ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናቶችን እናዘጋጃለን። የሚዘጋጀው የትምህርት ርእስ፣ "የእግዚአብሔር ሕዝብ" የሚባል ሲሆን፣ አርባ በሚሆኑ ቋንቋዎችም ይተረጐማሉ፤ በየዓመቱም በሺህ የሚቈጠሩ ሰዎች በዚህ ተከታታይ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ውስጥ ይካፈላሉ።

በድሩ ዲ. ቀትራጋ ከተባለው ሙስሊም ጓደኛዬ ጋር ለረጅም ጊዜያት ያካሄድነው ውይይት፣ ከሙስሊሞች ጋር የሚደረገውን ውይይት በተመለከተ ትልቅ ለውጥ አምጥቶአል። እኔና በድሩ በዩኒቨርስቲ ኦፍ ናይሮቢ እንዲሁም በኬንያታ ኮሌጅ ስለ ዓለም ሃይማኖቶች እናስተምር ነበር። ትምህርቱን በኅብረት በምናስተምርበትም ወቅት፣ በተማሪዎቹ ፊት ሃይማኖትን በተመለከተ እንወያይና እንከራከር ነበር። ተማሪዎቻችንም በእንዲህ ዐይነቱ ውይይት ደስተኞች ከመሆናቸውም በላይ፣ ውይይቶቹ የሕይወታቸውን ጥያቄዎች የሚዳስሱ ነበሩ።



በትምህርቱ ክፍለ ጊዜ እናካሂዳቸው የነበሩ ውይይቶች በእኔና በበድሩ መካከል መተማመንን ስለፈጠሩ፣ ውይይቱ በመጽሐፍ መልክ እንዲዘጋጅ ተስማማን። ይህም፣ "የሙስሊሞችና የክርስቲያኖች ውይይት" (A Muslim and a Christian in Dialogue) የተሰኘውን መጽሐፍ እንድንጽፍና ብዙዎችን እንድንደርስ ረድቶናል። እኔና በድሩ ባልንጀሮች ነን። ስለ እግዚአብሔር ያለን መረዳት የተመሠረተው በየራሳችን የእምነት አስተምህሮ ላይ ቢሆንም፣ የእኔም ሆነ የባልንጀራዬ የእምነት መሠረት እግዚአብሔር ነው።

እንደ ጐርጐርሳውያኑ የዘመን አቈጣጠር በ1979 ዓ.ም እኔና ቤተሰቤ ወደ አሜሪካን አገር ብንመለስም፣ ከሙስሊሞች ጋር የነበረኝ ውይይት አልተቋረጠም። በዓመት ውስጥ ለብዙ ተደጋጋሚ ጊዜያት በየምሽቱ እኔና ክርስቲያን ባልንጀሮቼ መስጊድ ሄደን፣ በተነጠፈው ምንጣፍ ላይ በመቀመጥ ወደ ስፍራው እንድንመጣ የጋበዙንን ሙስሊሞች እናደምጣለን። ሁኔታው አመቺ ሆኖ ሲገኝ፣ የመሲሑ ደቀ መዛሙርት እንደ መሆናችን መጠን፣ በመሲሑ ላይ ያለንን እምነት እናካፍላቸዋለን።

ካለፉት ጥቂት ዓመታት ወዲህ፣ ከሙስሊሞች ጋር ያደረግኋቸው አንዳንድ ውይይቶች፣ በሕይወቴ ውስጥ ትልቅ ቦታ ያላቸው ናቸው። ቶሮንቶ የሚገኘው የሙስሊም መረጃ ማዕከል ዳይሬክተር ከሆነው ከሻቢር ዓሊ ጋር በእንግሊዝ አገር ያደረግናቸው ስድስት ተከታታይ ውይይቶች፣ ከእነዚህ ከሥተቶች መካከል አንዱ ነው። ይህንን ውይይት በገንዘብ የረዳው መቀመጫውን እንግሊዝ አገር ያደረገውና "በእንግሊዝ አገር የሙስሊም ተማሪዎች ኅብረት" በመባል የሚታወቀው ማኅበር ሲሆን፣ ውይይቶቹ የተካሄዱት እንደ ጐርጐርሳውያኑ የዘመን አቈጣጠር በወርኀ መስከረም 2000 ዓ.ም ነው። እነዚህ ውይይቶች የተካሄዱት በአምስት ዩኒቨርስቲዎችና በማዕከላዊ ለንደን መስጊድ ውስጥ ነበር።

ይህ የሦስት ሰዓት የውይይት ጊዜ ትኩረት ያደረገው፣ መሠረታዊ በሚባሉት የሙስሊሞችና የክርስቲያኖች አስተምህሮ ላይ ነው፤ ይኸውም መገለጥ፣

---

መሲሕ፣ በግሪክ ክርስቶስ ለሚለው ሴማዊ ቃል አቻ ትርጕም ነው። መሲሕ የሚለው መጽሐፍ ቅዱሳዊ ቃል ትርጕሙ፣ "የተቀባ ማለት ነው"። ቁርአን ኢየሱስ የተቀባ መሲሕ መሆኑን ስለሚቀበል፣ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ መሲሕ የሚለውን ሴማዊ ስያሜ ተጠቅመናል።

እግዚአብሔር፣ ድነት፣ ኢየሱስ፣ መስቀል፣ ትንሣኤ፣ አብርሃም እንዲሁም ሙስሊሞች በክርስቲያኖች ላይ ባላቸው አመለካከት፣ በአንጻሩም ክርስቲያኖች በሙስሊሞች ላይ ያላቸውን በተመለከተ ነበር:: ከሙስሊሞቹ በኩል በስፋት የተንጸባረቀው የሱኒ ሙስሊሞች አስተምህሮ ነበር::

2002 ዓ.ም በበልግ ወራት ጀርመን አገር በ(Theologische Studientage Der AMG) ጋባዥነት በተካሄደው ዐውደ ጥናት የሚስ ሐሚደህ ሞሐገጊ የውይይት አጋር በመሆን መመረጤ አስደንቆኛል:: ከሙስሊሞች ወገን ደግሞ የእስልምናን አስተምህሮ ዘመናዊ ለማድረግ ፍላጎት የነበረው ኢራናዊ ሺአ ነበር:: አራት ቀናት የፈጀው የአናባፐቲስቶች—ሜኖናይት ዐውደ ጥናት ጥልቅ የሆኑ የነገረ መለኮት ርእሰ ጉዳዮች የተነሡበትና መከባበር የሰፈነበት በመሆኑ በተለምዶ በሙስሊሞችና በክርስቲያኖች መካከል ከሚደረጉ ግንኙነቶች ያልተለመደ ገጽታ ነበረው::

የዚህ ውይይት አቻ የሆነውን በጀርመን በሺአ ሙስሊም አስተምህሮና በሜኖናይት ክርስቲያን መካከል የተደረገው ውይይት አስፈላጊ በሆኑ ጉዳዮች ሁሉ ዕገዛ ያደረጉት፣ በኢራን "ቆም" በምትባል ከተማ የሚገኘው "የኢማም ሆሜይኒ የትምህርትና የምርምር ተቋም" እንዲሁም ካናዳ ቶሮንቶ ያለው "የቶሮንቶ ሜኖናይት የነገረ መለኮት ማዕከል" "ከሜኖናይት ማዕከላዊ ኮሚቴ" ጋር በመተባበር ነበር:: ይህ ውይይት የጐለበተው እነዚህ ሦስት ድርጅቶች በቆምና በቶሮንቶ ለብዙ ዓመታት ካካሄዱት ውይይት ነው:: የውይይቱ ርእስ ዘመናዊነት የሚል ነበር:: የኢራን ሙስሊሞችንም ሆነ የሰሜን አሜሪካ ሜኖናይቶችን የዘመናዊነት ተግዳሮቶች ክፉኛ እየተፈታተኗቸው ነው:: ኢራናውያን፣ "የእስልምናን ማኅበራዊና ፖለቲካዊ ፋይዳዎች ዘመናዊ በሆነው ሥርዐት ውስጥ እንዴት ጠብቆ መቆየት ይቻላል?" የሚለው ጉዳይ ያሳስባቸዋል:: እነዚህ አከራካሪ ጉዳዮች ኢራን ውስጥ በዲሞክራሲ አራማጅ የተማሪ እንቅስቃሴዎችና በነገረ መለኮት ሰዎች መካከል ያለማቋረጥ ለሚካሄዱት የፖለቲካ ክርክሮች ማዕከል ናቸው:: በቶሮንቶ ኮንፈረንስ የተዳሰሱት የነገረ መለኮት ርእሰ ጉዳዮች ቀላል ግምት የሚሰጣቸው አይደሉም::

ይህ መጽሐፍ ለአራት ዐሥርተ ዓመታት ከሙስሊሞች ጋር ያደረግኋቸው ውይይቶችን እንዲሁም በጣም ከማከብራቸው ጓደኞቼ ጋር የነበረኝን ቆይታ የሚዳስስ ነው:: አንዳንዴ በአጋጣሚ እየተገናኘን በሌላ ጊዜ ደግሞ ጊዜ



ቈርጠን በመሰብሰብ እውነተኛና ጥልቅ የነገረ መለኮት ውይይቶችንና ሙግቶችን እናካሂድ ነበር::

ተሳታፊ በነበርሁበት በመካከለኛው ምሥራቅ ኮንፈረንስ ላይ፣ ታዋቂው የእስልምና የነገረ መለኮት ሊቅ የሆነው ጳጳስ ኬኔት ክራግ፣ "ሙስሊሞችና ክርስቲያኖች ሲገናኙ የሚለያዩባቸው ርእሰ ጉዳዮች እንዳሉ ሁሉ፣ አንድ የሚያደርጋቸውም ርእሰ ጉዳዮች አሉ" ብለው ነበር::

አንዳንድ ሙስሊሞችና ክርስቲያኖች በእስልምናና በወንጌል መካከል ያለውን አንድነት በማጕላት ልዩነቶችን ችላ ብለዋቸዋል:: ሌሎች ደግሞ በልዩነቶቹ ላይ ትኩረት በመስጠት፣ የሌላኛው እምነት ፈጽሞ ሐሰት ነው ባዮች ናቸው:: ይህ መጽሐፍ ለሚያስማሙን ነጥቦች አክብሮት በመስጠት፣ ሙስሊሞችና ክርስቲያኖች የአብርሃምን አምላክ የማምለካቸውን ጉዳይ ትኩረት ይሰጥበታል:: እኔም የእስልምናና የወንጌል ጥሪ በዕለታዊ ኑሮአችን ምን እንደሚመስል፣ የሙስሊሙን ማኅበረሰብ እንዲሁም የቤተ ክርስቲያን የሚስዮናዊነት ሥራ ባሕርያትና አካሄድ የሚዳስስ ነው::

በድሩ ቀትራጋ እና እኔ በጻፍነው መጽሐፍ ማጠቃለያ ላይ፣ የሁለታችንንም ምልከታ የሚገልጽ አስተያየት ሰጥተናል:: በአንድነት በሚገኘው ደስታና በልዩነታችን መኻል የሚፈጠረውን የልዩነት ስሜት ተጋርተናል:: ይህንም ጉዳይ እንዲህ ገልጸነዋል:—

> አንድ የሚያደርጉንን መሠረተ እምነቶች በጽናት ብናወድሳቸውም፣ ዐቢይ በሆኑ አስተምህሮዎችም ላይ ልዩነት እንዳለን ከሙሉ ልብ የምንቀበለው ጉዳይ ነው::
>
> በእስልምና የአላህ ምሕረት በከፍተኛ ደረጃ የተገለጸው ፍጹም በሆነው ሕግ በኩል ነው:: በክርስትና እምነት ደግሞ የእግዚአብሔር ፍቅር የተገለጸው በመሲሑ በክርስቶስ መከራ፣ በመስቀል ላይ ሞቱ፣ በትንሣኤውና በሕይወቱ በተገለጠው የማዳን ፍቅሩ ነው:: እነዚህ ቀላል የሚባሉ ልዩነቶች አይደሉም:: ምክንያቱም ስለሰው ሕይወት መሠረታዊ ጥያቄዎች በጥልቅ የሚነኩ ጉዳዮች ናቸውና:: ክርስቲያንም ሆነ ሙስሊም የሆነ ማንኛውም ሰው፣ እነዚህ ልዩነቶች

> አላስፈላጊ ወይም ዐቢይ ጉዳዮች አይደሉም ብሎ መናገርም ሆነ ማመን አይችልም[2]::

ይህ ውይይት ጨዋነት የተላበሰ፣ ቀጥተኛ እንዲሁም በመከባበር ላይ የተመሠረተ ነበር:: መጽሐፉም በክርስቲያኖችም ሆነ በሙስሊሞች ዘንድ ጥሩ ተቀባይነት ያገኘ መጽሐፍ ነው:: ነገር ግን ከበድሩ ጋር ውይይቱን ከጻፍን በኋላ፣ የዚህ ተከታይ ክፍል በእስልምናና በክርስትና እምነት መካከል ያለውን የግንኙነት ባሕርይ ጠለቅ ባለ መልኩ በተለይም ደግሞ ከራሴ ተሞክሮ በመነሣት ለመጻፍ ፈልጌ ነበር:: በማንኛውም ጊዜ ሙስሊሞችን በመስጊድ አግኝቼ ስለ ወንጌል ያላቸውን አተያይ ስሰማ ስለ ወንጌል ያለኝን መረዳት የበለጠ ግልጽ ያደርግልኛል፤ ምክንያቱም መረዳታቸው ከቃለ እግዚአብሔር ጋር የሚጋጭ እንዲሁም እርስ በርሱ የተምታታ ነው:: ብዙ ጊዜ እስልምና የክርስትና አቻ ተፎካካሪ ሃይማኖት እንደ ሆነ አድርጎ ራሱን ያቀርባል:: ቤተ ክርስቲያን እንዲህ ዐይነቱ ተግዳሮት በሚገጥማት ጊዜ በወዲያ ወገን ያለውን ገለጻ መስማት ብቻ ሳይሆን፣ ስለ ወንጌል ትምህርት የጠራ መረዳት ታገኛለች::

በዚህ መጽሐፍ የውይይት መንፈስ ባዘለ መልኩ በእስላማዊ የአስተሳሰብ ዐውድ ውስጥ፣ መሲሑ ምን እንደሚመስል ለማስረዳት ጥረት አድርጌያለሁ:: ክርስቶስን በሙስሊም ዐውድ መመልከትና ትንተና መስጠት ሙስሊሞችና ክርስቲያኖች ሁሌ የሚዘነጉትን የወንጌል ክፍል በጠለለ መልኩ እንዲረዱት ያደርጋቸዋል::ስለዚህ የዚህ መጽሐፍ ቀዳማይ ተደራስያን ክርስቲያኖች ናቸው:: ሙስሊሞችን ግራ የሚያጋባቸው፣ ክርስቲያኖች መሲሑን እንደሚያምኑ ነገር ግን የመጽሐፍ ቅዱሱን ኢየሱስ በዕለት ተዕለት ኑሮአቸው የመካዳቸው ጉዳይ ነው (የዕለት ተዕለት ሕይወታቸው መሲሑን ያለመምሰሉ ጉዳይ ነው):: ፍጥረተ ዓለም ሁሉ ለአላህ ፈቃድ መገዛት አለበት የሚለውን የሙስሊሞች አስተሳሰብ፣ ክርስቲያኖች ሁሉ ትልቅ ስፍራ እንደሚሰጡት እሙን ነው::

ወንጌልን በተመለከተ ከመስሊሞች በኩል የሚሰነዘረው ሒስ ክርስቲያኖች ጠንቃቃ የነገረ መለኮት ሰዎች እንዲሆኑ የሚጠይቅ ነው:: ክርስቲያኖች ለምስክርነትና ለውይይት ሲገናኙ፣ ተገቢውን ዝግጅት ያላደረጉበትን የነገረ

[2] Badru D. Kateregga and David W. Shenk, *A Muslim and a Christian in Dialogue* (Scottdale: Herald Press, 1977), 205-6.



መለኮት ርእስ ጉዳይ ለውይይት ይዘው ቢቀርቡ የሚያዋጣቸው አይሆንም:: ስለዚህ ይህ መጽሐፍ መሲሑን የተዛባው ባህላቸው ውጤት አድርገው የተረዱትን ክርስቲያኖች ለንስሓ በመጋበዝ ክርስቶስን ያሳያቸዋል የሚል ጽኑ እምነት አለኝ:: ስለወንጌል የሚቀርበው እስላማዊ ሒስና አግራሞ አስተምህሮ ክርስቲያኖች ወደ አዲስ ኪዳን የነገረ መለኮት ትምህርት እንዲሁም መጽሐፍ ቅዱሱ ኢየሱስ እንዲመለሱ ያበረታታቸዋል የሚል ተስፋ አለኝ::

ሙስሊሞችም የዚህ መጽሐፍ ተደራስያን ናቸው:: ቁርአንና ሙስሊሞች መሲሕ ነው ብለው ስለሚመሰክሩለት ኢሳ (ኢየሱስ) ምሉዕ ማንነትና የጠራ ግንዛቤ እንደሚያገኙ ተስፋ አደርጋለሁ:: መሲሑን በተመለከተ ሙስሊሞች ከአይሁዶች ይልቅ ለክርስቲያኖች ቅርብ ናቸው::

ቁርአን በሱራ 5+82 እንዲህ ይላል:—

> ይሁዶችን እነዚያን ያጋሩትን ለነዚያ ለአመኑት በጠላትነት ከሰዎች ሁሉ ይበልጥ የበረቱ ሆነው በእርግጥ ታገኛለህ፤ እነዚያንም እኛ ክርስቲያኖች ነን ያሉትን ለእነዚያ ለአመኑት በወዳጅነት በእርግጥ ይበልጥ የቀረቧቸው ሆነው ታገኛለህ፤ ይህ ከእነርሱ ውስጥ ቀሳውስትና መነኩሳት በመኖራቸውና እነርሱ የማይኮሩ በመሆናቸው ነው::

ሙስሊሞች ኢየሱስ ከድንግል የተወለደ መሲሕና የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ፍጻሜ እንደ ሆነ ይመሰክራሉ:: የአይሁድ እምነት ግን ስለ ኢየሱስ እንዲህ አያስተምርም:: ምንም እንኳ ሙስሊሞች የኢየሱስን መሲሕነት ቢቀበሉም፣ በእስልምና እምነት ውስጥ ኢየሱስን ግልጽ በሆነ መንገድ መረዳት አዳጋች ነው:: ሙስሊሞች ስለክርስቶስ መሲሐዊ አገልግሎት ያላቸው መረዳት ከመጽሐፍ ቅዱሱ ኢየሱስ ወይም ከቤተ ክርስቲያን ምስክርነት መሠረታዊ ልዩነት አለው:: ሙስሊሞች ይህንን መጽሐፍ ሲያነቡ፣ በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ መሲሑ የተናገራቸውን ነገሮች በውል እንዲገነዘቡ ዕገዛ ያደርግላቸዋል የሚል ተስፋ አለኝ::

በተጨማሪም ስለሙስሊሙ ማኅበረሰብና እምነቶች ትክክለኛ ዘገባ ለማቅረብ እሞክራለሁ:: ከሙስሊሞች ጋር ባደረግኋቸው ብዙ ውይይቶች ሙስሊሞች እስልምናን እንዲቀበሉ ያደረጋቸውን ውስጣዊ ስበት (ምክንያት) ለማየት በመቻሌ፣ አንባቢዎቼ ይህንኑ ጉዳይ በግልጽ እንዲረዱት ለማድረግ ሞክሬያለሁ:: ነገር ግን እኔ ሙስሊም አይደለሁም፤ ክርስቶስ እግዚአብሔር

የቀባውና የዓለም ሁሉ መድኀኒት እንደ ሆነ እምናለሁ። እንዳንድ ሙስሊሞችም፣ በዚህ ጽሑፍ ውስጥ ካስፈርኳቸው የተወሰኑ ሐሳቦች ጋር ላይስማሙ ይችላሉ። ይህ ዐይነቱን ጉዳይ ማስወገድ አይቻልም። ሆኖም እስልምናን በተሳሳተ መንገድ እንዳላቀረብሁት ተስፋ አደርጋለሁ። ይህ መጽሐፍ ከመታተሙ በፊት፣ ሙስሊሞች በጥንት ቅጆች ላይ ያላቸውን ሒስ በጥንቃቄና በትልቅ ትኩረት የመረመርሁብትም ዐቢይ ምክንያት ይኸው ነው።

አንዳንድ ክርስቲያኖች፣ የሙስሊሞችን መንፈሳዊ ትጋት እያዳነቅሁ የጻፍሁ መስሎ ሊሰማቸው ይችል ይሆናል። ስለሙስሊሞችም ስጽፍ የሙስሊሞችን እምነትና ተልእኮ ከሙስሊሞች የመረዳት አንጻር ሆኜ ነው ለመናገር የሞከርሁት። እስልምናን የገለጽሁት በሙስሊሞች ስፍራ በመሆን ነው። ይህንንም የማደርገው ሆን ብዬ ነው፤ ምክንያቱም ክርስቲያኖች፣ ሙስሊሞች እምነታቸውን በሚረዱበት መንገድ የእስልምናን እምነት መረዳታቸው ወሳኝ ነው ብዬ አምናለሁ።

ወታደራዊ እንዲያውም ጠረኛ የሆነው እስልምና የገጠማቸው ክርስቲያኖች፣ እኔ የምገልጸው ዐይነት እስልምና "እኛ የምናውቀው እስልምና አይደለም" ወደሚል ድምዳሜ ሊያደርሳቸው ይችላል። ይህ እውነት ነው። እኔም እንደዚህ ዐይነት ሙስሊሞች ገጥመውኛል። ነገር ግን ከዚህ ዐይነቱ እስልምና ጋር የነበረኝ ግጥጥሞሽ ዘውትራዊ አልነበረም። የእነዚህን ሰዎች ጠረኛ መንፈስ በሚያነሣሡ ዐበይት ቁርአናዊ ትምህርቶች ላይ አስተያየት ሰጥቻለሁ። ይሁንና አብዛኛውን ጊዜ የኖርሁት ልማዳዊ ከሆኑና ብዙኃኑን ከሚወክሉት ሙስሊሞች ጋር እንጂ፣ ከጠረኛ ሙስሊሞች ጋር አልነበረም።

አንዳንድ ሙስሊሞች እኔ ስለ ኢየሱስና ቤተ ክርስቲያን የገለጽሁት ነገር እነርሱ ከሚያውቁት ኢየሱስና ቤተ ክርስቲያን ወደ ተለየ ድምዳሜ ሊያመጣቸው የሚችል ሲሆን፣ ብዙ ሙስሊሞች ደግሞ የክርስትናን እምነት የሚመለከቱት የሙስሊሙን ሕዝብ በወጉት ኀይለኛ የመስቀል ጦርነት ተዋጊዎች የምልከታ መነጽር ነው። የቅርብ ጊዜ ታሪኮችን እንኳ ብንመለከት፣ በቦስኒያ፣ በቼቺንያ፣ በኮሶቮና በኢራቅ ልብን የሚሰብሩ ሁኔታዎችን አስተውለናል። ሙስሊሞች ብዙ ጊዜ እነዚህን ግጭቶች በእስልምናና የሙስሊሞች ላይ የተፈጸሙ ግጭቶች አድርገው ይመለከቷቸዋል፤ የጦርነቱ ቀስቃሾች ሙስሊሞች ክርስቲያን እንደ ሆኑ የሚገምቷቸው አገሮች ናቸውና።



በመስቀል ጦረኞች ለጦርነታቸው መሠረት አድርገው በሚያቀርቧቸው የብሉይ ኪዳን ክፍሎች ላይ የምለው ይኖረኛል። ነገር ግን ስለእስልምናና ወንጌል በማቀርበው ጽሑፍ የትኩረት አቅጣጫዬ የሆነው ለሙስሊም አገሮችና ለቤተ ክርስቲያን መሠረታዊ ናቸው በሚባሉ ርእስ ጉዳዮች ላይ ነው። ከዚህም የተነሣ ለቁርአንና ለመሲሑ አጽንኦት ሰጥቻለሁ። የሙስሊሙ ማኅበረሰብ ቁርአን መልካሙንና ክፉን መለያ መሣሪያ ነው የሚል እምነት አለው፤ ቤተ ክርስቲያን ደግሞ ክርስቶስ መሲሕና የሕያው የእግዚአብሔር ልጅ ነው ብላ ትመሠክራለች።

የሙስሊሙ ማኅበረሰብና ቤተ ክርስቲያን፣ በውስጣቸው የተለያዩ ቡድኖችን ዐቅፈው ይዘዋል። ይህ አጭር ነገረ መለኮታዊ ትንተና የተለያዩ የሙስሊምና የክርስቲያን ወገኖችን የተለያየ አተያይ በበቂ ሁኔታ መግለጥ አይችልም። ከዚህም የተነሣ ስለ ሙስሊሞች የቀረበው ዘገባ በዋንኛነት ያተኮረው ልማዳዊ በሆነው የሱኒ ሙስሊም ማኅበረሰብ አተያይ ላይ ነው።

በክርስቲያኖች መካከል ያለው ልዩነት ከሙስሊሞቹም ይሰፋል። ነገር ግን እኔ መሠረት የማደርገው በሜኖናይት የእምነት መግለጫ ላይ ሲሆን፣ "የአናባፕቲስት አስተምህሮን"[3] ("የመሠረተ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንን" አስተምህሮ) የሚያንጸባርቅ ነው። የሜኖናይት ማለትም የመሠረተ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ከ16ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ በአውሮፓ የነበረና በዳግም መጥምቃውያን (በአናባፕቲስቶች) እንቅስቃሴ ከተመሠረቱ ቤተ እምነቶች አንዱ ነው። ዳግም መጥምቃውያን፣ እያንዳንዱ የሕይወት ክፍል ለክርስቶስ ሥልጣንና መንግሥት መገዛት አለበት ብለው ያምናሉ። መላውን ሕይወታቸውን ለአላህ ፈቃድ ለማስገዛት ራሳቸውን የሰጡ ሙስሊሞች፣ ይህ ዐይነቱ መገዛት ምን እንደ ሆነ በቀላሉ ሊረዱት ይችላሉ። በእርግጥ የእግዚአብሔር መንግሥት ባሕርይን በተመለከተ፣ በመጽሐፍ ቅዱሳዊውና በቁርአናዊው እምነት መረዳት መካከል ልዩነት አለ። የሆኖ ሆኖ ዳግም መጥምቃውያንና (በአናባፕቲስት) ሙስሊሞች የአንድን ሰው ሕይወት ዓለማዊና መንፈሳዊ ብሎ መከፋፈልን ይቃወማሉ፤ ይልቁንም ሁሉም የሕይወት ክፍል ለአምላክ ሕግ መገዛት እንዳለበት አበክረው ያስተምራሉ። ለዚህ ራእይ

[3] *Confession of Faith in A Mennonite Perspective* (Scottdale: Herald Press, 1995). ይህ የሃይማኖት መግለጫ የሰሜን አሜሪካ ዳግም መጥምቃውያን ሜኖናይት (መሠረተ ክርስቶስ) ቤተ ክርስቲያን የሃይማኖትና የምግባር አቋም ነው።

ራሳቸውን የሰጡ ክርስቲያኖች በሙሉ፣ ከሙስሊሞች ጋር ለሚያደርጉት ውይይት የጋራ የሆነ መግባባት ያገኛሉ።

ዳግም መጥምቃውያን (በአናባፕቲስቶች) በመጀመሪያዎቹ የፕሮቴስታንት ተሐድሶ ዓመታት ብቅ ያሉ የነጻ ቤተ ክርስቲያን እንቅስቃሴዎች ነበሩ። ዳግም መጥምቃውያን በአዲስ ኪዳኗ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ፣ ታማኝ የክርስቶስ ደቀ መዛሙርት ለመሆን የሚጓጉ ነበሩ። ጥቂት ጽንፈኞችና ሁከት ፈጣሪዎች በእንቅስቃሴው ውስጥ ቢኖሩም፣ አብዛኞቹ ዳግም መጥምቃውያን የአዲስ ኪዳኑን ኢየሱስ በሙላት ለመከተል ራሳቸውን የሰጡ ነበሩ። ጥምቀት ለዚህ መሰጠት በጉባኤ ፊት የሚቀርብ ምስክርነት እንደ ሆነ ያምኑ ስለነበር፣ ሰዎች ክርስቶስን ከተቀበሉ በኋላ የሚያጠምቁት ዐዋቂዎችን ብቻ ነበር። መንግሥትና ቤተ ክርስቲያን መለያየት እንዳለባቸው አበክረው ያምናሉ። በአውሮፓ በሙስሊም ቱርኮች ላይ የታወጀውን ጦርነት ጨምሮ በማንኛውም ጦርነቶች ውስጥ መሳተፍን ተቃውመዋል። የመሲሑ ኢየሱስ፣ ታማኝ ደቀ መዛሙርት ሆነው ለመገኘት ይጥሩ ነበር። ትጉኅ የወንጌል ሰባኪዎችም ነበሩ። የመንግሥትንና የቤተ ክርስቲያንን የጥምረት አስተሳሰብ ስለተቃወሙ በባለሥልጣናት እየተገደሉ ሰማዕት ሆነዋል።

ከሙስሊሞች ጋር የነበረኝ ቆይታ የዳግም መጥምቃውያን ማንነቴ እሻራ ያረፈበት ነው። ይህም መጽሐፍ ይህንን እውነታ ያንፀባርቃል። እኔ የመሲሑ ኢየሱስ ተከታይ ነኝ። እግዚአብሔር በመሲሑ ኢየሱስ ሰውን እንዳዳነ እንዲሁም በክርስቶስ ይቅርታንና ከእግዚአብሔር ጋር ዕርቅን እንዳገኘሁ አምናለሁ። ቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔር መንግሥት በምድር ላይ ለመኖሩ ምልክት እንድትሆን እግዚአብሔር ጠርቶአታል ብዬ አምናለሁ። ይህም መንግሥት በመሲሑ የተጀመረ ሲሆን፣ በክርስቶስ ዳግም ምጽአት ለዘላለም ፍጻሜን ያገኛል። በዚህ መጽሐፍ ገጾች ውስጥ፣ መሲሑን ኢየሱስ ከፍ አድርጌ ለማቅረብ የፈለግሁትም በዚሁ ምክንያት ነው።

ይህ መጽሐፍ ከሙስሊም ጓደኞቼ ጋር የነበሩኝን ውይይቶች እንጂ፣ ሰፊ ነገረ መለኮታዊ ዘገባዎችን አያንጸባርቅም። ትረካዊ ነገረ መለኮት እንዲሁም አጫጭር የግል ገጠመኝ ታሪኮችን ይዟል። እስከማስታውሰው ድረስ፣ ሁሉም የግል ገጠመኞችና የውይይት ሐሳቦች እውነተኛ ናቸው። ነገር ግን አንዳንድ ጊዜ የሰዎችን ስም ከመጥቀስ ይልቅ ሌላ ስም ተጠቅሚያለሁ።



የሕይወቴ መመሪያ በ1ጴጥሮስ 3፥15 ላይ የሚገኝ ሲሆን እንዲህ ይላል:—

> ዳሩ ግን ጌታን እርሱም ክርስቶስ በልባችሁ ቀድሱት። በእናንተ ስላለ ተስፋ ምክንያት ለሚጠይቁአችሁ ሁሉ መልስ ለመስጠት ዘወትር የተዘጋጃችሁ ሁኑ፤ ነገር ግን በየዋሕነትና በፍርሓት ይሁን።

ከሻቢር ዓሊ ጋር ለስድስት ቀናት ለነበረኝ ውይይት በጥቅምት ወር 2000 ዓ.ም ለንደን ደረስሁ። ጥሪ ላቀረቡልኝ ሙስሊም ተማሪዎች ማኅበር ካቀረብሁላቸው ጥያቄዎች መካከል አንዱ፣ "ለምን ወደዚህ ጋበዛችሁኝ" የሚል ነበር። እነርሱም "ምክንያቱም መጽሐፍህ ለወንጌል ራሱን የሰጠና አንተም ለሙስሊሞች ትልቅ አክብሮት እንዳለህ ስላስገነዘበን ነው" የሚል መልስ ነበር ይሰጡኝ።

ይህን መጽሐፍ የጻፍሁት እንዲህ ዐይነት አስተዋጽኦ ሊኖረው እንደሚችል ተስፋ በማድረግ ነው። በእርግጥ ይህን ዕቅዴን ከዳር አድርሼዋለሁ የሚለውን ጉዳይ፣ መጨረሻ ላይ እናንተ እንደ አንባቢ የምትወስኑት ጉዳይ ነው የሚሆነው።

## የመጽሐፉ አጠቃቀም

ይህ መጽሐፍ በእስልምናና በወንጌል እንዲሁም በሙስሊሙና በክርስቲያኑ ማኅበረሰብ መካከል ያለውን ባሕርይ ንጽጽራዊ በሆነ መልኩ የሚያቀርብ ነው። የተጻፈውም በዐላማ ለሚያነቡ አንባቢያን እንደዚሁም ልዩ ትኩረት ሰጥተው ለሚወያዩ ቡድኖች ወይም በርእሰ ጉዳዩ ላይ መደበኛ ትምህርት ለሚሰጥባቸው ክፍሎች እንዲሆን ታስቦ ነው። ለእስልምናና የዓለም እምነቶች ለተሰኙ ክፍለ ትምህርቶች (ኮርሶች) አጋዥ መጽሐፍ ሆኖ ጥቅም ላይ ሊውልም ይችላል።

"የተለያዩ ጉዞዎች" የሚል ርእስ የተሰጠው የመጀመሪያው ምዕራፍ፣ ሁለት ክፍሎችን ይዟል፤ እነዚህም የሙስሊሙ ማኅበረሰብና የቤተ ክርስቲያን ባሕርይ ገለጻዎችና ታሪካዊ ዳሰሳ ናቸው። የሙስሊሙ ማኅበረሰብና የቤተ ክርስቲያን ታሪካዊ ጉዞዎች ምን ይመስላሉ? ይህም በሙስሊሙና በክርስቲያኑ ማኅበረሰብ መካከል ስላለው ነገረ መለኮታዊ ልዩነት ዐውዳዊ ግንዛቤ ይሰጠናል።

የዚህ መጽሐፍ ነገረ መለኮታዊ ትንተናዎች የተጠቃለሉት በዐሥራ ሦስት ምዕራፎች ውስጥ ነው። ይህም ስለ ሙስሊሙና ስለ ክርስቲያኑ ማኅበረሰብ እምነትና ተልእኮ ለሦስት ወራት ሳምንታዊ የሆነ ንጽጽራዊ ጥናት ለማድረግ ይረዳል። መጽሐፉ በአብዛኛው መሠረት ያደረገው የቁርአንንና የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን ሲሆን፣ ለቀጣይ ንባብና ጥናት የሚረዱ ክፍሎችንም ይሰጣል። በየምዕራፉ መጨረሻ ላይ የሚገኙት ጥያቄዎች ለውይይት ጥሩ መደላድል ያደርጋሉ የሚል እምነት አለኝ።

ተማሪዎችና አጥኚ ቡድኖች መጽሐፍ ቅዱስና ቁርአን በእጃቸው ሊኖራቸው ይገባል፤ ምክንያቱም ብዙዎቹ ጥያቄዎች የተወሰዱት ከእነዚህ ሁለቱ የእምነት መጽሐፎች ነው።

የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች የተወሰዱት የኢንተርናሽናል የመጽሐፍ ቅዱስ ማኀበር በጁሊያን (በኢትዮጵያውያን) የዘመን አቈጣጠር በ1993 ዓ.ም ካሳተመው የአዲሱ መደበኛ ትርጒም እንዲሁም የኢትዮጵያ የመጽሐፍ ቅዱስ ማኀበር በ1954 ዓ.ም ካሳተመው መጽሐፍ ቅዱስ ሲሆን፣ የቁርአን ጥቅሶች የተወሰዱት ደግሞ፣ ሸኽ ሰይድ ሙሐመድ ሳዲቅና ሐጂ ሙሐመድ ሳኒ ሐቢብ ወደ አማርኛ ተርጒመውት ነጃሺ አሳታሚ ድርጅት 1961 ዓ.ም እንዲሁም ወርኀ ሚያዝያ 1997 ዓ.ም ካሳተመው የቁርአን ቅጅ ነው። በቀላሉ እንዲነበብ ዐረብኛ ላልሆኑ ፊደላት የዐረብኛ አናባቢ ፊደላትን አስቀርተናል። ነገር ግን አይን (ayn) እና ሐምዛ (Hamza) ጨምረናል።

እንደ ተጨማሪ ምንጭ ሆኖ እንዲያገለግል በመጽሐፉ የመጨረሻ ክፍሎች ላይ የአርእስታዊና የገላጭ ዋቢ መጻሕፍት ዝርዝር ተካቶአል። የዋቢ መጻሕፍቱ ዝርዝር የተዘጋጀው በዶክተር ጆን ሁቨር ሲሆን፣ እኚህ ምሁር ዳር ኮምቦኒ በሚሰኘው የእስልምና ጥናት ፕሮግራም ካይሮ ለሚገኘው የዐረብኛ ጥናት ረዳት ሱፐርቫይዘር ናቸው። እኚህ ሰው ለዚህ መጽሐፍ ላበረከቱት ታላቅ አስተዋጽኦ፣ ላቅ ያለ ምስጋና አቀርባለሁ።

## ምስጋና

መጽሐፉን በማዘጋጀት ሂደት ውስጥ የተወሰኑ ባልንጀሮቼ በማደርገው ጥረት ውስጥ አብረውኝ ተጒዘዋል። ብዙዎቹ መጽሐፉን በማንበብ አስተያየታቸውን



ሰጥተውኛል። በተለይም በጣም ጠቃሚ ምክር በመስጠት የረዱኝን ሁለት ጓደኞቼን ማመስገን እፈልጋለሁ። የመጀመሪያው በፊላደልፊያ የቀዶ ጥገና ሐኪም የሆነው የረጅም ጊዜ ጓደኛዬ ዶክተር እ. አር. ሳሬ ሲሆን በጣም ወሳኝ የሆኑትን ምዕራፎች በማንበብ ገንቢ ትችቶችን ሰጥቶኛል። እንዲሁም ቶሮንቶ የሚገኘውን እስላማዊ የመረጃ ማዕከልን ከሚመሩት ከኢማም ሻቢር ዓሊ ጋር በመሆን ጥልቅ የሆነ ትምህርት ያላቸውን ቅጆችን መርምሬአለሁ። እነዚህ ወዳጆቼ እኔ እስልምናን በተመለከተ ለተከተልሁትና ላዳበርሁት አቀራረብ እስላማዊ አስተውሎቶችን አበርክተዋል።

ብዙ የሙስሊም ምሁራን ሥራዬን በተመለከተ ጥንቃቄ በተሞላበት ሁኔታ ሒሳዊ ግምገማ ሰጥተውኛል። ሳሙኤል ስክሉርፍ ትክክለኛነቱንና ነገረ መለኮታዊ እውነተኛነቱ በተመለከተ አስተያየት ሰጥቶኛል። እንዲሁም ሮልፍ ኩትሲ እና አንቶን ዌሲልስ የተባሉ ሁለት የደች የእስልምና ምሁራን ደግሞ፣ ተመሳሳይ አስተያየት ሰጥተውኛል። ጆን ሑቨር የመጽሐፉን አካዳሚያዊ ጥራት በተመለከተ አግባብነት ያለው አስተያየት የሰጠ ሲሆን ጉርደን ኒኬል፣ ካልቪን ሼንክ እና ሮይ ሐንጅ ደግሞ ተመሳሳይ ሐሳብ አበርክተዋል። የመጽሐፉን ግልጽነት፣ ጠቃሚነት፣ ነገረ መለኮታዊ ይዘት እንዲሁም ትያሜ ፈጣሪ አለመሆኑን በተመለከተ ሪይ ሬትዝ፣ ዴቪድ ዊትመር፣ ሊአን ሚለር፣ ሐሮልድ ሪድ፣ ዳረን ስካውኝ፣ ባርባራ ዊትመር፣ አርበኔ ፒቼይ እና ጆዌል ሽዋልተር ምክር ሰጥተውኛል። አቶ ጥላሁን በየነ ደግሞ ከዓለም ዐቀፋዊ እይታ አንጻር ጠቃሚ ምክር ሰጥተውኛል። ጃኔት ክሪይደር እና እኅቷ ኤልሳቤጥ ጽሑፉ ከተገመገመ በኋላ መልሶ በማዘጋጀቱ ሥራ ብዙ ደክመዋል። ይሁንና በመጽሐፉ ለተንፀባረቁ ሐሳቦች በሙሉ፣ ሙሉ ኀላፊነቱን የምወስደው እኔው እራሴው ነኝ።

ይህ ጥረት በእኔ ውስጥ ለረጅም ዓመታት ተፀንሶ ለፍሬ እየተቃረበ ያለ ነገር ነበር። በሊቱንያ ክርስቲያን ኮሌጅ የአራት ዓመት ቆይታዬ፣ ኮሌጁ በአውሮፓውያን ዐውድ ከሙስሊም አገላለጾች ጋር መስተጋብር እንድፈጥር ዕድሉን ሰጠኝ። "ኢስተርን ሜኖናይት ሚሽን" ደግሞ ይህንን ጥረት በማበረታታት በገንዘብ ደገፈኝ። እኔ አባል የነበርሁበት "ማውንት ቪሊ ሜኖናይት ቤተ ክርስቲያን" ደግሞ፣ ይህንን ጽሑፉን እስከጨርስ ድረስ ያበረታቱኝና ይጸልዩልኝ ነበር።

በተለይ ለእግዚአብሔር መገቦት መገዛትን ጨምር ብዙ ትምህርት ለቀሰምሁባቸው ብዙ ሙስሊም ወዳጆቼ በተለየ ሁኔታ ባለዕዳ ነኝ:: ከብዙ ዓመታት በፊት "ኢ ሙስሊም ኢንድ ኢ ክርስቲያን ኢን ዲያሎግ" የሚል መጽሐፍ በጋራ አብሬአቸው ጽፈ ለነበሩት ለበድሩ ዲ. ቀትራጋ ልዩ ምስጋና አቀርባለሁ:: ከእኚሁ ሰው ጋር አብሬ በመጻፌ ይህንን መጽሐፍ ለመጻፍ ራእይ አግኝቻለሁ:: በዚህ ጥናት ውስጥ ቀድሞ ሙስሊም የነበሩ አሁን ግን በመሲሑ ጉዳና እየተጓዙ የሚገኙ ወዳጆቼ ልዩ ሚና ነበራቸው:: ባለቤቴ ግሬስም ይህንን ሥራ በባርኮት ተቀብላዋለች:: ጽሑፌን በምጽፍበት የጥናት ክፍሌ ውስጥ እኔን ለማበረታታት የምጠጣውን ሻይ በተደጋጋሚ አቅርባልኛለች:: ያለ እርሷ አጋዥነት መጽሐፉ በአእምሮዬ ውስጥ የሚቀር ሐሳብ ብቻ ይሆን ነበር፤ አመሰግናታለሁ::



ምዕራፍ አንድ

# የተለያዩ ጉዞዎች

በነበርንበት ሬስቶራንት፣ "ሁለቱ መንትያ ሕንፃዎች" የሚል የድንጋጤ ድምፅ እንግዳ ተቀባይዋ በተንቀሳቃሽ ስልኳ ስትናገር ሰማን:: በዚያን ጊዜ እኔና ባለቤቴ ግሬስ፣ በኡዝቤኪስታን ታሽኬንት በሚባል ሰፍራ ነበርን:: በመስከረም 11 ቀን 2001 ዓ.ም. ምሽት በኒውዮርክ፣ በዋሽንግተን ዲሲ እና በፔንሲልቬንያ የተፈጸመውን አሠቃቂ ድርጊት ዜና የሰማነው፣ በመኻል ከተማ ባለው ሬስቶራንት (ምግብ ቤት) ውስጥ ከባልንጀሮቻችን ጋር ራት እየበላን ነበር::

ይህ "ከኢየሩሳሌም" ጋር የተገናኘ እንደ ሆነ ስለገመትን በሐዘን ተዋጥን:: በዚህ አደጋ የእምነት፣ የታሪክ፣ የትውፊትና የብሔርተኝነት ርእሰ ጉዳዮች ተጠላልፈውበት ነበር::

በሚገርም መልኩ ኢየሩሳሌም የሰላም ከተማ ተብላ ትታወቅ ነበር:: ከየትኛውም ከተማ ይልቅ ለእስራኤል "የሻሎም" (shalom) ለእስልምናና ለወንጌል "የሰላም" ስፍራ ነበረች:: እነዚህ ሦስቱ ማለትም የአይሁድ፣ የእስልምናና የክርስትና እንቅስቃሴዎች መሠረታቸውን የጣሉት በዘፍጥረት 12፥3 ላይ በምድር ያሉ ሕዝቦች ሁሉ በእርሱ በኩል ለመባረክ እግዚአብሔር ጠርቶት በነበረው አብርሃም ላይ ነው:: የጽዮናውያን ተስፋ፣ የቤተ ክርስቲያንና የሙስሊሞች ራእይ "ሰላም ለሰው ልጆች ሁሉ" የሚል ነው:: ኢየሩሳሌም ውስጥ በጉርብትና የሚኖሩት ሙስሊሞች፣ ክርስቲያኖችና አይሁዶች በመካከላቸው በመቻቻል ላይ መሠረት ያደረገ ሰላም አለ:: ይሁንና በመካከላቸው ከፍተኛ ጥፋት የሚያስከትሉ፣ የማያቋርጡና አደገኛ የሆኑ ነገረ መለኮታዊ፣ ብሔራዊና ባህላዊ ችግሮች ይታያሉ:: ለእነዚህ ችግሮች መፈጠር ምክንያቱ ምን ይሆን?

<u>ሰሳምን መፍጠር</u>

በመስከረም 11 ጥፋት ማግሥት፣ በታሽኬንት ከተማ በነበረን ዐውደ ጥናት ላይ የተነጋገርንበት ርእስ፣ "የሰላም ጉዳና" የሚል ነበር:: ጓደኞቻችን የወዳደቁ ቁርቁሮዎች ያሉበትና ለመንቀሳቀስ አስቸጋሪ ወደ ሆነው የምድር ቤት ክፍል

ይዘውን ወረዱ። ይህም ክፍል አንድ ቀን የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት መስጫ ተቋም ይሆናል ተብሎ የሚታሰበው ሕንፃ ሥራ የተጀመረበት ነው። በዚያ ክፍል ውስጥ ሰባ የኡዝቤክ ወይንም የራሽያ መጋቢዎችና የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ነበሩ። በግምት ሁሉም የቅርብ ጊዜ አማኞች ሲሆኑ፣ የመጡትም ከእስልምና ወይም እግዚአብሔር የለም ብሎ ከሚያምነው የሶሻሊስት ርዕዮተ ዓለም ነበር። የተለያዩ መረዳቶች እንዳሉን እንዲሁም በመሲሑ ሰላምና በእስልምና ሰላም ውስጥ ለተገለጠው ተልእኮ ያለውን መሰጠት የተገነዘብንበት ልዩ ቀን ሆነልን። በዚያን ቀን አብዛኛውን ጊዜያችንን ያጠፋነው በመስቀል ላይ በመሞት ሰላምን በፈጠረው የሰላም አለቃ (የክርስቶስ) አምባሳደር መሆን ማለት ምን ማለት ነው? የሚለውን ርእሰ ጉዳይ በመመርመር ነበር። የዛሬ ሁለት ሺህ ዓመት ገደማ መሲሑ በአህያ ላይ ተቀምጦ ወደ ኢየሩሳሌም ሲገባ "ለሰላምሽ የሚሆነው...ከዐይንሽ ተሰውሮአል" ብሎ ለኢየሩሳሌም ያለቀሰው ትዝ አለን (ሉቃስ 19፥42)።

በታሽኬንት በተካሄደው ዐውደ ጥናት፣ ሰላምን ለመፍጠር/ለማምጣት የምንጠቀምበት መንገድ መሠረት ያደረገው፣ ነገረ መለኮታዊ አስተምህሮአችንን እንደ ሆነ መለየት ቻልን። ለምሳሌ ከ23 ዓመት በፊት (1978 ዓ.ም) ክርስቲያን የነበሩት የአሜሪካ ፕሬዚዳንት ጂሚ ካርተር፣ ሙስሊም የነበሩትን የግብፅ ፕሬዝዳንት አንዋር ሳዳትንና የአይሁድ እምነት ተከታይ የነበሩትን የእስራኤል ጠቅላይ ሚኒስትር ሜናኬም ቤጊንን ወደ አሜሪካ ጋብዘዋቸው ነበር። በሜሪላንድ ግዛት በካምፕ ዴቪድ ተገናኝተው፣ ለዐሥራ ሦስት ቀናት ያህል ሰላም ሊመጣ በሚችልበት መንገድ ላይ ትኩረት ሰጥተው ተነጋግረዋል። በመጀመሪያ ያደረጉት ነገር የየእምነት ተከታዮቻቸው ለየእምነታቸው ስለ ሰላም እንዲጸልዩ ጥሪ ማቅረብ ነበር። በሰላም ድርድሩ ወቅት ካርተር መጽሐፍ ቅዱስ ይዘው ነበረና እርሳቸውና ቤጊን በጋራ የሚያምኑትን ከየብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ክፍሎች ከፍተው አነበቡ። አንዋር ሳዳትም አንድ ቀን ሙስሊሞች፣ ክርስቲያኖችና አይሁዶች ዘላቂ የሆነ ሰላም ለማምጣት በሲና ተራራ ይገናኛሉ የሚለውን ተስፋቸውን አበሰሩ። በእምነት ረገድ የየራሳቸውን ሕዝብ የወከሉት እነዚህ ሦስት መሪዎች በዚህ ሁኔታ መገናኘታቸው፣ የሰላም ሂደቱ ቀጣይ ሊሆን እንደሚችል ያመለከተ ነበር።

[1] Jimmy Carter, *Keeping Faith: Memoirs of a President* (New York: Bantam Books, 1982), 273-403. Karl-Josef Kuschel, *Abraham: Sign of Hope for Jews, Christians, and Muslims* (New York: Continuum, 1995).



የሰላሙ ጉዞና ተልእኮ እንደ ታሰበው ሊሄድ አልቻለም። ከሦስት ዓመት በኋላ አንዋር ሳዳት ተገደሉ። ቀጥሎም ስለ ሰላም ይታገሉ የነበሩት የእስራኤል ጠቅላይ ሚኒስትር ይስሐቅ ራቢን በ1995 ዓ.ም ተገደሉ። ሰላምን ለመፍጠር መከራ መቀበል አስፈላጊ ነውን? ይህ መጽሐፍ ለዚህ ጥያቄ የሙስሊሞችንና የክርስቲያኖችን ምላሽ እንዲሁም የእስልምናንና የክርስትናን የነገረ መለኮት መሠረቶች ይዳስሳል።

## የአብርሃም ቅርስ

በየሳምንቱ ሙስሊሞች በመስጊዳቸው፣ ክርስቲያኖችና አይሁዶች በየቤተ ክርስቲያኖቻቸውና በምኩራቦቻቸው የአብርሃምን አምላክ ለማምለክ ይሰበሰባሉ። እነዚህ የኅብረተሰብ ክፍሎች የአብርሃምን እምነት የሚገልጡ እንዲሁም የአብርሃም ልጆች እንደ ሆኑ ያምናሉ። እያንዳንዱ የእምነት ቡድን፣ አምልኮና ታማኝነት ፈጣሪ ለሆነው አምላክ ብቻ እንደሚቀርብ ከሙሉ ልብ ይቀበላል። ነገር ግን እነዚህ የእምነት ክፍሎች ስለ ፈጣሪ ባላቸው መረዳት እንዲሁም ራሱን በገለጠበት መንገድ ላይ ልዩነት አላቸው። ሦስቱም እምነቶች እግዚአብሔር ለሰው ልጆች እውነትን እንደ ገለጠ ያምናሉ። እነዚህ አማንያን ስለፈጣሪና ስለ እርሱ ፈቃድ በተረዱት እውነት ታማኝ ሆነው መኖር ይፈልጋሉ። ይህም ማለት አይሁዶች ለቶራ፣ ክርስቲያኖች ለወንጌል፣ ሙስሊሞች ደግሞ ለቁርአን እውነት ይገዛሉ። እነዚህ የእምነት ማዕከሎች የተለያዩ የእምነት ቡድኖችን (ማኅበረሰብን) ይኸውም እስራኤልን፣ ቤተ ክርስቲያንንና ኡማን ፈጥረዋል። በዚህ ክፍል ስለ ኡማ እና ስለ ቤተ ክርስቲያን መናገር እፈልጋለሁ።

## የሙስሊሙ ማኅበረሰብ (ኡማ)

ኡማ ማለት ሕዝብ ወይንም ማኅበረሰብ ማለት ነው። የሙስሊሙ ማኅበረሰብ ለእስልምና እምነት (ለአላህ ፈቃድ) ራሳቸውን ያስገዙና በዓለም ዙሪያ ያሉ አማኞች ኅብረት (ኡማ) ነው። እስላም ማለት ለአላህ ፈቃድ መገዛት (ሰላም) ማለት ነው። ማንኛውም ሙስሊም ዜጋ ከሆነበት ከራሱ አገር ይልቅ ለዓለም ዐቀፉ የሙስሊሙ ማኅበረሰብ ታማኝ መሆን ይጠበቅበታል። የኅብረቱ ዋና ተልእኮ እስልምናን መጠበቅና ሙስሊሞች ወደ ተሳሳተ መንገድ እንዳይሄዱ

መከላከል ነው። እስልምና የሙስሊሙን ማኅበረሰብ መሥርቶአል፤ የሙስሊሙ ኅብረተሰብ ደግሞ እስልምና እንዳይጠፋ ይጠብቃል።

በእስልምና እምነት መሠረት የሰው ዘር ለሁለት ተከፍሎአል። ለእስልምና ሕግ የሚገዙ ሰዎች ሁሉ በሙስሊሙ ማኅበረሰብ ውስጥ ሲሆኑ፣ ያልተገዙት ግን ከዚህ ማኅበረሰብ ውጪ ናቸው። የሙስሊሙ ማኅበረሰብ (ኡማ) የሚከተለውን ምስክርነት ይሰጣል:— "ላ ኢላሃ ኢለላህ ሙሐመደን ረሱሉ ለላህ"። ይህም፣ "ከአንድ አምላክ (አላህ) በቀር ሌላ አምላክ የለም፤ መሐመድ የአላህ መልእክተኛ ነው" ማለት ነው። ይህንን ምስክርነት የሚሰጡ በሙስሊሙ ማኅበረሰብ (ኡማ) ውስጥ የሚገኙ ሲሆን፣ ይህን ምስክርነት ያልሰጡ ደግሞ ከኡማው ውጪ ናቸው።

በመዲና፣ በመሐመድ አስተዳደር ሥር የነበሩ ሙስሊሞች፣ መተዳደሪያ ደንብ ወይም ሕገ መንግሥት አርቅቀዋል። ሕገ መንግሥቱ "ሙስሊሞች ከሌላው ሕዝብ የተለዩ ልዩ የኅብረተሰብ ክፍል ናቸው"[2] ሲል ያብራራል።

የእስልምና ኡማ ሁሉንም የኀይልና የሥልጣን እርከኖች እስኪቈጣጠር ድረስ ምሉዕ እንደ ሆነ አይታሰብም። ይህም ሥልጣን አገራዊ ክልል አይገድበውም። በሙስሊም አስተዳደር ሥር ባልሆኑ አካባቢዎች የሚኖሩ የብዙ ሙስሊሞች የልብ ናፍቆት፣ ሙስሊሞች የፖለቲካ የበላይነት አግኝተው የሚመሠርቱትን የሙስሊሙ ማኅበረሰብ (ኡማ) ባሉበት አካባቢ ተፈጽሞ ማየትን ነው። በካሽሚር፣ በሚንዳናኦ፣ በመቄዶኒያ በቼችኒያ የተካሄዱት ዐመፆች የዚህ ናፍቆት ውጤት ናቸው። ይሁንና እንዲህ ዐይነት የፖለቲካ አጀንዳ የሌላቸው ሙስሊሞች ያሉ ሲሆን፣ ሙስሊም ባልሆነው ማኅበረሰብ ውስጥ እምነታቸውን ጠብቀው መኖር የመረጡና ባሉበት ሁኔታ ረክተው መኖር የሚፈልጉ ናቸው።

ሙስሊሞች፣ ኡማ "መካከለኛ የኅብረተሰብ ክፍል ነው" ብለው ያምናሉ። ይህም ከዐረቢያ የተገኘ ኅብረተሰብ እንዲሁም በሌሎች የኅብረተሰብ ክፍሎች መካከል ያለ ክልል ነው። እንዲሁም እስልምና ፍጹም ሚዛናዊ እንደ ሆነ ይታሰባል። ወደ መናኝነት ወይም ደግሞ ዓለማዊነት የተሳበ ጽንፈኝነት የለበትም። ሙስሊሞች፣ የአይሁድ እምነት በዚህ ዓለም ጕዳዮች ላይ

[2] W. Montgomery Watt, *Muhammad Prophet and Statesman* (New York: Oxford University Press, 1961), 94.



ሲያተኵር፣ ቤተ ክርስቲያን ደግሞ በመጪው/በመንፈሳዊው ዓለም ጕዳይ ላይ ታተኵራለች ብለው ያስባሉ። የሙስሊሙ መካከለኛ ማኅበረሰብ ግን ይህንን ዓለምና ከሞት በኋላ ያለውን ዓለም ሚዛናዊ በሆነ መንገድ እንደሚያጣምር ይታሰባል። ኡማ፣ "ከአምላክ ወገን"[3] የሆኑ ሰዎች "ኅብረት/ጉባኤ" ነው። ይህም ወገን ምርጥ ሕዝብና በዓለም ላሉ ሕዝቦች በሙሉ የመመስከር ተልእኮ ያለው ነው። ቁርአን እንዲህ ይላል:—

> በእናንተ ላይ መስካሪ ይሆን ዘንድ ምርጥ ሕዝቦች አደረግናችሁ።
>
> (ሱራ 2+143)[4]

## ቤተ ክርስቲያን

ቤተ ክርስቲያን ማለት "ጉባኤ" ማለት ነው። በአዲስ ኪዳን መጻሕፍት፣ ቤተ ክርስቲያን የሚለው ቃል በግሪክ ቋንቋ "ኤክሌሲያ" ተብሎ ይጠራል። ይህም ለአንድ ዐይነት ዐላማ በአንድ ቦታ ተሰብስበው የተበተኑ የሰዎችን ኅብረት ያመለክታል። ቤተ ክርስቲያን ሁለት ሺህ ዓመት ገደማ የክርስቶስ የመጀመሪያ ደቀ መዝሙር የነበረው ጴጥሮስ፣ "አንተ ክርስቶስ የሕያው የእግዚአብሔር ልጅ ነህ" ሲል እንደ መሰከረው የሚመሰክሩ ሰዎች ስብስብ ናት (ማቴ 16÷16)። ምስክርነቱም የቤተ ክርስቲያን መሠረት ነው። በዓለም ዙሪያ ያሉ ቤተ ክርስቲያናት በሙሉ ኢየሱስ ክርስቶስ ጌታና አዳኝ እንደ ሆነ ይመሰክራሉ።

ሐዋርያው ጴጥሮስ ቤተ ክርስቲያንን፣ "ቅዱስ ሕዝብ" 1ጴጥሮስ 2+9 ሲል ገልጾአታል። ዳሩ ግን በአዲስ ኪዳን፣ ልክ እንደ ሙስሊሙ ማኅበረሰብ ከፖለቲካ ወይም ከግዛታዊ ሥልጣን ጋር የተያያዘ አይደለም። ቤተ ክርስቲያን እንደ ቅዱስ ሕዝብ ከሌሎች ሕዝቦች መካከል ለድነት የተጠሩ ሰዎች ኅብረት ናት። ቤተ ክርስቲያን የሚለው ቃል ክርስቶስን ጌታና አዳኝ አድርገው የተቀበሉ ሰዎችን ሁሉ የሚጠቀልል ስም ሲሆን፣ ወደ ቤተ ክርስቲያን የሚቀላቀሉትም በኀጢአታቸው ንስሓ በመግባትና በመጠመቅ ነው። ትክክለኛ አማኝ መሆናቸውም ሆነ ከክርስቶስ አካል ጋር መቀላቀላቸው የሚታወቀውም በሕይወታቸው ከሚታዩት መንፈሳዊ ፍሬዎች ነው። የግዛትና የፖለቲካ

[3] ዝኒ ከማሁ፤ 213።

[4] የእንግሊዝኛው ቅጅ እንዲህ ይላል "Thus We have appointed you a middle nation, That ye may be witnesses against mankind" (Baqara [The Cow] 2:143).

የበላይነት አመለካከት፣ ከአዲስ ኪዳን ቤተ ክርስቲያን ባሕርይ ጋር የሚቃረን ነው።

ኢየሱስ ክርስቶስ፣ ቤተ ክርስቲያን በዓለም ሁሉ የእርሱ ምስክር እንድትሆን ተልእኮ ሰጥቶአታል። ወደ ሰማይ ከማረጉ ቀደም ብሎም የሚከተለውን ትእዛዝ አስተላልፎአል:—

> እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው፣ ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው፤ እነሆም እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁል ጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ (ማቴ 28+19-20)።

ክርስቲያኖች ይህንን ትእዛዝ፣ "ታላቁ ተልእኮ" በማለት ይጠሩታል። ለሁለት ሺህ ዓመት ይህ መልእክት ቤተ ክርስቲያን ለዓለም ዐቀፍ የወንጌል ተልእኮ እንድትነሣሣ ዐቢይ ምክንያት ሆኖአል።

ወንጌል መስካሪዎች ፖለቲካውን ወይም የሌሎችን ግዛት በመቈጣጠር አልመሰከሩም። ምስክርነቱም ሰዎችን በማስገደድ ላይ የተመሠረተ ሳይሆን፣ ምስክርነቱን የሰሙ ሰዎች በሚሰጡት አሉታዊም ሆነ አዎንታዊ ውጤት ላይ መሠረት ያደረገ ነው። የአዲስ ኪዳን ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስን የድነት መልእክት በመቀበል በመሲሑ ያመኑ ሰዎች ኅብረት ናት።

## ሕዝብና መንግሥት

ሕዝብና መንግሥት ዓለም ዐቀፋዊ ማኅበረሰብ አይደሉም። መንግሥታት የእግዚአብሔርን ሥልጣንና ልዕልና ሊቀበሉም ሆነ ላይቀበሉ ይችላሉ።

ይህ አባባል ለቤተ ክርስቲያን ወይም ለሙስሊም ኡማ አይሠራም። ሁለቱም የኅብረተሰብ ክፍሎች ለአምላክ የበላይነት ወይም ሥልጣን ይገዛሉ። በአሜሪካን የነጻነት በዓል ቀን ስለ ሃይማኖት ድርጅቶችና መንግሥት ግንኙነት የተመለከቱ ሁለት ትምህርቶች ሰምቻለሁ። አንደኛውን ትምህርት የሰጣሁት ከሱኒ ሙስሊሞች መስጊድ ሲሆን፣ ሁለተኛውን ደግሞ ከጻግም መጥምቃውያን (ከሜኖናይት) ክርስቲያኖች ቤተ ክርስቲያን ነበር።



የሙስሊሞቹ ኢማም (መሪ) እንዲህ ሲል ተናገረ፣ "የአገር ፍቅር ጥሩ ነው፤ ነገር ግን ገደብ ሊኖረው ይገባል። ታማኝነታችንን ማሳየት ያለብን በመጀመሪያ ለሙስሊሙ ማኅበረሰብ ነው። ይህም ዓለም ዐቀፋዊ ኅብረት ሲሆን፣ ከአገራዊ ክልል ደግሞ ያልፋል"።

ክርስቲያኑ መጋቢም እንዲህ አለ፤ "የአገር ፍቅር የራሱ ስፍራ አለው፤ ነገር ግን ጥንቃቄ ያስፈልገዋል። ታማኝነታችን በመጀመሪያ ለክርስቶስና ለቤተ ክርስቲያን ነው። ቤተ ክርስቲያን በዓለም ዙሪያ ካሉ ሕዝቦችና ኅብረተሰቦች ውስጥ የተጠሩ ሰዎች ኅብረት ስትሆን ዓለም ዐቀፋዊም ናት"።

ስለቤተ ክርስቲያንና ስለሙስሊም ኡማ ታሪካዊ ጕዞ ከዚህ የበለጠ አስተያየት መስጠት ያስፈልጋል። ስለ ታሪካዊ ጕዞው ማጥናት የሙስሊሙና የክርስቲያኑን ማኅበረሰብ ነገረ መለኮታዊ አስተምህሮና ተልእኮ ለመረዳትና በዓለም ማኅበረሰብ ውስጥ ሁለቱም ቡድኖች እንዴት አብረው እንደሚኖሩ ለማወቅ ይረዳል።

## ቤተ ክርስቲያን በሕዝቦች መካከል

በመጀመሪያ ስለቤተ ክርስቲያን ታሪክ በአጭሩ እንቃኝ። ቤተ ክርስቲያን "ወደ ዓለም ሂዱ፤ ወንጌልን ለፍጥረት ሁሉ ስበኩ" የሚለውን የክርስቶስን ትእዛዝ መሠረት በማድረግ፣ በዓለም ዙሪያ ስፍታለች። በሐዋርያት ዘመንም ከስፔን እስከ ሕንድ፣ ከሰሜን አፍሪካ እስከ ማዕከላዊ አውሮፓ ባሉት ኅብረተሰቦች ውስጥ እጅግ ከፍተኛ ተቀባይነት በማግኘት መሠረቱን ጥሎ ነበር። ቤተ ክርስቲያን ፈጣን ዕድገት ያሳየችውም በመከራ ውስጥ ነበር።

አንዳንዴም የነገሥታት ቍጣ በቤተ ክርስቲያን ላይ በኀይል ይነድ ስለነበር፣ የተወሰኑ ሐዋርያት ተገድለዋል። ይህ ተቃውሞ የመጣው ለምን ይሆን? የተቃውሞው ምክንያት ክርስቲያኖች፣ "ክርስቶስ የሁሉ የበላይ ባለሥልጣን ነው" ብለው በመመስከራቸው ነው። የተለያዩ ግዛቶችና ሕዝቦች ለሚያመልኳቸው አማልክትና ለሚሰግዱላቸው ሮማውያን ነገሥታት፣ ክርስቲያኖች ለመስገድም ሆነ አምልኮ ለማቅረብ ፈቃደኛ ባለመሆናቸው እንደ ከሐዲ ተቈሩ። ከዚህ የተነሣ ተሰደዱ። በሮማ ግዛተ ዐፄም ለዘጠኝ ዓመት (ከ303-312 ዓ.ም) በጣም ዘግናኝ የሆነ ስደትና እንግልት ደርሶባቸዋል።

## የቈስጠንጢኖስ አሻራ በምዕራቡ ቤተ ክርስቲያን

ከዚያ በኋላ ስደቱ አበቃ፡፡ የሮማ ንጉሠ ነገሥት የነበረው ቈስጠንጢኖስ ከቤተ ክርስቲያን ጋር ሰላምን በመፍጠር በ313 ዓ.ም. የመቻቻል ዐዋጅ አወጣ፡፡ በዚህ መልኩ በወቅቱ የነበረው የክርስቲያኖች ስደት ፍጻሜ አገኘ፡፡ ቈስጠንጢኖስ ከዚህ ያለፈም ሥራ ሠርቶአል፡፡ የግዛቲቱ መሪዎች ወዲያውኑ ክርስቲያኖችን መደገፍ ጀመሩ፤ ንጉሡም በቤተ ክርስቲያን ጒዳዮች በመሳተፉ፣ በክርስቶስ ማንነት ላይ የነበሩ አንዳንድ ያልጠሩ ምልከታዎችን ለማጥራት የጳጳሳት ጉባኤ በ325 ዓ.ም ላይ በኒቂያ ሰበሰበ፡፡

## ስደት በዳርቻዎች አካባቢ

በምሥራቅ እስያ አካባቢ የነበረው ስደት ብዙ ክርስቲያኖችን ያወከ ነበር፡፡ ይህ ያለመረጋጋት ውሉ አድሮ ከእስልምና መስፋፋት ጋር ግንኙነት ነበረው፡፡ ይህ ምን ማለት እንደ ሆነ በተለይም በሮም ግዛቶች ድንበር አካባቢ ለነበሩ ክርስቲያኖች መረዳቱ ትልቅ ጠቀሜታ አለው፡፡ ከኒቂያ ጉባኤ በኋላ የሮም መንግሥትና የምዕራቧ ቤተ ክርስቲያን ጳጳሳት፣ በቤተ ክርስቲያንና በመንግሥት መካከል ተገቢ ያልሆነ ግንኙነት እንዲመሠረት አደረጉ፡፡ ብዙም ሳይቆይ ጳጳሳቱ፣ ሰዎች የቤተ ክርስቲያንን አስተምህሮ እንዲቀበሉ የመንግሥትን ኀይል በመጠቀም ማስገደድ ጀመሩ፡፡

በሰሜን አፍሪካ፣ በግብፅና በምሥራቃዊ እስያ ያሉት ቤተ ክርስቲያናት ለዚህ ችግር የተጋለጡ ነበሩ፡፡ ለምሳሌ በሰሜን አፍሪካ በበርበር ሕዝቦች ውስጥ ዶናቲዝም የሚባለው ቡድን ከማንም ነጻ በሆነ መንገድ ከቤተ ክርስቲያን ውጭ በራሱ እንቅስቃሴ የሚያደርግ ታዋቂ ቡድን ነበር፡፡ ይህች አገር በቀል የሰሜን አፍሪካ ቤተ ክርስቲያን፣ በሮም መንግሥትና በቤተ ክርስቲያን ጥምረት ስደት እንዲሁም መገለል ደርሶባታል፡፡ ሁኔታውን ለዚህ ያደረሱት ጒዳዮች ውስብስብ ነበሩ፡፡ የሐሰት አስተምህሮዎች የችግሮቹ አካል ነበሩ፡፡ የሆነ ሆኖ የግጭቱ ዋነኛ ምክንያት የሮም መንግሥትም ሆነ ቤተ ክርስቲያን፣ በሮም ግዛት ሥር ባሉ አካባቢዎች ከእነርሱ ትእዛዝ ውጪ ቤተ ክርስቲያን እንዲኖር አለመፈለጋቸው ነው[5]፡፡ በ7ኛው ክፍለ ዘመን የሙስሊሙ ጦር ወደ ሰሜን

[5] W. H. C. Frend, *The Early Church* (London: Hodder & Stoughton, 1971), 93, 164.



አፍሪካ ሲዘምት የገጠመው፣ የተዳከመች ቤተ ክርስቲያን ነበር፡፡ ለቤተ ክርስቲያኒቱ መድከም ምክንያት የነበረው፣ ሁለት ምዕተ ዓመታት ቀደም ብሎ ክርስቲያን መንግሥት የነበረው የሮም መንግሥት፣ አገር በቀልና ራሳቸውን በራሳቸው የሚያስተዳድሩ ቤተ ክርስቲያናት እንዳይፈጠሩ በመከልከሉ ነው፡፡

## መረር ስደት በፐርዣያ

የሮም መንግሥትና የምዕራብ አውሮፓ ጳጳሳት ኅብረት መፍጠራቸው፣ በምሥራቅ እስያ ባሉ ቤተ ክርስቲያናት ላይ ጒጂ ውጤት አስከትሏል፡፡ ከክርስቶስ ልደት በኋላ ባሉት ሦስት መቶ ዓመታት ስደት የነበረባቸው በሮም ግዛት ሥር የነበሩ ቤተ ክርስቲያናት ነበሩ፡፡ ነገር ግን የቈስጠንጢኖስ ክርስትናን መቀበልና የመንግሥትና የጳጳስ ኅብረት በምዕራብ በመፈጠሩ ምክንያት በምሥራቅ እስያ የነበሩት አብያተ ክርስቲያናት የአሳዳጆች ቍጣ ያርፍባቸው ጀመር፡፡ በቈስጠንጢኖስ ሥር ባለው በምዕራቡ ክፍል ክርስትና የመንግሥት ሃይማኖት በመሆኑ፣ ለምዕራቧ ቤተ ክርስቲያን የሰላም ዘመን ሆነ፡፡ የኢዶሳው ጳጳስ ማር ያዕቆብ ሲጽፍ እንዲህ ብሏል፣ "ቈስጠንጢኖስ የአሸናፊዎች መሪ ነገሠ፤ አሁን ደግሞ የንጉሡ መስቀል በዘውዱ ላይ ከፍ አለ"[6]፡፡

በፐርዥያ ግን እንዲህ ዐይነት ደስታ አልነበረም፤ ምክንያቱም የፐርዥያ ቤተ ክርስቲያን በሁለት ግዛቶች በተፈጠረ ግጭት ተወጥራ ነበርና፡፡ ለሦስት ምዕተ ዓመት የፐርዥያና ዐልፎ ዐልፎ እርስ በርሳቸው የሮም ገዢዎች ይዋጉ ነበር፡፡ ቆይቶም ሌላ የጦርነት አደጋ ሲያንዣብብ፡፡ ቈስጠንጢኖስ ለፐርዥያው ንጉሥ ዳግማዊ ሻፑር፣ እንዲህ ሲል ጻፈለት፣ "ጥቂት በማይባሉ የፐርዥያ ክፍሎች ውስጥ ክርስቲያኖች እንዳሉ ስሰማ ደስ ብሎኛል...አንተ ጠንካራ ሃይማኖተኛ ስለሆንህ እንድትንከባከባቸው አሳልፌ ሰጠሁህ፤ በአንተም ጥበቃ ሥር ይሁኑ"[7]፡፡ ይህ ለፐርዥያ ንጉሥ ላሳሃ የላከው መልእክት አንድ ነው፡፡ ይኸውም፤ የዞሮአስትሪያን እምነት የምትከተለውን ፐርዥያን በስውር ለማፍረስ የተጐነጐነ ሤራ እንዲሁም ክርስቲያኖች የሮም ዐላማ አስፈጻሚዎች ናቸው ማለት ነው፡፡

[6] Samuel Hugh Moffett, *A History of Christianity in Asia: Beginnings to 1500,* vol 1 (Maryknoll, N. Y.: Orbis, 1998), 138.

[7] Theodoret, *Ecclesiastical History* 1, quoted in Moffett, 144.

ከሃያ ዓመት በኋላ ቈስጠንጢኖስ ከጳጳሳት ጋር በመሆን በፐርዥያ ላይ ጦሩን አዘመተ:: በጊዜው የቤተ ክርስቲያን የታሪክ ጸሓፊ የነበረው አውሳብዮስ ጳጳሳት ቈስጠንጢኖስን ያጀቡት፣ "እግዚአብሔር ድል እንዲሰጠው በጸሎት ለመርዳት ነው" ሲል ጽፎአል[8]::

ከዚህ የተነሣ የፐርዥያውያን ቍጣ በክርስቲያኖች ላይ ያለ ልክ ነደደ:: ከሃያ ዓመታት በላይ በፐርዥያ ግዛት ያሉት ክርስቲያኖች በረቀቀ ዘዴ ታደኑ፤ ተገረፉ፤ ተገደሉ:: በዚህ ታላቅ ስደት የፐርዥያ ቤተ ክርስቲያን ወደ መጥፋት ደረሰች:: ከዚያ በኋላም ስደቱ ካስከተለው ጥፋት ማገገም አልተቻለም::

## በምሥራቅ እስያ የነበሩት ቤተ ክርስቲያናት

ይህ ዐይነቱ የነገሮች አካሄድ በምሥራቅ እስያ የነበረችው ቤተ ክርስቲያን ወዲያውኑ ከምዕራብ ቤተ ክርስቲያን ራስዋን ማራቅ እንዳለባት ግልጽ አደረገላት:: ቈስጠንጢኖስና እርሱን ተከትለው የተነሡ መሪዎች፣ ኋላም ቅዱስ የሮም ግዛት የምሥራቋ ቤተ ክርስቲያን የምዕራቧ ቤተ ክርስቲያን አካል ስለመሆኗ አቋሟን እንድትገልጽ ግፊት ተደርጉባታል:: ምንም እንኳ ከምዕራባውያን ክርስቲያኖች ጋር አንድነቷን ብትገልጽም ንስጥሮሳውያን ክርስቲያኖች እንደ መናፍቃን ተቈጥረው ነበር[9]::

ጻፉ ግን አረንድ ቲኦዶር ቫን ሊወን የተባለው የደች የሃይማኖት ታሪክ ጸሓፊ፣ በቤተ ክርቲያን መካከል የነበረው ክፍፍል ለእስልምና መስፋፋት በር እንደ ከፈተ ይናገራል:: እንዲህ ሲልም ጽፎአል፣ "እስላማዊ ኀይሎች...ከየትኛውም የክርስቲያን የመናፍቅ አስተምህሮ ቡድኖች በጣም በላቀ መልኩ ፀረ-ቢዛንታይን አስተምህሮ አሠራጭተዋል"[10]::

ሆኖም በምዕራቧ ቤተ ክርስቲያንና መንግሥት ላይ ከነበረው የተቃውሞ መግለጫ የተነሣ፣ ሁሉም ክርስቲያኖች ወደ እስልምና አልተለወጡም::

[8] Eusebius, *Life of Constantine*, 4:56, quoted in Moffett, 138.

[9] Arend Theodoor van Leeuwen, *Christianity in World History, The Meeting of Faiths East and West*, translated from Dutch by H. H. Hoskins (New York: Charles Scribner's Sons, 1964), 210.

[10] ዝኒ ከማሁ፤ 211::



አንዳንድ ጊዜም የምሥራቅ እስያ ቤተ ክርቲያናት፣ ወንጌልን በማሠራጨት የራሳቸውን እምነት ተገቢነት ይገልጡ ነበር:: ለአንድ ሺህ ዓመታት ያህል ሚስዮናውያንን ወደ ማዕከላዊው የእስያ ክፍል በመላክ የምሥራቹን ቃል አሠራጭተዋል:: እነዚህ ጥቂት ቤተ ክርስቲያናት የመንግሥት አጀንዳ ያልያዘ የወንጌል ተልእኮ ፈጽመዋል:: ከቈስጠንጢኖስ በኋላ ለመስፋፋት ሲባል ቤተ ክርስቲያንና መንግሥት አብረው ከሚያዘጋጁት ሚስዮናዊ አገልግሎት ጋር ሲነጻጸር ከፍ ያለ ልዩነት ነበረው::

የምሥራቅ ቤተ ክርስቲያናት ሁሌም በቍጥር አነስተኛ፣ አብዛኛውን ጊዜ የሚሰደዱና አንዳንዴም እስከ መጥፋት የሚደርሱ ናቸው:: ይሁንና ከእነዚህ ውስጥ የተወሰኑት ለአንድ ሺህ ዓመታት ያልተቋረጠ የወንጌል ሥርጭት እስከ ቻይና ድረስ በሚዘልቅ አገልግሎት ይሰጡ ነበር:: እጅግ ትኩረት የሚስብ ታሪክ ነው:: የፐርዥያ ቤተ ክርስቲያናት በሙስሊሞች ቍጥጥር ሥር ከወደቁም በኋላ፣ ለአምስት መቶ ዓመታት ለዓለም ሁሉ ወንጌልን ማሠራጨታቸውን ቀጥለዋል::

## ክፍፍል በምዕራቡ ቤተ ክርስቲያን

ውሎ አድሮ ስለተፈጠሩት ክሥተቶች አጭር ዳሰሳ እናድርግ:: በ1054 ዓ.ም የሮም ግዛት ምዕራቡ ክፍል ሮምና የምሥራቁ ክፍል ቢዛንታይን በመባል ለሁለት በመከፈሉ በቤተ ክርስቲያንም ክፍፍል ተፈጠረ:: የምዕራቡ ቤተ ክርስቲያን መከፈል፣ የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያንና የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን መፈጠር ምክንያት ሆኖአል::

ይሁን እንጂ እነዚህ የተለያዩ አብያተ ክርስቲያናት፣ የመንግሥትና የቤተ ክርስቲያን አንድነትን ለመጠበቅ ሞክረዋል:: ስለዚህ የምዕራቧ ቤተ ክርስቲያን ሁል ጊዜ ራሷን እንደ መንግሥት ትቈጥራለች:: ይህም ማለት ከቈስጠንጢኖስ በኋላ አብያተ ክርስቲያናት ካቶሊክ፣ ኦርቶዶክስ ወይም ፕሮቴስታንት በሚል ጐራ ቢከፈሉም መንግሥትና ቤተ ክርስቲያን የተቈራኙ ተቋማት ነበሩ::

በዘመናችን የተከሠቱ ሦስት ኩነቶችን እንደ ምሳሌ ልጥቀስ፤ አንደኛ፤ የራሺያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ጳጳሳት ራሺያ በቼችኒያ ዐማፅያን ላይ ድል እንድታገኝ ጸልየዋል:: ሁለተኛው፤ ክርስቲያን ሰርቦች ባልካንን ከሙስሊሞች ለማስወገድ ተዋግተዋል:: ሦስተኛው፤ የአሜሪካ የወንጌላውያን አብያተ

ክርስቲያናት መሪዎች፣ በኢራቅ ላይ የተደረገው ጦርነት ፍትሐዊ በመሆኑ ክርስቲያኖች ድጋፍ ሊሰጡ ይገባል ሲሉ ተከራክረዋል።

በዘመናችንም እንኳ የምሥራቋ ቤተ ክርስቲያን ከምዕራቧ ቤተ ክርስቲያን ያላትን ግንኙነት በተመለከተ አቋሟን እንድትለይ የግድ ይሆንባታል። በቅርቡ አሜሪካ የፀረ-ሽብርተኝነትን ዘመቻ እየመራች ትገኛለች። በዘመቻው የተሳተፉ እንደ አንዳንድ ክርስቲያኖች አነጋገር ከሆነ፣ የምሥራቋ ቤተ ክርስቲያን ከምዕራቧ ቤተ ክርስቲያን የተለየች መሆኗን ግልጽ እንድታደርግ የሚያደርጓት ናቸው። በዋሽንግተን ዲ. ሲ. የተቃጣው አደጋ አንዳንድ ጊዜ በምሥራቅ በሚገኙት ክርስቲያኖች ላይ ሲፈጸም የነበረ ነው። የቈስጠንጢኖስ ወይም የ11ኛው ክፍለ ዘመን የመስቀል ተዋጊዎች፣ የመስቀል ምልክት ይዘው ወደ ምሥራቅ ያደረጉት ወረራ ዛሬም ይታያል። የዘመኑ ቈስጠንጢኖሶች ወይም የመስቀል ጦርነት ተዋጊዎች፣ የምሥራቅ ቤተ ክርቲያናትን ለአደጋ እያጋለጡ ናቸው[11]። በሚሊዮን የሚቈጠሩ እስያውያን በምዕራባውያን አካሄድ ግራ ስለተጋቡ እስልምናን እንደ አማራጭ ለመቀበል እያሰቡ ናቸው።

## አማራጭ መንገዶች

በምዕራቧ ቤተ ክርስቲያን ውስጥም በቈስጠንጢኖስ የተጀመረውን የቤተ ክርስቲያንና የመንግሥት ኅብረት የማይቀበሉ ክርስቲያኖች አሉ። ይህንን አማራጭ የሚቃወሙ ክርስቲያን ቡድኖች፤ ለምሳሌ የሰሜን አሜሪካ መጥምቃውያን ቤተ ክርስቲያናት በአሜሪካ ሕገ መንግሥት፣ መንግሥትና ቤተ ክርስቲያን እንዲለያዩ የማይናቅ ሚና ተጫውተዋል።

በ16ኛው ክፍለ ዘመን በፕሮቴስታንት ተሐድሶ የተፈጠሩ ዳግም መጥምቃውያን (አናባፕቲስቶች) የአዲስ ኪዳን ቤተ ክርስቲያን ለመሆን በጽናት ታግለዋል። እነዚህ ኅብረቶች በሕይወታቸው ሁሉ የክርስቶስ ደቀ መዝሙር የመሆን ራእይ ሰንቀው ነበር። የኢየሱስ እምነትንና ሥነ ምግባርን እንዲሁም ሰላምን የመፍጠር ጥሪን ጨምሮ ተግባራዊ ለማድረግ ሞክረዋል። እርግጥ ነው፤ ይህ ቤተ ክርስቲያንና መንግሥት መለያየት አለባቸው ማለት ነው።

---

[11] Alex Awad, "Learning to Live with Muslims," *The Mennonite* (19 November 2002): 8-10.



# ኡማውና ሕዝቦቹ

ከዚህ በመቀጠል የእስልምናን ታሪካዊ ጕዞ በአጭሩ እንመለከታለን። ከ610 ዓ.ም ጀምሮ ለዐሥራ ሁለት ዓመት መሐመድ በመካ እስልምናን ሰብከዋል። ከፍተኛ የሆነ ስደትም ገጥሞአቸዋል። በ622 ዓ.ም 250 ማይል በስተ ሰሜን ወደምትገኘው መዲና ከተማ መሐመድና ተከታዮቻቸው በድብቅ ተሰደዋል። ይህም ስደት (ሒጅራ) የሙስሊሞች አዲስ ምዕራፍ መጀመር ምልክት ሆኖአል።

ሒጅራ በጣም ጕልሕ ሚና ያለው ለምንድን ነው? ሒጅራ በጣም ወሳኝ ምዕራፍ የሆነበት ምክንያት፣ መሐመድ በመዲና ጠንካራ የሙስሊም ማኅበረሰብ በመመሥረት የነቢይነት አገልግሎታቸው እንዲቀጥል ስላደረጉ ነው። የሙስሊሙን ግዛት ለመመሥረት፣ ከጥቃት ለመከላከልና ወደ ተለያየ አቅጣጫ ለመስፋፋት የሚያስችሉ ፖለቲካዊ፣ ምጣኔ ሀብታዊና ወታደራዊ ተቋማትን አቋቁመዋል። በመዲና የነበረው መሠረት በጣም ውጤታማ ነበር። በዐሥር ዓመታት ውስጥ መካን ጨምሮ አብዛኛው የዐረቢያ ክፍል በሙስሊሞች ቊጥጥር ሥር ወድቋል።

መሐመድ ከመሞታቸው (632 ዓ.ም) በፊት ወደ ጐረቤት አገሮች ማለትም ወደ አቢሲኒያ፣ ፐርዥያና ቢዛንታይን መልእክተኞችን ልከዋል። መልእክተኞች የላከበትም ዐላማ፣ የእስልምና ግዛትን ከዐረቢያ ዐልፎ ወደ ጐረቤት አገሮች ለማስፋፋት ነበር። በተወሰኑ ዓመታት ውስጥ የሙስሊም ሰራዊት የዐረብያን ጠረፍ አካባቢዎች ተቈጣጠረ። የዘመናችን ሙስሊም ዐቃቤ እምነቶች (apologists) እነዚህ አካባቢዎች የተያዙት ራስን ለመከላከል ነው ይላሉ[12]፤ ልክ በቊርአን አንቀጾች እንደ ተገለጸው ማለት ነው:—

> እነዚያንም የሚጋደሉዋችሁን (ከሓዲዎች) በአላህ መንገድ ተጋደሉ፤ ወሰንንም አትለፉ፤ አላህ ወሰን አላፊዎችን አይወድምና። ባገኛችኋቸውም ስፍራ ሁሉ ግደሉዋቸው፤ ከአወጧችሁም ስፍራ አውጧቸው፤ መከራም ከመግደል ይበልጥ የበረታች ናት፤ በተከበረው መስጊድም ዘንድ በርሱ ውስጥ እስከሚጋደሏችሁ ድረስ አትጋደሉዋቸው፤ ቢጋደሉዋችሁም ግደሉዋቸው፤ የከሐዲዎች ቅጣት እንደዚህ ነው። ቢከከለከሉም አላህ መሓሪ አዛኝ ነው። እውከት እስከማይገኝና

---

[12] Badru D. Kateregga and David W. Shenk, *A Muslim and a Christian in Dialogue*, (Scottdale, Pa.: Herald Press, 1997), 108-9.

> ሃይማኖት ለአላህ ብቻ እስከሚኾን ድረስ ተጋደሉዋቸው፤ ቢከለከሉም ወሰንን ማለፍ፤ በበዳዮች ላይ እንጂ የለም (ወሰን አትለፉባቸው) (ሱራ 2፥190-193 በቅንፍ ያለውን ይጨምራል)፡፡

ሆኖም ግን ከመሐመድ ሞት በኋላ የአስተዳደር መዋቅሩን ለማጥራትና ለማጠናከር ሙስሊሞች ጥረት እያደረጉ በነበሩበት ወቅት፣ በሙስሊሞች መካከል የነበረውን ውጥረት በወታደራዊ ድሎች መሸፈን አልተቻለም፡፡ በመጀመሪያዎቹ ዘመናት ሙስሊሞችን እንደ ሙስሊም ማኅበረሰብ ማደራጀት በራሱ ትልቅ ፈተና ነበር፡፡ ከመሐመድ ሞት በኋላ በነበሩት 29 ዓመታት ምሪትን በትክክል ባገኙ መሪዎች (ካሊፎች) ሙስሊሞች ተመርተዋል፡፡ በእነዚህ ዘመናት የሙስሊሙ ማኅበረሰብ አስቸጋሪ የሆኑ ፈተናዎች ገጥመውት ነበር፡፡ የመጨረሻዎቹ ሁለት ከሊፋዎች ማለትም ኡስማንና ዓሊ ተገድለዋል፡፡

ከዚያ በኋላ እስካሁን ድረስ ፈውስ ያላገኘው የሱኒና የሺአ ሙስሊሞች ክፍፍልና የእርስ በርስ ጦርነት ተከሠተ፡፡ ሺአ ሙስሊሞች የሙስሊሙን ማኅበረሰብ ሊመሩ የተገባቸው የመሐመድ ዘሮች ናቸው የሚል ጠንካራ አቋም ሲኖራቸው፣ በአንጻሩ ሱኒዎች ደግሞ መሪዎች መመረጥ ያለባቸው በሙስሊሞች ነው የሚል እምነት አላቸው፡፡ የሆኖ ሆኖ ምንም እንኳ በአስተዳደሩ ውስጥ ጠብ ቢኖርም እስከ ዓሊ ዘመን (661 ዓ.ም) የመካከለኛው ምሥራቅ በአጠቃላይ ማለትም ከግብፅ እስከ ፐርዥያ በሙስሊሞች እጅ ወድቋል፡፡

ከመሐመድ ሞት በኋላ ባሉት ስድስት ዓመታት (638 ዓ.ም) ብቻ የሙስሊም ሰራዊት ኢየሩሳሌምን ተቈጣጥሮአል፡፡ ሙስሊሞች የሙስሊም ኡማ በዓለም ላሉ ሕዝቦች በሙሉ ምስክር ሊሆን ይገባል ብለው ያምናሉ፡፡ የሙስሊሙ ግዛት ለክርስቲያኖችና ለአይሁዶች ጕልሕ ሚና ወዳላት ከተማ (ኢየሩሳሌም) መዝለቁ ከሙስሊም ተልእኮ ጋር የሚስማማ ነው፡፡

## ከብ ጣሪያ ያለው መስጊድ (አል-አቅሳ)

ካሊፍ አብድ አል-ማሊክ በተልእኳቸው ውስጥ በራስ የመተማመን መንፈስ ስለነበራቸው በ691 ዓ.ም አንደኛውና ሁለተኛው የአይሁድ ቤተ መቅደስ በተሠራበት ቦታ ላይ ከብ ጣራ ያለው የድንጋይ መስጊድ አነጹ፡፡ መስጊዱ የተሠራውም ሃይማኖታዊ ጕዞ የሚደረግበት ቦታ እንዲሆን ታስቦ ነው፡፡ የሕንፃው ዲዛይን የሶሪያ ቤተ ክርስቲያንን ይመስላል፡፡ እስካሁን ድረስ ያለ



አስደናቂ ሕንፃ ነው፡፡ መስጊዱም በኢየሩሳሌም ከሚገኙ ቤተ ክርስቲያናት እንዲሁም ሕንፃዎች ከፍ ተደርጐ ተሠርቶአል፡፡ ሕንፃው በጥሩ ሁኔታ የተሠራ ሲሆን፣ በአሁን ጊዜ ከሚገኙ ሕንፃዎች ጥንታዊ የሆነ የሙስሊም ሕንፃ (መስጊድ) ነው፡፡

ይህ መስጊድ የተሠራው ያለምንም ጥርጥር እስልምና ከአይሁድና ከክርስትና እምነት በላይ የላቀና የሚበልጥ መሆኑን ለማሳየት ነው፡፡ ይህም መስጊድ የተሠራው አል-አቅሳ (በጣም ሩቅ በሆነ ስፍራ) ሲሆን፣ መሐመድ በተአምራዊ ሁኔታ በአንድ ሌሊት ከመካ ወደ ኢየሩሳሌም ባደረጉት ጕዞ (ሚዕራጅ) ያረፉበት ቦታ ነው ተብሎ ይታመናል፡፡ ሙስሊሞች መስጊዱ ከተሠራበት ቦታ ቀጥታ ወደ ሰማይ በማረግ የነቢያዊ ተልእኮአቸውን እንዲቀጥሉና እንዲሰብኩ ከአላህ ዘንድ አበረታች መልእክትን ተቀብለዋል ብለው ያምናሉ፡፡ በመስጊዱ ውስጥ ተቀርጸው የሚገኙት ጽሑፎች እስልምና የአይሁድና የክርስትና እምነትን ይበልጣል እንዲሁም ይተካል የሚለውን የሙስሊሞችን እምነት ያሳያል[13]፡፡

እስልምናና መሐመድን የሚያሞጋግሱ፣ ብዙ ጽሑፎች በመስጊዱ ውስጥ በተለያዩ ቦታዎች ተጽፈው ይገኛሉ፡፡ ከጕልላቱ ሥር ከሱረቱ አል-ኒሳእ የተጠቀሰው እንዲህ ይላል:—

> "እናንተ የመጽሐፉ ሰዎች ሆይ! በሃይማኖታችሁ ወሰንን አትለፉ፤ በአላህም ላይ እውነት እንጅ አትናገሩ፤ የመርየም ልጅ አልመሲሕ ዒሳ የአላህ መልእክተኛ ወደ መርየም የጣለው (የኹን) ቃሉም ከእርሱ የሆነ መንፈስም ብቻ ነው፤ በአላህና በመልእክተኞቹም እመኑ፤ (አማልክት) ሦስት ናቸው አትበሉም፤ ተከልከሉ፤ ለእናንተ የተሻለ ይኾናልና፤ አላህ አንድ አምላክ ብቻ ነው፡፡ ለእርሱ ልጅ ያለው ከመሆን የጠራ ነው፡፡ በሰማያትና በምድር ያሉ ሁሉ የእርሱ ነው፡፡ መመኪያም በአላህ በቃ" (ሱራ 4፥171 በቅንፍ ያለውን ይጨምራል)፡፡

## ክርስቲያኖች በሙስሊም አስተዳደር ሥር

የሙስሊም ገዢዎች ኢየሩሳሌምን መያዛቸው፣ በሙስሊም ሰራዊት ከተገኙት በርካታ አስደናቂ ድሎች መኻል አንዱ ነበር፡፡ ከሒጅራ አንድ መቶ ዓመታት

---

[13] Andrew Rippin, *Muslims: Their Religious Beliefs and Practices* (London: Routledge, 2002), 63-65.

በኋላ፣ የምድራችን ነዋሪ ከነበረው የክርስቲያን ኅብረተሰብ ውስጥ፣ ግማሹ በእስልምና ቍጥጥር ሥር ውሏል:: አሳዛኙ ገጽታ፣ ክርስቲያኖችና አይሁዶች ሙስሊማን በሆኑ ክልሎች ውስጥ እንዲኖሩ የተደረገው፣ ከሌላው ኅብረተሰብ በተለየ ሁኔታ ጥበቃ እየተደረገላቸው መሆኑ ነው:: ይህም አስተዳደራዊ አካሄድ "ዚሚ" ተብሎ ይጠራል:: የሚቀጥለው ምዕራፍ በዚህ ጉዳይ ላይ ማብራሪያ ይሰጣል:: የሙስሊም ሰራዊት የተቀሩትን አካባቢዎች ለመቈጣጠር፣ ወደ ምሥራቅና ምዕራብ ተንቀሳቅሷል:: በአራት የትውልድ ዘመናት ውስጥ እስላማዊው አስተዳዳር፣ ከኢንደስ ወንዝ እስከ መካከለኛው ምሥራቅ እንዲሁም ሰሜን አፍሪካን አቋርጦ እስከ ስፔንና ደቡባዊ ፈረንሳይ ድረስ መሠረቱን ጥሎአል::

## የክርስቲያኖች ቍጥር ከፉኛ መመናመን

ሙስሊሞች ለረጅም ጊዜያት በገዙባቸው አካባቢዎች ቤተ ክርስቲያናት ለሙስሊም ኡማ ታማኝነታቸውን እንዲያረጋግጡ በተደረገው እንቅስቃሴ፣ የክርስቲያኖች ቍጥር ክፉኛ ሊመናመን ችሎአል:: እንዲያውም በየመን፣ በሰሜን አፍሪካና በሰሜናዊ ሱዳን የሚገኙ ጥንታዊ ቤተ ክርስቲያናት ሙሉ ለሙሉ ጠፍተዋል:: የቤተ ክርስቲያናቱ መጥፋት በጥቂት ዓመታት ውስጥ የተፈጸመ ክሥተት ግን አይደለም:: ቤተ ክርስቲያናት የሚደርስባቸውን ከፍተኛ ተጽእኖዎች በመቋቋም ለብዙ ዓመታት በክርስትናቸው ጸንተው ቆመዋል:: ነገር ግን የማታ ማታ፣ የሰሜን አፍሪካ ቤተ ክርስቲያናትን ጨምሮ፣ ሰማዕት ሆነው የቆዩት እነዚህ ቤተ ክርስቲያናት በእስልምና ተጽእኖ ጠፍተዋል::

በጣም አስገራሚው ጉዳይ፣ እስልምና እነዚህን አካባቢዎች በሚቈጣጠርበት ወቅት፣ በየትኛውም ቤተ ክርስቲያን ውስጥ መጽሐፍ ቅዱስ በአገሬው (በአካባቢው) ቋንቋ አለመተርጐሙ ነው:: መጽሐፍ ቅዱስ በራሳቸው ቋንቋ የነበራቸው ቤተ ክርስቲያናት ግን፣ ፈተናውን በጽናት ዘልቀው ዐልፈዋል:: ከእነዚህም ውስጥ ግብፅ፣ ሶሪያና ኢትዮጵያ ይጠቀሳሉ:: በተቃራኒው የሰሜን አፍሪካ ቤተ ክርስቲያናት፣ ወደ ላቲን የተተረጐመውን መጽሐፍ ቅዱስ ይጠቀሙ ነበር:: የላቲን ቋንቋ የአውሮፓ ቅኝ ገዢዎች ቋንቋ ነው:: ላቲን የሰሜን አፍሪካ ቋንቋ ባለመሆኑ ምክንያት፣ ቤተ ክርስቲያን አገር በቀል በሆነ መልኩ በኅብረተሰቡ ዘንድ ዘልቃ እንዳትገባ ማነቈ ከመሆኑም በላይ፣ ወንጌል በሰሜን አፍሪካውያን ባህልና አመለካከት ውስጥ ሰርጾ እንዳይገባ ደንቃራ ፈጥሮአል::



## ከሥልጣኔ ጋር የተደረገ ግብግብ

በመጀመሪያዎቹ ዘመናት እስልምና ከዐረቢያ ምድር ወደ ሌሎች አካባቢዎች የተስፋፋው ሥርዐትን በጠበቀ መልኩ ነው:: የመስፋፋት ዘመቻው የተካሄደው ንብረትና ሕዝብን አውዳሚ በሆነ መልኩ አልነበረም:: በተጨማሪም በኡማያድና በአባሲድ ሥርወ መንግሥት ወቅት የነበረው መስፋፋት፣ ሌሎችን የእምነት ቡድኖች ፈጽሞ በማጥፋት ላይ ያነጣጠረ ሳይሆን፣ ሌሎችን የማቀፍ መርሕ የተከተለ ነበር[14]:: የአባሲድ ካሊፎች (ሥርወ መንግሥት) ወርቃማው የእስልምና ዘመን ተብሎ የሚጠራውን ከስምንተኛው እስከ ዐሥራ አንደኛው ምዕተ ዓመት ያሉትን ዘመናት መርተዋል:: ታላላቅ የትምህርትና የባህል ማዕከሎች ናቸው የሚባሉት የክርስቲያኖች፣ የዕብራውያን፣ የግሪካውያን (የሔለኒዝም)፣ የአርመናውያን፣ የግብፃውያን እንዲሁም የአሲሮ-ባቢሎናውያን አስተምህሮ እስልምና በተስፋፋባቸው አካባቢዎች እንዲካተት ተደርጓል[15]::

የሙስሊሞች የአራት መቶ ዓመታት የበላይነት ዘመን፣ በተለይም በተለያዩ ዘርፎች ያስመዘገቡት የቴክኖሎጂ ዕድገት፣ ከዚያ በኋላ ላለው የእስልምና እንቅስቃሴ አስተዋጽኦ አድርጓል:: አውሮፓውያን ወደ "ጨለማው ዘመን" ሲገቡ፣ በተቃራኒው ሙስሊሞች በራሳቸው በተጀመሩና በራሳቸው በሚመሩ የተለያዩ ጥናቶችና ምርምሮች ውስጥ ገብተዋል፤ ይህም የእስልምና ወርቃማ ዘመን ነው::

አስገራሚው ጉዳይ ግን እስልምና ሥር እየሰደደና እየተስፋፋ ሲመጣ፣ የምርምር ሥራውና ዕድገቱ እየጠፋ ሄደ:: እንዲያውም በሙስሊሞች ተቀባይነት ሊኖራቸው የማይችሉ የጥናት ዘርፎችም ነበሩ:: ከእነዚህም ውስጥ በቀደምትነት የሚጠቀሱት የግሪኮች የፖለቲካ ሥርዐት፣ ምርምርና ምክኑያዊ ፍልስፍና ናቸው:: ከጊዜ በኋላ እነዚህ የጥናት ዘርፎች የምዕራባውያን ዕድገት መሠረቶች ሲሆኑ፣ ሙስሊም አገሮች ግን እንደ ተቃወሙት ኖረዋል[16]:: ከሙስሊሞች ትምህርት ጋር የማይሄዱ ሌሎችንም የጥናት ዘርፎች አውድመዋል::

---

[14] H. A. R. Gibb, *Muhammedism* (New York: Oxford University Press, 1969), 3-5.
[15] Van Leeuwen, *Christianity in World History*, 254.
[16] Gibb, *Muhammedism*, 8.

ቫን ሊዌን እንዲህ ሲል አስተያየት ሰጥቶአል:—

> እስልምና የራሱን አሻራ እንደጠበቀና በትምህርቱ ይዘቶች ላይ መሠረታዊ ለውጥ ሳያደርግ በግዛቱ ሥር ባሉ ሌሎች ሥልጣኔዎች ላይ ውጫዊ የሆኑ ቅርፆቹን ሳይቀይር መዝለቁ የምስጢራዊ ኀይሉ አካል ነው[17]::

የእስልምና ምሑር የሆነው ኤች. ኤ. አር. ጊብ እንዲህ ሲል ጽፎአል:—

> ሁሉም የምርምር ዘርፎች በሃይማኖት ቊጥጥር ሥር እንዲወድቁ የተደረገው ትግል ለብዙ ምዕተ ዓመታት የዘለቀና ወደ ሌሎችም የሙስሊም ግዛቶች የተዛመተ ጒዳይ ነበር:: የምርምር ዘርፎችን ለማጠናከርና እንዲቀጥሉ ለማድረግ አንዳችም እንቅስቃሴ አልተደረገም:: የእስልምና ባህል የምርምሩን እንቅስቃሴ ሥር እንዳይሰድ ከማድረጉም በላይ፣ በገደብ እንዲንቀሳቀሱ በመፍቀድ ለራሱ መጠቀሚያ አድርጓቸዋል:: ጥቅም ላይ የሚያውላቸውን እንደ ሕክምና ምርምርና ሒሳብ የመሳሰሉ ሂደቶች ዕድገታቸው ተቀጨ፤ ወይም ጠፋ[18]::

ጊብ በመቀጠል:—

> የሳይንሳዊ ምርምሮችን ስፍራ በአንድ ሆነ በሌላ መንገድ የወሰደው የነገረ መለኮት ጥናት አልነበረም:: ሙስሊሞች የሳይንሶች ሁሉ የበላይ አድርገው የሚመለከቱት የሕግ ትምህርት (የሸሪአ) ነው[19]::

ይህ እስልምና እያደገ ሲመጣ፣ የተለያዩ የሥልጣኔ ዘርፎች ከፉኛ እየተዳከሙ መምጣታቸውን የሚያሳይ ነው:: አንዳንድ ምሁራን በዚህ ጒዳይ ላይ የተለያየ አቋም ይዘው ይከራከራሉ:: ይሁን እንጂ፣ ትምህርትን በተመለከተ ማንኛውም የዕውቀት ዘርፍ በተገለጠው የአላህ ፈቃድ (ቁርአን) መቃኘት አለበት:: ከአላህ ዘንድ የተሰጠውም መመሪያ ግልጽ በሆነ መልኩ ከሸሪአ ሕግ ጋር እንዲስማማ ተደርጎ ተተርጒሞአል::

## እስልምናና የምዕራቡ ዓለም

ሙስሊም አገሮችና የምዕራቡ ዓለም በመተማመን ላይ የተመሠረተ ግንኙነት መፍጠር አዳጋች ሆኖባቸዋል:: በቅጡ የሚያግባባ የጋራ መሠረትም ማግኘት ቀላል አልሆነላቸውም:: እነዚህ ቡድኖች በተደጋጋሚ እርስ በርሳቸው ይዋጉ

[17] Van Leeuwen, *Christianity in World History,* 255.

[18] Gibb, *Muhammedism,*9.

[19] ዝኒ ከማሁ::



ነበር:: በመጀመሪያዎቹ የእስልምና ዘመናት ሙስሊሞች ሰሜን አፍሪካን ተሻግረው ቢዛንታይንንና ስፔንን ወግተዋል:: ከመሐመድ ሞት መቶ ዓመት በኋላ አውሮፓውያን ለሙስሊሞቹ አጸፋ በመስጠት በ732 ዓ.ም ደቡባዊ የፈረንሳይ ክፍል በሆነው በቱር ዐውደ ግንባር (Battle of Tours) ከሙስሊሞች ጋር ተዋግተዋል:: ከሦስት ምዕተ ዓመታት በኋላ በመስቀል ጦርነት (ክሩሴድ) "ቅድስቲቱ ምድር" በክርስቲያኖች እጅ ገባች::

በመጀመሪያው የመስቀል ጦርነት (ክሩሴድ) ኢየሩሳሌም በነበሩት ሙስሊሞችና ክርስቲያኖች ላይ የተፈጸመው የጅምላ ጭፍጨፋ ዘግናኝ ነበር:: ያኔ የተፈጸመው የጅምላ ፍጅት መቼም የሚዘነጋ አይደለም:: ስለ ሁኔታው ሊባኖሳዊው ጋዜጠኛ አሚን ማዕሉፍ እንዲህ ሲል ጽፎአል:—

> በሙስሊሙና በክርስቲያኑ ዓለም መካከል ያለው ጥላቻ የተጀመረው በመስቀል ጦርነት ጊዜ እንደ ሆነ ምንም ጥርጥር የለውም፤ እስከ ዛሬ ድረስ ዐረቦች ይህን ድርጊት አስገድዶ ከመድፈር የተለየ ተግባር አይደለም በማለት በቊጭት ያስቡታል[20]::

የመስቀል ጦርነት ከግጭቱ መገለጫዎች ውስጥ አንዱ ነው:: ባለፉት ዐሥራ አራት ምዕተ ዓመታት፣ በየጊዜው በምዕራባውያንና በሙስሊሞች መካከል ጦርነቶች ተካሂደዋል:: ከመስቀል ጦርነቶች በኋላ ሙስሊሞች በበቀል ስሜት ተነሣሥተው በመዋጋታቸው ጦርነቱ ወደ ምሥራቃዊ የአውሮፓ ክፍል ተዛምቶአል:: በ16ኛው ክፍለ ዘመን ቪየና ከተማ በሙስሊሞች ተከባ ነበር:: አብዛኛው አውሮፓም ለጦርነት ተንቀሳቅሶ ነበር:: አውሮፓ በዚህ ዐይነት ሁኔታ በነበረበት ጊዜ ነው የፕሮቴስታንት የተሐድሶ እንቅስቃሴ የተጀመረው:: አንዳንድ የተሐድሶ አራማጆች ከካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ጋር በመተባበር አውሮፓን ከጥቃት ለመከላከል ወታደራዊ ድጋፍ ሰጥተዋል:: ማርቲን ሉተር ግን በነገሩ ላይ ያመነታ ነበር:: ክርስቲያኖች ቤተ ክርስቲያንን ወክለው መዋጋት አይችሉም፤ እንደ አገር ዜጋ ግን በጦርነቱ መሳተፍ ይችላሉ ብሏል[21]::

[20] Paul Crawford, "A Deadly Give and Take," *Christian History* 21, no. 2 (August 2002): 24.

[21] Gregory Miller, "From crusades to Homeland Defense" *Christian History* 21, no. 2 (August 2002): 31-34.

## የዳግም መጥምቃውያን ምላሽ

የማርቲን ሉተር አቋም የመነጨው ክርስቲያኖች በሁለት መንግሥታት (በእግዚአብሔርና በምድራዊ መንግሥት) ውስጥ የሚኖሩ ናቸው ከሚለው አስተምህሮው ነው። ይሁንና ሁሉም ክርስቲያኖች የእርሱን እምነት አይጋሩም። ዳግም መጥምቃውያን ሁሉ፣ ሁለት መንግሥታት አሉ በሚለው ጉዳይ ላይ ቢስማሙም፣ ክርስቲያኖች ቅድሚያ መስጠት ያለባቸው ለእግዚአብሔር መንግሥት ነው ይላሉ። ክርስቶስ ከበቀል ይልቅ ፍቅርን ለጠላቶቹ ገልጦአል። ክርስቲያኖችም እንደዚሁ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል[22]።

ስለዚህ በአውሮፓ የፍርሓትና የጭንቀት ዘመን፣ ዳግም መጥምቃውያን ከቱርኮች ጋር በሚደረገው ጦርነት ለመሳተፍ ፈቃደኛ አልነበሩም፤ ምክንያቱም ለእነርሱም ክርስቶስ ሞቶላቸዋል የሚለው አቋማቸው ከሙስሊሞቹ ጋር እንዳይዋጉ አድርጓቸዋል። የዳግም መጥምቃውያን መሪ የነበረው ሚካኤል ሳትለር ከመገደሉ በፊት በዚህ ረገድ ያለውን አቋም ገልጾአል[23]። ክርስቲያኖች ቱርኮችን ሊወዱዋቸውና ወንጌልን ሊሰብኩላቸው እንጂ ሰይፍ ሊመዙባቸው በጭራሽ አይገባም ባይ ነው። ዳግም መጥምቃውያን ከጦርነት ይልቅ ሰላም ለመፍጠር በነበራቸው ጽኑ አቋም ምክንያት እንደ ከሐዲ ስለተቈጠሩ፣ በሰማዕትነት ማለፍ ግድ ሆኖባቸዋል። መንግሥትና ቤተ ክርስቲያን የተቀላቀሉበትን የክርስቲያን ግዛት ተቃውመዋልና። መንግሥትና ቤተ ክርስቲያን የተዳበሉበት ግዛት፣ የእግዚአብሔር መንግሥት ማለት አይደለም ሲሉም ተከራክረዋል።

## የምዕራባውያን ጣልቃ ገብነት

በሙስሊሞችና በምዕራባውያን መካከል የነበረው ፖለቲካና ወታደራዊ ሁኔታ ለተወሰነ ጊዜ ሚዛኑን ስቶ ነበር። ኋላ በ1683 ዓ.ም ቪየናን ለመያዝ በተደረገው የመጨረሻ ጦርነት፣ የሙስሊም ወታደሮች ወደ ኋላ አፈግፍገዋል። ከአንድ ምዕተ ዓመት በኋላ በ1798 ዓ.ም ናፖሊዮን ጦሩን በግብፅ አስፍሮአል። ይህ ክሥተት ከዚያ በኋላ ለሆኑ ዘመናዊ ክሥተቶች ሁሉ ወሳኝ ተግባር ነው።

[22] Cornelius J. Dyck, *An Introduction to Mennonite History* (Scottdale: Herald Press, 1993), 39, 57-59.
[23] Myron S. Augsburger, *Pilgrim Aflame* (Scottdale: Herald Press, 1967), 252-68.



በምሥራቅ አውሮፓ የሚደረጉ ጦርነቶች ከማዕከላዊው የእስልምና ግዛቶች በጣም የራቁ ነበሩ፤ ነገር ግን ግብፅ በጣም ቅርብ ነበረች። የምዕራባውያን ወደ መካከለኛው የእስልምና ግዛት መግሥገሥ ከሁለት መቶ ዓመት በፊት ናፖሊዮን ጀብደኛ ዘመቻ እስከ ፈጸመበት ጊዜ ድረስ ቆይቶአል።

የምዕራባውያን ምጣኔ ሀብትና ባህል መስህብና ኀይል የማግኘቱ ምክንያት ምን እንደ ሆነ ለሙስሊም አገሮች እንቈቅልሽ ነው። የሙስሊም ኡማ ተልእኮ በዓለም ላይ ምስክር መሆን ነው። ባለፉት በርካታ ዓመታት ግን ይህ ሲሆን አልታየም[24]። በዚህ ረገድ አንድ ምሳሌ ልጥቀስ:— በምዕራባውያን ዩኒቨርስቲዎች ትምህርታቸውን የሚከታተሉ ተማሪዎች፣ ራሳቸውን ዕድለኛ አድርገው ይቈጥራሉ። በተቃራኒው በሙስሊም ማኅበረሰብ ውስጥ ያሉ ተማሪዎች ግን፣ ትምህርታቸውን በሙስሊም ዩኒቨርስቲዎች ለመከታተል ደስተኛ አይደሉም። የዚህ ችግር መንሥኤው ምንድን ነው?

ባህላዊ ጥያቄዎች በቀላሉ መልስ የሚያገኙ አይመስሉም። ፖለቲካዊና ወታደራዊ አካሄዶች የበለጠ አዋኪዎች ናቸው። ከናፖሊዮን ጊዜ ጀምሮ የሙስሊሙ ማኅበረሰብ በምዕራባውያን ተፅዕኖና ዛቻ ሥር ቆይቶአል። ሙስሊሞች ስለምዕራቡ ዓለም የተሳሳተ ግንዛቤ እንዲኖራቸውና ራሳቸውን እንዲያገሉ የሚያደርግ ክሥተት በሌላ የታሪክ ዘመን በሙስሊም ክልል እምብርት ላይ ተፈጠረ[25]።

በ1917 ዓ.ም የአይሁዶችን የፍልስጥኤም ምድር የይገባኛል ጥያቄ የሚደግፍ የባልፎር መግለጫ በእንግሊዝ መንግሥት ታወጀ። ፍልስጥኤማውያንን በጉዳዩ ላይ ያማከራቸው ወገን አልነበረም። የአቶማን ግዛት አንደኛው የዓለም ጦርነትን ተከትሎ በቨርሳይልስ (1919 ዓ.ም) ስምምነት ከአባልነት ተሰረዘ። ቀጥሎም አውሮፓውያን መካከለኛው ምሥራቅን ተቈጣጥረዋል።

በከማል አታቱርክ ወታደራዊ አመራር (1924 ዓ.ም)፣ ቱርክ የሱኒ ከሊፋትን በማስወገድ ዓለማዊ ሪፐብሊክ ሆነች።

[24] Bernard Lewis, *What went Wrong? Western Impact and Middle Eastern Response* (New York: Oxford University Press, 2002).
[25] ዝኒ ከማሁ፤ 1-63።

የእስራኤል መንግሥት በ1948 ዓ.ም ተመሠረተ:: ይህ በመሆኑ ምክንያት፣ በተባበሩት መንግሥታት ዕርቅ አፈላላጊ ኮሚሽን ሪፖርት መሠረት፣ 750,000 ፍልስጥኤማውያን ከመኖሪያቸው ተፈናቅለዋል:: ከዚያ በኋላ በ1967 ዓ.ም እስራኤል የኢየሩሳሌም፣ የዌስት ባንክ፣ የጋዛንና የጐላንን ተራሮች ተቈጣጠረች:: ለብዙ ዓመታት እስራኤል የሲናን ባሕረ ሰላጤ ይዛ ቆይታለች:: ከዚያም ደቡባዊ ሊባኖስንም ተቈጣጠረች፤ በመቀጠልም እስራኤል በፍልስጥኤማውያን ግዛቶች የሰፈራ ፕሮግራሞችን ማካሄድ ጀመረች:: በ2002 ዓ.ም በተያዙት ግዛቶች ውስጥ፣ በመቶ አርባ የሰፈራ መንደሮች ውስጥ ለሁለት መቶ ሺህ እስራኤላውያን የመኖሪያ ቤቶች ተገንብተዋል::

በ1991 ዓ.ም በአሜሪካ የሚመራው የኅብረ ብሔሩ ጦር ለኩዌይት ነጻነት ወደ ኢራቅ ዘመተ:: የአሜሪካ ጦር፣ የእስልምና እምብርት በሆነችው ሳውዲ ዐረቢያ ከዐሥር ዓመታት በላይ ቆይቶአል:: እነዚህ ክሥተቶች በምዕራቡና በሙስሊሙ ዓለም መካከል ለተፈጠረው ቅራኔ የራሳቸው የሆነ አስተዋጽኦ አላቸው::

## አል-አቅሳ መስጊድ

ነገር ግን ሙስሊሞች አል-አቅሳ ብለው የሚጠሩት በኢየሩሳሌም የሚገኘው መስጊድ፣ ከምንም በላይ ቅሬታውን አባብሶአል:: በመግቢያው ላይ ስለ መስጊዱ አመሠራረት የተወሰነ ማብራሪያ ተሰጥቶአል:: መስጊዱ የተሠራው በ7ኛው ክፍለ ዘመን ሲሆን፣ ለአንድ ሺህ ሦስት መቶ ዓመታት ሳይፈርስ በተራራው ላይ ቆይቶአል:: ይሁንና ከ1967 ዓ.ም ጀምሮ ተራራው በእስራኤል ቊጥጥር ሥር ይገኛል::

መስጊዱን ማን ይቈጣጠረው የሚለው ጥያቄ መልስ እስካላገኘ ድረስ፣ በእስራኤልና በፍልስጥኤም መካከል ሰላም ማስገኘት አይቻልም:: በሐምሌ 2000 ዓ.ም የአሜሪካው ፕሬዝዳንት ቢል ክሊንተን፣ ከፍልስጥኤም መሪ ያሲር አራፋትና ከእስራኤል ጠቅላይ ሚኒስትር ኢሁድ ባራክ ጋር ስብሰባ አድርገው ነበር:: በሁለት ሳምንታት የካምፕ ዴቪድ ስብሰባቸው ስለ ኢየሩሳሌም የተነጋገሩ ሲሆን፣ ትልቅ ትኵረት የሰጡበት ጒዳይ የአል-አቅሳ መስጊድ ጒዳይ ነበር:: ተሳታፊዎቹ ይህ ጒዳይ መፍትሔ ካገኘ ሌሎቹን ችግሮች መፍታት ቀላል ነው የሚል እምነት ነበራቸው::



በኢየሩሳሌም ያሉት አብያተ ክርስቲያናት በጒዳዩ ለመሳተፍ ቢጠይቁም በስብሰባው አልተጋበዙም:: ክርስቲያኖቹ እንደ ሙስሊሞችና አይሁዶች መስጊዱ የቆመበት ስፍራ ቅዱስ ነው የሚል አቋም ስለሌላቸው ጒዳዩ ችግር የሚያስከትል ሆኖ አልተገኘም:: ኢየሩሳሌም በክርስቲያኖች ዘንድ ትልቅ ስፍራ አላት:: ነገር ግን ለሙስሊሞችና ለአይሁዶች የሆነችውን ያህል አይደለም:: ምንም እንኳ ሦስቱም ተሳታፊዎች ሃይማኖታዊ ሕዝቦች ቢሆኑም፣ ይህን ስፍራ በተመለከተ አንዱ የሌላውን መንፈሳዊነት ለመስማት ዐቅም የለውም[26]:: ከዚህ አስቸጋሪ ጒዳይ የተነሣ ድርድሩ ተደናቀፈ::

ከሁለት ወር በኋላ በመስከረም 28 ቀን ኤሪየል ሻሮን የቤተ መቅደሱን ስፍራ አንድ ሺህ በሚጠጉ የእስራኤል ወታደሮች ታጅበው ከጐበኙ በኋላ፣ በተቀደሰችው ተራራ ላይ ሉዓላዊነታችንን ማረጋገጥ እንፈልጋለን፤ "ለእኛ ቅዱስ ስፍራችን ናትና"[27]:: በማለት መናገራቸው የፍልስጥኤማውያንን ኢንቲፋዳ (ዐመፅ) የሚያቀጣጥል ክብሪት ሆኖአል::

ከዓመት በኋላ መስከረም 11 ቀን 2001 ዓ.ም ሙስሊም ታጣቂዎች አውሮፕላኖችን በመጥለፍ በፔንታጐን፣ በዋሺንግተን ዲ. ሲ እንዲሁም በዓለም የገበያ ማዕከል ላይ ጥቃት አድርሰዋል:: የአሜሪካ አስተዳደር ከጥቃቱ በኋላ በአሸባሪነት ላይ ጦርነት ዐውጆአል:: የጥቃቱ ጠንሳሽና ፈጻሚ በአፍጋኒስታን የነበረው የታሊባን አስተዳደርና መቀመጫውን አፍጋኒስታን ያደረገው የአል-ቃይዳ ድርጅት እንደ ሆነ ተገመተ:: በዓለም ዙሪያ ያሉ ሙስሊሞች ራሳቸውን መከላከል እንዳለባቸው ተሰማቸው:: አንዳንድ ሙስሊሞች አሜሪካ ዘመናዊ የመስቀል ጦርነት እያካሄደች እንዳለች አመኑ::

ከመጋቢት 19 ቀን 2003 ዓ.ም ጀምሮ አሜሪካ በኢራቅ ላይ ጦርነት ዐወጀች:: በመላው የመካከለኛው ምሥራቅ ክልል ቊጣ ተቀሰቀሰ:: በአሜሪካ የሚመራውን ጦር የደገፉት የመካከለኛው ምሥራቅ ዐረብ መንግሥታት በተጠንቀቅ መቆም እንዳለባቸው አሰቡ:: ብዙ ሙስሊሞች ጦርነቱን ምዕራባውያን፣ በእስልምናና በሙስሊም አገሮች ላይ የከፈቱት ጥቃት አድርገው ወስደውታል::

---

[26] Charles M. Sennott, *The Body and the Blood, the Holy Land's Christians, and the turn of a new Millennium* (New York: Public Affairs, 2001), 323-26.
[27] ዝኒ ከማሁ፣ 334-35::

# የመካከለኛው ምሥራቅ ክርስቲያኖች

በአሁኑ ዘመን የመካከለኛው ምሥራቅ ቤተ ክርስቲያናት ከምዕራቡ ቤተ ክርስቲያናት የተለየ አቋም እንዳላቸው በግልጽ እንዲያስታውቁ እየተገደዱ ነው:: በቅርቡ በአሜሪካ መሪነት በሽብርተኝነት ላይ የሚደረገው ጦርነት እንዲሁም አንዳንድ ክርስቲያኖች ጦርነቱን የመቀላቀላቸው ጉዳይ ጥያቄውን እያጉላው መጥቶአል:: በዋሽንግተን ላይ ያነጣጠረው ጥላቻ በመካከለኛው ምሥራቅ በሚገኙ ክርስቲያናዊ ማኅበረሰቦች ላይ እየተንጸባረቀ መጥቶአል:: ቈስጠንጢኖስም ሆነ የ11ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የመስቀል ጦርነት ተዋጊዎች፣ ወደ ምሥራቅ የዘመቱት የመስቀል ምልክት አንግበው ነበር:: የዘመኑ ምዕራባውያን/ቈስጠንጢኖሶች ወይም የመስቀል ጦርነት ተዋጊዎች፣ የምሥራቅ አብያተ ክርስቲያናትን ለጥቃት አጋልጠዋቸዋል የሚል አስተሳሰብ አለ[28]::

በ20ኛው ክፍለ ዘመን፣ በመካከለኛው ምሥራቅ የተፈጠሩ ነውጦች ለክርስቲያኖች ቍጥር መመናመን አስተዋጽኦ አድርገዋል:: በ1914 ዓ.ም በኦቶማን ግዛት የክርስቲያኖች ቍጥር ሃያ አራት ከመቶ (24%) ነበር:: ይህ ግዛት የሚያጠቃልለው ቱርክን፣ ሶሪያን፣ ኢራቅን፣ ሊባኖስን፣ ፍልስጥኤምን/እስራኤልን፣ ዮርዳኖስንና ግብፅን ነበር:: በ21ኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ በእነዚህ አገሮች ያለው የክርስቲያኖች ቍጥር ወደ አራት በመቶ (4%) አሽቈልቍሉአል[29]::

ለክርስቲያኖች ቍጥር መመናመን ዋነኛው ምክንያት፣ በ20ኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ላይ የኦቶማን ግዛት መፈረካከሱ ነው:: የግዛቱ መውደቅ፣ አውዳሚ በሆነ ሁኔታ የእርስ በርስ ብጥብጥን አስከተለ:: በአርሜንያ ክርስቲያኖች ላይ የተፈጸመው የጅምላ ጭፍጨፋ፣ እጅግ በርካታ ቍጥር ያለው የክርስቲያኖች ማኅበረሰብ እንዲጠፋ ምክንያት ሆኖአል:: እነዚህም ክርስቲያኖች አሠቃቂ በሆነ ሁኔታ ተገድለዋል፤ እንዲሁም ወደ ግሪክና ወደ ሌሎች የአርሜንያ ግዛቶች ተሰደዋል:: ይህ የዘር ማጥፋት ወንጀል የተፈጸመው፣ የመካከለኛው ምሥራቅ ፖለቲካ በሙስሊሞች ኀይል ሥር በወደቀበት ጊዜ ነው:: የኦቶማን ሙስሊም መንግሥት ሥልጣን ላይ በነበረ ጊዜ፣ ይህ ዐይነቱ ድርጊት ታይቶ አይታወቅም::

[28] Awad, "Learning to Live with Muslims," 8-10.
[29] Sennott, *The Body and the Blood*, 22.



ለክርስቲያኖች ቍጥር መመናመን ሌላኛው ምክንያት ክርስቲያኖች እስልምናን ለመቀበል የወሰዱት ምርጫ ነበር:: ነገር ግን ከቱርክ ጭፍጨፋ በስተቀር በ20ኛው ክፍለ ዘመን መጨረሻ ክርስቲያኖች ከመካከለኛው ምሥራቅ ወደ ሌሎች አገሮች መፍለሳቸው እንደ ዋና ምክንያት ይጠቀሳል::

ፍልሰት በመካከለኛው ምሥራቅ ያለውን የክርስቲያኖች ቍጥር በከፍተኛ ሁኔታ እንዲቀንስ አድርጉአል:: በተለይም በእስራኤል/በፍልስጥኤም ቍጥራቸው ከፉኛ ተመናምኖአል:: በ1947 ዓ.ም በእስራኤል/ፍልስጥኤም የነበረው የዐረብ ክርስቲያን ቍጥር፣ በቤተ ክርስቲያን ቈጠራ ሃያ በመቶ (20%) ሲሆን፣ በእንግሊዝ መንግሥት ቈጠራ ደግሞ ዐሥራ ሦስት በመቶ (13%) ነበር:: ከሃምሳ ዓመት በኋላ ማለትም በምዕተ ዓመቱ መጨረሻ ላይ የክርስቲያኖች ቍጥር ሁለት ከመቶ (2%) በታች ሆኖአል[30]:: ዛሬ በእስራኤል/ፍልስጥኤም ካሉት የዐረብ ክርስቲያኖች ቍጥር ይልቅ፣ በሲድኒና በአውስትራሊያ የሚኖሩ የዐረብ ክርስቲያኖች ቍጥር የበለጠ ነው[31]::

የዮርዳኖሱ ንጉሥ ሀሰን፣ ከአንድ ክርስቲያን ጋዜጠኛ ጋር ባደረጉት ቃለ ምልልስ እንዲህ በማለት ተናግረዋል:— "ፍልሰቱ የሚያሳዝነኝ ብቻ ሳይሆን የሚያሳስበኝም ጉዳይ ነው:: በዚህ ዓለም ውስጥ ክርስቲያኖች ሳይኖሩ የእምነት ብዝኃነት ይኖራል ብሎ ማሰብ እንዴት ይቻላል? ለእኛ እጅግ እውናዊ የሆነ አንገብጋቢ ጥያቄ ነው"[32]::

በአካባቢው የክርስቲያኖች ቍጥር እየቀነሰ መምጣቱ፣ የተለያዩ ሃይማኖቶች በአካባቢው የመኖራቸውን ጉዳይ አጣብቂኝ ውስጥ የሚያስገባ ነው:: እነዚህ አካባቢዎች አንድ ዐይነት አመለካከት የሆነውን እስልምናን ወይም በእስራኤል አንዳንድ ግዛቶች ደግሞ የይሁዲ እምነትን እያንፀባረቀው ነው:: የክርስቲያኖች ቍጥር መቀነስ፣ በአካባቢው የሚኖሩ ሌሎች ሰዎች ወንጌል የመስማታቸው ዕድል እየጠበበ መምጣቱን አመላካች ነው::

የክርስቲያኖች ቍጥር ክፉኛ ይመናመን እንጂ፣ ክርስቲያኖች በመካከለኛው ምሥራቅ ያላቸው ተጽእኖ እጅግ ከፍተኛ ነው:: አገር በቀል የሆኑ

[30] ዝኒ ከማሁ፤ 22-23::
[31] ዝኒ ከማሁ፤ 252::
[32] ዝኒ ከማሁ::

የመካከለኛው ምሥራቅ ቤተ ክርስቲያናት፣ ለአካባቢው በመጸለይ እንዲሁም በሙስሊሞች መካከል እየኖሩ ወንጌልን የመመስከር ባህልን አዳብረዋል። አንዳንዶቹም በእስራኤልና በፍልስጥኤም መካከል እየተካሄደ ባለው የሰላም ሂደት ውስጥ እውናዊ ተሳትፎ እያደረጉ ነው። አንዳንዶም በአካባቢው በሚገኙ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያናትና ምዕራባውያን በሆኑ ሚስዮናውያን እርስ በርስ በመተባበር አድናቆት የሚቸራቸው ዐይነት አገልግሎቶችን ይሰጣሉ። በእስራኤል የሚገኘው የናዝሬት ሆስፒታል የክርስቲያኖችን እውናዊ ተሳትፎ ከሚያመለክቱ በርካታ ናሙናዎች ወስጥ አንዱ ነው። በዚህ ሆስፒታል ክርስቲያኖች ለበርካታ ዘመናት ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይሉ የክልሉን ኅብረተሰብ አገልግለዋል። በክልሉ፣ ከፍተኛ የሆነ የማስተማር ጥራት አላቸው የሚባሉ ትምህርት ቤቶችም የክርስቲያኖች የመሆናቸው ጉዳይ፣ ክርስቲያኖች በክልሉ ያላቸው ተጽእኖ በቀላል የሚገመት እንዳልሆነ የሚያሳይ ነው።

በቅርቡ እኔ ተሳታፊ በነበርሁበት የመስጊድ ውስጥ ውይይት፣ ክርስቲያኖች በእግዚአብሔር ላይ የስድብን ቃል የሚናገሩ ሰዎች ናቸው የሚል ክስ በአንዳንድ ወገኖች ተሰንዝሮ ነበር። ይህ ክስ የውይይቱን መንፈስ ክፉኛ በረዘው። በመግባባት ላይ ተመሥርቶ የነበረውን ውይይት ያበላሸውን መንፈስ አንድ ፓኪስታናዊ መሐንዲስ እንዲህ በማለት ጭጋጉን ገፈፈው፣ “እኔ ባደግሁባት ፓኪስታን በጣም ጥሩ የሚባሉ ትምህርት ቤቶች የክርስቲያኖች ነበሩ። እነዚያ ክርስቲያን አስተማሪዎች በእነዚያ የክርስቲያን ትምህርት ቤቶች ባይኖሩ ኖሮ፣ እኔ መሐንዲስ ባልሆንሁ ነበር። እኔ ስለ ቤተ ክርስቲያንም ሆነ ስለክርስቲያኖች እምነት መቼም ቢሆን አንቋሸሼ የመናገር ዐቅም የለኝም”።

ክርስቲያኖች፣ ፓኪስታናዊው ሙስሊም እንደ ተናገረው ይህንን መልካም ምሳሌ አጥብቀው ሊከተሉ ይገባል። መጽሐፍ ቅዱስ፣ “ሕይወትን የሚወድ፣ መልካም ቀኖችን ሊያይ የሚፈልግ፣ ምላሱን ከክፉ፣ ከንፈሮቹንም ተንኰል ከመናገር ይከልከል። ከክፉ ይራቅ፤ መልካምንም ያድርግ፤ ሰላምን ይፈልግ፤ ይከተላትም” (1ጴጥሮስ 3፥10-11) ሲል ያስተምራል።



## ምዕራፍ ሁለት

# ዐረባዊ ጅማሬ

እስልምና በዐረብ ምድር መስፋፋት በጀመረበት ወቅት፣ ክርስቲያኖች በተለያዩ የነገረ መለኮት ርእስ ጉዳዮች ዙሪያ፣ እርስ በርስ ይወዛገቡ ነበር። ክርስቲያኖች የነገረ መለኮት እሰጣገባ ከሚፈጥሩባቸው ርእስ ጉዳዮች መኻል፣ የሚከተሉት ቀዳሚውን ስፍራ ይወስዳሉ:–

- “ድንግል ማርያም የአምላክ እናት ናት”
- “ይህ በፍጹም ሊሆን አይችልም! ሴት አምላክን እንዴት ትወልዳለች? ቅድስት ድንግል ማርያም የክርስቶስ እናት ነች!”

- “የእግዚአብሔር ልጅ በመስቀል ላይ ተሰቅሎ ሞተ”
- “አምላክን መግደል በፍጹም አይቻልም! ስለዚህ በመስቀል ላይ የሞተው ሰው የሆነው ክርስቶስ ነው፤ መለኮታዊው ልጅ ኢየሱስ ግን አልሞተም፤ እግዚአብሔር ከሞት አስመልጦ ወደ ራሱ ወስዶታል”።

- “ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ *ሆኖአል*”
- “እንደዚያ ሳይሆን፣ ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ዘላለማዊ ልጅ ስለሆነ፣ ከጊዜ በኋላ የእግዚአብሔር ልጅ *አልሆነም*”

- “ክርስቶስ አምላክ ነው!”
- “ይህ በፍጹም ሊሆን አይችልም! አምላክ ክርስቶስ ነው!”

መሐመድ የተወለዱት፣ ክርስቲያኖች በተለያዩ የነገረ መለኮት ርእስ ጉዳዮች በተለይ ደግሞ መሲሑን ኢየሱስ በተመለከተ የተለያየ አመለካከት ወግነው ይወዛገቡ ባነበሩበት፣ በ6ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ላይ ነው። ክርስቲያኖች በእንዲህ ዐይነቱ ክርክር ውስጥ በነበሩበት ወቅት መሐመድ መወለዳቸው፣ እምነታቸውን በተመለከተ ግራ ለተጋቡ ክርስቲያኖች ትክክለኛውን መንገድ ለማሳየት እንደ ሆነ ሙስሊሞች ያምናሉ። ይህንኑ የሙስሊሞች እምነት ቁርአን እንዲህ ሲል ይገልጸዋል:–

> ከነዚያም እኛ ክርስቲያኖች ነን ካሉት የጠበቀ ቃል ኪዳናቸውን ያዝን። በርሱም ከታዘዙበት ነገር ፈንታውን ተዉ፤ ስለዚህ እስከ ትንሣኤ ቀን ድረስ በመካከላቸው ጠብንና ጥላቻን ጣልንባቸው፤ አላህም ይሠሩት የነበሩትን ሁሉ

> በእርግጥ ይነግራቸዋል። ...እናንተ የመጽሐፉ ሰዎች ሆይ! አብሳሪና አስፈራሪ አልመጣልንም እንዳትሉ፤ ከመልእክተኞች በመቋረጥ ጊዜ ላይ ሲሆን (ሕጋችንን) የሚያብራራ ኾኖ መልእክተኞችን በእርግጥ መጣላችሁ። አብሳሪና አስፈራሪም በእርግጥ መጣላችሁ (ሱራ 5+14:19)።

የሙስሊሙ ማኅበረሰብ የጀመረው፣ ቤተ ክርስቲያን ከተቈረቈረች ከስድስት መቶ ዓመታት በኋላ ነው። በዚህ ምዕራፍ፣ እስልምና ሲጀመር የዐረብ ነባራዊ ሁኔታ ምን ይመስል ነበር? በሙስሊሙ ማኅበረሰብ (ኡማ) እና በክርስቲያኖች ወይም በአይሁዶች መካከል የነበረው ግንኙነት ምን መልክ ነበረው? ነገረ መለኮትን በተመለከተ ሙስሊሞች ለክርስቲያኖች ማብራሪያ የመስጠት ኀላፊነት እንዳለባቸው የሚያምኑት ለምንድን ነው? የሚሉትን ርእሰ ጒዳዮች እንመለከታለን።

ለሙስሊሞች እንቅስቃሴና ለቍርአን ተጽእኖ ያደረጉት ሃይማኖታዊ፣ ነገረ መለኮታዊና ባህላዊ ተጽእኖዎች የትኞቹ ናቸው? ይህ ለክርስቲያኖች ዋነኛ ርእሰ ጒዳይ ነው፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር ለቅዱሳን ሰዎች መጽሐፍ ቅዱሳዊውን መገለጥ ሲሰጥ፣ ያሉበትን ታሪካዊ ዐውድ ባገናዘበ መልኩ ነው የሚለው መሠረታዊ እምነት በክርስቲያኖች ዘንድ ስላለ ነው። ነገር ግን በዚያን ጊዜ የነበረው ታሪካዊ ዐውድ፣ በእስልምና አስተምህሮና በቁርአን መልእክት ላይ ተጽእኖ አለው የሚለው አባባል በሙስሊሞች ዘንድ ተቀባይነት የለውም። ለዚህ ዐቢይ ምክንያቱ፣ የቁርአን መልእክት ከሰማይ በቀጥታ የወረደና ከማናቸውም ዐይነት ታሪካዊ ተጽእኖዎች በላይ ነው የሚል እምነት ስለለ ነው። ቁርአን በዚያን ጊዜ ለነበሩት ችግሮች የተሰጠ ወቅታዊ መፍትሔ አይደለም፣ "ከታሪካዊ ሁኔታ ጋር አንዳችም ግንኙነት የሌለው መገለጥ ነው"[1] (በምዕራፍ አምስትና ስድስት ላይ ይህን ጒዳይ በስፋት እንመለከተዋለን)። በቀጣይ አንቀጾች ግን ይህን የሙስሊሞችን አመለካከትና ስሜት ሳንዘነጋ በመሐመድ ዘመን የነበረውን የዐረብ ታሪካዊ ዐውድ እንዲሁም ይህ ሁኔታ በእስልምና ላይ ያለውን ተጽእኖ እንዳስሳለን።

## በመሐመድ ዘመን የዐረብያ ሁኔታ

መሐመድ የተወለዱት እንደ ጐርጐሮሳውያኑ የዘመን አቈጣጠር በ570 ዓ.ም በመካ ሲሆን፣ ዘመኑም የዝሆን ዓመት ተብሎ ይጠራል። ዘመኑ፣ የዝሆን

[1] Andrew Rippin, *Muslims: Their Religious Beliefs and Practices* (New York: Routledge, 2001), 236-38.



ዓመት ተብሎ የተጠራበት ምክንያት፣ ክርስቲያን የሆነው የኢትዮጵያ ጦር ዝሆኖችን እንደ ጦር ታንክ በመጠቀም፣ መካን ያጠቃበት/የወረረበት ዓመት ስለ ነበር ነው። ጦርነቱም በ6ኛው ክፍለ ዘመን፣ የዐረብን ምድር ከበው የነበሩ የክርስቲያኖችን የበላይነት ያረጋገጠ ሲሆን፣ በተቃራኒው ደግሞ የዐረብ ምድር ከዓለም ኅብረተሰብ የተገለለና ኋላ ቀር አካባቢ እንደ ሆነ ያመላከተ ነበር። ከዐረብያ በመለስ ያለው የዓለም ክፍል የነበረበትን የዕድገት ሁኔታ ጠንቅቀው ያወቁት ጥቂት የዐረብ መሪዎች፣ ዐረቦች ካደጉ ሕዝቦችና መንግሥታት ጋር እኩል የሚሆኑበትን ቀን በተስፋ ይጠባበቁ ነበር። በዝሆን ዓመት የሚወለድ ነቢይ ይህን ተስፋ እውን ያደርጋል የሚል እምነትም ነበራቸው። ይህ የዐረቦች ተስፋ በሚፈጸምበት ወቅት የዐረብያ ታሪካዊ ሁኔታ ምን ይመስል ነበር?

በዚያን ዘመን አራት ዐይነት የእምነት ቡድኖች በዐረቦች ምድር ነበሩ። እነርሱም:— (1) የመድብለ አማልክት አምላኪዎች (2) የክርስቲያኖች (3) የአይሁድ እምነት ተከታዮች (4) በአንድ አምላክ የሚያምኑ ዐረቦች ናቸው።

## ጃሂሊያ

"ጃሂሊያ" ከመሐመድ በፊት የነበረውን ዘመን የሚያመላክት ሲሆን፣ በእስልምናና በቁርአን ውስጥ ላሉ ትምህርቶች በምንጭነት ይጠቀሳል። ጃሂሊያ "የጨለማው ዘመን" የሚል ትርጓሜም አለው። ዘመኑም የአላህን መንገድ የሚያሳዩ ነቢያት የተላኩበት ዘመን እንደ ሆነ ቁርአን እንዲህ ሲል ይገልጸዋል:— "ከአንተ በፊት ምንም አስፈራሪ ያልመጣላቸውን ሕዝቦች ታስፈራራ ዘንድ ከጌታህ በኾነ ችሮታ (ላክንህ)" (ሱራ 28+46) በእነዚህ ዘመናት በዐረብ ምድር የመድብለ አማልክት አምላኪዎች በከፍተኛ ሁኔታ ተስፋፍተው ነበር። በጃሂሊያ ዘመን የጣዖት አምልኮ ማዕከል የነበረውም የመካ ከተማ ነው። አምልኮው በሚፈጸምበት በካዕባ ቤተ መቅደስ ውስጥ፣ "የተቀደሰው ድንጋይ" እየተባለ የሚጠራው ጥቍር ድንጋይ፣ በዚያ ስፍራ ተቀምጦ ነበር። ካዕባንና ዙሪያው "ሐራም" አካባቢ ተብሎ ይጠራል። "ሐራም" ማለት የተከለከለ ማለት ነው። ሐራም ተብሎ በተከለለው አካባቢ ሰላምን ሊያደፈርስ የሚችል ማንኛውም ዐይነት ተግባር መፈጸም በፍጹም የተከለከለ ነበር።

እርስ በርሳቸው ይዋጉ የነበሩ የዐረብ ጐሣዎችም፣ የሰላም ስምምነት ሲያደርጉ ስምምነቱን የሚፈጽሙት ወደ አማልክቶቻቸው ወደ ካዕባ በመምጣት ነበር። በዚህ ዐይነት መንገድ ሰላም ይመጣ ነበር፤ ምክንያቱም የሁለቱ ጐሣዎች አማልክት አብረው በካዕባ ውስጥ በሰላም ይኖራሉ ብለው ስለሚያምኑ ነው።

ቅዱስ ቤተ መቅደስ (ካዕባ) እና በዙሪያው ያሉ አካባቢዎች ሐራም ክልል ተብለው ስለሚጠሩ፣ ለብዙ ዓመታት የሰላም ቀጣና በመሆን ኖሮአል:: የዐረብ ጐሣዎች ከሌሎች ጐሣዎች የሰላም ስምምነታቸውን ዳግም ለማደስ፣ ዓመታዊ የጸሎት ጉዞ ወደ ካዕባ ያደርጋሉ:: አንዳንድ መረጃዎች፣ እያንዳንዱን ጐሣ የሚወክሉ አንዳንድ ጣዖታት በአጠቃላይ፣ 360 ጣዖታት በካዕባ ውስጥ እንደ ነበሩ ያስረዳሉ[2]::

መሐመድና ተከታዮቹ፣ ካዕባ የአምልኮ ስፍራቸው እንድትሆን ሲወስኑ፣ የሰላም ቀጠና እንደ ሆነች ከሙሉ ልባቸው አልተቀበሉም ነበር፤ ምክንያቱም ካዕባ በጣዖታት ተበክላለች የሚል አመለካከት ስለነበራቸው ነው:: ይሁንና መካ በነቢዩ መሐመድ ቁጥጥር ሥር ስትወድቅ፣ በካዕባ የነበሩትን ጣዖታት በማጥፋት ካዕባን ከጣዖት አምልኮ ነጻ አድርገዋል:: ኋላም ካዕባ ለአላህ አምልኮ የሚቀርብባት ቅዱስ ስፍራ እንድትሆን ለዩአት:: ስለዚህም በመድብለ አማልክት አምላክያን የአምልኮና የሰላም ቀጣና ተብሉ ይጠራ የነበረው ስፍራ ማለትም ካዕባ፣ የአንድ አምላክ ማለትም የአላህ የሰላም ስፍራ ተብሉ ተጠራ:: ይህም ማለት የመስጊዱ ሰላምና ዐረባዊ የሆነው የባህላዊው ሃይማኖት ሰላም ተቀላቀሉ ማለት ነው[3]::

## የክርስቲያኖች መገኘት

በእስልምና አስተምህሮም ሆነ በቁርአን ውስጥ ላሉ መሠረተ እምነቶች በምንጭነት ከሚጠቀሱት ውስጥ፣ ክርስትና ሁለተኛውን ስፍራ ይይዛል:: እንደሚገኘውም የዐረብ ሕዝብ መሐመድ ስለክርስቲያኑ ማኅበረሰብ፣ በዐረብያ ዙሪያ ስላሉ ክርስቲያን ነገሥታትና ስለ ክርስትና እምነት ያውቁ ነበር:: የክርስቲያኖችና የአይሁዶች የአስተሳሰብ፣ የአኗኗርና የእምነት ዘይቤዎች በዐረቦች የዕለት ተዕለት ኑሮ ውስጥ ይንጸባረቁ ነበር:: መጽሐፍ ቅዱስን በማንበብ እንኳ ባይሆንም፣ ስለክርስትና እምነት በቃል ብቻ ሰምተው የክርስትናን እምነት ከተቀበሉ ክርስቲያኖች ጋር መሐመድ የቅርብ ግንኙነት ነበራቸው:: በሙስሊሞችና በክርስቲያኖች መካከል ይህ ዐይነቱ ግንኙነት እንደ ነበረ ቁርአን የተወሰኑ ፍንጮችን ይሰጣል:: ግንኙነቱ አንዳንዴ በመከባበር ላይ

---

[2] Badru D. Katerrega and David W. Shenk, *A Muslim and a Christian in Dialogue* (Scottdale, Pa.: Herald Press, 1997), 69.

[3] Kenneth Cragg, *Muhammad and the Christian: A Question of Responses* (Maryknoll, N.Y.: Orbis, 1984), 36.



የተመሠረተ ሲሆን፣ በሌላ ጊዜ ደግሞ አንደኛው ወገን ሌላኛውን ወገን በመንቀፍ ላይ ያተኮረ ነበር::

ሙስሊሞች የኢየሱስ ክርስቶስን ማንነት በተመለከተ፣ በክርስቲያኖች ዘንድ አለመግባባቶችና ውዝግቦች እንደ ነበሩ ያውቁ ነበር:: ከላይ ለማየት እንደ ሞከርነው የእስልምና አንደኛው ተልእኮና ግብ ይህንን ግርታ በማጥራት ለክርስቲያኖች ስለክርስቶስ ማንነት ትክክለኛ የሆነውን ትምህርት መስጠት እንደ ሆነ፣ ሙስሊሞች ጠንካራ አቋም ነበራቸው::

በዚህ ዘመን ያለችውን የአፍሪካ ቤተ ክርስቲያን ስንመለከት፣ በሺህ የሚቈጠሩ ቤተ እምነቶችን እናገኛለን:: ቤተ ክርስቲያናቱ ከሚሰጡአቸው ትምህርቶች ውስጥ የተወሰኑት፣ ከመጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮ ወጣ ያሉ ሲሆን፣ በአንጻሩ ደግሞ ሁሉም በሚስዮናውያን የተተከሉ ቤተ ክርስቲያናትን የሚያሒሱ/የሚተቹ ናቸው:: ምናልባት የመጀመሪያው የሙስሊም ማኅበረሰብ በተወሰነ መልኩም ቢሆን የዋናው ክርስቲያናዊ እንቅስቃሴ ሒስ አቅራቢ እንደ ሆነ ማሰቡ በጣም የራቀ ይሆንን? ክርስቲያኖች፣ መሐመድን ከነቢያቶቻቸው እንደ አንዱ አድርገው አለመቀበላቸው ሙስሊሞችን የሚያስገርም ብሎም የሚያሳዝን ነገር ነበር::

## የአይሁዶች መገኘት

ለሙስሊም ማኅበረሰብ (ኡማ) መፈጠር አስተዋጽኦ ካደረጉ አካላት መካከል በሦስተኛ ደረጃ የሚገኘው፣ የአይሁድ እምነት/ሕዝብ ነው:: በእስልምና ሃይማኖትና በአይሁድ እምነት መካከል ጉልሕ መመሳሰሎች አሉ:: ከመመሳሰሉቹ ውስጥ ጥቂቶቹ፣ እግዚአብሔር የፍጥረተ ዓለሙ ፈጣሪ ነው፤ እግዚአብሔር ቅዱሳት መጻሕፍትን ለነቢያቱ ሰጥቶአል፤ ነቢያትን ልኮአል፤ ለእግዚአብሔር/ለአላህ ሕግ መገዛት ይገባል የሚሉት ትምህርቶች ይገኙበታል:: ይሁን እንጂ መሐመድ በተለይ በመዲና ከነበሩት አይሁድ የሚበዙቱ እንደ እግዚአብሔር ነቢይ አድርገው ስላልተቀበሏቸው ማዘናቸው አልቀረም:: በመዲና፣ በሙስሊሞችና በአይሁዶች መካከል የነበረው ግንኙነት አንዱ ሌላውን በመንቀፍ ላይ ያተኮረ ሲሆን፣ ኋላም ግጭትን አስከትሎአል:: የግጭቱ መንሥኤም አይሁዶች የሙስሊሞችን እንቅስቃሴ ለማዳከም እያሤሩ ናቸው የሚል ጥርጣሬ በሙስሊሞች ዘንድ ስለነበር ነው::

በተለይ በሙስሊሙ ማኅበረሰብ ጅማሬ ወቅት አይሁዶች የጐላ ሚና ቢኖራቸውም፣ ግንኙነታቸው ባመዛኙ ፍጥጫ የነገሠበት ነበር:: በቁርአን ውስጥ

የሚገኙት ማኅበረሰባዊ ሕጎችና ማኅበራዊ ግንኙነቶችን በተመለከተ የይሁዲ እምነት ያለው አስተምህሮ የመመሳሰሉ ጉዳይ የሚያስደንቅ ነው፡፡

በቶሮንቶ የነገረ መለኮት ትምህርት ቤት የእስልምና ሃይማኖት ምሁር የሆነው ዱድሌይ ውድቤሪ ስለ እስልምና እንቅስቃሴ ሲናገር፣ እስልምና "የአይሁድ እምነት በድኅረ ክርስቶስ ዘመን ያለውን እምነት የሚመስል ሃይማኖት ነው" ይላል፡፡

መሐመድ ከአይሁዶች ጋር ዕርቅ ለመመሥረት ያደርጉ የነበረውን ፍላጎትና ጥረት እርግፍ አድርገው የተውት፣ ነገሮች በዚህ መልክ እየተካረሩ በመሄዳቸው ነበር፡፡ ነገር ግን በሙስሊሞችና በአይሁዶች መካከል የነበረው ቅራኔ መፈታት ስላልተቻለ፣ መሐመድ የሃይማኖት ሥርዐቶች ለውጥ አደረጉ፡፡ በዚህም መሠረት ቀድሞ ወደ ኢየሩሳሌም አቅጣጫ ይሰገድ የነበረው ሶላት ወደ መካ እንዲዞር እንዲሁም በአይሁድ የሰንበት ቀን ወይም በክርስቲያኖች የአምልኮ ቀን (እሑድ) የነበረው የሙስሊሞች የአምልኮ ቀን፣ ወደ ዐርብ እንዲዞር ተደረገ፡፡ በሙስሊሞችና በአይሁዶች መካከል የነበረው ቅራኔ እየተባባሰ ሲሄድ፣ በአይሁድ የሥርየት ቀን የነበረው የሙስሊሞች ጾም፣ በወር ተራዝሞ ወደ ረመዳን ወር እንዲሸጋገር ተደረገ፡፡ ከእነዚህ ለውጦች በኋላ፣ ሙስሊሞች እምነታቸውን ከአይሁዶችና ከክርስቲያኖች እምነት በተለየ መልኩ እንዲደራጅና እንዲቀጥል ጥረት የማድረግ እንቅስቃሴ ጀመሩ፡፡

## የአብርሃም እምነት

"ሐኒፍ" የተሰኘው የእምነት ቡድን፣ በዐረብ ምድር ከሚገኙት እምነቶች አንዱ ሲሆን፣ በእስልምና ውስጥ ትቶት ባለፈው አሻራ በአራተኝነት ይፈረጃል፡፡ የሐኒፍ እምነት አስተምህሮ ያተኰረው በፈጣሪ አንድነት ላይ ነው፡፡ አንዳንድ የሐኒፍ እምነት ተከታዮች፣ ስለአብርሃም በቂ ግንዛቤ የነበራቸው ሲሆን፣ የአብርሃምን አምላክ እንደሚያመልኩ ይገልጻሉ፡፡

የመሐመድ የእምነት ጉዞ ከሐኒፍ እምነት ተከታዮች ጋር በአያሌው የተጣጣመ ነበር፡፡ የአብርሃምን አምላክ እናመልካለን የሚለው የሐኒፎች እምነትና አስተምህሮ በሙስሊሙ ማኅበረሰብ ውስጥ በስፋት ሲንጸባረቅ ይታያል፡፡ የሙስሊሙ ማኅበረሰብም እያደገ ሲመጣ፣ እስልምና ከአይሁድ እምነትና ከክርስትና የተለየ እንደ ሆነ፣ ነገር ግን እስልምና የአብርሃም እምነት ነው የሚል አስተምህሮ ማራመድ ጀመረ፡፡ በካዕባ የሚደረጉት ሃይማኖታዊ ሥርዐቶች፣ አብርሃም ወደ አላህ ቤት ያደረገውን ጉዞ ለማስታወስ እንደ ሆነ



ይነገራል፡፡ ታሪክ እንደሚያሳየን ዐረቦች የእስማኤል ዘሮች ናቸው፡፡ መሐመድም ከዚሁ የዘር ሐረግ የተገኘ ነው፡፡ ስለዚህ እስልምና ደብዝዞ የነበረውን የአብርሃም እምነት ዳግም ተመልሶ እንዲታደስ አደረገ፡፡ አብርሃም አላህ ልጁን መሥዋዕት እንዲያደርግ ባዘዘው ጊዜ በፍጹም ልቡ እንደታዘዘ ሁሉ፣ ሙስሊም የሚለውም ቃል የሚገልጸው፣ እንደ አብርሃም በፍጹም ልባቸው ለአላህ የሚታዘዙ ሰዎችን ነው፡፡

ለእስልምና እንቅስቃሴ አብርሃምና እስማኤል መንፈሳዊ አባቶች ተደርገው ከተወሰዱ በኋላ፣ እስልምናና አይሁድ የተለያዩ እምነቶች ሆነው ጉዞ ጀመሩ፡፡ በሙስሊሙ ማኅበረሰብ ዘንድ እስራኤል፣ "ለዓለም ሕዝቦች ብርሃን ናት" የሚል ስያሜ ተሰጥቶአታል[4]፡፡

ከመሐመድ በፊት በነበሩት ዘመናት ስለአብርሃምና ስለእስማኤል ያለው ታሪክና አስተምህሮ፣ በዐረቦች መካከል በስፋት ተሠራጭቶ ይገኝ ነበር፡፡ ስለአብርሃምና ስለእስማኤል ለነበረው አስተምህሮ መስፋፋት አስተዋጽኦ ያደረጉት ደግሞ፣ የሐኒፍ እምነት ተከታዮች ናቸው፡፡ ይህ ለመሆኑ ከሚቀርበው ማስረጃ መካል አንዱ፣ ሐኒፎች ስለአብርሃምና ስለእስማኤል ያስተምሩ ስለነበር እንዲሁም እምነታቸው የአብርሃም እምነት እንደ ሆነ አጠንክረው የሚናገሩ መሆናቸው ነው፡፡ በዚያን ጊዜ በዐረብ ምድር ዐረቦች የሚያመልኳቸው በርካታ አማልክት ቢኖሩም፣ ሐኒፎች ግን የሁሉ ፈጣሪ የሆነውን አምላክ (አላህን) ብቻ እናመልካለን ይሉ ነበር፡፡ መሐመድ አንድ አምላክ (አላህን) ከሚያመልኩ ሰዎች መካከል አንዱ ነበር፡፡ መሐመድ መዲና ይኖሩ የነበሩት አይሁዶች ነቢይነቱን አንቀበልም ሲሉ፣ እስልምና የአብርሃም እምነት ነው የሚለውን አመለካከት አጠናክሮ ቀጠለ[5]፡፡

ቀደም ብለን እንደ ተመለከትነው የጃሂሊያ፣ የክርስትና፣ የአይሁድና የሐኒፍ እምነቶች ለሙስሊም ማኅበረሰብ (ኡማ) መፈጠርና መስፋፋት የየራሳቸው አስተዋጽኦ አድርገዋል፡፡ ስለዐረብ ምድርና ስለሙስሊም እንቅስቃሴ በጥልቀት ማጥናት የሚፈልጉ ሰዎች፣ የፍሊፕ ሒይቲን [Philip K. Hitti, *History of the Arabs*, rev., 10th ed. (New York: Macmillan, 2002)] መጽሐፍ ቢያነቡ፣ ጠቃሚ የሆኑ መረጃዎችን ያገኛሉ[6]፡፡

---

4 W. Montgomery Watt, *Muhammad Prophet and Statesman* (New York: Oxford University Press, 1969), 117-118.

5 Cragg, *Muhammad and the Christian*, 90.

6 Philip K. Hitti, *History of the Arabs*, rev., 10th ed. (New York: Macmillan, 2002).

የጥናታችን ትልቁ ትኩረት የሙስሊም ማኅበረሰብና የቤተ ክርስቲያን ነገረ መለኮታዊ መሠረት ምን እንደ ሆነ መረዳት ስለሆነ፣ በመሐመድ ዘመን የነበረው የቤተ ክርስቲያን እንቅስቃሴ ምን እንደሚመስል መዳሰሱ ተገቢ ይሆናል::

## የቤተ ክርስቲያን ሁኔታ

በሰባተኛው ክፍለ ዘመን በዐረብያ የጠረፍ አካባቢዎች ክርስትና መስፋፋት ጀምሮ ነበር:: የደቡባዊ የመን ግዛት ነዋሪዎች፣ ክርስቲያኖች እንደ ነበሩ ይገመታል:: ኢትዮጵያና ግብፅ የክርስቲያን አገሮች ሲሆኑ፣ መጽሐፍ ቅዱስ በራሳቸው ቋንቋ እንዲተረጐም አድርገዋል:: በግብፅ መጽሐፍ ቅዱስ በሦስት የግብፅ ቋንቋዎች ተተርጉሞ ነበር:: የፍልስጥኤም፣ የሶሪያና የመስጴጦምያ አብዛኛው ነዋሪ ክርስቲያን ነበር:: በመስጴጦምያ የኢዴሳ መንግሥት ተከታታይነት ያለው የወንጌል ሥርጭት ወደ ፐርዥያና ወደ ቻይና ያደርግ ነበር:: በዚህ መጽሐፍ ምዕራፍ አንድ ላይ በፐርዥያ ስላለችው ቤተ ክርስቲያን እንዲሁም በ4ኛው ክፍለ ዘመን በዚያ ስለነበረው ስደት ተመልክተን ነበር:: ነገር ግን በዚያ ስፍራ የነበረችው ቤተ ክርስቲያን፣ ዘገምተኛ ማገገም ማሳየት ጀምራለች:: በኢዴሳ እንዳለችው ቤተ ክርስቲያን በፐርዥያ የምትገኘውም ቤተ ክርስቲያን ሚስዮናውያንን ወደ ሌሎች አካባቢዎች የምትልክ ቤተ ክርስቲያን ነበረች:: በሚያደርጉትም የወንጌል ሥርጭት መካከለኛው እስያንና ቻይናን በወንጌል ለመድረስ ችለዋል::

ከዚህ በተጨማሪ በዐረብያ ምድር የክርስቲያኑ ማኅበረሰብ እንዲሁም ተበታትነው ይኖሩ የነበሩ ክርስቲያኖች ይገኙ ነበር:: ዳሩ ግን በዐረብያ ክርስቲያኖች ይኑሩ እንጂ፣ በዐረብኛ ቋንቋ የተዘጋጀ መጽሐፍ ቅዱስ አልነበራቸውም[7]:: ዐረቦች በዚህ ዐይነት ሁኔታ ውስጥ እንዳሉ ነበር መሐመድ የቁርአን መልእክት ከአላህ ዘንድ ተቀብያለሁ ያሉት (ሱራ 13÷30-31: 36-39):: ይህ ክሥተት ለዐረቦች አስደናቂ ተአምርና ከዓለም ሥልጣኔ ወደ ኋላ ለቀረችው የዐረብ ምድር ታላቅ የምሥራች ነበር::

በሌላ አንጻር ደግሞ የክርስቲያኑ ማኅበረሰብ በነገረ መለኮታዊ ጉዳዮች በተለይም ደግሞ የክርስቶስ ባሕርያትን በተመለከተ ከፍተኛ ውዝግብ ውስጥ ነበር:: ቤተ ክርስቲያናት ከመንግሥት ጋር ሊኖራቸው የሚገባው ግንኙነት ምን መልክ ይኑረው የሚለውን ጥያቄ ለመመለስም ጭንቅ ውስጥ ነበሩ::

[7] John P. Kealy and David W. Shenk, *The Early Church and Africa* (Nairobi: Oxford University Press, 1975), 168-88.



እነዚህ ሁለቱ ጉዳዮች ማለትም የክርስቶስ ባሕርያትና የቤተ ክርስቲያንና የመንግሥት ግንኙነት፣ የቤተ ክርስቲያን ቀዳሚ አጀንዳዎች ነበሩ:: ከእነዚህ ጉዳዮች ጋር በተያያዘ በክርስቲያኖች መካከል የነበሩት ችግሮች፣ በ7ኛው ክፍለ ዘመን በነበረው የሙስሊሞችና የክርስቲያኖች ማኅበረሰብ ላይ ተፅዕኖ ነበረው:: ከዚህ በመነሣት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የነበሩ ችግሮች ለሙስሊም ማኅበረሰብ መፈጠር ያደረጉትን አስተዋጽኦና የሙስሊሙ ማኅበረሰብ ከቤተ ክርስቲያን ጋር የነበረውን ግንኙነት ለመዳሰስ እንሞክራለን::

## ኢየሱስ ማን ነው?

ከክርስቶስ ልደት በኋላ ባሉት ሦስት መቶ ዓመታት ውስጥ፣ የቤተ ክርስቲያን ዕድገት ተስፋ ሰጪ ቢሆንም፣ አመርቂ የሚባል ግን አልነበረም:: አንዳንዴ ክርስቲያን ካልሆኑ ሰዎች የሚነሣው ስደት፣ የቤተ ክርስቲያንን ዕድገት ሲፈታተን ቆይቶአል:: ነገር ግን እንደ ጉርጉሮሳውያኑ የዘመን አቆጣጠር ከ313 ዓ.ም ጀምሮ በሮማ ግዛት የነበረውን ስደት የሚሽር ዐዋጅ በመውጣቱ ምክንያት የስደቱ ዘመን ሊያበቃ ችሎአል:: ብዙም ሳይቆይ የሮማ ባለሥልጣናት በግዛቲቱ የሚኖሩ ሰዎች ክርስትናን እንዲቀበሉ መስበክ ጀመሩ:: በመሆኑም በብዙ ሚሊዮን የሚቈጠሩ ሰዎች ከጣዖት አምልኮ ወደ ክርስትና መጥተዋል:: በዚህ ሂደት ውስጥ ቤተ ክርስቲያን በሚሊዮን ለሚቈጠሩ አዲስ አማኞች የሥላሴን አስተምህሮ የምታስተምረው እንዴት ነው? የሚለው ጥያቄ መልስ ማግኘት ያለበት ጉዳይ ነበር:: ይህ እንዳለ ሆኖ የመጀመሪዪቱ ቤተ ክርስቲያን ብዙ የክርስትና ቡድኖች ያሉባት ብትሆንም፣ የእምነት አቋሞችዋን በትክክል ማስቀመጥ እንዳለባት አላስተዋለችም ነበር:: ነገር ግን በ4ኛው ክፍለ ዘመን በሮማ መንግሥት ሥር የነበሩ አካባቢዎች የክርስትናን እምነት ሲቀበሉ፣ አንዳንድ ሰዎች ግን የሥላሴ አስተምህሮን በተመለከተ የነበራቸው አስተሳሰብ፣ የሥላሴ አስተምህሮ መድብለ አማልክትን (ጣዖታትን) ከማምለክ የሚለይ አይደለም የሚል ነበር:: ከዚህ ችግር የተነሣ ክርስቶስ ማን ነው? የሚለው ጥያቄ በብዙዎች ዘንድ ለውይይት የሚቀርብ ርእስ ጉዳይ ነበር::

ግብፅ ላይ በተካሄደው የቤተ ክርስቲያን ጉባኤ ላይ አርዮስ የተባለ ሰው የቤተ ክርስቲያን መጋቢዎችን፣ “ማመን ያለብን አንድን አምላክ ነው፤ ክርስቶስ መለኮታዊ የእግዚአብሔር ልጅ አይደለም” በማለት ስለተከራከራቸው መጋቢያኑ ከቶኛ መደናገጥ ጀመሩ:: የአሪዮስ አስተምህሮ በክርስቲያኖች መካከል ስለክርስቶስ ማንነት ክርክር እንዲነሣ አደረገ:: ክርክሩ በአጠቃላይ

በግብፅ ሕዝብ ይኸውም በገበሬዎች፣ ሸቀጥ በመንገድ ዳር በሚቸረችሩ ሰዎች፣ ዕቃ በግመል ጭነው ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ በሚያጓጉዙ ሰዎች እንዲሁም በሌሎች ሰዎች ዘንድ የውይይት ርእስ ሆነ። በ4ኛው ክፍለ ዘመን የአርዮስ ትምህርት ግብፅን ዐልፎ እንደ ሰደድ እሳት ወደ ሌሎች አካባቢዎች በአጭር ጊዜ ውስጥ ተዛመተ። ከጣዖት አምልኮ ወደ ክርስትና ለመጡ ክርስቲያኖች የአርዮስ ትምህርት የሥላሴን አስተምህሮ ለመረዳት የተሻለ አማራጭ ሆኖ ስላገኙት የአርዮስን ትምህርት መርጠዋል።

የሮማ ንጉሠ ነገሥት የነበረው ቈስጠንጢኖስ እንኳ ሳይቀር፣ በክርክሩ ተሳትፎአል። የሮም ንጉሥ የሁሉም አብያተ ክርስቲያናት ጳጳሳት በኒቂያ ተሰብስበው በክርስቶስ ማንነት ላይ እንዲነጋገሩና ውሳኔ እንዲያሳልፉ ሲያደርግ፣ ክርስቲያኖች በሙሉ ሊደነቁ እንደሚችሉ ማሰብ እንችላለን። የመደነቃቸውም ምክንያት ከጥቂት ዓመታት በፊት ማለትም እንደ ጎርጎሮሳውያኑ የዘመን አቈጣጠር ከ303-312 ዓ.ም ላይ ቤተ ክርስቲያን በሮም መንግሥት ከፍተኛ ስደት ሲደርስባት ስለ ነበር ነው። እንደ ጎርጎሮሳውያኑ የዘመን አቈጣጠር በ325 ዓ.ም ይኸውም ስደቱ ካበቃ ከ13 ዓመት በኋላ፣ ቈስጠንጢኖስ ሕጋዊ የሆነ የቤተ ክርስቲያን ጉባኤ በኒቂያ እንዲዘጋጅ አደረገ። በዚህ ጉባኤ ወደ ሦስት መቶ የሚደርሱ ጳጳሳት ተካፋዮች ነበሩ። ስብሰባው ለሦስት ወራት ያህል የተካሄደ ነበር። የቤተ ክርስቲያን ጉባኤው በክርስቶስ ማንነት ላይ በጥልቀት ከተወያየ በኋላ፣ ስለ ክርስቶስ ማንነት የሚከተለውን መግለጫ አውጥቶአል። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ "ከአምላክም አምላክ፣ ከብርሃንም ብርሃን፣ ከእውነተኛ እግዚአብሔር እውነተኛ እግዚአብሔር፣ የተወለደ ነገር ግን ያልተፈጠረ፣ ከአብ ጋር አንድ ዐይነት ባሕርይ ያለው ነው"[8]። ይህ የሃይማኖት መግለጫ የኒቂያ የሃይማኖት መግለጫ በመባል ይታወቃል።

## እስልምናና የአርዮሳውያን እምነት

እየዋለ እያደረ የአርዮሳውያን እንቅስቃሴ እየተዳከመ ሄደ። ቤተ ክርስቲያን በጉባኤ ኒቂያ መሠረተ እምነቷን ይፋ እንዳደረገችው ሁሉ፣ ቤተ ክርስቲያናት የአሪዮሳውያንን አስተምህሮ ሊቀበሉ አልቻሉም። በጣም የሚያሳዝነው ግን ቤተ ክርስቲያንና መንግሥት አሪዮሳውያንን ለማጥፋት ኀይልን የመጠቀማቸው

[8] J. W. C. Wand, *A History of the Early Church to A.D. 500* (New3 York: Methuen & Co., 1965), 157.



ጉዳይ ነው። ይህ እንዳለ ሆኖ አሪዮሳውያን ስለ ክርስቶስ ማንነት ያላቸው አስተምህሮ፣ የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ከሚያስተምሩት መሠረታዊ አስተምህሮ ጋር የሚጣጣም አልነበረም። ይህ ለአሪዮሳውያን እምነት መዳከም እንደ ዋነኛ ምክንያት የሚጠቀስ ጉዳይ ነው። ለጊዜው ብዙ ሰዎች ወደዚህ እምነት ቢሳቡም እንኳ፣ አስተምህሮው የወንጌልን እውነት ስለማይገልጥ የኋላ ኋላ እየከሠመ ሊሄድ ችሎአል።

አስገራሚው ጉዳይ ግን አርዮሳውያን ከተነሡ ከሦስት መቶ ዓመታት በኋላ የእስልምና እምነት ሲቈረቈር፣ ቁርአን ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ማንነት የሚያስተምረው ትምህርት ከአርዮስ አስተምህሮ ጋር ተመሳሳይነት ያለው ሆኖ መገኘቱ ነው። በእስልምና ሃይማኖት ኢየሱስ ክርስቶስ (ኢሳ) የተከበረ ነው ቢባልም እንኳ፣ ኢየሱስ የእግዚአብሔር መገለጥ ነው የሚለው የክርስቲያኖች እምነት በሙስሊሞቹ ዘንድ ተቀባይነት የለውም። ሙስሊሞች የኢየሱስን መሲሕነት ቢቀበሉም፣ የእግዚአብሔር ልጅ ነው የሚለውን ጉዳይ አጥብቀው ይቃወማሉ። ስለዚህ የአርዮስ አስተምህሮ ከቤተ ክርስቲያን ቢወገድም፣ የእስልምና እምነት ከአርዮስ ትምህርት ጋር ተመሳሳይ የመሆኑ ጉዳይ፣ የአርዮስ አስተምህሮ መልኩን ቀይሮ ተገለጠ ማለት ይቻላል።

## ኢየሱስ ክርስቶስና ፈላስፎች

የአርዮስ አስተምህሮ በተነሣበት ዘመን፣ ቤተ ክርስቲያንን የሚያውክ ሌላ የነገረ መለኮት ውዝግብ ተነሥቶ ነበር። ቀደም ብለን እንደ ተመለከትነው የአርዮስ ትምህርት ክርስቲያኖች የመድብለ አማልክት አምላኪያን ናቸው ለሚለው ትምህርት ምላሽ ነበር። ነገር ግን ከዚህ እንቅስቃሴ በኋላ በግሪክ የተነሣው አዲሱ አፍላጦናዊነት፣ መንፈስ ሠናይ (ጥሩ) ሲሆን ሥጋ (ቍስ አካል) ግን እኵይ (ክፉ) ነው የሚል ነበር። ምንም እንኳ ይህ ትምህርት በስፋት የተሠራጨ ቢሆንም፣ አንዳችም መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት አልነበረውም።

እነዚህ ፈላስፎችም ስለ ክርስቶስ እንዲህ ሲሉ ይጠይቁ ነበር፤ "ሠናይ እንዲሁም መንፈስ የሆነው እግዚአብሔር፣ ሰው ከሆነው ከናዝሬቱ ኢየሱስ ጋር እንዴት አንድ ሊሆን ይችላል? ዘላለማዊ መንፈስ የሆነ አምላክ በመስቀል ላይ ተሰቅሎ እንዴት ሊሞት ይችላል?"። ከእነዚህ ክርክሮች የተነሣ እንደ ጎርጎሮሳውያኑ የዘመን አቈጣጠር በ451 ዓ.ም በኬልቄዶን የተካሄደው ጉባኤ እንዲሁም ሌሎች መሰል ጉባኤዎች በዚህና ይህን መሰል በሆኑ ርእስ ጉዳዮች

ላይ ትኩረት ያደረጉ ነበሩ። ይህ ወቅት ለቤተ ክርስቲያን ፈታኝ ወቅት ነበር።
ቤተ ክርስቲያን በእነዚህ ችግሮች ውስጥ እንዳለች፣ በእስያ ያሉት የምሥራቅ ቤተ ክርስቲያን አማኒያን በመንግሥት ከምትደገፈው ከምዕራቧ ቤተ ክርስቲያን ራሳቸውን ለማግለል ወሰኑ። ከዚያ በኋላ የንስጥሮሳውያን አስተምህሮ በምሥራቋ ቤተ ክርስቲያን ሥር እየሰደደና እየተጠናከረ መጣ። ይህም በምዕራብ ለሚገኘው የክርስትና አስተምህሮ አማራጭ ትምህርት ሆኖ ቀረበ።

ጳጳስ ንስጥሮስ ድንግል ማርያም የክርስቶስ እናት እንጂ፣ የአምላክ እናት መባል የለባትም የሚል ሐሳብ አቀረበ። ይህም ሐሳብ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ረጅም ክርክር እንዲነሣ አደረገ። በምሥራቅ የሚገኙት አብያተ ክርስቲያናት፣ ጳጳሳትና መንግሥት በአንድነት ከሚሠሩባት ከምዕራቧ ቤተ ክርስቲያን ጋር ልዩነት እንዳላቸው አስታወቁ። ልዩነቱ አስተምህሮአዊና፣ አስተምህሮአዊ ባልሆኑ ርእስ ጉዳዮችም ላይ እንደ ሆነ ይፋ አደረጉ። ከእነዚህም ውስጥ አንዳንድ የምሥራቅ አብያተ ክርስቲያናት የንስጥሮስን አስተምህሮ ተቀብለዋል[9]።

በሰባተኛው ክፍለ ዘመን ሙስሊሞች የምሥራቁንና የምዕራቡን ክርስቲያን ግዛቶች ሲቈጣጠሩ፣ በክርስትና ውስጥ ያሉትንና ያወዛግቡ የነበሩትን የነገረ መለኮት ርእስ ጉዳዮች ለማብራራትና ሰላምን ለማውረድ ተልእኮ እንዳላቸው ይገልጹ ነበር። እነዚህ ሙስሊሞችም የሥላሴ አስተምህሮ ስሕተት መሆኑን፣ ክርስቶስ፣ ሰው እንጂ አምላክ እንዳልሆነ፣ በመስቀል ላይ ተሰቅሎም እንዳልሞተ፣ ሊሞትም እንደማይችል ይገልጹና ይከራከሩ ጀመር።

ቀስ በቀስ ብዙ ክርስቲያኖች ይህ የሙስሊሞች አስተምህሮ ትክክል እንደ ሆነ ተቀበሉ። በሰሜን አፍሪካና በመካከለኛው ምሥራቅ የሚኖሩ አብዛኞቹ ሙስሊሞች የዘር ሐረጋቸውን ስንቈጥር እንዝላቶቻቸውና እንጅላቶቻቸው በአንድ ዘመን ክርስቲያኖች የነበሩ ናቸው። ክርስቲያኖች ወደ እስልምና እንዲቀየሩ ያደረጋቸው፣ የእስልምና እምነት አስተምህሮዎች ክርስቲያኖችን የሚስቡ ስለሆኑ ብቻ ሳይሆን፣ በሙስሊም ግዛቶች ውስጥ የሚኖሩ ክርስቲያኖች የእስልምናን ሃይማኖት እንዲቀበሉ ጫና ይደረግባቸው ስለ ነበር ነው።

---

[9] Ibid., 223.



## በሰው ዐይን የማይሞላ እምነት

የክርስትና እምነት እንቅስቃሴ የጀመረው፣ ዝቅተኛ ኑሮ ከሚኖሩ ሰዎች መካከል ነው። በናዝሬት ከተማ የምትኖር ድንግል፣ በግርግም የተኛ ሕፃን፣ መንጐቻቸውን በኩረብቶች አካባቢ የሚያሠማሩ እረኞች፣ ከምሥራቅ የመጡ የከዋክብት ተመራማሪዎች፣ ወደ ግብፅ የተሰደደ ቤተሰብ፣ ከኢየሩሳሌም ውጪ በኩረብታ ላይ ያለ መስቀል፣ ዓሣ ያጠምዱ የነበሩትን ደቀ መዛሙርት በሐይቅ ዳር ያገኘ የትንሣኤ ጌታ። እነዚህ ሁሉ ክሥተቶች የተፈጸሙት በሰው ዐይን እዚህ ግቡ በማይባሉ ሰዎች እንደ ሆነ ሁሉ፣ ቤተ ክርስቲያንም እንደዚህ ዐይነቱን የኅብረተሰብ ክፍል በወንጌል በመድረስ ወንጌል በሰው ሕይወት ውስጥ የሚያስከትለውን መለኮታዊ ኀይል በማሳየት ታላቅ ተሐድሶን አምጥታለች። ነገር ግን በንጉሥ ቈስጠንጢኖስ አማካይነት የተካሄደው ለውጥ፣ በምዕራቧ ቤተ ክርስቲያን የሚገኙ ጳጳሳት በማኅበረሰቡ ውስጥ እጅግ ትልቅ ሥልጣን እንዲኖራቸው አድርጉአል። ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ቤተ ክርስቲያን ዝቅተኛ ከሚባለው የማኅበረሰብ ክፍል ተነሥታ፣ የሥልጣን ማዕከል ወደ መሆን እንዲሁም የነገሥታትን ሥልጣን ጠባቂ ወደ መሆን ተሸጋግራለች።

በተመሳሳይ ሁኔታ እስልምናም ያቈጠቈጠው ዝቅተኛ ከሆነ የማኅበረሰብ ክፍል ነው። የዐረቡ ዓለም የኀይል የበላይነት ያልነበረውና በሠለጠኑት የጉረቤት መንግሥታት ከፋኛ የሚናቅ አካባቢ ነበር። ከእስልምና በፊት ዐረቦች ትኩረት የተሰጣቸው ሕዝቦች አልነበሩም። የሙስሊሙ ኅብረተሰብ ጠንክሮ ለዓለም ሕዝቦች ሁሉ ምስክር እንዲሆን ያደረገው የአላህ ቸርነት እንደ ሆነ ሙስሊሞች ያምናሉ።

ሙስሊሞች፣ ከአነስተኛና ከተናቀ የዐረብ ጐሣ የተነሣው የሙስሊሙ ማኅበረሰብ (ኡማ) በተከፋፈሉት ክርስቲያኖችና አይሁዶች መካከል ሰላምን የማምጣት ተልእኮ ከፈጣሪ ዘንድ እንደ ተሰጠው ጠንካራ እምነት ነበራቸው። ኡማው፣ በወቅቱ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ክርስቶስን አስመልክቶ ይካሄዱ የነበሩትን እሰጣገባዎች የመፍታት ተልእኮ አለው የሚል እምነት በሙስሊሞች ዘንድ አለ። ሙስሊሞች የዓለም ማኅበረሰብን በተመለከተ ትልቅ ራእይ እንዳላቸው ያምናሉ። ሙስሊሞች፣ የነቢያት መደምደሚያ በሆነው፣ ፊደል ባልቈጠረውና ያለወላጅ ባደገው መሐመድ አማካይነት የተጀመረው ሃይማኖታዊ እንቅስቃሴ፣ ለዓለም ሕዝቦች ሁሉ የቁርአንን እውነት የመመስከር ኀላፊነት ከአላህ ዘንድ እንደ ተሰጠው ይናገራሉ። በሌሎች ሕዝቦች ዘንድ ተንቆ የነበረውም የዐረብኛ ቋንቋ፣ አላህ የመጨረሻውን መገለጥ ያስተዋወቀበት ቋንቋ እንደ ሆነ ሙስሊሞች ያምናሉ። በሙስሊሞች

አመለካከት በሌሎች ሕዝቦች የተረሱት ዐረቦች፣ አላህ ለዓለም ሁሉ ሕዝብ የሚሆን መልእክት በእነርሱ በኩል ልኳል የሚል ጽኑ እምነት አላቸው።

## ለሁሉ ቦታ የሚሆን እምነት

ሙስሊሞች የእስልምና ሃይማኖት በዓለም ላሉ ሕዝቦች ሁሉ የሚሆን እምነት እንደ ሆነ ያምናሉ። ከዚህ የተነሣም ሙስሊሞች፣ ሰዎች የእስልምናን ሃይማኖት እንዲቀላቀሉ ጥሪ ከማቅረብ ባለፈ፣ እስልምናን የተቀበሉ በአላህ አገዛዝ ሥር መኖር እንደሚጀምሩ ይናገራሉ። በእስልምና ሃይማኖት የምስክርነት አገልግሎትና የግዛት ጥያቄ አብረው የሚታዩ ጉዳዮች ናቸው። በሙስሊሞች አመለካከት የአላህ መገለጥ (ቁርአን) የአላህን ፍጹም ፈቃድ የሚያስታውቅ ስለሆነ፣ እስልምና አንድን አካባቢ ሲቈጣጠር በአካባቢው ያሉ ሕዝቦች ሁሉ በአላህ መንግሥት ቍጥጥር ሥር እንደ ሆኑ ይታሰባል። የእስልምና ቀዳማይ ተልእኮ ፍጽምናን በማኅበረሰብ ውስጥ ማስረጽ ነው። ይኸውም እስልምና—ፍጹም ሃይማኖት፣ ቁርአን—ፍጹም የሆነ የአላህ መገለጥ፣ መሐመድ—ፍጹም ሰው፣ የሸሪአ ሕግ—ፍጹም የሆነ መሪ እንዲሁም የሙስሊም ኡማ—ሚዛናዊና ምርጥ ማኅበረሰብ የሚሉት ናቸው።

ከላይ የተጠቀሱት እነዚህ መሠረታዊ ነጥቦች ሊሆን ያለውን ፍጹም ነገር የሚያመለክቱ በመሆናቸው፣ በእነርሱ ላይ ምንም ዐይነት ትችት መሰንዘር በጥብቅ የተከለከለ ነው። ስለዚህ የሙስሊሙ ማኅበረሰብ የሚያደርገው ነገር በሙሉ ትክክል ነው። ፍጹም ለሆነው የእስልምና እምነት መገዛት ደግሞ በራስ የመተማመንን መንፈስ እንደሚሰጥ ይገለጻል።

ሙስሊሞች በተቈጣጠሯቸው አካባቢዎች ከክርስቲያኖች ጋር እንዴት አብረው መኖር እንዳለባቸው ነቢዩ መሐመድ መመሪያ ሰጥተው ነበር። በዚህም መሠረት ሙስሊሞች ለክርስቲያኖች የደኅንነት ዋስትና ይሰጣሉ። ክርስቲያኖች ደግሞ የደኅንነት ከለላውን የሚያገኙ ሕዝቦች (ዚሚ) ተብለው ይጠራሉ። እስልምና ወደ ተለያዩ ቦታዎች ሲስፋፋ፣ ክርስቲያኖች በሙስሊም ግዛቶች ስለሚያገኙአቸው ከለላዎች የተጠናከረ መመሪያ ወጥቶ ነበር። ለጊዜው ይህንን ጉዳይ በስፋት የምንመለከተው አይሆንም። በደኅንነት ከለላው መሠረት ክርስቲያኖች የማምለክ ነጻነት ነበራቸው። ነገር ግን ሌሎችን ወደ ክርስትና ማምጣት በፍጹም የተከለከለ ነው። በእስልምና ቍጥጥር ሥር በወደቁ አካባቢዎች፣ ከእስልምና ውጪ ሌሎች ሃይማኖቶች እንዲስፋፉ በጭራሽ አይፈለግም። ሃይማኖታዊ እንቅስቃሴዎችን የተመለከቱ ሕጎች ይወጡ



የነበረው ከዚህ ዐላማ አንጻር ብቻ ነው። የጋብቻ ሕግጋት፣ የቤተ ክርስቲያን ሕንፃ ግንባታ፣ ወደ ሌላ እምነት የመቀየርና የቀረጥ ሕጎች በሙሉ፣ የእስልምናን እንቅስቃሴ በሚያበረታታ መልኩ ይዘጋጁ ነበር። በሙስሊም ግዛት ውስጥ የሚኖሩ ክርስቲያኖች ዐልፎ ዐልፎ መብታቸው ተጠብቆ ቢኖሩም እንኳ አብዛኛውን ጊዜ ግን የሚጣሉባቸው እጅግ በርካታ ገደቦች አለመጠን ጥብቅ ነበሩ። አንዳንዴም ጭቆናና ስደት ይደርስባቸው ነበር። ለምሳሌ እንደ ጐርጐርሳውያኑ አቈጣጠር በ807 ዓ.ም ካሊፍ ሐሩን አል-ራሺድ አዳዲስ ቤተ ክርስቲያናት በሙሉ እንዲፈርሱ አድርጓል[10]።

በዚህ ዐይነቱ አካሄድ ከዝቅተኛ የኅብረተሰብ ክፍል የተነሣው የእስልምና ሃይማኖት፣ ወደ ተለያዩ ቦታዎች በፍጥነት ተስፋፋ። በተቃራኒው ደግሞ በሙስሊም ግዛቶች ውስጥ ያሉ ቤተ ክርስቲያናት ያላቸው ተቀባይነትና ዐቅም እየቀነሰ መጣ። ክርስቲያኖች ለዚህ ችግር ምላሽ መስጠት ያለባቸው በምን መልክ ነበር?

## ዝቅተኛውን የማኅበረሰብ ክፍል መሠረት ያደረገ ምስክርነት

ልክ ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱን ዝቅ በማድረግ ወንጌልን ለዝቅተኛው የኅብረተሰብ ክፍል እንደ ሰበከ ሁሉ፣ ለዝቅተኛው የማኅበረሰብ ክፍል ወንጌልን መስበክ የቤተ ክርስቲያን የተልእኮ አካሄድ መሆን አለበት። በሙስሊም ግዛቶች ውስጥ ያሉ ቤተ ክርስቲያናት የተገፉና በመከራ ውስጥ የሚያልፉ በመሆናቸው፣ እንደ ምዕራቧ ቤተ ክርስቲያን ሃይማኖትና መንግሥት ሰላልተጋቡ ቈስጠንጢኖስ ክርስትናን ከመቀበሉ በፊት በክርስቲያኖች ላይ የሚደርሰው መከራ ስለሚደርስባቸው በምስክርነታቸው የወንጌል እውነት ይጸናል። ይሁንና ክርስቲያኖች እግዚአብሔር የሁሉ ነገር ፈጣሪ ሆኖ ሳለ፣ ራሱን ለዓለም የገለጠው በክርስቶስ በኩል በበረት ውስጥ እንዲሁም መኻታውን ግርግም በማድረግ እንደ ሆነ ያምናሉ። ልክ እንደዚሁ የወንጌሉም ሥራ ከትንሽ ወደ ትልቅ ነው።

10 "Three Phases of Christian-Muslim Interaction," *Christian History* 21, no.2 (August 2002): 26.

*የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባብ*

ዮሐንስ ወንጌል 1፥1-18፡ 29-34

*የቁርአን ምንባብ*

ሱራ 2፥135-147

## የአስተውሎትና የውይይት ጥያቄዎች

1. ስለ እስልምና ካወቁት/ከተረዱት ነገር ሁሉ፣ ያስደነቅዎት ነገር ምንድን ነው? በሰባተኛው መቶ ክፍለ ዘመን የነበረችውን ቤተ ክርስቲያን በተመለከተ ያስገረምዎት ነገር ምንድን ነው?
2. ሙስሊሞች ከተሰጣቸው ኀላፊነቶች መካል አንዱ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ማንነት ለክርስቲያኖች ማብራሪያ መስጠት እንደ ሆነ ያምናሉ የሚለውን ሐሳብ ሲያነቡ ምን ዐይነት ስሜት ተሰማዎ? ለዚህ ዐይነቱ ምልከታ ክርስቲያኖች ምላሽ መስጠት ያለባቸው እንዴት ነው?
3. የክርስትናም ሆነ የእስልምና ሃይማኖት እንቅስቃሴዎች የተጀመሩት እዚህ ግባ ከማይባል ዝቅተኛ ስፍራ ነው፡፡ እነዚህ እንቅስቃሴዎች ራሳቸውን የዐቅመ ቢሶች አጋር አድርገው መቀጠር ቀጥለዋል? ለሚሰጡት ምላሽ አጥጋቢ ምክንያት ይስጡ፡፡
4. በሰባተኛው ክፍለ ዘመን፣ በዐረብያ የሚገኘው የሙስሊም ኡማ እንዴት እንደ ተጀመረ ማብራሪያ ይስጡ፡፡
5. በሰባተኛው መቶ ክፍለ ዘመን የሙስሊም ኡማ ሲጀመር አስተዋጽኦ ስላደጉት ስለ አራቱ የእምነት ክፍሎች አስተያየት ይስጡ፡፡ ከአራቱ ውስጥ ለሙስሊም ኡማ መፈጠር ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያለው የትኛው ነው?
6. የዐረብኛው ቁርአን ለዐረቦች በጣም አስፈላጊ የሆነው ለምንድን ነው?
7. በእስያ ምሥራቅ ያሉ ቤተ ክርስቲያናት ከምዕራቧ ቤተ ክርስቲያን የተለዩ መሆናቸውን ማሳወቅ ያስፈለገባቸውን ምክንያቶች ይዘርዝሩ፡፡
8. እርስዎ በሙስሊም ግዛት ውስጥ ከሚኖሩ ክርስቲያኖች (ዚሚ) ውስጥ አንዱ ቢሆኑ እምነትዎን የሚገልጹትና ወንጌልን የሚመሰክሩት እንዴት ባለ መንገድ ይሆናል? በነጻነት የሚኖሩ ክርስቲያኖች በሙስሊም ማኅበረሰብ ውስጥ ከሚኖሩ እንዲሁም የተለያዩ ዐይነት ገደቦች ከሚጣልባቸው ክርስቲያኖች ምን ሊማሩ ይችላሉ?



## ምዕራፍ ሦስት

# በኤድን ገነት

አብዱላሂና እኔ በሶማሊያ አገር ጆሀር በተባለው ስፍራ ወደ አንድ የመንግሥት መሥሪያ ቤት ለመግባት ቀጠሮ ይሰጠን ዘንድ እየተጠባበቅን ነበር፡፡ እንደ ወትሮው ሁሉ የእኔና የአብዱላሂ ውይይት ያተኰረው በእግዚአብሔርና በተፈጥሮ ውስጥ የእግዚአብሔር ተአምራቶች (ምልክቶች) ላይ ነበር፡፡ አብዱላሂ እንዲህ አለኝ፤ "የእግዚአብሔር ተአምራቶችን ተመልከት፤ ነፋስን፣ ዛፎችን፣ አሀዎችንና የራስህን አካል፡፡ እነዚህ ነገሮች ሁሉ የእግዚአብሔር ተአምራቶች ናቸው፤ የእግዚአብሔር ተአምራቶች (አያት) በየትኛውም ስፍራ አሉ፡፡ እነዚህ ተአምራቶች (ምልክቶች) የእግዚአብሔርን ታላቅነት ይገልጣሉ"፡፡

## ፍጥረት

ክርስቲያኖችና ሙስሊሞች እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን እንደ ፈጠረ ያምናሉ፡፡ እንዲሁም ሁለቱም ወገኖች፣ አዳምና ሔዋን (ሐዋ) እግዚአብሔር ባዘጋጀው በኤድን ገነት ውስጥ የመጀመሪያ ነዋሪዎች እንደ ሆኑ ይስማማሉ፡፡ እስልምናም ክርስትናም ፍጥረት መልካም እንደ ሆነና እግዚአብሔር ግን ከፍጥረቱ የተለየና ምጡቅ[1] አምላክ እንደ ሆነ ያምናሉ፡፡ እግዚአብሔር በፍጥረቱ ውስጥ ራሱን እንደ ገለጠም ይስማማሉ፡፡

መጽሐፍ ቅዱስ በሮሜ 1፥20 ላይ እንዲህ ይላል፡— "ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ የማይታየው የእግዚአብሔር ባሕርይ ይኸውም ዘላለማዊ ኀይሉና መለኮትነቱ፣ ከፍጥረቱ በግልጽ ይታያል፤ ስለዚህ ሰዎች ማመካኛ የላቸውም"፡፡

ቁርአን በሱረቱ አል-ጋሺያህ 88፥17-21 ላይ ሰዎች ሁሉ በተፈጥሮ ውስጥ የተገለጠውን የእግዚአብሔርን ተአምራቶች (ምልክቶች) በማየት፣ እግዚአብሔርን እንደ አምላክነቱ መጠን እንዲያከብሩት እንዲህ ሲል ጥሪ ያቀርባል፡—

(ከሓዲዎች) አይመለከቱምን?
ወደ ግመል እንዴት እንደ ተፈጠረች!
ወደ ሰማይም እንዴት ከፍ እንደ ተደረገች!

[1] transcendent

> ወደ ተራራዎችም እንዴት እንደ ተቸከሉ!
> ወደ ምድርም እንዴት እንደ ተዘረጋች (አይመለከቱምን?)
> አስታውስም፣ አንተ አስታዋሽ ብቻ ነህና።

መጽሐፍ ቅዱስና ቁርአን ሰማይና ምድር የእግዚአብሔር ፍጥረታት፣ የልዑል አምላክ የእጅ ሥራዎች እንደ ሆኑ ያስተምራሉ። እግዚአብሔርም ይሁኑ አለ፣ ተፈጠሩም! (ዘፍጥረት 1፥3-31፣ ሱራ 2፥117፣ 16፥40)። ፍጥረታት የእግዚአብሔርን ታላቅነት የሚገልጡ ናቸው። እኛም ለእነዚህ ምልክቶች አስፈላጊውን አክብሮት እንድንሰጥና ክብርን ሁሉ ለእግዚአብሔር እንድናቀርብ ታዘናል። እንዲሁም እያንዳንዱ ፍጥረት የተፈጠረው ለዐላማ ነው።

ቁርአን በሱራ 21፥16 እንዲህ ይላል፦ "ሰማይንና ምድርን በመካከላቸው ያለውንም ሁሉ ቀላጆች ኾነን አልፈጠርንም"። ስለዚህ ፍጥረትን ከእግዚአብሔር ጋር የሚያስተካክሉ ወይም ፍጥረትን መለኮት ነው የሚሉ ሰዎች ጠንካራ ቅጣት እንደሚጠብቃቸው በሱራ 21፥18 እንዲህ ተጽፎአል፦

> በእርግጥ እውነትን በውሸት ላይ እንጥላለን፤ አንጎሉን ያፈርሰዋልም፤ ወዲያውም እርሱ ጠፊ ነው፤ ለናንተም ከዚያ (ሚስትንና ልጅ አለው በማለት) ከምትመጥኑት ነገር ብርቱ ቅጣት አላችሁ፤ (ወዮላችሁ)።

እግዚአብሔር ፍጥረትን የፈጠረበት ዐላማ ምን እንደ ሆነ በእስልምና መረዳት ምን ይመስላል? በእስልምና አስተምህሮ ምድር የሰው ልጆች እንዲጠቀሙባት፣ እንዲጠብቋትና እንዲደሰቱባት የተሰጠች የአምላክ ስጦታ ነች። ይህንን ሐሳብ በተመለከተ ቁርአን እንዲህ ይላል፦

> ግመልን ከብትን ፍየልንም በርሷ (ብርድ መከላከያ) ሙቀት ጥቅሞችም ያሉባት ስትኾን ለእናንተ ፈጠረላችሁ፤ ከእርሷም ትበላላችሁ። ለእናንተም በርሷ ወደ ማረፊያዋ በምትመልሷት ጊዜ በምታሰማርዋትም ጊዜ ውበት አላችሁ። ጓዞቻችሁንም በነፍሶች ችግር እንጂ ወደማትደርሱበት አገር ትሸከማለህ፤ ጌታችሁ በእርግጥ ሩኅሩኅ አዛኝ ነውና። ፈረሶችንም፣ በቅሎዎችንም፣ አህዮችንም፣ ልትቀመጡዋቸውና ልታጌጡባቸው (ፈጠረላችሁ)፤ የማታውቁትንም ድንቅ ነገር ይፈጥራል (ሱራ 16፥5-8 በቅንፍ ያለውን ይጨምራል)።

እስልምና ሰዎች እግዚአብሔር በተፈጥሮ ውስጥ የገለጣቸውን ምልክቶች እንዲያከብሩ ያዛል። ዛፎች ለማገዶ ተፈልገው ካልሆነ መቈረጥ የለባቸውም ይላል። እኔ በምሥራቅ አፍሪካ ሙስሊም ተማሪዎችን እያስተማርሁ እያለሁ፣ ከእኔ ጋር ያገለግል የነበረ አሜሪካዊ ጓደኛዬ፣ ዕብድ ውሻ ተኩሶ ገደለ።



ተማሪዎቼ ተናደው "ያለምንም ምክንያት ውሻን መግደል አትችልም!" አሉት። ነገር ግን ጓደኛዬ "እኔ ውሻዪቱን መግደሌ ምሕረት እንዳደረግሁላት ይቈጠራል፤ ምክንያቱም ስለታመመች መሞቷ አይቀርምና" አላቸው። በዚያን ጊዜ ተማሪዎቹ በመልሱ ረኩ፤ ደስም አላቸው።

በእስልምና እምነት ውሃ እንኳ መባከን የለበትም የሚል አቋም አለ። አንድ ሰው ገላውን ሲታጠብ ውሃን በቊጠባ መጠቀም አለበት። ምግብም ሲበላ የሚባክን ምግብ መኖር የለበትም[2]። ለተፈጥሮ ክብካቤ ማድረግ ተገቢ ነው፤ ያለአንዳች ጥቅም የሚቀር ማናቸውም ዐይነት የአላህ ፍጥረት እንደሌለ የእስልምና ሃይማኖት ያስተምራል።

ተፈጥሮ በራሱ ፍጥረታት ሁሉ እግዚአብሔርን እንዲያመልኩ ያነሣሣቸዋል። ስለዚህ ጉዳይ ቁርአን እንዲህ ይላል ፦

> ወደዚያ ከማንኛውም ነገር አላህ ወደ ፈጠረው ጥላዎቹ እነርሱ የተዋረዱ ሲኾኑ ለአላህ ሰጋጆች ኾነው ከቀኝና ከግራዎች ወደሚዛወሩት አላዩምን? ለአላህም በሰማያት ያለው ከተንቀሳቃሽም በምድር ያለው ሁሉ መላእክትም ይሰግዳሉ፤ እነርሱም አይኮሩም። ጌታቸውን ከበላያቸው ሲኾን ይፈሩታል፤ የታዘዙትንም ሁሉ ይሠራሉ (ሱራ 16፥48-50)።

በአንድ ዩኒቨርስቲ ውስጥ ከሙስሊም ባልንጀራዬ ጋር በነበረን ውይይት ጓደኛዬ እንዲህ ሲል ተናግሮ ነበር ፦ "የቁርአን ምንባባት የአላህ ምልክት (ተአምር) እንደ ሆኑ ሁሉ፣ ፍጥረት የእግዚአብሔር ምልክት (ተአምር) ነው። ቅዱሳት መጻሕፍት እንኳ ባይኖሩ፣ የእግዚአብሔርን እውነት ከተፈጥሮ መገንዘብ እንችላለን"።

መጽሐፍ ቅዱስ ፍጥረት የእግዚአብሔር የእጁ ሥራ እንደ ሆነ ይገልጻል። እኛም በመልካሚቱ ምድር ውስጥ እንድንደሰት ተጋብዘናል። መጽሐፍ ቅዱስ ሰዎች ከፈጣሪ ይልቅ ተፈጥሮን ወደ ማምለክ እንዳያዘነብሉ ያስጠነቅቃል (ሮሜ 1፥25)። በእርግጥም በተለያዩ ሃይማኖቶች ውስጥ፣ ሰዎች ከፈጣሪ ይልቅ ፍጥረታትን ሲያመልኩ ይስተዋላል። በዚህ ዘመንም እግዚአብሔር የለም የሚሉ ወገኖች እግዚአብሔርን ወደ ጐን በመተው፣ የሁሉ ነገር ባለሥልጣን ሳይንስና ተፈጥሮ ነው ይላሉ።

---

[2] Badru D. Kateregga and David W. Shenk, *A Muslim and a Christian in Di* (Scottdale, Pa.: Herald Press, 1997), 40.

ቁርአንም ሆነ መጽሐፍ ቅዱስ፣ እግዚአብሔርን ትቶ ተፈጥሮን የማምለክ ዝንባሌን አጥብቀው ይቃወማሉ። እግዚአብሔር ከፍጥረቱ የተለየ ምጡቅ የሆነ አምላክ ነው። ፍጥረቱን በሙሉ በተፈጥሮ ሕግ እንዲንቀሳቀስና እንዲኖር የሚያደርግ ጌታ ነው። ነገር ግን አምላክና ፍጥረት አንድ አይደሉም። በማንኛውም መልኩ ፍጥረትን የሚያመልኩ ሰዎች ሐሰተኛ አማልክትን ያመልካሉ። አምልኮና ስግደት የሚገባው፣ እግዚአብሔር ብቻ ነው።

## አዳምና ሔዋን

ስለ ተፈጥሮ ያለው ግንዛቤ፣ በኤድን ገነት አዳምና ሔዋንን በተመለከተ በቁርአንና በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የምናገኛቸው ገለጻዎች ናቸው። በእያንዳንዱ ባህልና እምነት ውስጥ ስለምድርና ስለሰው አፈጣጠር ያለው አስተምህሮ፣ ሰዎች ስለ ሰው ማንነትና ሁኔታ ባላቸው አመለካከት መሠረት ነው። በተለያየ ማኅበረሰብ ውስጥ ስለ ሰው አፈጣጠር ያሉ ታሪኮች እኛ ማን እንደሆንና ወዴት እየሄድን እንዳለን እንዲሁም ምን ዐይነት እምነት ሊኖረን እንደሚገባ ስለሚነግሩን በዚህ ረገድ ጕልሕ ሚና አላቸው።

በሚከተሉት አንቀጾች ቁርአንና መጽሐፍ ቅዱስ በዚህ ርእስ ጕዳይ ላይ የሚያስተምሩትን ትምህርት በዳሰሳ መልክ እንቃኛለን። ምንም እንኳ ከዚህ በታች የምዘረዝራቸው ሐሳቦች በአንባብያን የሚታወቁ ቢሆኑም፣ የሁለቱን ሃይማኖቶች አመለካከት ለማነጻጸር የተወሰኑ ሐሳቦችን ለማቅረብ እሞክራለሁ። የምዕራፉ ማጠቃለያ የክርስቲያንና የሙስሊም ገለጻዎች ምን ዐይነት እንድምታ እንዳላቸው በንጽጽር ያቀርባል።

### መጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮ

መጽሐፍ ቅዱስ በመጀመሪያዎቹ ሦስት ምዕራፎች ውስጥ፣ የሰዎች ሁሉ አባትና እናት ስለሆኑት ስለአዳምና ስለሔዋን ይናገራል። እግዚአብሔር አዳምንና ሔዋንን የፈጠረው በስድስተኛው ቀን፣ ሌሎች አጥቢ እንስሳትን በተፈጠረበት ጊዜ ነበር። እግዚአብሔር ሰውን በመልኩ ፈጠረ። እነርሱም ከእግዚአብሔር ጋር ቃል ኪዳን ያላቸው ፍጡሮች ሲሆኑ፣ ሰብአዊነታቸውም የተገለጠው ከእግዚአብሔር ጋር በነበራቸው ትክክለኛና አስደሳች ኅብረት ነው። እግዚአብሔር ለመጀመሪያ ጊዜ ከእነርሱ ጋር ያደረገው ቃል ኪዳን የተመሠረተው፣ እንዲፈጽሙት በሰጣቸው ሕግጋት ላይ ነበር። ሕግጋቱም ብዙ ተባዙ፤ ምድርን ግዙአት፤ ምድርንና ዛፎችን ጠብቁ፤ ምድርን ዕረሱ፤ እንስሳትን ጠብቁ፤ ለእንስሳትም ስም አውጡ የሚሉ ነበሩ።



እግዚአብሔርም አዳምንና ሔዋንን ወስዶ በኤድን ገነት አስቀመጣቸው። በኤድን ገነት ውስጥም፣ ሁለት ዐቢይ ትርጕም ያዘሉ ዛፎች ነበሩ። አንደኛው መልካሙንና ክፉውን የሚያስታውቀው ዛፍ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ የሕይወት ዛፍ ነው። እግዚአብሔር፣ ለአዳምና ለሔዋን መልካሙንና ክፉውን ከሚያስታውቀው ዛፍ እንዳይበሉ አዞአቸው ነበር።

እግዚአብሔር አዳምን ከምድር ዐፈር አበጀው። ከአዳምም ጐን ዐጥንት ወስዶ ሔዋንን ሠራ፤ ምክንያቱም ከእንስሳት ውስጥ ለአዳም ረዳት የሚሆነው ፍጥረት ስላልተገኘ ነው። አዳምም በደስታ እንዲህ ብሎ ተናገረ ፦

> ይህች ዐጥንት ከዐጥንቴ ናት፤ ሥጋም ከሥጋዬ ናት፤ እርስዋ ከወንድ ተገኝታለችና ሴት ትባል" (ዘፍጥረት 2፥23)።

ከዚህ በመቀጠልም እንዲህ የሚል ሐሳብ እናነባለን ፦

> ስለዚህ ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል፤ በሚስቱም ይጣበቃል፤ ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ። አዳምና ሚስቱ ሁለቱም ዕራቁታቸውን ነበሩ፤ አይተፋፈሩም ነበር (ዘፍጥረት 2፥24-25)።

በዚህ ክፍል በአዳምና በሔዋን መካከል የተደረገውን ጋብቻ እንመለከታለን። ይህም ሐሳብ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ፣ ስለ ጋብቻ ለተጻፉት ትምህርቶች መሠረት ነው። አዲስ ኪዳንም ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንን እንደወደደ ባል ሚስቱን ይውደዳት በማለት፣ በጋብቻ ውስጥ ያለውን ቃል ኪዳን በሰፊው ያብራራል (ኤፌ 5፥25)። እንዲሁም ሚስት ባልዋን እንድታከብርና በቤት ውስጥ እንድትታዘዘው ተጽፎአል (ኤፌ 5፥22-24:33)። ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባብ የሚጀምረው፣ "እያንዳንዳችሁ በክርስቶስ ፍርሓት የተገዛችሁ ሁኑ" (ኤፌ 5፥21) በሚለው ዐቢይ ትእዛዝ ነው። ትዳር ከእግዚአብሔር መልካም ስጦታዎች መካል አንዱ ነው። በርግጥም እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ያለው ዐላማ አስደናቂ ነው።

ዳሩ ግን ብዙም ሳይቆይ አሳዛኝ አደጋ ተፈጠረ። ሔዋን መልካሙንና ክፉውን ከሚያስታውቀው ዛፍ እንድትበላ እባብ አሳሳታት። አዳምም ከእርሷ ጋር በመተባበር ከዛፉ ወስዶ በላ። ይህ የተከለከለው ዛፍ የተለያየ ዐይነት ትርጕም አለው። ዛፉ በኤድን ገነት ውስጥ ያለ ሲሆን፣ ሰዎች ከእግዚአብሔር ሥልጣን ይልቅ ወደ ተፈጥሮ በልባቸው ማዘንበላቸውን የሚያሳይ የፈተና ምልክት ነው። በዚህም መሠረት አዳምና ሔዋን እግዚአብሔርን ከመታዘዝ ይልቅ ልባቸውን ወደ ተፈጥሮ አዘነበሉ።

እግዚአብሔርን ከመታዘዝ በተመለሱ ጊዜ፣ የዋህነታቸውን ጣሉ። ዕራቁታቸውን በመሆናቸውም ተቁፈሩ፤ ሐፍረተ ሥጋቸውንም ለመሸፈን የበለስን ቅጠሎች ሰፍተው አገለደሙ። የእግዚአብሔርን ድምፅ በሰሙ ጊዜም በገነት ዛፎች ሥር ተሸሸጉ።

እግዚአብሔርም እንዲህ ሲል ጠራቸው :— "አዳምና ሔዋን ወዴት ናችሁ?" እግዚአብሔር አምላክም በገነት ዛፎች ውስጥ ተሸሽገው አገኛቸው። እግዚአብሔር በሠሩት ሥራ ክፉኛ አዘነ። እርሱን ባለመታዘዛቸውም ምክንያት የሚደርስባቸውን አበሣና ሥቃይ ነገራቸው። እንዲሁም አላቸው:— በምትወልጂበት ጊዜ ጭንቅሽ ይበዛል፣ በወንድና በሴት መካከል መከፋፈል ይሆናል፣ ወንዱ ገዢሽ ይሆናል፣ ሥራ አድካሚ ተግባር ይሆንባችኋል፣ እንደ ቀድሞው ተፈጥሮ ዘወትር አስደሳች ብቻ ሳትሆን አስቸጋሪ ትሆንባችኋለች፣ ሰው ምድርን ከመከባከብ ይልቅ አግባብነት በሌለው መንገድ መጠቀም ይጀመራል፣ የሰው ልጆች ምድርን ከመጠበቅና የተሻለ ከማድረግ ይልቅ በምድር ላይ ያሉትን ነገሮች ያበላሻሉ። በመጨረሻም ከሕይወት ዛፍ በልተው ለዘላለም እንዳይኖሩ እግዚአብሔር አዳምንና ሔዋንን ከኤድን ገነት አስወጣቸው። አዳምና ሔዋን ብቻ ሳይሆኑ እግዚአብሔርን ካለመታዘዛችን የተነሣ የእነርሱ ዝርያዎች የሆንን ሁሉ በኀጢአት ወደቅን። ሞትም ወደ ሁላችን መጣ። ጥቂት ቆይቶም በአዳም ቤተሰብ ውስጥ ሞት በመግባቱ ቃየን አቤልን ገደለ።

ከዚህ አሳዛኝ ታሪክ በኋላም ቢሆን፣ እግዚአብሔር አዳምንና ሔዋንን እንዲሁም የሰውን ዘር አልተወም። እግዚአብሔር አዳምና ሔዋን ኀጢአት በሠሩ ጊዜ በኤድን ገነት እንደፈለጋቸው፣ እኛም የትም ብንኖር ምንም ዐይነት ኀጢአት ቢኖርብን እግዚአብሔር ይፈልገናል። ፈጣሪ አምላክ የክፉ መገለጫ ለሆነውና ሰዎችን ወደ ፈተና ለጣለው እባብ እንዲህ ሲል ተናግሮታል:— "በአንተና በሴቲቱ መካከል፣ በዘርህና በዘርዋም መካከል ጠላትነትን አደርጋለሁ፤ እርሱ ራስህን ይቀጠቅጣል፤ አንተም ሰኰናውን ትቀጠቅጣለህ" (ዘፍ 3፥15)። ይህ ተስፋ ምን ማለት ነው? ብዙ ክርስቲያኖች በመጽሐፍ ቅዱስ ስለመሲሑ የተነገረ ተስፋ ነው ብለው ያምናሉ[3]። የክርስቶስ አገልግሎት ከሞት ፍርድ ነጻ ሊያወጣን፣ ኀጢአተኛ ከሆነው ማንነታችን ሊያድነንና ከእግዚአብሔር ጋር ሊያስታርቀን ነው። ለዚህም አገልግሎት እርሱ ለኀጢአተኞችና ለዐመፀኞች ታልፎ በመሰጠት በመስቀል ላይ ሞተ። "ሰኰናውም ቈሰለ"። ይሁንና የሞትን

[3] C. K. Leaman, *Biblical Theology: Old Testament*, vol. 1 (Scottdale, Pa.: Herald Press, 1971), 65.



ጣር አሸንፎ ከሞት ተነሣ፤ በመስቀል ላይ ሞቱና በትንሣኤው የክፉን ራስ ሲቀጠቅጥ፣ ኀጢአተኛነትና ሞት ድል ተነሣ።

እንደዚህ ዐይነት አመለካከት ያላቸው ክርስቲያኖች ዘፍ 3፥15 ላይ ያለው ቃል በዮሐንስ 3፥16 "በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና" በሚለው ቃል ተፈጽሞአል ይላሉ።

መጽሐፍ ቅዱስ ከእንስሳት ቈዳ ልብስ ሠርቶ ለአዳምና ሔዋን አለበሳቸው ይላል። ይህም ልብስ እነርሱ ከበለስ ቅጠል ሰፍተው ካገለደሙት ግልድም በእጅጉ የተሻለ ነው። እግዚአብሔር ያለበሳቸውን ልብስ ለማግኘት እንስሳትን ማረድ (መሥዋዕት ማድረግ) የሚጠይቅ ነው። በባህላዊ እምነቶች ውስጥ ለኀጢአት ይቅርታ ሲባል እንስሳቶችን መሥዋዕት ማድረግ ከዚህ ታሪካዊ ሁኔታ የተቀዳ ይሆንን?[4] ከዚህ ጋር በተያያዘ እንዲህ የሚል ሌላ ጥያቄ ማሰብ ተገቢ ነው:— እግዚአብሔር ለአዳምና ሔዋን ልብስ ሲያለብሳቸው በመፈለጉ ምክንያት እንዲሠዋ ያደረገው እንስሳ ወደ ፊት ለዓለም ሁሉ ኀጢአት መሥዋዕት ስለሆነው መሲሕ ምሳሌ አይደለምን? እንዴታ! ይሆናል እንጂ! በዮሐንስ 1፥29 ከመሲሑ ስሞች ውስጥ "የዓለምን ሁሉ ኀጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ" የሚለው ስም ይህንኑ እውነት የሚያመላክት ነው።

## ቁርአናዊ አስተምህሮ

ከዚህ በመቀጠል ቁርአን ከላይ ባየነው ርእሰ ጉዳይ ዙሪያ የሚያስተምረውን ትምህርት ደግሞ እንመልከት። ቁርአን እግዚአብሔር አዳምን በገነት (ጀና) ውስጥ እንደ ፈጠረው ይናገራል። እግዚአብሔር አዳምን ከሸክላ አበጀው፤ መናፍስትን (ጂኒዎችን) ደግሞ ከእሳት። እግዚአብሔር መንፈሱን በአዳም ውስጥ ዕፍ አለበት። ፈጣሪ አምላክ ለአዳም ከጂኒዎች፣ ከመላእክትና ከእንስሳት የላቀ የአስተሳሰብ ብቃትን ሰጠው። አዳም ከመላእክት እንደሚበልጥ በቁርአን በሱራ 15፥29 እንዲህ ተጽፎአል:—

> ፍጥረቱን ባስተካከልኩትና በውስጡ ከመንፈሴ በነፋሁበትም ጊዜ ለእርሱ ሰጋጆች ኾናችሁ ውደቁ።

[4] René Girard, *I See Satan Fall Like Lightning*, translated by James G. Williams (Maryknoll, N. Y.: Orbis, 2002) and Girard, *Violence and the Sacred*, translated by Patrick Gregory (Baltimore: Johns Hopkins University Press, 1981).

ለዚህም ይመስላል መላእክት እግዚአብሔር ስለአዳም በነበረው ዕቅድ እምብዛም ያልተደሰቱትና ያላወቁት። እግዚአብሔር በምድር ላይ ሰውን እንደሚያስቀምጥ ሲናገራቸው መላእክት እንዲህ በማለት ተቃውመው ነበር፦

(መሐመድ ሆይ) ጌታህ ለመላእክት፦ እኔ በምድር ላይ ምትክን አድራጊ ነኝ፤ ባለ ጊዜ (የኾነውን አስታውስ፤ እነርሱም) እኛ ከማመስገን ጋር የምናጠራህ ላንተም የምንቀድስ ስንኾን በርሷ ውስጥ የሚያጠፋንና ደሞችንም የሚያፈስን ታደርጋለህን? አሉ፤ (አላህ) እኔ የማታውቁትን ነገር ዐውቃለሁ አላቸው። (ሱራ 2፥30 በቅንፍ ያለውን ይጨምራል)።

የአዳም የማሰብና የማስተዋል ችሎታው መላእክትን ጨምሮ ከሁሉም ፍጥረት የላቀ ነበር። እርሱም እግዚአብሔር እንዳስተማረው የእንስሳት ስምና ሌሎች የፍጥረት ሁኔታዎች በሙሉ በአእምሮው ለማወቅ ችሎ ነበር። እንደ ቁርአን ትምህርት፣ መላእክት እንኳ ይህንን ተግባር ሊፈጽሙት አይችሉም። ሰይጣንም በአዳም የአእምሮ ብቃት ስለቀና፣ እግዚአብሔር መላእክትን በሙሉ ለአዳም እንዲሰግዱ ባዘዛቸው ጊዜ ሰይጣን (ኢብሊስ) አልሰግድም ብሎ ዐመፀ። አዳምን የፈጠርኸው ከሸክላ ነው፤ እኔን ግን የፈጠርኸኝ ከእሳት ነው በማለት ስግደቱን ተቃወመ። በዚህም ምክንያት እግዚአብሔር ሰይጣንን ከገነት አስወጣው።

ነገር ግን ሰይጣን የማታለል ሥራውን ከመሥራት አልቦዘነም። እግዚአብሔር ለአዳም ሚስት እንድትሆን ሔዋንን ከፈጠራት በኋላ፣ እግዚአብሔር በገነት ውስጥ ካሉት ዛፎች ነገር ግን አላህ እንዳይበሉ ከከለከላቸው ዛፍ በሰይጣን አሳሳችነት በሉ። ስለዚህ አላህ አዳምንና ሔዋንን ከገነት አስወጣቸው፤ እነርሱና ዘራቸው ወደሚኖሩባት ምድር አመጣቸው። ለተወሰኑ ዘመናት በምድር ላይ ለፈተና አስቀመጣቸው። ፈተናው ምንድን ነው? ፈተናውም ለአላህ ምሪት መገዛታቸው ወይም አለመገዛታቸው ነው፤ የአላህም ምሪት እስልምና ነው። ከሌሎች እንስሳት ለየት ያለ ኀላፊነት ተሰጥቶአቸው ነበር። እርሱም የምድር ጠባቂዎች (ኻሊፋ) እንዲሆኑ ነው።

ቁርአን አዳምና ሔዋን ከአላህ ዘንድ ለኀጢአታቸው ይቅርታ እንደ ጠየቁ ያስተምራል፦

ጌታችን ሆይ! ነፍሶቻችንን በደልን፤ ለእኛ ባትምር ባታዝንልንም በእርግጥ ከከሳሪዎቹ እንኾናለን አሉ (ሱራ 7፥23)።

እግዚአብሔር ለአዳምና ለሔዋን ምሕረት አድርጎላቸዋል። ይህንን ሐሳብ ቁርአን እንዲህ ያብራራዋል፦



ከርሷም ሰይጣን እንዳለጣቸው፤ በውስጡም ከነበሩበት (ድሎት) አወጣቸው፤ ከፍላችሁም ለከፊሉ ጠላት ሲኾን ውረዱ፤ ለናንተም በምድር ላይ እስከ ጊዜ (ሞታችሁ) ድረስ መርጊያና መጠቀሚያ አላችሁ አልናቸው። አዳምም ከጌታው ቃላትን ተቀበለ፤ በርሱ ላይም (ጌታው ጸጸትን በመቀበል) ተመለሰለት፤ እነሆ እርሱ ጸጸትን ተቀባይ አዛኝ ነውና"። (ሱራ 2፥36-37 በቅንፍ ያለውን ይጨምራል)።

እግዚአብሔር ለአዳምና ሔዋን ያደረገው ምሕረት የተገለጠው እርሱ በሰጣቸው ምሪት ነው፤ ምሪቱም እስልምና ነው። ምሪቱም (እስልምና) እግዚአብሔር ለአዳምና ሔዋን ለሐፍረታቸው መሸፈኛ እንዲሆን የሰጣቸው ልብስ እንደ ሆነ ተገልጿል። ይህንን አስደናቂ ምሕረት ቁርአን እንዲህ ይገልጸዋል፦

የአዳም ልጆች ሆይ! ሐፍረተ ገላችሁን የሚሸሽግን ልብስ ጌጥንም በእርግጥ በናንተ ላይ አወረድን፤ አላህን የመፍራትም ልብስ ይህ የተሻለ ነው፤ ይህ ከአላህ ታምራቶች ነው፤ ይገሠጹ ዘንድ (አወረደላቸው)። (ሱራ 7፥26 በቅንፍ ያለውን ይጨምራል)።

እንደ ቁርአን ትምህርት፣ አዳም እግዚአብሔር የእስልምናን እምነት የገለጠለት የመጀመሪያው ነቢይ ነው። የአዳምና የሔዋን መኖሪያቸው በመካ አካባቢ በሚገኘው አራፋት በተባለው ሜዳ ላይ እንደ ነበረ ሙስሊሞች ያምናሉ። አዳም የመጀመሪያ ነቢይ ሲሆን፣ እርሱና ሔዋን ደግሞ የመጀመሪያዎቹ ሙስሊሞች ናቸው። በአሁኑ ጊዜ ሙስሊሞች በመካ ወደሚገኘው ካዕባ እንደሚሰግዱ አዳምና ሔዋን እንደሙስሊሞች በካዕባ እግዚአብሔርን ያመልኩ ነበር። ካዕባ ተብሎ የሚጠራው በመካ መካከለኛው ስፍራ ላይ የሚገኘው ጥቁር ድንጋይ ነው። እንደ ሙስሊሞቹ እምነት ከሆነ በዚህ ስፍራ አዳም የመጀመሪያውን የአላህ ቤት (የአምልኮ ስፍራ) ገንብቶ ነበር። በዚሁ ስፍራ አብርሃምና ልጁ እስማኤል፣ የእግዚአብሔር ቤት እንደ ገና አንጸው ነበር።

እግዚአብሔር አዳምና ሔዋን እንዲሁም ዘሮቻቸው በምድር ላይ እንዲኖሩ ያደረጋቸው ለኀጢአታቸው መቀጣጫ አይደለም። እነርሱም ሆኑ የሰው ዘር በሙሉ የሚወለደው የውርስ ኀጢአት ኖሮበት አይደለም። አዳምና ሔዋን ሲፈጠሩ በመልካም አብነት (ፍጥራህ) ነው፤ የሰው ልጅም እንደዚሁ ነው። ማንኛውም ሰው የሚወለደው ጥሩ ሙስሊም ሆኖ ነው። ሰዎች ቢያውቁም ባያውቁም፣ እግዚአብሔር የፈጠራቸው ከወሰነው መልካም ነገር አኳያ ነው።

ወደ እውነት ተዘንባይ ሆነህም፣ ፊትህን ለሃይማኖት ቀጥ አድርግ፤ የአላህን ፍጥረት ያችን አላህ ሰዎችን በርስዋ ላይ የፈጠረባትን (ሃይማኖት ያዙዋት)፤

> የአሳሁን ፍጥረት መለወጥ የለም፤ ይህ ቀጥተኛ ሃይማኖት ነው፤ ግን አብዛኞዎቹ ሰዎች አያውቁም (ሱራ 30፥30 በቅንፍ ያለውን ይጨምራል)።

በሙስሊሞች አመለካከት ሕፃናት ሁሉ ጥሩ ሙስሊሞች ሆነው ይወለዳሉ። ነገር ግን ባለማወቅ ወይም በተሳሳተ ትምህርት ምክንያት ከእውነተኛው መንገድ ይወጣሉ። እነዚህ ኃጢአት የሌለባቸው ሕፃናት፣ እንዴት መኖር እንዳለባቸው የሚያሳይ ምሪት ያስፈልጋቸዋል፤ ምሪቱም የእስልምና እምነት ነው። የእስልምና አስተምህሮ (ምሪቱ) አዳምንና ሔዋንን እንዲሁም ሰዎችን በሙሉ ምድርን ኃላፊነት በተሞላበት ሁኔታ እንዲጠብቁአትና እንዲንከባከቧት ረድቶአቸዋል።

ሆኖም እግዚአብሔር ለአዳምና ለሰው ዘር ሁሉ የሰጠውን ይህንን ታላቅ ኃላፊነት ከዳር ማድረስ በሰው ዐቅም የሚቻል አይመስልም። እግዚአብሔር ሰውን የፈጠረው የእርሱ ወኪል (ኸሊፋ) እንዲሆን ነው። እግዚአብሔር ለአዳም የፍጡራንን ስም ሁሉ ያስተማረው፣ በፍጥረት ላይ ሥልጣን እንዲኖረው ነበር።

እግዚአብሔር ለአዳም ይህንን ሥልጣን የሰጠው፣ የፍጡራንን ስም በሙሉ ባስተማረው ጊዜ ነበር፤ እንዲሁም ሥልጣኑ በአዳም ላይ እንዲኖር የተደረገው እግዚአብሔር አዳምን በፈጠረበት ጊዜ ነው። በዚያ ጊዜ እግዚአብሔር በአዳም ላይ መንፈሱን ዕፍ ብሎበታል። ሙስሊም የነገረ መለኮት ምሁራን፣ እግዚአብሔር መንፈሱን በሰው ላይ አደረገ በሚለው ሐሳብ ዙሪያ የተለያየ አመለካከት አላቸው። አንዳንዶች ይህ ስጦታ ሰው በፍጥረት ላይ ሥልጣን እንዲኖረው የሚያደርገው ነው ይላሉ። ወኪል (ኸሊፋ) የሚለው ሐሳብ የእግዚአብሔር መንፈስ በሰው ላይ ሆነ የሚለውን ሐሳብ ለማብራራት ይረዳል። ቀትራጋ የተባለው ሙስሊም ምሁር ይህን መንፈስ ልዩ ስጦታ ነው ይላል:—

(ሀ) እውነትን ከሐሰት፣ እኩይን ከሠናይ፣ እውነታን ከቅዠት ለመለየት የሚረዳ ዕውቀት ነው።

(ለ) መልካሙን ከክፉ፣ እውነትን ከሐሰት፣ ሠናይን ከእኩይ በነጻነት ለመምረጥ የሚያስችል ፈቃድ ነው።

(ሐ) ሰው በዙሪያው ያሉትን ነገሮች የመላመዱና የመጠቀሙ ሥልጣን ነው።

(መ) የመናገር ኀይል ነው። ይህም ፈጣሪውን ለማምለክ መቻሉ ነው[5]።

[5] Kateregga and Shenk, *A Muslim and a Christian in Dialogue*, 42-43.



ከላይ የተመለከትናቸው የቁርአንና የመጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮዎች፣ ሙስሊሞችና ክርስቲያኖች ፍጥረትን በተመለከተ ያላቸውን የተለያየ አመለካከት እንድናውቅ ይረዱናል። በቁርአንና በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶች መኻል የተወሰኑ ምስስሎች ቢኖሩም፣ መሠረታዊ በሆነ ደረጃ ግን አማንያኑን የሚመሩት በተለያየ አቅጣጫ መሆኑን ልብ ማለት አለብን።

## የተለያዩ ጉዳናዎች

ከፓኪስታን ወደ ናይሮቢ የመጣ ሙስሊም ሚስዮናዊ፣ እርሱ እስልምናን የሚሰብከው ክርስቲያኖች ወንጌልን ከሚሰብኩበት መንገድ በተለየ መሆኑን ነገረኝ። ብዙ ጊዜ ከቤታችን ትንሽ ራቅ ብሎ ባለው አስፋልት ላይ እስልምናን ይሰብካል። ከብዙ ጊዜ በኋላ ስለ እስልምና ሃይማኖት ሊነግረን እቤታችን መጣ። በውይይታችንም ወቅት ስለ አዳምና ሔዋን መጽሐፍ ቅዱስ ምን እንደሚያስተምር ነገርሁት። እኔም ከአንድ ሳምንት በኋላ የእርሱን ምላሽ ለመስማት ወደ ቤቱ ሄድሁ። ስለታሪኩ እንዲህ አለኝ፣ "ይህ ታሪክ ትክክለኛ ያልሆነ እጅግ መጥፎ ታሪክ ነው። በጣም ቅር አሰኝቶኛል፤ በእውነት በጣም ነው ያስቀየመኝ"።

ይህንን ፓኪስታናዊ ሙስሊም ሚስዮናዊ ቅር ያሰኘው ጉዳይ፣ በዚህ ጥያቄ ዙሪያ የሚያጠነጥን ነበር:— "ሰው መሆን ማለት ምን ማለት ነው?"። ግለሰቡ ሰው በእግዚአብሔር አምሳል ተፈጥሮአል የሚለውን መጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮ ለመቀበል በእጅጉ ተቸግሮአል። እንዲሁም ሰው የእግዚአብሔርን ፈቃድ ባለመጠበቁ የተነሣ በኃጢአት ወድቆአል፤ አዳኝም ያስፈልገዋል፤ የሚለው አስተምህሮ በእያሌው ረብሾታል። ሰው በኃጢአት ስላልወደቀ ለድነት ወደ ትክክለኛው መንገድ የሚመራው ምሪት እንጂ፣ አዳኝ አያስፈልገውም ሲል ይህ ኢማም[6] አጥብቆ ተከራከረ።

ከተወሰኑ ዓመታት በኋላ፣ በመካከለኛው ለንደን በሚገኝ መስጊድ ውስጥ በነበረን የማታ ውይይት እንዲህ ስል ተናገርሁ :— "መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ሰው ተፈጥሮ የሚያስተምረው ትምህርት ለእውነታ የቀረበ ነው። ኃጢአተኛ መሆናችንን በግልጽ ያስተምራል። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በስም የተጠቀሱት ነቢያት እንኳ እንከን አለባቸው። የእምነት ሰው የነበረው አብርሃም እንኳ፣ ሚስቱን እህቴ ናት በማለት ውሸት በመናገሩ ኃጢአት ሠርቶአል"።

[6] "ኢማም" በመስጊድ ውስጥ ጸሎት ለሚያደርሱ ሰዎች መሪ ነው ወይም ታዋቂ የሆነ የሙስሊሙ ማኅበረሰብ መሪ ነው። በሺአይት ሙስሊሞች ዘንድ ደግሞ የዘር ሐረጉ ከመሐመድ ወገን የሆነ የሃይማኖቱ መሪ ነው።

ይህ ቃል ከአፌ እንደ ወጣ፣ በመስጊዱ ውስጥ የነበሩ አምስት መቶ የሚሆኑ ሙስሊሞች በአንድነት፣ "ይህ በፍጹም አይሆንም!" ሲሉ ልቋቋመው በማልችለው ዐይነት ድምፅ ተቃወሙኝ:: አብሮኝ የነበረው ሙስሊም ጓደኛዬ እንዲህ ሲል መለሰልኝ:— "አብርሃም ነቢይ ስለሆነ ኀጢአት አልሠራም:: የአብርሃም ውሸት ምክንያታዊ ነበር:: ኀጢአት ሊባል አይገባውም:: ነቢያት ሁሉ ጻድቃን ናቸው፤ ኀጢአትም አይሠሩም"::

እነዚህ ውይይቶች ስለ ሰው ማንነት በቁርአንና በመጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮዎች ላይ ልዩነቶች እንዳሉ ያመላክታሉ:: በዚህ ርእስ ዙሪያ በሁለቱ መጻሕፍት ውስጥ ያሉትን አስተምህሮዎች በአጭሩ እንመልከት :—

1. ሙስሊሞችም ሆኑ ክርስቲያኖች ሕያዋንና ግዑዛን፣ የሚታዩና የማይታዩ፣ ምድርና በውስጥዋ ያሉት ነገሮች ሁሉ በእግዚአብሔር እንደ ተፈጠሩ ያምናሉ:: ተፈጥሮንም በቀጣይነት እንዲኖር የሚያደርገው እግዚአብሔር እንደ ሆነ ይስማማሉ:: ተፈጥሮ የእግዚአብሔርን ኀያል ክንድ የሚገልጽ ምልክት ነው::
2. ሙስሊሞችም ሆኑ ክርስቲያኖች፣ አዳምና ሔዋን (ሐዋ) የመጀመሪያዎቹ የሰው ልጆች እንደ ሆኑ ያምናሉ:: የሰው ዘር ሁሉ የመጣው ከእነርሱ ነው:: ስለዚህ ሰው ሁሉ አንድ ነው::
3. ሁለቱም፣ ሰው ከእንስሳት እንዲሁም ከቍሳዊው ዓለም ጋር የሚጋራው ነገር እንዳለና የተፈጠረውም ከዐፈር እንደ ሆነ ያምናሉ::
4. መጽሐፍ ቅዱስ አዳምና ሔዋን በእግዚአብሔር አምሳል እንደ ተፈጠሩ ይገልጻል:: ይህ ፅንሰ ሐሳብ የተለያዩ የትርጒም አቅጣጫዎች ያሉት ነው:: ዋነኛው እውነታ ግን ሰዎች የተፈጠሩት ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት ለማድረግ ነው የሚለው ነው:: እግዚአብሔር እኛ ለእርሱ የቃል ኪዳን ሕዝቦቹ እንድንሆን ይፈልጋል:: ቁርአን ደግሞ አዳም የእግዚአብሔርን መንፈስ እንደ ተቀበለ ይናገራል:: የሙስሊም ነገረ መለኮት አስተማሪዎች በዚህ ጕዳይ ላይ እየተከራከሩ ይገኛሉ:: ነገር ግን ብዙዎቹ የሚያምኑት፣ ሰዎች የእግዚአብሔር ወኪል (ኸሊፋ) እንዲሆኑ ሥልጣን የሚሰጥ መንፈስ ነው ወደሚለው ሐሳብ ነው::
5. መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ትዳር የሚያስተምረው ትምህርት የሚገኘው ስለኤድን ገነት በተጻፈው ታሪክ ውስጥ ነው:: ነገር ግን ብዙም ሳይቆይ ሰዎች ስለ ትዳር ያለውን ሕግ መጠበቅ እንዳልቻሉ መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል:: ይሁንና ስለ ጋብቻ ያለው አስተምህሮ መሠረት የተጣለው በአዳምና ሔዋን የትዳር ግንኙነት ውስጥ ነው:: ከመሠረተ ሐሳቦቹ ውስጥ:— አንድ ሥጋ



መሆናቸው፣ አንድ ወንድ ለአንድ ሴት፣ በእግዚአብሔር የተመሠረተና ሊፈርስ የማይችል ጥምረት እንዳላቸው የሚያሳይ ነው:: ልጆች ስጦታ ናቸው ግዴታ ግን አይደሉም:: ባል ራሱን እንደሚወድ ሚስቱን እንዲወድና እንዲከባከብ የሚለው ሕግ ግልጽ የሆነ ኅብረትና መተማመን እንዲሰፍን የሚያደርግ ነው:: እንዲሁም ያለ ትዳር መኖር ተቀባይነት ያለው ሲሆን፣ የሰዎች ደስታ ፍጹም የሚሆነው ግን ከእግዚአብሔር ጋር ባላቸው ኅብረት እንጂ በጋብቻ አይደለም:: ጋብቻ አስፈላጊ ነገር ቢሆንም ሳያገቡ መኖርም ተፈቅዶአል::

ቁርአን የጋብቻን ትርጒም ከመጀመሪያዎቹ ጣምራዎች (አዳምና ሔዋን) ሕይወት ጋር በማያያዝ ያስተምራል (ሱራ 4+1):: ነገር ግን ቁርአን ስለ ጋብቻና ስለሴቶች ዘርዘር ያለ ሐሳብ ይሰጣል:: ሙስሊም ላልሆነ ሰው፣ ስለ እስልምና አስተምህሮ የሙስሊሞችን አመለካከት በትክክል በሚወክል መልክ ማቅረብ እጅግ አስቸጋሪ ስለሆነ፣ ጋብቻና ሴቶችን በተመለከተ ከእስልምና ምንጮች የተወሰዱ ሐሳቦችን ያለምንም ማብራሪያ ለማቅረብ እሞክራለሁ::

መሐመድ በአንድ ወቅት፣ "ከእናንተ በጣም የተሻለ የሚባለው ሰው ለሚስቱ በጣም ጥሩ የሆነላት ሰው ነው"[7] ብለው ነበር

> ወንዶች በሴቶች ላይ ቋሚዎች (አሳዳሪዎች) ናቸው፤ አላህ ከፊላቸውን በከፊሉ ላይ በማብለጡና (ወንዶች) ከገንዘቦቻቸው (ለሴቶች) በመስጠታቸው ነው:: መልካሞቹም ሴቶች (ለባሎቻቸው) ታዛዦች አላህ ባስጠበቀው ነገር ሩቅን ጠባቂዎች[8] ናቸው:: እነዚያንም ማመጣቸውን የምትፈሩትን ገሥጹዋቸው፤ በመኝታዎችም ተለዩዋቸው (ሳካ ሳታደርሱ) ምቱዋቸውም:: ቢታዘዙዋችሁም (ለመጨቆን) በነርሱ ላይ መንገድን አትፈልጉ፤ አላህ የበላይ ታላቅ ነውና (ሱራ 4+34 በቅንፍ ያለውን ይጨምራል)::

> ሴቶቻችሁ ለናንተ እርሻ ናቸው፤ እርሻችሁንም በፈለጋችሁት ሁኔታ እረሱ፤ ለነፍሶቻችሁም (መልካም ሥራን) አስቀድሙ፤ አላህንም ፍሩ፤ እናንተም

---

[7] Muhammad Hamidullah, *Introduction to Islam* (Paris: Centre Culturel Islamique, 1969), 134.

[8] "ሩቅን ጠባቂዎች" የሚለውን ሐሳብ ቁርአን በግርጌ ማስታወሻው ላይ እንዲህ ተብሎ ተጽፎአል፣ "ባሎቻቸው በሩቁ ጊዜ መብታቸው እንዳይደፈርና ገንዘባቸውን ጠባቂዎች"::

ተገናኝዎቹ መሆናችሁን ዕወቁ፤ ምዕመናንንም (በገነት) አብሥር (ሱራ 2፥223 በቅንፍ ያለውን ይጨምራል)።

ነቢዩ መሐመድ ወደ መካ ለመጓዝ ሲዘጋጁ ለተከታዮቻቸው እንዲህ ብለዋቸው ነበር፦—

> ሴቶችን እንድትንከባከቡ እነግራችኋለሁ፤ ምክንያቱም እነርሱ በቤታችሁ ውስጥ እንዳለ እስረኛ ናቸውና፤ የራሳቸው የሆነ ንብረትም የላቸውምና፤ ለእናንተም ከአላህ ዘንድ የተሰጡ ስጦታዎች ናቸው። እንዲሁም በሴቶቻችሁ ሰውነት እንድትደሰቱ የአላህ ቃል ያዛል። ሴቶችን በተመለከተ አላህን ፍሩ፤ ሴቶችንም እንድትንከባከቡ አዛችኋለሁ። ልብ በሉ ! እኔ ተናገርሁ? አ አላህ ምስክር ነው[9]

ከዐሥር ዓመት በፊት ባልቲሞር በሚባል ስፍራ በሚገኝ መስጊድ በአንድ ምሽት ውስጥ ብዙ ክርስቲያኖችና ሙስሊሞች ለውይይት ተሰብስበው ነበር። የሙስሊሞቹ መሪ (ኢማም) ሴቶችንና ጋብቻን በተመለከተ የሙስሊሞች አመለካከት ምን እንደሚመስል ትምህርት ሰጠ። እኔም በዚህ ጉዳይ ላይ መጽሐፍ ቅዱስ ምን እንደሚያስተምር ተናገርሁ።

የሙስሊሞቹ መሪ (ኢማም) እንዲህ ሲል ተናገረ፦— "እስልምና ነባራዊ ሁኔታዎችን ያገናዘበና ትክክለኛ ነው። እናንተ ክርስቲያኖች የምታስተምሩት ነባራዊ ሁኔታዎችን ያላገናዘበና ተግባራዊ ሊሆን የማይችል ነገር ነው"።

ከእኛ መካከል አንድ ሰው እንዲህ ሲል መለሰ፦— "አንተ የምትለው ነገር ትክክል ሊሆን ይችላል። ነገር ግን የእግዚአብሔር መንፈስ ሰዎችን አዲስ ፍጥረት በማድረግ በመጽሐፍ ቅዱሳዊው ጋብቻ እንዲኖሩ ወይም በብቸኝነት ኑሮ ውስጥ በቅድስና እንዲመላለሱ ኀይልን ይሰጣቸዋል"።

6. መጽሐፍ ቅዱስ ኤድን ገነት በምድር ላይ እንደ ነበረች ያስተምራል። ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱሳዊው ትምህርት በዚያ አያበቃም። በመጽሐፍ ቅዱስ የመጨረሻው ክፍል በጣም ስለተዋበችውና እግዚአብሔር በዘመኑ መጨረሻ ላይ ለቅዱሳን ሁሉ ስላዘጋጀላቸው ስለ ቅድስቲቱ ከተማ ይገልጻል። እግዚአብሔር በኤድን ገነት የጀመረውን ታሪክ፣ የነገሮች ሁሉ ፍጻሜ ወደ

[9] Hamidullah, (cf. Ibn Hisham), 135.



ሆነችው ወደ ታላቂቱና ቅድስቲቱ ከተማ እንዲመጡ ጥሪ በማቅረብ ታሪኩን ይቋጫል።

በቁርአን የአዳምና የሔዋን የመጀመሪያ መኖሪያቸው መንግሥተ ሰማያት ነበር። እግዚአብሔር በፈተናቸው ጊዜ ወደ ምድር ተጥለዋል። ሰው በምድራዊ ኑሮው በሁለት ጉዳናዎች መካከል ይገኛል። እርሱም ከገነት በመባረሩ ምክንያት ዕድሉን ማጣቱ አንዱ ሲሆን፣ በመጨረሻው ዘመን የምትገለጠዋ መንግሥተ ሰማይ፣ ለእግዚአብሔር ታማኝ የሆኑ ሰዎች ብቻ የሚያገኟት ናት የሚለው ደግሞ ሁለተኛው ነው።

7. በመጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር አዳም ለእንስሳት ሁሉ ስም እንዲያወጣ ሥልጣን ሰጥቶታል። በቁርአን ግን እግዚአብሔር ለአዳም የእንስሳትንና የፍጥረትን ሁሉ ስም አስተምሮታል።

በመጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር ለሰዎች አስገራሚ ፈቃድንና ተጠያቂነትን ሰጥቶአል። ይህ በጣም ትልቅ ኀላፊነት ነው። ሰው በእግዚአብሔር ፍጥረት ላይ ጥሩ ያልሆነ ነገር ሠርቶአል። ሰው በጣም ጥሩ የሆኑ በአንጻሩ ደግሞ እጅግ ጥሩ ያልሆኑ ነገሮችን አድርጎአል። ለምሳሌ ናይትሮጅን የተባለውን ንጥረ ነገር በመጠቀም የመሬት ማዳበሪያ እንደ ሠራ ሁሉ፣ ይህንኑ ንጥረ ነገር ለኬሚካል ጦር መሣሪያነት ተጠቅሞበታል።

በቁርአን አስተምህሮ መሠረት ለማንኛውም ሥራ እግዚአብሔር ተጠያቂ ነው። ገና ከጅምሩ ለእንስሳት ስም የማውጣቱ ሥራ ሰው ከእግዚአብሔር የመጣውን ትእዛዝ መቀበሉን እንጂ፣ በራሱ ስም አላወጣም። ሰው የእግዚአብሔር ወኪል ስለሆነ ምድርን የመጠበቅና የመከባከብ ኀላፊነት ከእግዚአብሔር በሚሰጠው ትእዛዝ መሠረት መፈጸም አለበት።

ስለዚህ እነዚህ የተለያዩ አመለካከቶች አንድን ማኅበረሰብ ለምጣኔ ሀብት፣ ለልማትና ለሳይንስ ባለው ምልከታ ላይ ምን ዐይነት ተጽእኖ ይኖራቸዋል? እኔ ሁል ጊዜ ይህ ጥያቄ ያሳስበኛል። ለዚህም ጥያቄ ሁለት ምሳሌዎችን እንመልከት።

ሶማሊያ በነበርንበት ጊዜ አብዲ መሐመድ ከተባለ ወጣት ተማሪ ጋር አንድ ምሽት በቤታችን ሻይ እየጠጣን (አብዲ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪ ነው)፣ አብዲ እንዲህ ሲል ጠየቀኝ፤ "ዓለማዊ ሰው መሆን እፈልጋለሁ፤ ነገር ግን እግዚአብሔርን መካድ አልፈልግም። ክርስትና ለዓለማዊ ሰው የሚሆን እምነት ነውን?"።

እንዲህ ስል ጠየቅሁት:— "ይህ ዐይነቱን ጥያቄ ለምን ጠየቅሽኝ" አብዲ እንደዚህ ሲል መለሰልኝ፣ ""በአገሬ ክርስቲያን የሆኑ ሚስዮናውያን፣ የልማትን ሥራ በመሥራቱ ረገድ ግንባር ቀደም ተጠቃሽ ናቸው:: በቤተ ክርስቲያን የተሠሩ የልማት ሥራዎች፣ የቀለም ትምህርት ቤቶች፣ የሕክምና አገልግሎት መስጫ ተቋማት፣ የመሠረተ ትምህርት አገልግሎት፣ ግብርና፣ የኢኮኖሚ ልማት፣ የንግድ ሥራዎችና የቤት ትምህርት ቤቶች በርካታ ናቸው::..

ከናይሮቢ መስጊድ ፊት ለፊት ባለው ቤቴ ውስጥ በኖርሁባቸው ዘመናት ሁሉ የአብዲን ጥያቄ ሁል ጊዜ አሰላስለው ነበር:: በዚያ ሰፍራ የሚኖሩት ሙስሊሞች፣ ሁል ጊዜ ምሽት ሦስት ሰዓትና ዐሥር ሰዓት ገደማ ላይ ወደ መስጊድ ለጸሎት ሲሄዱ እሰማ ነበር:: እነርሱ ወደ መስጊድ በሚሄዱበት ወቅት እኔ መኝታ ላይ ነኝ:: በዚያን ጊዜ እኛ የተለያየ አገልግሎት እንድትሰጥ በማሰብ ባቋቋምናት ትንሽ የክርስትና ማዕከል ለሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ለጥናት የሚሆኑ ማንበቢያ ክፍሎችን እያደራጀን ነበር:: ለድኻ ልጆችም የትምህርት ቤት ክፍያ እንከፍልላቸዋለን:: የሙስሊሞቹ መሪ (ኢማም) ሴት ልጆች እንኳ ለትምህርት ቤት የሚሆን ክፍያ ገንዘብ የሚወስዱት ከእኛ ነበር:: ነገር ግን ሙስሊሞች ከዐረብ አገሮች የሚገኘውን የገንዘብ ዕርዳታ ለዐረብኛና ለቁርአን ትምህርት ቤቶች ማስፋፊያነት ይጠቀሙበታል:: ክርስቲያኖች በልማት ዘርፍ ሲሠማሩ ሙስሊሞች ግን ሃይማኖታዊ ሥራዎችን ይሠራሉ::

በዚህች ምድር የሚኖር ክርስቲያን እንደ መሆኔ መጠን፣ መጽሐፍ ቅዱሳዊ እምነት የልማት ሥራ እንዲስፋፋ እንዴት እንዳደረገ የሚገልጹ ሁለት መጻሕፍት አንብቤ ነበር[10]:: የእነዚህ መጻሕፍት ጸሓፍያን፣ ሰዎች መጽሐፍ ቅዱሳዊውን እምነት አንግበው በማኅበረሰቡ ባህል ውስጥ በመገኘት፣ የሰዎችን አመለካከት በመለወጥ ለልማት ሥራዎች እንዲነሣሡ ታላቅ ዕገዛ አድርገዋል ሲሉ ጽፈዋል:: የጸሓፍቱ አባባል ትክክል ነውን? ለዚህ ጥያቄ የአብዲ አባባል በጣም ጥልቅ መልእክት አለው:: ስለ ሰው ተጠያቂነት፣ ነጻነትና ስለ ታሪክ አስፈላጊነት ያለን መረዳት በልማት ሥራዎች እንድንሳተፍ ምን ያህል ተጽእኖ አድርጉብን ይሆን?

[10] እነዚህ ሁለት መጻሕፍት የሚከተሉት ናቸው Lesslie Newbigin, *Honest Religion for Secular Man* (London: SCM 1966) and Arend Theodoor van Leewen, *Christianity in World History*, translated by H. H. Hoskins (New York: Charles H. Scribner, 1964), 324-33.



8. መጽሐፍ ቅዱስ አዳምና ሔዋን ከእግዚአብሔር ፊታድ መውጣታቸው እንዲሁም ከኀጢአት የተነሣ ሰው ከእግዚአብሔር ጋር፣ ሰው ከሰው ጋር፣ ሰው ከሥራ ጋር እንዲሁም ሰው ከፍጥረት ጋር የነበረውን ኅብረት ምን ያህል እንዳበላሸው ያስተምራል:: በሰዎች ሕይወት ውስጥ ዘወትር እንደሚታየው አዳምና ሔዋን እግዚአብሔርን የሕይወታቸው መሠረት አላደረጉም:: በሰው ሁሉ ውስጥ ያለው፣ በእግዚአብሔር አምሳል የተፈጠርንበት ምልክት በሚያሳዝን ሁኔታ ተበላሽቶአል::

ቁርአን፣ የአዳምና የሔዋን አለመታዘዝ በእግዚአብሔር ይቅርታ ያገኘ ስሕተት ነው የሚል አቋም አለው:: በአዳምና በሔዋን የተገለጠው ሰብአዊነት፣ ኀጢአት ባስከተለው ጥፋት እንዳችም ችግር አልደረሰበትም፤ ሰው ሁሉ ሲወለድ ኀጢአት የሌለበት ንጹሕ ፍጡር ነው::

9. መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚያስተምረው እግዚአብሔር ወደ ኤድን ገነት በመምጣት አዳምና ሔዋን ተደብቀው ባሉበት አገኛቸው:: ከዚያም ከገነት አስወጣቸው:: ነገር ግን የቁዳ ልብስን አለበሳቸው:: ወደ ፊት ከሴቲቱ የሚወለደው ልጅ የእባቡን ሰኩና ይቀጠቅጣል፤ ነገር ግን ልጁ የክፉን ራስ በመቀጥቀጥ ድልን እንደሚነሣ እግዚአብሔር ተስፋ ሰጥቶአቸዋል::

ቁርአን ደግሞ እግዚአብሔር አዳምን የመጀመሪያ ነቢይ በማድረግ ለሕይወቱ መመሪያ የሚሆን መልእክት ሰጥቶታል ይላል:: ከአንድ ሙስሊም የነገረ መለኮት ምሁር ጋር የኅብረት ውይይት ካደረግን በኋላ እንዲህ አለኝ:— "እግዚአብሔር አዳምና ሔዋንን ለመፈለግ ወደ ኤድን ገነት መጣ የሚለው አመለካከት ያበሳጨናል"::

እኔም እንዲህ ስል መለስሁለት:— "ይህ ጉዳይ ሊያበሳጭ እንደሚችል እገምታለሁ:: ይሁንጂ ይህ የወንጌል ታላቅ ምሥራች ነው:: እግዚአብሔር ፈቃዱን ብቻ ከሰማይ አልላከልንም:: ይልቁንም በሰዎች ታሪክ ውስጥ እውናዊ ተሳትፎ በማድረግና ታሪካችንን በመጋራት ከገባንበት አረንቋ አወጣን:: እኛ ከእግዚአብሔር ብንደበቅም እርሱ ግን ያለንበት ድረስ በመምጣት ታሪካችንን ታሪኩ በማድረግ ፈለገን:: እግዚአብሔር በሉዓላዊነቱ ፈለገን፤ በመሲሑ ሥቃይ፣ መሲሑ ባፈሰሰው ደምና በቈረሰው ሥጋ በኩል አጻነን"[11]:: በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉ ታሪኮች ለሰዎች አለኝታና ተስፋ የሚሰጡት በዚህ መልክ ነው::

[11] Miroslav Volf, *Exclusion and Embrace* (Nashville: Abingdon, 1996), 35-166.

## የውይይት ጥያቄዎች

1. ቁርአን እኛ በምድር ላይ የእግዚአብሔር ወኪሎች እንደ ሆንን ሲያስተምር፣ መጽሐፍ ቅዱስ ደግሞ በእግዚአብሔር አምሳል እንደ ተፈጠርን ያስተምራል (ሱራ 2+30፤ ዘፍጥረት 1+27)። በእነዚህ አመለካከቶች ላይ ያልዎትን መረዳት ይግለጹ።
2. "ለእንስሳት ስም ማውጣት" የሚለው ሐሳብ ላይ ከቁርአንና ከመጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮ አኳያ የእርስዎን አስተያየት ይስጡ (ሱራ 2+30-32፤ ዘፍጥረት 2+19-20)። እነዚህ የተለያዩ መረዳቶች ምን ዐይነት ትርጒም ያዘሉ ይመስልዎታል?
3. "መጽሐፍ ቅዱሳዊ እምነት ለዓለማዊ ሰው ትክክለኛ እምነት ነውን?" ለሚለው ለአብዲ ጥያቄ የእርስዎ መልስ ምንድን ነው?
4. ስለ ኀጢአት እንዲሁም ኀጢአት ስላስከተለው ጥፋት መጽሐፍ ቅዱሳዊና ቁርአናዊ አስተምህሮዎችን ያነጻጽሩ (ሱራ 2+36-37፤ 7+14-23፤ ዘፍጥረት 3+1-4:9)።
5. በአሁኑ ጊዜ እስልምና ስለ ሰው ተፈጥሮና ኀጢአት ያለው አስተምህሮ ክርስትና ስለ ሰው ውድቀት ካለው አስተምህሮ ይልቅ በሰዎች ዘንድ ተቀባይነት አለው ወይ? ለመልስዎ ማስረጃዎችን ይስጡ። ከሰው ልጆች የዕለት ተዕለት ኑሮ አንጻር የትኛው አመለካከት ለእውነታው የቀረበ ይመስልዎታል?
6. እግዚአብሔር መመሪያን ላከልን በሚለውና እግዚአብሔር አዳነን በሚሉት አስተምህሮዎች መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው (ሱራ 2+37-38፤ ዘፍጥረት 3+15)?
7. "ታማኝ የሙስሊም ኡማ የጥንቱን አዳም ያመለክታል፤ ታማኝ ቤተ ክርስቲያን ደግሞ የአሁኑንና የወደፊቱን ክርስቶስ ታመለክታለች" (ሱራ 30+30፤ ዘፍጥረት 3+15፤ ዮሐንስ 3+16፤ ራእይ 1+7፤ 22+20) ስለሚለው ሐሳብ የእርስዎን አስተያየት ይስጡ።
8. ቁርአን በሱራ 4+34 እንዲሁም 2+223፣ ስለ ሴትና ስለ ትዳር ለእውነት የቀረበ ትምህርት ያስተምራል። ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ በዘፍጥረት 1+27 እና 2+20-25 ላይ ስለ ሴትና ትዳር የሚያስተምረው ትምህርት ተፈጥሮን የሚቃረንና እውነታን ያገናዘበ አይደለም፣ ለሚሉ አመለካከቶች የእርስዎን አስተያየት ይስጡ።



ምዕራፍ አራት

# የአብርሃም ልጆች
## እስማኤል—ይስሐቅ

በአሜሪካን አገር ፔንሲልቬኒያ በሚባለው ክፍለ አገር ዴቨን በሚባል ቦታ በሚገኝ አንድ መስጊድ ውስጥ፣ ሰባ አምስት የምንሆን ክርስቲያኖችና ሙስሊሞች የማታ የውይይት ጊዜ ነበረን። በውይይቱ ጊዜ የሙስሊሞቹ ኢማም (መሪ)፣ "እስልምና ለማንኛውም ሰው የሚሆን ሃይማኖት ነው። ያልተዛባ ሥነ አመክንዮም ሆነ ፍልስፍና ሰዎችን ወደ እስልምና ሃይማኖት ይመራቸዋል" ሲል ቈፍጠን ብሎ ተናገረ።

እኔም ለሙስሊሞቹ መሪ እንዲህ ስል መለስሁለት፣ "በዚህ ጒዳይ ወንጌል ከእስልምና ይለያል። የሰው ፍልስፍናም ሆነ ሰብአዊ የሆነ ሃይማኖት የወንጌልን የምሥራች በእውኑ ይቅርና በህልሙ እንኳ ሊያስበው አይችልም። ወንጌል ማለት እግዚአብሔር በመሲሑ አማካይነት በሰዎች መካከል እንዴት እንደ ገባና ፍቅሩን እንዴት እንደ ገለጠ የሚያስረዳ ታላቅ የምሥራች ነው። እግዚአብሔር በመሲሑ በኩል በእኛ ምክንያት እንዲሁም ለእኛ ሲል ተሠቃየ። ከመሲሑ አገልግሎት የምንረዳው፣ እግዚአብሔር ኀጢአተኞችን እንደሚወድና ኀጢአተኞችንም ለማዳን እንደሚፈልግ ነው። ይህን እውነት ፍልስፍና ውስጥ ማግኘት አይቻልም። እግዚአብሔር ለሰዎች ኀጢአት ሲል በመሲሑ በኩል የገለጠውን ጸጋ ወይም የእግዚአበሔርን ምሕረት ማወቅና መቀበል የምንችለው በእምነት አማካይነት ብቻ ነው"። ለእኔ ምላሽ፣ የሙስሊሞቹ መሪ ፊቱን ቅጭም አድርጎ እንዲህ ሲል በአጽንኦት ተናገረ፣ "በመሠረቱ እግዚአብሔር ይህን ያህል ሰዎችን ሊወድ አይችልም"።

### የእምነት ጒዞ

ፔንሲልቬኒያ በነበረን የውይይት ጊዜ የሙስሊሞቹ መሪ፣ "እስልምና ተፈጥሮአዊና ለሰዎች ልምምድ የቀረበ ነው"። በማለት የተናገረው ነገር የተጋነነ ይመስላል። አብዛኛው ሙስሊም የቁርአን መገለጥ ተአምራዊ ነው የሚል እምነት አለውና። ይሁንና በዴቨን መስጊድ ውስጥ በነበረን ውይይት ወቅት እንነጋገርበት የነበረው ርእሰ ጒዳይ፣ "ለማንኛውም ሰው የሚገባ

(ሰብአዊ/ተፈጥሮአዊ) ሃይማኖት ወይስ ሰዎችን በሚያስደንቅ ጸጋ የሚነካ እምነት?" የሚለውን ትኩረት ያደረገ ነበር:: ከአራት ሺህ ዓመት በፊት በአብርሃም ቤት ውስጥ የነበረው ግራ መጋባት፣ ከዚህ ርእስ ጉዳይ ጋር ተመሳሳይነት አለው:: በአብርሃም ሕይወትና ቤት ውስጥ ይስተዋል የነበረው ግራ መጋባት፣ በአሁኑ ዘመን ባለው የሙስሊም ማኅበረሰብ (ኡማ) እንዲሁም በተወሰነ ደረጃ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ይስተዋላል:: በአብርሃም ሕይወት ጥያቄ እንደ ነበረ ሁሉ እኛም፣ "ቀላልና ተፈጥሮአዊ በሆነ ሁኔታ መኖር ወይስ እግዚአብሔር ለሰዎች የማይገባቸውን ምሕረት በገለጠበት ጸጋ ውስጥ መመላለስ?" በሚሉት ሁለት አማራጮች መካከል እንዋዥቃለን::

አብርሃም እግዚአብሔር የሰጠኝ ተስፋ የሚፈጸመው እንዴት ነው? የሚለውን ጉዳይ ዘወትር ያወጣና ያወርድ ነበር:: እግዚአብሔር ለአብርሃም ልጅ እንደሚሰጠው ቃል የገባለት ቢሆንም እንኳ፣ ሚስቱ ሣራ መካን ነበረች:: አብርሃም ልጅ ለመውለድ ከባሪያዪቱ ከአጋር ጋር መተኛት ነበረበት ወይስ ተስፋ አስቈራጭ ቢመስልም እንኳ፣ ሣራ ልጅ ትወልዳለች ብሎ እግዚአብሔርን መታመን? አብርሃም መኖር ያለበት እንደ ማንኛውም ሰው ተፈጥሮአዊ የሆነውን ኑሮ ወይስ እግዚአብሔር የሰጠኝን ተስፋ ይፈጽምልኛል በሚለው ልዕለ ተፈጥሮአዊ (መለኮታዊ) እምነት? ሣራ በሴቶች የሚታየው ወግ ከእርስዋ ከቀረ በኋላ፣ ልጅ እወልዳለሁ የሚለውን ጉዳይ እርሷም ሆነች አብርሃም በእያሌው ተጠራጥረውታል:: ስለዚህ አብርሃምና ሣራ ሰብአዊ በሆነ አካሄድ ልጅ ለማግኘት ፈለጉ:: አብርሃም ከአገልጋዩ ከአጋር ጋር በመተኛቱም እስማኤል ተወለደ (ዘፍጥረት 16)::

እስማኤል ከተወለደ በኋላ፣ እግዚአብሔር ወደ አብርሃም በመምጣት በዘፍጥረት 17፥15-16 እንዲህ ሲል ኪዳኑን አደሰ:— "እግዚአብሔርም አብርሃምን አለው:— የሚስትህን የሦራን ስም ሦራ ብለህ አትጥራ፤ ስምዋ ሣራ ይሆናል እንጂ:: እባርካታለሁ፤ ደግሞም ከእርስዋ ልጅ እሰጥሃለሁ፤ እባርካትማለሁ፤ የአሕዛብ እናት ትሆናለች፤ የአሕዛብ ነገሥታት ከእርስዋ ይወጣሉ"::

አብርሃም፣ እግዚአብሔር የሰጠው ተስፋ አይፈጸምም ብሎ ስላሰበ ከእግዚአብሔር ጋር ለመከራከር ፈለገ:: አብርሃምም ለእግዚአብሔር:— "እስማኤል በፊትህ ቢኖር በወደድሁ ነበር አለው" (ዘፍጥረት 17፥18):: በሣራ ልጅ የመውለድ ጉዳይ ፈጽሞ ተስፋ ቈርጦአልና::



እግዚአብሔር ለአብርሃም እንዲህ ሲል መለሰለት:—

> በእውነት ሚስትህ ሣራ ወንድ ልጅን ትወልድልሃለች፤ ስሙንም ይስሐቅ ብለህ ትጠራዋለህ፤ ከእርሱ በኋላ ለዘሩ የዘላለም ቃል ኪዳን እንዲሆን ቃል ኪዳኔን ከእርሱ ጋር አቆማለሁ:: ስለ እስማኤልም ሰምቼሃለሁ፤ እነሆ ባርኬዋለሁ፤ ፍሬያማም አደርገዋለሁ፤ እጅግም አበዛዋለሁ፤ ዐሥራ ሁለት አለቆችንም ይወልዳል፤ ታላቅ ሕዝብም እንዲሆን አደርገዋለሁ (ዘፍጥረት 17፥19-20)::

የእግዚአብሔር መልአክ የዘጠና ዓመት ዕድሜ ያላት ሣራና የመቶ ዓመት ዕድሜ ያለውን አብርሃምን ልጅ ትወልዳላችሁ ሲላቸው፣ ቀልድ መስሏቸው ነበር:: እየተነጋገሩ ሳለም ሣራ በድንኳን ውስጥ ሆና ስትሥቅ የእግዚአብሔር መልአክ ሰማት:: አብርሃምም በሣቅ ተሞልቶ ነበር::

የአብርሃም ሁለተኛ ልጅ የይስሐቅ መወለድ ለሰዎች ሁሉ አስደናቂ ክሥተት ነበር:: ነገር ግን በእስማኤል መወለድ ማንም ሰው አልተደነቀም፤ ተፈጥሮአዊ ሕግን የተከተለ ነውና::

በእርግጥ ከስሙ መረዳት እንደሚቻለው ይስሐቅ ማለት "ሣቅ" ማለት ነው:: የይስሐቅ መወለድ ብዙ ደስታንና መገረምን አምጥቶአል:: ሣራ የዘጠና ዓመት ሴት ሆና ይስሐቅን መውለድዋ፣ በየትኛውም ዘመን የሚኖሩ ሰዎችን ይህ ጉዳይ እንደሚያሥቃቸው ተናግራ ነበር:: ልጅዋ ይስሐቅ በእርግጥም የኪዳኑ ልጅ እንዲሁም የእግዚአብሔር አስደናቂ ስጦታ ነው::

ዳሩ ግን እስማኤልም በእምነት የተወለደ ልጅ ነው:: እስማኤል የሚለው ስም ትርጒሙ፣ "እግዚአብሔር ይሰማል" ማለት ነው:: እግዚአብሔር ለአብርሃም ዘር እንደሚኖረው ተስፋ ሰጥቶት ነበርና::

አብርሃምና ሣራ እግዚአብሔር ተስፋውን ለመፈጸም እንዳይከብደው እርሱን ለማርዳት/ለማገዝ ወሰኑ:: ከዚህም ውሳኔ የተነሣ አብርሃም ከአጋር ጋር ተኛ:: አብርሃምና ሣራ እምነታቸውን ሥነ አመክንዮአዊ እንዲሁም ሰውኛ በሆነ አስተሳሰብ ገለጹት::

## ወደ ጽድቅ የሚደረግ ጕዞ

የመጽሐፍ ቅዱሳዊ ታሪኮች እውነትነት የሚያስደንቅ ነው:: አብርሃም የአማኞች ሁሉ አባት ነው:: አንዳንዴ ግን አብርሃም የሚሠራውን ሥራ ለማመን መቸገሩንና ግራ መጋባቱን የሚያሳዩ ናቸው:: አብርሃም፣ ሣራን

ይፈልግ የነበረው ንጉሥ እንዳይገድለው በመፍራት ሚስቱን ሁለት ጊዜ እህቴ ናት በማለት ዋሽቶአል። ይህ ዐይነቱ ድርጊት፣ ለአብርሃም ሙሉ ጥንቃቄ ለማድረግ ሙሉ ችሎታ ያለውን አምላክ መታመኑን ያመለክታልን?

በአብርሃም ቤተሰብ ውስጥ የነበረው ቤተሰባዊ ሥርዐት እየተበላሸ መጣ። እስማኤል ከተወለደ በኋላ ሣራ አገልጋይዋ የሆነችውን አጋር ምርር ብሏት ከቤት እስክትጠፋ ድረስ በነገር ትነዘንዛት ነበር። ይስሐቅ ከተወለደ በኋላ ግን ሣራ፣ ሠራተኛዪቱ አጋርንና ልጅዋን እስማኤልን፣ አብርሃም ከቤት እንዲያባርራቸው ግፊት ታደርግ ነበር። ይህን ያደረገችበት ዐቢይ ምክንያት፣ የሠራተኛዪቱ ልጅ እስማኤል ከልጇ ይስሐቅ ጋር በሰላም አብረው መኖር አይችሉም በሚል አስተሳሰብ ነው (ዘፍጥረት 16፤ 21+8-14)።

የአብርሃም የወንድም ልጅ የነበረው ሎጥ፣ ወይን ጠጅ ጠጥቶ በስካር ራሱን በሳተ ጊዜ፣ ከሁለት ሴት ልጆቹ ጋር የዝሙት ኀጢአት ፈጸመ። ከዚያ በኋላ ርብቃ ይስሐቅን በማታለል፣ በሁለቱ ልጆቻቸው በያዕቆብና በኤሳው መካከል የመረረ ጠብ እንዲፈጠር አደረገች።

## እምነትን መሠረት ያደረገ ጽድቅ

ይሁን እንጂ የእግዚአብሔር ጸጋ ምሕረትና ታማኝነት ሕይወታቸው ከኀጢአት ባልጸዳ በእነዚህ ሰዎች ላይ ሰፈነ። ምንም እንኳ አብርሃምና ሣራ እግዚአብሔር ለሣራ በስተ እርጅናዋ ልጅ እንደሚሰጣት የተናገራትን አስደናቂ ኪዳን ለማመን ቢቸገሩም፣ ሣራ የዘጠና ዓመት ሴት ሆና ሳለ እግዚአብሔር ይስሐቅን በመስጠት ባርኮአቸዋል።

አብርሃም በእግዚአብሔር ላይ ያለውን እምነት ሰብአዊ በሆነ አካሄድ ቢገልጽም፣ እግዚአብሔር ግን በጸጋው ባርኮቱን አበዛለት። የአብርሃም ሕይወትና የቤተሰቡ ሥርዐት ከስሕተት የጸዳ ባይሆንም፣ እግዚአብሔር ለአብርሃም እምነት ዕውቅና ሰጥቶአል። መጽሐፍ ቅዱስ በዘፍጥረት 15+6 ላይ፣ "አብርሃምም በእግዚአብሔር አመነ፤ ጽድቅም ሆኖ ተቈጠረለት" ይላል።

አብርሃም እግዚአብሔርን መታመን ቀላል ጒዳይ ሆኖ ባያገኘውም ታማኝ ሆኖ ለመገኘት ሲዳክርና ሲውተረተር እናገኘዋለን። አንዳንዴም በሁለት ሐሳብ ያነክስ ነበር። ነገር ግን የእግዚአብሔርን ጥሪ በመከተልና የእግዚአብሔርን የተስፋ ቃል በማመን ሕይወቱን በትጋት ኖሮአል። አብርሃም ላሳየው የእምነት ትጋት፣ በእግዚአብሔር አምላክ "ጻድቅ ሰው" ተብሎ ተጠራ። ማናችንም



ብንሆን ለእግዚአብሔር ጸጋ የተገባን ሰዎች አይደለንም። ነገር ግን ለእግዚአብሔር በእምነት ምላሽ ስንሰጥ እግዚአብሔር የጽድቅንና የድነትን ልብስ ያጐናጽፈናል (ኢሳይያስ 61+10)።

ከሁለት ሺህ ዓመታት በኋላ፣ "ጽድቅ በእምነት ይገኛል" የሚለው ሐሳብ ግልጽ በሆነ ሁኔታ ለሰዎች ተገለጠ። ይህም የተገለጠው በመሲሑ አገልግሎት ውስጥ ነው። በመሲሑ አገልግሎት ውስጥ በእርግጥም እግዚአብሔር ኀጢአተኞችን እንደሚወድ መገንዘብ ችለናል።

መጽሐፍ ቅዱስ፣ "ልዩነት የለምና፤ ሁሉ ኀጢአትን ሠርተዋልና የእግዚአብሔርም ክብር ጐድሎአቸዋል" ይላል (ሮሜ 3+23)። እንዲሁም በሮሜ 5+8 ላይ፣ "ነገር ግን ገና ኀጢአተኞች ሳለን ክርስቶስ ስለ እኛ ሞቶአል፤ እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን የራሱን ፍቅር ያስረዳል" ይላል።

ይህንን የእግዚአብሔርን የጸጋ ስጦታ ሐዋርያው ጳውሎስ በዚህ መልክ ይገልጸዋል:—"ጻድቅ በእምነት ይኖራል" ሮሜ 1+17። በወንጌል እንደ ተጻፈው የእግዚአብሔር ጽድቅ ተገልጦአል። ይህም ጽድቅ ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ በእምነት የሚሆን ጽድቅ ነው። እንዲሁም ሐዋርያው ጳውሎስ በኤፌሶን 2+8-9 ላይ፣ "ጸጋው በእምነት አድኖአችኋልና፤ ይህም የእግዚአብሔር ስጦታ ነው እንጂ ከእናንተ አይደለም፤ ማንም እንዳይመካ ከሥራ አይደለም" ይላል።

የወንጌል አንኳር መልእክት፣ ድነት በጸጋ አማካይነት በእምነት ይገኛል የሚለው ትምህርት ነው። የወንጌል ዘር የተዘራው፣ "አብርሃም አመነ ጽድቅም ሆኖ ተቈጠረለት" በሚለው ታሪክ ውስጥ ነው። አብርሃም ጻድቅ የተባለው የሠራው ሥራ ሁሉ ትክክል ሆኖ ስለተገኘ አይደለም። የጽድቁ ፍሬ የተፈጸመውና ግልጽ ሆኖ የታየው፣ በመሲሑ አገልግሎትና ተልእኮ ውስጥ ነው።

እስልምና የእግዚአብሔር ርኅራኄና ምሕረት ለጻድቅ ሰዎች ብቻ እንደሚገለጥ ያስተምራል። ቁርአን በሱራ 19+96 እንዲህ ይላል:— "እነዚያ ያመኑና በጎ ሥራዎችን የሠሩ አልራሕማን ለእነሱ ውዴታን ይሰጣቸዋል"።

አንድ ቀን በአንድ ዩኒቨርሲቲ በተካሄደ ረዘም ያለ የአደባባይ ውይይት ሙስሊም ጓደኛዬ ስለ አብርሃም እንዲህ ሲል ተናገረ:— "አብርሃም በፊቱ ተደፍቶ ለእግዚአብሔር ሰገደ። በፊት ተደፍቶ ለእግዚአብሔር መስገድ

ትክክለኛው የስግደት ዐይነት ነው:: ስለዚህ የእግዚአብሔርን ምሕረት ለመቀበል እንደ አብርሃም በፊታችሁ ተደፍታችሁ እንድትሰግዱ ጥሪ አቀርብላችኋለሁ”::

እግዚአብሔር ለአብርሃም ጸጋን የሰጠው ለምንድን ነው? አብርሃም ሃይማኖታዊ ጸሎትንና ስግደትን በሥርዐትና በታማኝነት በመፈጸሙ ነውን? ወይስ የእግዚአብሔር ጸጋ ያገኘው የእግዚአብሔርን የተስፋ ቃል በማመኑ ነው?

በዚህ ምዕራፍ የእግዚአብሔርን ምሕረትና ጸጋ በስፋት ለመመልከት እንሞክራለን:: የእስማኤልና የይስሐቅ ታሪክ የእግዚአብሔርን ጸጋና ምሕረት በጥልቀት እንድንመለከት ይረዳናል::

## አብርሃምና እስማኤል

እግዚአብሔር ልጁን መሥዋዕት እንዲያደርግ አብርሃምን ያዘዘው ትእዛዝ፣ ለአብርሃም ፈታኝ ነበር:: ቁርአን አብርሃም ልጁን መሥዋዕት አድርጎ ለማቅረብ አዘጋጅቶ እንደ ነበር ይነግረናል:: አብርሃምና ልጁ ለአላህ ፈቃድ በመታዘዝ መሥዋዕቱ ወደሚካሄድበት ስፍራ ሄዱ (ሱራ 37+99-113):: ነገር ግን በሚያስደንቅ ሁኔታ እግዚአብሔር ጣልቃ ገብቶ በልጁ ፈንታ የመሥዋዕቱን በግ አዘጋጀ:: ቁርአን በሱራ 37+107 እንዲህ ይላል:— “በታላቅ ዕርድም (መሥዋዕት) ተቤዠነው”::

መጽሐፍ ቅዱስ አብርሃም ልጁ ይስሐቅን መሥዋዕት ለማድረግ ተዘጋጅቶ እንደ ነበር፣ ነገር ግን እግዚአብሔር በኪነ ጥበቡ የመሥዋዕቱን በግ እንዳዘጋጀ ያስተምራል (ዘፍ 22):: ቁርአን ለመሥዋዕት የቀረበው ልጅ ማን እንደ ሆነ አይናገርም:: ነገር ግን ሙስሊም ምሁራን ለመሥዋዕት የቀረበው ልጅ እስማኤል ነው ይላሉ[1]::

በየዓመቱ በሚደረገው የሐጅ ጉዞ ወቅት፣ ከዓለም ዙሪያ የሚመጡት ሙስሊሞች፣ እግዚአብሔር ጣልቃ በመግባት እስማኤልን ከሞት ያዳነበትን ዕለት ለመዘከር፣ እንስሳትን በማረድ እንዲሁም ያረዱትን እንስሳ በመብላት ቀኑን ያከብራሉ:: ለሐጅ ጉዞ ወደ መካ የተጓዙ ምዕመናን ደግሞ ሚንስ

[1] Abdullah Yusuf Ali, *The Holy Qur'an: Text, Translation, and Commentary* (Beirut: Dar Al Arabia, 1958), Commentary and Notes, no. 4101, p. 1205.



በተሰኘው ኩረብታ አጠገብ መሥዋዕት ያቀርባሉ:: መሥዋዕት የማቅረቡ ሥርዐት የሚፈጸመው አብርሃም እስማኤልን ለመሠዋት በቀረበ ጊዜ እግዚአብሔር የመሥዋዕቱን በግ ማዘጋጀቱን ለማስታወስ ነው::

## መሐመድና እስማኤል

የአብርሃምና የእስማኤል ታሪክ ሙስሊሞች ለራሳቸው ባላቸው ግንዛቤ ላይ ጉልሕ የሆነ አሻራ አሳርፎአል:: በመሐመድ ዘመን ከመሐመድ ዘመዶች ውስጥ የሐኒፍ እምነት ተከታዮች ነበሩ:: የሐኒፍ እምነት ተከታዮች በዐረብያ ውስጥ የሚኖሩ ሲሆን፣ አንድ አምላክ ብቻ የሚያመልኩ ነበሩ:: ከእነርሱ ውስጥ አንዳንዶቹ፣ እምነታቸው ከአብርሃም ዘመን ጀምሮ እንደ ነበር ያምናሉ:: እነርሱ የሚያመልኩት አላህ የተሰኘው ፈጣሪ አምላክ ሲሆን፣ ኋላም ሙስሊሞች ይህን ስም ለፈጣሪ አምላክ መጠቀም ጀምረዋል:: የሐኒፎች አምላክና የሙስሊሞች አምላክ አንድ እንደ ሆነ ሙስሊሞች ያምናሉ:: አላህ የሚለው ስም በዐረብኛ እግዚአብሔር ማለት ሲሆን፣ አብርሃም የጠራው እግዚአብሔር “ኤል” ወይም “ኤሉሂም” ከሚለው ስም ጋር ተመሳሳይ ነው:: እግዚአብሔር ለአብርሃም ከመገለጡ በፊት ኤሉሂም በተራራ ላይ ሰፍሮ የሚኖር አምላክ እንደ ሆነ ይቈጠር ነበር:: ከመሐመድ ዘመን በፊት ለዐረቦች አላህ ማለት ፈጣሪ አምላክ ማለት ነው:: በእርግጥ በዐረብያ ከፈጣሪ አምላክ (አላህ) ባሻገር ሌሎችም አማልክት ይመለኩ ነበር:: ባህላዊ እምነት ከሚያምኑ ዐረቦች ውስጥ አላህ ሦስት ሴት ልጆች አሉት ብለው ያምኑ ነበር:: እነርሱም አል-ላት፣ አል-ኡዛ እና አል-መናት (ዕጣ ፈንታ፣ ጨረቃ እና ቬነስ) ይባላሉ:: አይሁዶችና ክርስቲያኖች እንዲህ ዐይነቱን የጣዖት አምልኮ እንደሚቃወሙ ሁሉ፣ መሐመድም በዐረብያ የነበረውን የጣዖት አምልኮ ተቃውሞአል:: መሐመድ አላህ ሴት ልጆች ቀርቶ እርሱን የሚመስለው የለም ሲሉ ሰብከዋል:: እስልምና የጣዖት አምልኮን በማስቀረት፣ አላህ ብቻውን ፈጣሪ አምላክ ነው የሚል እምነት እንዲመሠረት አድርጎአል::

በሙስሊሞቹ አላህና በአብርሃም አምላክ (ኤሉሂም) መካከል መመሳሰሎች አሉ:: ሙስሊሞች የአብርሃም አምላክ የመሐመድም አምላክ እንደ ሆነ ሙሉ እምነት አላቸው:: አላህ የአብርሃም አምላክ ነው ይላሉ:: ከመሐመድና ከሙስሊም ኡማ ምሥረታ በፊት ሐኒፎች ለብዙ ዓመት አላህን የማምለክ ሥርዐት በዐረብያ እንዲቆይ አድርገዋል:: ሐኒፎች አንድ ፈጣሪን ብቻ የሚያመልኩና የዐረቦችን የጣዖት አምልኮ ለዘመናት የተቃወሙ ናቸው::

ለመሐመድ በተለይ በመዲና ቆይታቸው ከአብርሃምና ከእስማኤል አምላክ ጋር መገናኘት ወሳኝ ቢሆንም ከአይሁድ ማኅበረሰብ ግን የከፋ ተቃውሞ ደርሶባቸዋል[2]:: አይሁዶች ለመሐመድ፣ "ነቢያት በሙሉ አይሁዶችና የአብርሃም ልጆች ናቸው:: ዐረብ ነቢይ መሆን አይችልም" ሲሉ ተቃወሙአቸው::

ከዚህም የተነሣ ሙስሊሞች በአይሁዶች ላይ ያላቸው ጥላቻ እየከረረ ሄደ:: ሙስሊሞቹ "መሐመድ ሐኒፍ ነው፤ የሐኒፎች መነሻ አብርሃምና እስማኤል ናቸው" ሲሉ የአይሁዶችን ተቃውሞ መከላከል ጀመሩ::

## የመሐመድ የዘር ሐረግ

በእርግጥ ሙስሊሞች እንደሚሉት የመሐመድ የዘር ሐረግ እስከ እስማኤል ይደርሳል:: መሐመድ የሐኒፍ እምነት ተከታይ ብቻ ሳይሆኑ፣ ቤተሰባቸው የእስማኤል ዘር የሆነው የቁረይሽ ጐሣ አባል ናቸው:: የአብርሃምና የእስማኤል ደም በመሐመድ ውስጥ ነበር::

የዐረብን የዘር ሐረግ በተመለከተ ግጥም የሚገጥሙ አንዳንድ ሙስሊሞች የመሐመድ የዘር ሐረግ ከአብርሃም ዐልፎ እስከ አዳም ድረስ ይዘልቃል በማለት ዝርዝር ያቀርባሉ:: በምድር ላይ ያለ ሰው በሙሉ የአዳምና የሔዋን ዘር መሆኑ እሙን ነው:: ይሁንና በዚህ የዘር ሐረግ ቀመር መሐመድ የአብርሃም ዘር ብቻ ሳይሆኑ፣ የአዳምም ዘር እንደ ሆኑ ግልጽ ነው:: ሙስሊሞች እንደሚያስረዱት፣ በመሐመድ የዘር ሐረግ ስሌት፣ መሐመድ በመካከለኛው ዘመን ከተነሡ የእስልምና ነቢያት አንዱ እንዲሁም ከአብርሃምና የነቢያት መጀመሪያ ከሆነው ከአዳም ዘር የተገኙ ናቸው::

በመዲና ለነበሩ ሙስሊሞች የዘር ሐረግ መቍጠር አስፈላጊ እንደ ነበረ ሁሉ፣ ከዚያ በኋላ ለመጡ ሙስሊሞችም ጕልሕ ስፍራ አለው:: ከነቢዩ መሐመድ ሞት በኋላ የሺአ ሙስሊሞች ከሱኒ ሙስሊሞች ጋር የመለየታቸው ዋነኛ ምክንያት የዘር ሐረግ ጒዳይ ነው:: ሺአ ሙስሊሞች፣ "የሙስሊሙን ማኅበረሰብ የሚመራው ኢማም (የሃይማኖቱ መሪ) የመሐመድ ዘር" መሆን አለበት ሲሉ ይከራከራሉ:: በተቃራኒው ሱኒ ሙስሊሞች ደግሞ፣ "ኻሊፋ (ፖለቲካዊና መንፈሳዊ መሪ የሚሆነው ሰው) በሙስሊሙ ኅብረተሰብ

[2] "Ibrahim," *Encyclopedia of Islam*, vol. 3, new ed. (Leiden: Brill, 1960), 980-81.



ስምምነት መመረጥ አለበት እንጂ፣ የዘር ሐረግን በመቍጠር መሆን የለበትም" ሲሉ ተቃውሞውን ይከላከላሉ::

ሺአ ሙስሊሞች የመሐመድ የዐጐት ልጅና የፋጡማ ባል የነበረው፣ ዓሊ ቢኒ አቡ ጣሊብ የሙስሊሙ ማኅበረሰብ መንፈሳዊ መሪ ሆኖ ማገልገል አለበት የሚል እምነት ዐደረባቸው:: እርሱ ከሞተ በኋላም ሁሴን የተሰኘው የዓሊ ልጅ በአመራሩ ቦታ እንዲተካ ፈልገው ነበር:: በዚህ አሰጣገባ ውስጥ፣ በሱኒና በሺአ ሙስሊሞች መካከል ግጭት ተፈጥሮ ሁሴን ተገደለ:: ከዚህ በኋላ ሱኒዎችና የሺአ ሙስሊሞች እንደ ተለያዩ ቀሩ::

ይሁንና የዘር ሐረግ በሺአ ሙስሊሞች ብቻ ሳይሆን በሱኒ ሙስሊሞችም ዘንድ ትልቅ ዋጋ አለው:: በዘመናችን የሚገኙ በብዙ ሚሊዮን የሚቈጠሩ የሱኒና የሺአ ሙስሊሞች፣ የራሳቸውንና የመሪዎቻቸውን የዘር ሐረግ እስከ መሐመድ ድረስ ይቈጥራሉ:: እንዲሁም የሱፊ መንፈሳዊ መሪዎች የዘር ሐረጋቸው እስከ መሐመድ ድረስ እስከሚደርስ ይዘረዝራሉ::

የዘር ሐረጋቸውን በመቍጠር አንጻር፣ የሶማሌ ሕዝብ በቀደምትነት ተጠቃሽ ነው:: ሶማሌዎች ሁሉ የመሐመድ ዘሮች እንደ ሆኑ ይናገራሉ:: ለአንድ የሶማሌ እረኛ ልጅ ዘርህ ምንድን ነው? ስል ጠየቅሁት:: በጣም ደስታ በተሞላበት ፊት እንዲህ ሲል ነገረኝ፣ "ስሜ መሐመድ የኡመር ልጅ፣ የአህመድ ልጅ፣ የፍዶው ልጅ፣ የሮብሌህ ልጅ፣ የአቡበከር ልጅ፣ የአዶዋ ልጅ፣ የጉኤልድ ልጅ፣ የሐሰኔ ልጅ፣ የሳማተር ልጅ፣ የዩሱፍ ልጅ፣ የጉኡድ-አዴህ ልጅ፣ የጉሬይ ልጅ፣ የባስ-ጋብ ልጅ፣ የሁሴይን ልጅ፣ የመሐመድ ልጅ፣ የአብደላህ ልጅ፣ የሳሞ-ታሊስ ልጅ፣ የሐዋድሌ ልጅ፣ የመሐመድ ልጅ-የእኔ ጐሣ አባት ነው":: የጐሣው አባት የሆነውን የዘር ሐረግ ቈጠራ የጨረሰው፣ የነቢዩ መሐመድ ልጅ የሆነችው ፋጡማ ላይ በመድረስ ነው[3]:: ይህ ፊደል ያልቈጠረ እረኛ ልጅ፣ የነቢዩ መሐመድ ዘር በመሆኑ እንዲሁም እስልምና በደም ሥሮቹ ውስጥ እንዳለ በማሰብ በደስታ ተፍነከነከ::

ዳሩ ግን በዚህ የዘር ሐረግ ቈጠራ እብዝቶ የመደሰቱ ጒዳይ በጥንቃቄ መታየት አለበት:: ቁርአን ትክክለኛ የአብርሃም ዘሮች የሚባሉት እግዚአብሔርን ያመኑ ሰዎች እንደ ሆኑ በሱራ 3፥68 ላይ በትክክል አስፍሮአል:—

[3] David W. Shenk, *Global Gods* (Scottdale, Pa.: Herald Press, 1999), 48.

ከሰው ሁሉ በኢብራሂም ተገቢዎቹ እነዚያ የተከተሉትና ይህ ነቢይ እነዚያም ያመኑት ናቸው፤ አላህም የምእመናን ረዳት ነው::

## የበኩር ልጅ

እስማኤል የአብርሃም የመጀመሪያ ልጅ ነው:: በሴማውያን ባህል መሠረት የቤተሰብን ኃላፊነት የሚሸከመው የመጀመሪያ ልጅ እንደ ሆነ የሙስሊም ነገረ መለኮት ምሁራን ይናገራሉ:: የአብርሃምና የይስሐቅ ታሪክ በጣም አስደናቂ ታሪክ ነው:: ነገር ግን ለዓለም ሕዝብ ሁሉ የበረከት ምንጭ የሆነው የኅብረተሰብ ክፍል የሙስሊሙ ማኅበረሰብ እንደ ሆነ፣ ይህም በረከት የመጣው በአብርሃም የመጀመሪያ ልጅ በእስማኤል በኩል ነው ሲሉ እነዚህ ምሁራን ያስረዳሉ:: ምሁራኑ እግዚአብሔር እስራኤልን የመረጠው ለተወሰነ ጊዜ ብቻ እንደ ሆነ ከሱራ 2፥122 በመጥቀስ ይሞግታሉ:: እግዚአብሔር ለአብርሃም አንተንና ዘርህን "ለሕዝብ ሁሉ ኢማም (መሪ)" አደርጋችኋለሁ ሲል የሰጠው ተስፋ፣ በመሐመድ መምጣት ምክንያት በአሁኑ ዘመን በሙስሊሙ ኡማ አማካይነት ተፈጽሞአል ሲሉ እነዚህ ሙስሊም ምሁራን ያስረዳሉ:: በእርግጥ አብርሃም አይሁድም ሆነ ክርስቲያን አልነበረም፤ ነገር ግን እንደ አላህ ፈቃድ ለአላህ የሚሰግድና ለአላህ የሚታዘዝ ሰው ነበር:: የአላህን ፈቃድ የፈጸመው በእስልምና እምነት ነው (ሱራ 3፥67)::

አብደላ ዩሱፍ ዓሊ የተባለው የእስልምና ሃይማኖት ምሁር፣ "እግዚአብሔር ለእስራኤል የጸጋ ስጦታ ሰጥቶአል የሚለው ክርክር ግሩም በሆነ ሁኔታ ተጠናቋል፤ አሁን መዞር ያለብን በአብርሃም በኩል ለዐረቦች የመጣውን መንፈሳዊ ስጦታ ወደሚመለከተው ጉዳይ ነው ብሏል"[4]::

የሙስሊሙ ዓለም በእስማኤል በኩል አገኘሁት በሚለው መንፈሳዊ በረከት ሐሴት ያደርጋል:: ሙስሊሞች ይህ ታሪክ ምክንያታዊና አመክንዮአዊ ነው የሚል እምነት አላቸው:: የአብርሃም የመጀመሪያ ልጅ የሆነው እስማኤል ከብዙ ዓመታት በኋላ የእምነትና በዐረብያ የሙስሊም ማኅበረሰብ መመሠረት የሚያበሥር ችቦ ይዞ ቢነሣ የሚያስደንቅ አይደለም:: የመጨረሻው ነቢይ የእስማኤል ዘር እንደሚሆን ግምት ነበር:: ሙስሊሞች፣ እስራኤል ከዓለም ሕዝብ መካከል የተመረጠች የመሆኗ ጉዳይ እየደበዘዘ መምጣቱ፣ እግዚአብሔር የሙስሊሙን ማኅበረሰብ የዓለም ሕዝብ ሁሉ ብርሃን እንዲሆን

[4] Ali, *The Holy Qur'an*, 52.



ለመምረጡ ሁነኛ ማስረጃ ነው የሚል እምነት አላቸው:: እግዚአብሔር ለሙስሊሙ ማኅበረሰብ የሰጠው አገልግሎት፣ ውስን ለሆነ ጊዜ እግዚአብሔር ለእስራኤል ከሰጣት አገልግሎቶች እጅግ ከፍ ያለ እንደ ሆነ ይታሰባል:: አንድ የሙስሊም ሼክ፣ "በአግባቡ የማገናዘብ ችሎታ ያለው ሰው፣ ውሎ አድሮ የእስልምናን ትክክለኛነት መረዳቱ አይቀርም" ብሎ ሲናገር ሰምቼአለሁ::

## አብርሃምና ይስሐቅ

መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ይስሐቅ የሚያቀርበው ታሪክ፣ ከእስልምናው አቻ ታሪክ በጣም በተለየ መንገድ እንድንመለከተው ያደርገናል:: ቁርአን ስለ አብርሃምና ስለ እስማኤል ያለውን ትምህርት ተመልክተናል፣ አሁን ደግሞ መጽሐፍ ቅዱስ ስለ አብርሃምና ስለ ይስሐቅ ምን እንደሚያስተምር እንመልከት:: ይህ ጥንቃቄ በተሞላበት ሁኔታ የምናካሂደው ጥናት ይሆናል፤ ምክንያቱም እስልምና ይስሐቅ ተባርኮአል ስለሚል እንዲሁም በተመሳሳይ ሁኔታ መጽሐፍ ቅዱስ እስማኤልም ተባርኮአል ስለሚል ነው:: ይህ ለጥናታችን ጠቃሚ የአትኩሮት ቦታ ነው:: የእስልምና ነገረ መለኮት ለእስማኤል ቀዳሚውን ስፍራ ይሰጣል፤ ይስሐቅን ያከብራል፤ ይባርከዋልም:: መጽሐፍ ቅዱሳዊው ነገረ መለኮት ደግሞ በይስሐቅ በኩል በረከት ለሰዎች ሁሉ እንደ መጣ ሲያስተምር፣ የእስማኤልንም መባረክ ይቀበላል:: በእርግጥ በዘፍጥረት 17፥20 ላይ ትልቅ ሕዝብ እንዲሁም ዐሥራ ሁለት አለቆች ከአብርሃም የመጀመሪያ ልጅ ከእስማኤል እንደሚወጡ ጌታ እግዚአብሔር ተናግሮ ነበር::

### በሁለት ልጆች መካከል ያለ ትግል

በይስሐቅ ሕይወት ውስጥ የተፈጸመው አስደናቂ ነገር በወንጌል ውስጥ ላለው አስደናቂ ነገር ምልክት ነው:: ይስሐቅ ለአብርሃምና ለሣራ ከእግዚአብሔር ዘንድ የተሰጣቸው ነጻ ስጦታ ነው:: የወንጌልም ባሕርይ እንደዚሁ ነው:: በወንጌል ውስጥ ለሰዎች የተሰጠው የእግዚአብሔር ስጦታ ከሰዎች ፍልስፍና እንዲሁም ሃይማኖታዊ ከሆነ ሥርዐት እጅግ ያለፈ ነው:: ማንኛውም ዐይነት ሰብአዊ ሥነ አመክንዮ፣ ፍልስፍና ወይም ሃይማኖት በወንጌል ውስጥ ያለውን እውነት የተከተለ ወይም ግምት ውስጥ ያስገባ አልነበረም:: እግዚአብሔር በሰው ታሪክ ውስጥ ሰው ሆኖ በመገኘት ከሰዎች ጋር በመኖር ለሰዎችና በሰዎች ምክንያት መከራ ተቀብሎ ፍቅሩን ለእኛ ይገልጣል ብሎ እንኳን በውኑ በህልሙ ያሰበ እንኳ የለም:: ለእኛ የተሰጠን ስጦታ ይህ ውድ የሆነ

የምሥራች ወንጌል ነው። ይህ ስጦታ በእኛ ጥረት ወይም መልካም ሥራ ምክንያት ያገኘነው ሳይሆን፣ በእምነትና በምስጋና የምንቀበለው ነው።

ከአብርሃም ዘመን ሁለት ሺህ ዓመት በኋላ፣ አዲስ ኪዳን በአብርሃም ቤት ውስጥ በሣራና በአጋር እንዲሁም በይስሐቅና በእስማኤል መካከል የነበረው ግጭት ምን ዐይነት የነገረ መለኮት ገጽታ እንዳለው በስፋት ያብራራል (ገላትያ 4፥21-31)። ሐዋርያው ጳውሎስ በአብርሃም ቤት የነበረው ትግል፣ በተራ እምነትና እግዚአብሔር በመሲሑ በኢየሱስ በኩል በገለጠው እምነት መካከል ያለውን ትግል የሚያሳይ ምሳሌ እንደ ሆነ ተናግሯል።

የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት፣ አብርሃም ከአጋር ጋር የነበረው ጥምረትና የእስማኤል መወለድ፣ ሰዎች እግዚአብሔርን ለማስደሰት የሚያደርጉትን ጥረት የሚያሳይ ተምሳሌት እንደ ሆነ ይገልጻሉ። በሌላ በኩል ደግሞ የይስሐቅ መወለድ፣ እግዚአብሔር ያለ ሰው አነሳሽነት በራሱ የጊዜ ሰሌዳ ለአብርሃምና ለሣራ የሰጣቸው ነጻ ስጦታ ነው። ማንኛውም ዐይነት ሃይማኖታዊ ሥርዐት ይስሐቅን አላስገኘም። የሁለቱ ሴቶችና የሁለቱ ልጆች ታሪክ የሚያሳየን፣ የማይገባንን የእግዚአብሔርን ጸጋ በእምነት በመቀበልና የእግዚአብሔርን ተስፋና በረከት የተለያዩ ሃይማኖታዊ ሥርዐቶችን በመፈጸም ከእግዚአብሔር እጅ ለመቀበል የሚደረገውን ሙከራ በንጽጽር የሚያሳይ ነው።

ሐዋርያው ጳውሎስ እነዚህ ሁለት የተለያዩ ጉዞዎች፣ የእግዚአብሔርን ጸጋ በሃይማኖታዊ ሥርዐቶችና በሰብአውያን ጥረት ለማግኘት የሚደረግ ጉዞ እንዲሁም በእግዚአብሔር ጸጋ የሚገኝ ችሮታ ተምሳሌቶች እንደ ሆኑ ጽፎአል። ሃይማኖታዊ ሥርዐቶችና የሰዎች ጥረት የእግዚአብሔርን ጸጋ ሊያመጡ ይችላሉን? እንደዚህ ከሆነ የእግዚአብሔርን ጸጋ ለማግኘት ምን ያህል ሃይማኖታዊ ሥርዐት መፈጸም አለብኝ? አልያ የእግዚአብሔር ጸጋ በእምነት ብቻ የሚገኝ ስጦታ ነው?

አንድ ጊዜ ከሙስሊም ጓደኞዬ ጋር ለአንድ ሳምንት ያህል በነበረን ጉዞ ወቅት እንዲህ ሲል አስተያየቱን ሰጥቶኛል፣ "ወንጌል አንተ እንደምትለው ከሆነ ክርስቲያን ከመሆን ይልቅ ሙስሊምነቴ በጣም ነጻ ያደርገኛል ማለት ነው"። ይህ ሰው ምን ማለቱ ነው? እኔ ምን ማለቱ እንደ ሆነ በእርግጠኛነት መናገር ይቸግረኛል። እኔ ያየሁት ነገር ቢኖር እየተጓዝን በነበርንበት ወቅት ለእስልምና ታማኝ የሆኑ ሙስሊም ጓደኞቼ ዕረፍት በምናደርግበት ጊዜ ሁሉ፣ ሃይማኖታዊ የጸሎት ሥርዐት (ሶላት) ለመፈጸም ሲጨናነቁ ተመልክቼአለሁ።



## የተሰያዩ የእምነት ምላሾች

የእስማኤልና የይስሐቅ ታሪክ ለሙስሊም ኡማና ለቤተ ክርስቲያን ያለው አስተዋጽኦ ምንድን ነው? በሙስሊም ኡማና በቤተ ክርስቲያን መካከል ያለው መሠረታዊ ልዩነት፣ በእስማኤልና በይስሐቅ መካከል የነበረው ልዩነት ቀጣይ ገጽታ ነውን? በሁለቱ የአብርሃም ልጆች መካከል የነበረው ልዩነት ውጤት ነው ማለት አይቻልም። ይልቁንም አብርሃም በውስጡ ለእግዚአብሔር ቃል ኪዳን ምላሽ ለመስጠት ያደረገውን ትግል ያመለክታል።

አብርሃም የእግዚአብሔርን ፈቃድ በራሱ ጊዜ ለመፈጸም ርምጃ መውሰድ (እስማኤል) ወይስ የእግዚአብሔርን ጥሪ በመከተልና እግዚአብሔር ቃል ኪዳኑን በራሱ መንገድና ጊዜ እንዲፈጽም (ይስሐቅ) መጠበቅ ነበረበት? አብርሃም የእግዚአብሔርን ፈቃድ ተራ በሆነ መንገድ መፈጸም (እስማኤል) ወይስ እግዚአብሔር ራሱ በተኣምራዊና በሚያስደንቅ ሁኔታ እንዲፈጽመው (ይስሐቅ) መጠበቅ ነበረበት። እነዚህ ታሪኮች ስለ እስልምናና ስለ ወንጌል የሚያስተምሩት ትምህርት አላቸውን?

ቀደም ብሎ እንደ ተገለጸው ትግሉ ያለው በሙስሊም ኡማና በቤተ ክርስቲያን መካከል አይደለም። ይልቁንም ትግሉ የሚካሄደው በእኛ ነፍስ ውስጥ ሲሆን፣ ዕለት ተዕለት ለሚገጥሙን ተግዳሮቶች ምላሽ በምንሰጥበት ጊዜ የሚፈጠሩ ትንቅንቆች ናቸው። በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ ተካፋዮች የምንሆነው፣ ሃይማኖታዊ ሥርዐቶችን በመፈጸም ነው ወይስ እግዚአብሔር ራሱ መንግሥቱን በሚያስደንቅ ሁኔታ እንዲመሠርት በተስፋ በመጠበቅ? ይህ ነው እንግዲህ ዐቢዩ ጥያቄ።

## ዘርዐ ሐረግ

ልማዳዊ የሆነው የሰው አካሄድ በዘር ሐረግ ቈጠራና ግንኙነት የሚመራ ነው። ለምሳሌ እናትህ ማን ናት? አያትህን የማውቀው ይመስለኛል፤ ትልቅ ሰው ነበር። ቅድመ አያቴ ታላቅ ሰባኪ ነበር። አንተ ሦስተኛው የዐጐቴ ልጅ ነህ። ከቅድመ አያቶቼ ውስጥ አንዱ፣ በ16ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የአናባፕቲስት ሰማዕት ነው። በተመሳሳይ ሁኔታ መሐመድና የሙስሊም ኡማ ከቁረይሽ እስከ እስማኤል ላለው የዘር ሐረግ ትልቅ ክብር ይሰጣሉ።

መጽሐፍ ቅዱሳዊው ታሪክ፣ አብርሃምን በእነዚህ የምልከታ ንጽሮቶች እንጻር እንድናየው አያደርጉንም:: በመሠረቱ የዘር ሐረጉች የተወሰነ ጠቀሜታ አላቸው:: ይሁንና እዚህ ግባ የሚባል አይደለም:: የአብርሃምን ታሪክ ስንመለከት መልከ ጼዴቅ የተባለ ከእግዚአብሔር ዘንድ የተላከ ካህን እናገኛለን:: አብርሃም ነገሥታትን ገድሎና ዘርፎ ሲመለስ፣ ይህ ካህን አብርሃምን በመንገድ አግኝቶ ባረከውና ለእርሱ እንዲሁም ከእርሱ ጋር ለነበሩት ዳቦና ወይን ጠጅ ሰጣቸው:: አብርሃምም ከሰበሰበው ንዋይ ሁሉ አንድ ዐሥረኛውን ለመልከ ጻዴቅ ሰጠው::

ዕብራውያን 7፥3 መልከ ጼዴቅ፣ "አባትና እናት፣ የትውልድም ቍጥር የሉትም" ይላል:: ይሁንና መልከ ጼዴቅ ከአብርሃም ይበልጣል:: ከዚህም የተነሣ መልከ ጼዴቅ አብርሃምን ባረከው፤ አብርሃምም ለመልከ ጼዴቅ ዐሥራትን ሰጠ::

የትውልድ ሐረጋችን እኛ የምናስበው ያህል አስፈላጊ እንዳልሆነ ልብ ልናደርግ ይገባናል:: ማንነቱ በውል ከማይታወቀው ከመልከ ጼዴቅ ሕይወት ከምንማራቸው ቍም ነገሮች መካከል ይህ አንዱና ዋነኛው ነው::

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያለውን የይስሐቅን ታሪክ ብንመለከት የዘር ሐረግ ቈጠራ የምናስበውን ያህል ትልቅ ሚና እንደሌለው እንገነዘባለን:: የአብርሃም ሁለተኛው ልጅ ይስሐቅ የቃል ኪዳን ልጅ ተባለ:: እስማኤል በእግዚአብሔር ተባርኮአል፤ ነገር ግን እግዚአብሔር ዓለምን ለመባረክ ቃል ኪዳን የገባው በሁለተኛው ልጅ በይስሐቅ በኩል ነው:: በእርግጥ እንዲህ ዐይነቱ ግርን|ፊዋ (የተገላቢጦሽ) አካሄድ ለበርካታ ባህሎች ባይተዋር ነው::

## የአብርሃም ቤተሰብ

ከዓለማችን ነዋሪ ግማሽ የሚሆነው ሕዝብ የክርስትና፣ የእስልምናና የአይሁድ እምነት ተከታይ ስለሆነ፣ እምነቱን ከአብርሃም ጋር ያያይዛል:: የእምነት ዘር የተዘራው በአብርሃም ቤት ሲሆን፣ ላለፉት አራት ሺህ ዓመታት ይህ ዘር በዓለም ዙሪያ ሲፈካና ሲያብብ ቆይቶአል:: በእነዚህ የእምነት ቡድኖች መካከል የሚታዩት ዐበይት አንድነቶችና ልዩነቶች በአብርሃም ቤት ውስጥ የነበሩ ናቸው:: እኛም በአብርሃም እምነት ጥላ ሥር ተገኝተናል:: የአብርሃም የሕይወት ጕዞ እስማኤልንና ይስሐቅን አስገኝቶአል::



የአብርሃም የሕይወት ጕዞ ለአይሁዶች፣ ለክርስቲያኖችና ለሙስሊሞች መሠረት ነው:: የሙሴ መጻሕፍት (ቶራ) ብቻ ሳይሆኑ፣ አዲስ ኪዳንና ቁርአን ለአብርሃም የእምነት ጕዞ የራሳቸው የሆነ ጉልሕ ምላሽ አላቸው:: ከፍ ብለን ያየናቸው እነዚህ እውነታዎች ከሙስሊሞች ጋር ላለን ውይይት እንደመሠረት ሆነው ማገልገል አለባቸው::

*የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባብ*

ዘፍጥረት 2፥11-20

*የቁርአን ምንባብ*

ሱራ 21፥24-29

## የአስተውሎትና የውይይት ጥያቄዎች

1. እግዚአብሔር ለአብርሃም ስለ ዘሩ ተስፋ ሰጥቶታል:: ሚስቱ ሣራ መካን ነበረች:: የእስማኤልና የይስሐቅ ታሪክ አብርሃም በእግዚአብሔርና እርሱ የሰጠውን ተስፋ ለማመን የሚያደርገውን ትግል ይገልጻል:: እርስዎ፣ በአብርሃም ሕይወት ውስጥ ያለውን ትግል በምን ዐይነት መንገድ ሊረዱት ይችላሉ?
2. ቀጥሎ ባለው ዐረፍተ ነገር ላይ አስተያየት ስጥበት:: በእስማኤልና በይስሐቅ መካከል ያለው ትግል የሚያሳየን እስልምናን ማዕከል ባደረገና ወንጌልን ማዕከል ባደረገ እምነት መካከል የሚደረገውን ትግል ነው (ገላ 4፥21-31)::
3. ከፍ ብሎ በነበረን ውይይት እንደተገለጸው ሙስሊም ጓደኛዬ ሲናገር ለእርሱ በሙስሊምነቱ ወንጌል በጣም ነጻ ያደርጋል ብሎ ነበር:: የተናገረው እውነት ነውን? ለመልስህ መረጃ ስጥ::
4. የዘር ሐረግ በሙስሊም ኡማ ውስጥ ምን ያህል ጉልህ ሚና እንዳለው ተመልከት:: የዘር ሐረግን በተመለከተ የክርስቲያኖች ትኩረት ምን ላይ እንደሆነ ምሳሌዎችን አገናዝብ:: የመልከጼዴቅ ታሪክ የትውልድ ቍጥር ላይ ከፍተኛ ትኩረት መስጠትን የሚተቸው እንዴት ነው? (ሱራ 106፥1-4፤ ዘፍጥረት 14፥18-20፣ ዕብራውያን 7፥1-10)
5. አብርሃም ለሙስሊሞች የመካከለኛ ዘመን ነቢይ መሆኑና ለክርስቲያኖች የእምነት አባት መሆኑ ያለውን ትርጉም አዘልነት አነጻጽር:: (ሱራ 3፥96-97፣ ሮሜ 4፥12:16)
6. የአብርሃም ውርስ በአይሁዶች፣ በክርስቲያኖችና በሙስሊሞች መካከል ሰላምን ለመፍጠር ምን ያህል አስተዋጽኦ ሊያደርግ ይችላል?

## ምዕራፍ አምስት

# መሪዎች

# የነቢያት መደምደሚያ—መሲሑ

ኢየሱስ መሲሕ ነው። ኢየሱስ መሲሕ እንደ ሆነ ሙስሊሞችም ሆኑ ክርስቲያኖች በአንድ ይስማማሉ። እንዲሁም ሙስሊሞችና ክርስቲያኖች ነቢያት የእግዚአብሔር ቃል እንዳበሠሩ ከሙሉ ልብ ያምናሉ። ነገር ግን በእስልምናና በክርስትና ስለ መሲሑና ስለ ነቢያት የሚሰጠው ትርጓሜ እጅግ ለየቅል ነው።

ለምሳሌ ሙስሊሞች ሁሉ፣ መሐመድ የነቢያት መደምደሚያ ናቸው እንዲሁም መሐመድ የእግዚአብሔርን የመጨረሻ እንዲሁም የተጣራና የማይለወጥ መልእክት ሰብከዋል ብለው ያምናሉ። ነገር ግን ክርስቲያኖች የመሐመድ መልእክት የመሲሑን መልእክት ተክቶአል የሚለውን የእስልምና ትምህርት ፈጽመው አይቀበሉም። ምክንያቱም ክርስቲያኖች ሁሉ ኢየሱስ ክርስቶስ ጌታና አዳኝ ነው ብለው ከሙሉ ልብ ስለሚያምኑና ስለሚመሰክሩ ነው። ይህም ምስክርነት ሙስሊሞች ስለ መሲሑ ካላቸው እምነት በእጅጉ የተለየ ነው።

መሲሑን በተመለከተ በክርስቲያኖችና በሙስሊሞች መካከል ያለው ልዩነት በቀላሉ የሚታይ ጉዳይ አይደለም። ይህ ምዕራፍ፣ ይህን ርእሰ ጉዳይ በተመለከተ በሁለቱ ሃይማኖቶች መካከል ያለውን መሠረታዊ ልዩነት መዳሰስ፣ የትኩረት አቅጣጫው ነው። ስለ መሲሑ ሕይወትና አገልግሎት የክርስቲያኖች መሠረተ እምነት ምንድን ነው? በአንጻሩ ሙስሊሞች ስለ መሲሑ ያላቸው መረዳት ምን ይመስላል? የነቢያት መደምደሚያ እንደ ሆኑ ስለሚታመነው ስለ ነቢዩ መሐመድ ሙስሊሞች ያላቸው ግንዛቤ ምንድን ነው? በርእሰ ጉዳዩ ላይ ሙስሊሞችና ክርስቲያኖች የሚስማሙባቸው ነጥቦች የትኞቹ ናቸው? እነዚህ ሁሉ ርእሰ ጉዳዮች የሚያመጡት ለውጥ ምንድን ነው?

## መሲሑ በክርስትና እምነት

ምዕራፍ ሦስት ስለ አዳምና ስለ ሔዋን በተለይ ደግሞ መልካሙንና ክፉውን ከሚያስታውቀው ዛፍ ከበሉ በኋላ እግዚአብሔር ለእነርሱ ያደረገውን ክብካቤ/ጥንቃቄ ምን እንደሚመስል ይዳስሳል። በእስልምና ሃይማኖት

የመጀመሪያ ነቢይ ነው ተብሎ የሚታመነው አዳም ሲሆን፣ ቁርአን እግዚአብሔር ለአዳም መመሪያን እንዳወረደለት ይገልጻል። መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር ከሴቲቱ ዘር የሚወለደው መሲሕ፣ የክፉውን (የእባቡን) ራስ እንደሚቀጠቅጥ በአንጻሩ ደግሞ ክፉው (እባቡ) የመሲሑን ሰኰና እንደሚመታ (ዘፍጥረት 3፥15) ያስተምራል። እግዚአብሔር ይመጣል ብሎ ለሰው ልጆች የሰጠው ተስፋ፣ ሰኰናው የሚቀጠቀጠው ወይም መከራን የሚቀበለው አዳኝ፣ መሲሑ እንደ ሆነ ክርስቲያኖች ያምናሉ[1]። በእስልምና እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ምሪትን ይሰጣቸው ዘንድ ተስፋ እንደ ገባላቸው ሲታመን፣ በክርስትና (በመጽሐፍ ቅዱስ) ግን እግዚአብሔር ሰዎችን ለማዳን ምሪትን ሳይሆን መድኀኒትን እንደ ሰጠ ያስተምራል።

## መጽሐፍ ቅዱሳዊ ተስፋ—መሲሑ

አዳምና ሔዋን በኤድን ገነት ኀጢአት ከሠሩበት ጊዜ ጀምሮ፣ መሲሑ እስከ መጣበት ጊዜ ድረስ፣ እግዚአብሔር በመጽሐፍ ቅዱስ አማካይነት ደግሞ ደጋግሞ ያስረገጠው ተስፋ፣ በሞትና በኀጢአት ላይ ድል የሚነሣውን ቤዛ/አዳኝ እንደሚልክልን ነው። በዚህ አጭር አሰሳዊ ጥናት፣ እግዚአብሔር የሰጠውን ተስፋና ኪዳን የሚገልጹትን መልክቶች በጥልቀትና በዝርዝር እንመለከታቸዋለን። እግዚአብሔር በየዘመናቱ ያስነሣቸው ነቢያት በሙሉ፣ ይህን የተስፋ ልጅ አስመልክቶ ትንቢት ተናግረዋል። ነቢዩ ኢሳይያስ ይህን የተስፋ ቃል አስመልክቶ ከየትኛውም ነቢይ ይልቅ በዚህ መልኩ በግልጽ ተናግሮአል:— "ሕፃን ተወልዶልናልና ወንድ ልጅም ተሰጥቶናልና አለቅነትም በጫንቃው ላይ ይሆናል፤ ስሙም ድንቅ መካር፣ ኀያል አምላክ፣ የዘላለም አባት፣ የሰላም አለቃ ተብሎ ይጠራል። ከዛሬ ጀምሮ እስከ ዘላለም ድረስ በፍርድና በጽድቅ ያጸናውና ይደግፈው ዘንድ በዳዊት ዙፋንና በመንግሥቱ ላይ አለቅነቱ ይበዛል" (ኢሳይያስ 9፥6-7)።

ኢሳይያስ ከኖረበት ከብዙ ዓመታት በፊት፣ እግዚአብሔር አብርሃምን ሲጠራው ስለዚህ ተስፋ ገልጦለት ነበር። እግዚአብሔር ለአብርሃም በዘሩ ሕዝቦች (አሕዛብ) ሁሉ እንደሚባረኩ በዘፍጥረት 12፥1-3 ላይ እንዲህ ሲል ተናግሮታል:— "ከአገርህ ከዘመዶችህም ከአባትህም ቤት ተለይተህ እኔ

[1] አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ምሁራን ዘፍጥረት 3፥15 የመሲሑን ቤዛዊ ሥራ የሚገልጽ ተስፋ ነው የሚል እምነት የላቸውም። አብዛኞቹ ሊቃውንት እንዲሁም በርካታ ቤተ ክርስቲያናት፣ ይህ ኪዳን በመሲሑ በኢየሱስ ሕይወትና አገልግሎት ሙሉ ለሙሉ እንደ ተፈጸመ ከሙሉ ልባቸው ያምናሉ።



ወደማሳይህ ምድር ውጣ. . .የምድር ነገዶችም ሁሉ በአንተ ይባረካሉ"። ይህ የተስፋ ቃል፣ የአብርሃምን እምነት የተጋሩትን የእግዚአብሔርን ሰዎች ማመልከቱ እሙን ቢሆንም፣ በሌላ አንጻር ደግሞ ስለ መሲሑ መምጣት የሚያስተምር እንደ ሆነ ቅዱሳት መጻሕፍት ያስረዳሉ (ገላትያ 3፥16)።

እግዚአብሔር በአብርሃም የእምነት መስመር እንዲመላለሱ የእስራኤልን ሕዝብ የቃል ኪዳን ሕዝብ አድርጉ መረጠ[2]። እግዚአብሔር የእስራኤልን ሕዝብ የመረጠው ለዚህ ተልእኮ ለዓለም ሁሉ ብርሃን እንዲሆኑ በማሰብ ነበር (ኢሳይያስ 49፥6)። ይህን የቃል ኪዳን ሕዝብ ስናስብ ልንደነቅ እንችላለን። እስራኤላውያን የእግዚአብሔር የቃል ኪዳን ሕዝብ መሆን ማለት ምን ማለት እንደ ሆነ መረዳት ሲጀምሩ በግብፅ የፈርዖን ባሮች ሆኑ።

## እግዚአብሔር "እኔ ነኝ" ሲል ራሱን ገለጦአል

አብርሃም ከኖረበት ከአምስት መቶ ዓመት በኋላ፣ እግዚአብሔር እስራኤላውያንን ከግብፅ ባርነት ነጻ ያወጣቸው ዘንድ ሙሴን ላከላቸው። እግዚአብሔር ሙሴን የተገናኘበትና የጠራበት ሁኔታ እጅግ አስደናቂ ነበር። ይህ የጥሪ ሁኔታም የመሲሑን አገልግሎት ፍንትው አድርጉ የሚያሳይ ነው። እግዚአብሔር ለሙሴ የመገለጡ ጉዳይ ለእስራኤላውያን የእግዚአብሔር የቃል ኪዳን ሕዝብ የሚል ማንነት አጐናጽፎአቸዋል።

እግዚአብሔር ለሙሴ በሚገለጥበት ወቅት፣ ሙሴ በሲና ተራራ አጠገብ በጐችን ይጠብቅ ነበር። ሙሴም በቍጥቋጦ ውስጥ እሳት ሲነድ አየ፤ ነገር ግን እሳቱ ቍጥቋጦውን አላቃጠለውም። ሙሴ ወደ ቍጥቋጦው እየቀረበ ሲመጣ እግዚአብሔር ሙሴን፣ "ሙሴ"፣ "ሙሴ" ሲል ጠራው። ወደ ግብፅ ሄዶም እስራኤላውያንን ዐርነት እንዲያወጣቸው አዘዘው።

ሙሴም በመደነቅ፣ "ስምህ ማን ነው?" ሲል እግዚአብሔርን ጠየቀ። እግዚአብሔርም "ያለና የሚኖር እኔ ነኝ" አለው (ዘፀአት 3፥1-15)። የነገረ መለኮት ምሁራን ያካሄዷቸው ጥናቶች እንደሚያስረዱት፣ "ያለና የሚኖር" የሚለው ሐረግ ትርጕሙ፣ በተወሰነ መጠንም ቢሆን ያህዌ በሚለው

[2] እስራኤል ማለት፣ እግዚአብሔርን አጥብቆ የሚሻ/የሚፈልግ ማለት ነው። ምንም እንኳ እግዚአብሔር ዘወትር ታማኝ ቢሆንም፣ የኪዳኑ ሕዝብ የሆነው እስራኤል ግን ሁል ጊዜ ለአምላኩ ለእግዚአብሔር ታማኝ አይደለም። የእግዚአብሔር ሕዝብ ታሪክ፣ ከእግዚአብሔር ጋር ያደረገውን ትግል የሚያሳይ ነው።

የእግዚአብሔር ስም ውስጥ እንደሚገኝ ይገልጻሉ። ነገር ግን "ያለና የሚኖር" የሚለው ሐረግ፣ እግዚአብሔር በየትኛውም ዐይነት ስም ሊገለጽ እንደማይችል አመላካች ነው። እርሱ ያለ፣ የነበረና ወደ ፊትም የሚኖር ነው። እርሱ እኛን በየግላችን በማንነታችን የሚገናኘን አምላክ ነው። እግዚአብሔር የግል፣ የኪዳንና የጽድቅ አምላክ ሲሆን፣ ፈቃዱን ብቻ ሳይሆን፣ ራሱንም እንኳ ለሰው ልጆች የገለጠ ጌታ ነው። እኛን ከእስራት ለማውጣት በላከልን መገለጦች አማካይነት ይሠራል። እግዚአብሔር እስራኤላውያንን ከፈርዖን የባርነት ቀንበር ነጻ እንዳወጣቸው፣ እርሱን የሚከተሉትን በሙሉ ከክፉ እስራት ነጻ ያወጣቸዋል።

እግዚአብሔር ለሙሴ በቁጥቋጦ ውስጥ የተገለጠበት ክሥተት ለመጽሐፍ ቅዱሳዊው ነገረ መለኮት አዲስ ምዕራፍ ከፍቶአል። አብርሃም እግዚአብሔርን የሚያውቀው ኤሎሂም በሚለው ስሙ ነበር። ቀደም ብሉ ባለው ምዕራፍ ውስጥ አላህ የሚለው የዐረቦቹ ስያሜ ኤሎሂም ከሚለው ከብሉይ ኪዳኑ የእግዚአብሔር ስም ጋር ተመሳሳይነት እንዳለው ገልፀን ነበር። ነገር ግን እግዚአብሔር ለሙሴ "ያለና የሚኖር" አምላክ በማለት ራሱን ሲገልጥለት፣ እርሱ የቃል ኪዳን አምላክና ሰዎችን በግል የሚገናኝ እንደ ሆነ አስታውቆታል። እኛም ለእግዚአብሔር ጥሪ ምላሽ ስንሰጥና ከእርሱ ጋር ኅብረት ስናደርግ፣ "ያለና የሚኖር አምላክ የእኔና የእናንተ አምላክ ነው" ማለት እንጀምራለን።

ይህ ዐይነቱ ለውጥ እግዚአብሔርን ማወቅ እንደ ሆነ፣ መጽሐፍ ቅዱስ በዘፀአት 6፥2-3 እንዲህ ሲል ይገልጻል፡— "እግዚአብሔርም ሙሴን ተናገረው፤ አለውም፤ እኔ እግዚአብሔር ነኝ፤ ለአብርሃምም፣ ለይስሐቅም፣ ለያዕቆብም ሁሉን እንደሚችል አምላክ ተገለጥሁ፤ ነገር ግን ስሜ እግዚአብሔር አልታወቃቸውም ነበር"።

## የመሲሑ ስሞች

የመሲሑ አገልግሎት እግዚአብሔር ራሱን፣ "ያለና የሚኖር" በማለት ካስተዋወቀው መገለጥ ጋር ይስማማል። የእግዚአብሔር ዋና ትኩረት ፈቃዱን እንጂ ከሰው ጋር ያለውን መስተጋብር/ግንኙነት ያላካተተ ቢሆን ኖሮ፣ በወንጌል ውስጥ የተገለጠው የመሲሑ አገልግሎት ትርጉም አልባ ይሆን ነበር። ሆኖም ግን መልአኩ ስለ ኢየሱስ መወለድ ሲያበሥር፣ እግዚአብሔር ለአብርሃምና ለሙሴ ከሰጠው መገለጥ ጋር የሚስማሙ ሁለት ስሞችን ለመሲሑ ሰጥቶታል።



የመጀመሪያው ስም ኢየሱስ የሚል ነው። መልአኩ፣ "ልጅም ትወልጃለሽ፤ እርሱ ሕዝቡን ከኀጢአታቸው ያድናቸዋልና፤ ስሙን ኢየሱስ ትይዋለሽ" (ማቴዎስ 1፥21) ሲል ለሕፃኑ ስም አወጣለት። ኢየሱስ የሚለው ስም የሹዋ ከሚለው የዕብራይስጥ ስም የተወሰደ ሲሆን ትርጉሙም፣ "ያህዌ ያድናል" ማለት ነው። ነገር ግን የሚያድነን ከምንድን ነው? መልአኩ ሲናገር "ሕዝቡን ከኀጢአታቸው ያድናቸዋል" ብሎአል። ከኀጢአታቸው የሚያድናቸው እንዴት ነው? እግዚአብሔር በመሲሑ በኩል ወደ ሰው ታሪክና ወደ እያንዳንዳችን ሕይወት ፈቃዱን ከማስታወቅ በበለጠ ሁኔታ መጥቶአል። ምንም እንኳ ኀጢአታችን ብዙ ቢሆንም፣ ከኀጢአትና ኀጢአት ካስከተለው ሞት ሊያድነን ወደ እኛ መጥቶአል። እግዚአብሔር በራሱ አነሳሽነት እንዴት ወደ ሰው እንደ መጣ በሚቀጥለው ምዕራፍ በስፋት እንመለከታለን።

የመሲሑ ሁለተኛ ስም አማኑኤል የሚለው ስም ነው። አማኑኤል ማለት "እግዚአብሔር ከእኛ ጋር" ነው ማለት ነው። ኢየሱስ አገልግሎት ሲጀምር ልክ እንደ እግዚአብሔር በሥልጣን ይሠራ ስለነበር፣ ሰዎች ሁሉ ይደነቁበት ነበር። የክርስቶስ ሕይወት በእውነት፣ "እግዚአብሔር ከእኛ ጋር" እንዳለ የሚያሳይ ነበር። ጌታ ኢየሱስ ሲናገር፣ "እኔን ያየ አብን አይቶአል" ብሎአል (ዮሐንስ 14፥9)፤ ምክንያቱም እርሱ የአብ ብቸኛና ፍጹም ወኪል ስለሆነ ነው[3]።

ከሁለቱ ስሞች በተጨማሪ ኢየሱስ፣ "የእግዚአብሔር በግ" የሚል ስያሜ ተሰጥቶታል። ኢየሱስ ክርስቶስ አገልግሎት ከመጀመሩ በፊት በዮርዳኖስ ወንዝ ሲጠመቅ፣ እርሱን ያጠመቀው መጥምቁ ዮሐንስ ስለ ኢየሱስ እንዲህ ሲል ተናግሮአል፡— "እነሆ የዓለምን ኀጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ"።

ወደ ኋላ መለስ ብለን ስንመለከት፣ የአብርሃምን ልጅ ለማዳን እግዚአብሔር የመሥዋዕቱን በግ አዘጋጀ። ክርስቲያኖች ይህ መሥዋዕት እኛ ከእግዚአብሔር ዘንድ ይቅርታ እንድናገኝና እንድንድን በእኛ ፈንታ መሥዋዕት የሆነውን ኢየሱስን ያመለክታል ብለው ያምናሉ። በሚቀጥለው ምዕራፍ ይህን ጉዳይ በስፋት ለመመልከት እንሞክራለን።

---

[3] በኢትዮጵያ "የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን" በመባል የሚታወቀው የሃይማኖት ድርጅት፣ ኢየሱስ ክርስቶስ እግዚአብሔር አብ ነው ወይም ኢየሱስና አብ አንድ አካል ናቸው የሚል የተሳሳተ ትምህርት ያስተምራል። የዚህን ሃይማኖት መናፍቃዊ ትምህርት በስፋት መመልከት ከፈለጉ፣ ተስፋዬ ሮበሌ፤ *ሰባልዮሳውያን፡— "የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን" የሥላሴ አስተምህሮ በቃለ እግዚአብሔር ሲመዘን፤* (ቅጽ 1) በሚል ርእስ ያዘጋጀውን መጽሐፍ ይመለከቷል።

ይህንን ነገር ሁሉ ማየት ያስፈለገው የመጽሐፍ ቅዱስ ምስክርነት እንደሚነግረን፣ አፍቃሬ አባታችን የሆነው እግዚአብሔር፣ እኛን ለማዳን ቤዛና አዳኝ ሆኖ በመሲሑ በኩል መገለጡን እንድንረዳ ታስቦ ነው። ይህ እውነት የነገረ መለኮት ምሁራን ሆን ብለው የፈጠሩት ታሪክ አይደለም። ይልቁንም የኢየሱስ ክርስቶስ ሕይወት፣ ምስክርነትና አገልግሎት ይህንን እውነት በተጨባጭ የሚያሳየን ታሪክ ነው። ሐሳቡን በደንብ ለመገንዘብ የተወሰኑ ምሳሌዎችን እንመልከት:—

በአንድ አጋጣሚ ኢየሱስ "አብርሃም ሳይወለድ እኔ አለሁ" ብሎ ለአይሁድ ሲነግራቸው፣ እጅግ ተገርመው ነበር። "እኔ አለሁ" የሚለው ዐረፍተ ነገር እግዚአብሔር ለሙሴ ሲገለጥ፣ "ያለና የሚኖር" በማለት ራሱን ይፋ ካደረገበት ስም ጋር አንድ ነው።

በሌላ አጋጣሚ ኢየሱስ ከደቀ መዛሙርቱ መካከል ከሦስቱ ጋር በተራራ ላይ ነበር። በዚያ ጊዜ ሙሴና ኤልያስ ተገልጠው ከኢየሱስ ጋር ተነጋግረው ነበር። ሙሴና ኤልያስ በብሉይ ኪዳን ታላላቅ ነቢያት (ዐበይት ነቢያት) ከሚባሉት የእግዚአብሔር ነቢያት መካከል ናቸው፤ ምክንያቱም ሙሴ ሕግ ሰጪ ሲሆን፣ ኤልያስ ደግሞ ታላላቅ ተአምራትን ያደረገ ነቢይ ነው። ኢየሱስና ደቀ መዛሙርቱ በተራራው ላይ እንዳሉ ሙሴና ኤልያስ ተሰወሩባቸው፤ ደመናም ተራራውን ሸፈነው፤ እግዚአብሔርም በደመና ውስጥ፣ "በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው፤ እርሱን ስሙት" ሲል ተናገረ። ከሞቱና ከትንሣኤው በኋላ ኢየሱስ፣ "ሥልጣን ሁሉ በሰማይና በምድር ተሰጠኝ" ሲል ተናግሮአል (ማቴ 28+18)።

## መሲሑ ኢየሱስ ማን ነው?

ይህ ምን ማለት ነው? እነዚህ አስደናቂ የሆኑ ነገሮች ከመሲሑ ከኢየሱስ ጋር ያላቸውን ግንኙነት፣ አንድ ሰው በነገረ መለኮት ቋንቋ እንዴት ሊገልጻቸው ይችላል?

ከክርስቶስ ሞት፣ ትንሣኤና ዕርገት በኋላ የአዲስ ኪዳን ጸሐፍያን ክርስቶስን እንዲህ ሲሉ ገልጸውታል:—

> እግዚአብሔርም ሙላቱ ሁሉ በእርሱ ይሆን ዘንድ ወዶአልና፤ በመስቀሉ ላይ በፈሰሰው ደሙ ሰላምን በማድረግ በምድርም ሆነ በሰማይ ያለውን ነገር ሁሉ በእርሱ በኩል ከራሱ ጋር አስታረቀ (ቈላ 1+19-20)።
>
> ከጥንት ጀምሮ እግዚአብሔር በብዙ ዐይነትና በብዙ ጐዳና ለአባቶቻችን በነቢያት ተናግሮ፣ ሁሉን ወራሽ ባደረገው ደግሞም ዓለማትን በፈጠረበት በልጁ በዚህ ዘመን መጨረሻ ለእኛ ተናገረን፤ እርሱም የክብሩ መንጸባረቅና የባሕሪዩ ምሳሌ ሆኖ ሁሉን በሥልጣኑ ቃል እየደገፈ፣ ኀጢአታችንን በራሱ ካነጻ በኋላ በሰማያት በግርማው ቀኝ ተቀመጠ (ዕብራውያን 1+1-3)።

እኔና ቤተሰቦቼ ሶማሊያን በረገጥንበት ወቅት፣ ከመሲሑ ደቀ መዛሙርት ውስጥ አንዱ የሆነውን ሱማሊያዊ በሚኖናይት ሚስዮን ትምህርት ቤት ቅጥር ግቢ ውስጥ አገኘነው። በወቅቱ ከእግራችን በታች ምግብ ፍለጋ ወዲህ ወዲያ የሚርመሰመሱትን ጕንዳኖች በማመላከት፣ ይህ ግለሰብ እንዲህ አለኝ:— "የእነዚህ ጕንዳኖች ጓደኛ ለመሆን ፈልገሃል እንበል። አንተ ወደ እነርሱ ስትጠጋ ፈርተው ከአንተ ይሸሻሉ፤ ወደ ጕድጓዳቸውም ይገባሉ። የጕንዳን ጓደኛ ለመሆን ከፈለግህ፣ ብቸኛው መንገድ ጕንዳን መሆን ነው ያለብህ"።

ንግግሩን በመቀጠል፣ "እግዚአብሔር በመሲሑ በኩል ያደረገው ነገር ከዚህ ጋር ተመሳሳይ ነው። እኛ በእግዚአብሔር ፊት እንደ ጕንዳኖች ነን። ይሁንና እግዚአብሔር የሰው ወዳጅ መሆን ፈለገ። ከዚህም የተነሣ እግዚአብሔር በመሲሑ በኩል ከእኛ እንደ አንዱ ሆነ"።

መሲሕ የሚለው ስም ምን ማለት ነው? መሲሕ ማለት፣ "የተቀባ" ማለት ነው። ተልእኮውስ ምንድን ነው? ከክርስቶስ ልደት ከአምስት መቶ ዓመታት በፊት ነቢዩ ኢሳይያስ ስለ መሲሑ ተልእኮ እንዲህ ሲል ጽፎአል:—

> የጌታ የእግዚአብሔር መንፈስ በእኔ ላይ ነው፤ ለድኾች የምሥራችን እሰብክ ዘንድ እግዚአብሔር ቀብቶኛልና፤ ልባቸው የተሰበረውን እጠግን ዘንድ፣ ለተማረኩትም ነጻነትን፣ ለታሰሩትም መፈታትን እናገር ዘንድ ልኮኛል። የተወደደችውን የእግዚአብሔርን ዓመት፣ አምላካችንም የሚበቀልበትን ቀን እናገር ዘንድ፣ የሚያለቅሱትንም ሁሉ አጽናና ዘንድ እግዚአብሔር ለክብሩ የተከላቸው የጽድቅ ዛፎች እንዲባሉ ለጽዮን አልቃሾች አደርግላቸው ዘንድ፣ በዐመድ ፈንታ አክሊልን፣ በልቅሶም ፋንታ የደስታን ዘይት፣ በሐዘንም መንፈስ ፋንታ የምስጋናን መጐናጸፊያ እሰጣቸው ዘንድ ልኮኛል" (ኢሳይያስ 61+1-3)።

ኢየሱስ ክርስቶስ አገልግሎቱን በናዝሬት ሲጀምር ኢሳይያስ 61+1-3 ያለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ለአይሁድ ጉባኤ አንብቦ ነበር። መጽሐፉን ካነበበ በኋላ፣ "ዛሬ ይህ መጽሐፍ በጆሮአችሁ ተፈጸመ ይላቸው ጀመር" (ሉቃስ 4+21)። ይህ ዐይነቱ ንግግር በሕዝቡ ላይ ታላቅ መደነቅን የፈጠረ ነበር። ይህ ነው እንግዲህ የኢየሱስ ክርስቶስ ተልእኮ። ሙስሊሞች የነቢያት መደምደሚያ የሚሏቸው የነቢዩ መሐመድ ተልእኮና ግብስ ምን ነበር?

## የነቢያት መደምደሚያ በእስልምና ሃይማኖት

መሐመድ የእግዚአብሔር መልእክተኛ (ረሱል) እንደ ሆኑ ሙስሊሞች ያምናሉ። ይህ እርሳቸው ለሰው ልጆች የአላህን መልእክት የሚናገሩ ነቢይ ናቸው ማለት ነው። እስልምና በዓለም ላይ ላሉ ሕዝቦች ሁሉ ነቢያት ተልከውላቸዋል ሲል ያስተምራል። ነገር ግን መልእክተኛ (ረሱል) የሚለውን ቦታ የሚጐናጸፉት እግዚአብሔር መጻሕፍትን እንዲጽፉ መገለጥን የሰጣቸው ሰዎች (ነቢያት) ብቻ ናቸው።

መሐመድ የመጨረሻ መልእክት የሆነውን ቁርአን፣ ከእግዚአብሔር ዘንድ የተቀበሉ የመጨረሻው መልእክተኛ ናቸው። መሐመድ የነቢያት ሁሉ ማሳረጊያ/ማከተሚያ ናቸው፤ ይህም ማለት እርሳቸው በመጨረሻው ዘመን የመጡና የነቢያት ሁሉ መደምደሚያ ናቸው ማለት ነው። ስለ ነቢዩ መሐመድ ቁርአን እንዲህ ይላል:—

> መሐመድ ከወንዶቻችሁ የአንድ ሰው አባት አይደለም፤ ግን የአላህ መልእክተኛና የነቢዮች መደምደሚያ ነው፤ አላህም በነገሩ ሁሉ ዐዋቂ ነው (ሱራ 33+40)።
>
> አንተንም ለሰዎች ሁሉ በመላ አብሳሪና አስፈራሪ አድርገን ቢኾን እንጂ አልላክንህም፤ ግን አብዛኞቹ ሰዎች አያውቁም (ሱራ 34+28)።
>
> እርሱ ያ አጋሪዎቹ ቢጠሉም መልእክተኛውን በመምሪያ (መጽሐፍ)፣ በእውነተኛው ሃይማኖትም (በኢስላም)፣ ከሃይማኖት ሁሉ በላይ ይፋ ሊያደርገው የላከ ነው (ሱራ 61+9 በቅንፍ ያለውን ይጨምራል)።

መሐመድ የመጨረሻ ነቢይ ሲሆኑ፣ የቀድሞ ነቢያቶች ያስተማሩትን ትምህርት ለማጽናትና ለማብራራት የተላኩ የእግዚአብሔር መልእክተኛ



ናቸው። ሙስሊሞች፣ ቀደምት ነቢያት የመጨረሻ ነቢይ ስለሆኑት ስለመሐመድ ተልእኮ እንደ ተነበዩ ጠንካራ እምነት አላቸው። ከዚህም የተነሣ አንዳንድ ሙስሊም ምሁራን፣ ስለ ነቢዩ መሐመድ መምጣት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ትንቢት ተነግሮ እንደ ሆነ በሚል፣ መጽሐፍ ቅዱስን ማጥናት ጀምረዋል።

## መጽሐፍ ቅዱስና መሐመድ

ሙስሊሞች ስለ መሐመድ መምጣት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ትንቢት ተነግሮአል የሚለውን ግምታዊ ትምህርት እውን ቢሆን በሚል፣ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉት ነቢያትና ኢየሱስ ክርስቶስ የተናገሩዋቸውን ንግግሮች በጥንቃቄ እያጠኑ ነው። በብሉይ ኪዳን ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ የተነገሩ ትንቢቶች ለመሐመድ የተነገሩ ናቸው ሲሉ ይከራከራሉ። ለምሳሌ የሚከተለውን ክፍል እንደ ማስረጃ ያቀርባሉ:—

> እግዚአብሔርም አለኝ:— የተናገሩት መልካም ነው፤ ከወንድሞቻቸው መካከል እንደ አንተ ያለ ነቢይ አስነሣላቸዋለሁ፤ ቃሌንም በአፉ አደርጋለሁ፤ ያዘዝሁትንም ቃል ሁሉ ይነግራቸዋል፤ በስሜም የሚናገረውን ቃሌን የማይሰማውን ሰው እኔ እበቀልለታለሁ (ዘዳግም 18+17-19)።

ሙስሊሞች ይህንን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል፣ ሙሴ ስለ መሐመድ መምጣት የተናገረው ትንቢት ነው ሲሉ በእርግጠኝነት ይገልጻሉ። ሙስሊሞች በተለየ ሁኔታ እንቈቅልሽ የሚሆንባቸው፣ ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ ነቢዩ መሐመድ የተናገረው አንዳችም ትንቢት የለም የሚለው ጕዳይ ነው። ይህ ጕዳይ ለሙስሊሞች እንቈቅልሽ የሆነበት ዐቢይ ምክንያት ቁርአን በሱራ 61+6 እንዲህ ስለሚል ነው:— "የመርየም ልጅ ኢሳም:— የእስራኤል ልጆች ሆይ እኔ ከተውራት በፊት ያለውን የማረጋግጥና ከእኔ በኋላ በሚመጣው መልእክተኛ ስሙ አሕመድ በሆነው የማበሥር ስሆን፣ ወደናንተ (የተላክሁ) የአላህ መልእክተኛ ነኝ ባለ ጊዜ (አስታውስ)፤ በግልጽ ታምራቶች በመጣቸውም ጊዜ ይህ ግልጽ ድግምት ነው አሉ"።

ቁርአን ስለ ነቢዩ መሐመድ መምጣት ኢየሱስ ትንቢት ተናግሮአል ካለ፣ ትንቢቱ በየትኛው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ውስጥ ተጽፎ ይገኛል? ሙስሊም ምሁራን በመደነቅ፣ "ስለ መሐመድ ኢየሱስ የተናገረውን ትንቢት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አግኝተነዋል" ይላሉ።

ሐኒስበርግ በሚገኘው የሙስሊም ማዕከል ይሠራ የነበረ አንድ የሙስሊሞች መሪ (ኢማም)፣ ምስጋና በተሞላበት አንደበት፣ "እግዚአብሔር ይመስገን" ብሎ አምላኩን ካመሰገነ በኋላ፣ "ኢየሱስ ክርስቶስ፣ መሐመድ ሲመጣ ሰዎችን ሁሉ ወደ እውነት ይመራል ሲል ትንቢት ተናግሮአል። ነገር ግን እጅግ በሚያሳዝን ሁኔታ መሐመድ የሚለውን ቃል መንፈስ ቅዱስ በሚለው ቃል በመቀየር ኢየሱስ ስለ መሐመድ የተናገረውን ትንቢት ለውጠውታል" ሲል ተናገረኝ።

ይህ የሙስሊሞቹ መሪ (ኢማም) ንግግር፣ በዓለም ዙሪያ በሚገኙ የሙስሊም የነገረ መለኮት ማዕከሎች ሁሉ የሚሰጥ ትምህርት በመሆኑ፣ አስተያየት ልንሰጥበት ይገባል። በግሪክ ወደ ተጻፈው መጽሐፍ ቅዱስ በመሄድ ሙስሊሞች የሚጠቅሷቸው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ምን እንደሚሉ መመልከት ያሻል። በዮሐንስ 14፥16:26፤ 16፥7 ኢየሱስ አጽናኙ እንደሚመጣ ተናግሮአል። የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባባት ደግሞ፣ አጽናኙ መንፈስ ቅዱስ እንደ ሆነ በግልጽ ያስተምራሉ። የግሪኩ መጽሐፍ ቅዱስ፣ "ፓራክሊቶስ" የሚለው ቃል በአማርኛ ቅጆች ላይ "አጽናኝ" ተብሎ ነው የተተረጎመው። ነገር ግን ሙስሊም ምሁራን፣ ክርስቲያኖች መጽሐፍ ቅዱስን ስለበረዙት እንጂ በመጀመሪያ በዚህ ክፍል ላይ የተነገረው ቃል፣ "ፐሪክሉቶስ" ወይም "የተከበረው" የሚለው ቃል ነበር በማለት ይከራከራሉ[4]። በዐረብኛ መሐመድ የሚለው ቃል፣ "የተከበረ" የሚል ትርጒም አለውና። ስለዚህ ሙስሊሞች ኢየሱስ የተናገረው ስለ መንፈስ ቅዱስ ሳይሆን ስለ መሐመድ ነው በዮች ናቸው።

እኔም ለሙስሊሞቹ መሪ (ኢማም) እንዲህ ስል መልስ ሰጠሁት:— "ሙስሊሞችም ሆንን ክርስቲያኖች እግዚአብሔር ወደ እውነት ሁሉ እንዲመራን እንጸልያለን። የሙስሊሞችም ሆነ የክርስቲያኖች ቅዱሳት መጻሕፍት ሰዎች ቅዱሳት መጻሕፍትን ቅንጣት ታህል እንዳይቀይሩ ወይም እንዳያበላሹ ያስጠነቅቃሉ። ዛሬ አምስት ሺህ የሚሆኑ ጥንታዊ የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ቅጆች በእጃችን አሉ። እነዚህ ጥንታዊ ቅጆች ሁሉ "አጽናኙ" ይመጣል እንጂ፣ "የተከበረው" ይመጣል አይሉም። ይልቁንስ አሁን በዐጸደ ሥጋ ያለን እኛ የሃይማኖት ሰዎች፣ መጽሐፉ የማይለውን እያልን መጽሐፉን እንበርዘው"።

[4] Abdullah Yusuf Ali, *The Holy Qur'an: Text, Translation and Commentary* (Beirut: Dar Al Arabia, 1958), 1540, note 54438.



"በእነዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች፣ ኢየሱስ መንፈስ ቅዱስን እንደሚልክ ተስፋ ሰጥቶ ነበር። ስለመንፈስ ቅዱስ የሚናገሩትን ምንባባት፣ ስለ ነቢይ ይናገራሉ ብሎ መከራከር ጥበብ ያለበት አካሄድ አይደለም[5]። እግዚአብሔርንም ሆነ እውነትን ማወቅ የምንችለው፣ በመንፈስ ቅድስ ዕገዛ ብቻ ነውና"።

## መሐመድ የሙስሊሞች አብነት

እንደ ቁርአን ትምህርት፣ በእግዚአብሔርና በመልእክተኛው ማመን ከቶውኑ የማይነጣጠሉ ነገሮች ናቸው። በመጽሐፍ ቅዱስ ግን፣ በእግዚአብሔርና በእግዚአብሔር በመልእክተኛ መካከል እንዲህ ዐይነት ምስስል ፈጽሞ የለም። ለምሳሌ ለእስራኤላውያን የእምነታቸው መሠረት የሆነው ሐሳብ በዘዳግም 6፥4 ላይ እንዲህ ይላል:— "እስራኤል ሆይ ስማ አምላካችን እግዚአብሔር አንድ እግዚአብሔር ነው" እንጂ፣ በክፍሉ ነቢያት አልተጠቀሱም። በመጽሐፍ ቅዱስ ነቢያት ከእግዚአብሔር ፍርድ በታች ናቸው። ሙሴ እንኳ በሰዎች ፊት እግዚአብሔርን ስላላከበረ ወደ ተስፋይቱ ምድር እንዳይገባ እግዚአብሔር ቀጥቶታል (ዘኍልቍ 27፥12-17)።

በእስልምና እምነት ውስጥ የሚታየው በእግዚአብሔርና በነቢዩ መሐመድ መካከል ያለው ዐይነት የጠበቀ ጥምረት፣ መጽሐፍ ቅዱስ በእግዚአብሔርና በነቢያቱ መካከል አለ የሚል ትምህርት አያስተምረንም። ሌሎች ልዩነቶችም አሉ። ለምሳሌ መሐመድ ለሙስሊሞች ኑሮ እንከን የሌላቸው ተምሳሌት ናቸው። መጽሐፍ ቅዱስ ግን ነቢያት ለአማኞች እንከን የሌላቸው ተምሳሌት ናቸው አይለንም። በመጽሐፍ ቅዱስ የብዙ ነቢያት ዝርዝር ሕይወት በውል የማይታወቅ ሲሆን፣ በተወሰነ መጠንም እንኳ ቢሆን ሕይወታቸውና አኗኗራቸው የሚታወቀው የእግዚአብሔር ሰዎች፣ ሰው ስለሆኑ እንደማንኛውም ሰብአዊ ፍጡር ድካምም ሆነ ኀጢአት ነበረባቸው።

ለምሳሌ በብሉይ ኪዳን፣ ሙሴ የእግዚአብሔርን ቃል ባለመጠበቁ ወደ ተስፋይቱ ምድር አልገባም። ነቢዩ ዮናስ ለነነዌ ሰዎች የንስሓን መልእክት

[5] በሦስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን፣ ማኒ በመባል የሚታወቅ የፋርስ (የኢራን) ተወላጅ፣ ማንቼይዝም በመባል የሚታወቅ መናፍቃዊ እንቅስቃሴ ጀምሮ ነበር። ይህ ሐሰተኛ መምህር፣ "ኢየሱስ ይመጣላችኋል ያለው መንፈስ ቅዱስ እኔ ነኝ" ይል ነበር። ቤተ ክርስቲያን ይህን መናፍቃዊ እንቅስቃሴ በአንድ ድምፅ ኰንናዋለች። መጽሐፍ ቅዱስ ስለ መንፈስ ቅዱስ የሚናገረውን ትንቢት ስለ ነቢይ የሚናገር ነው የሚለው ይህ ዐይነቱ ትምህርት፣ መሐመድ ከኖረበት ከብዙ መቶ ዓመት በኋላ የተጀመረ መናፍቃዊ ንቅናቄ ነው።

እንዲሰብክ በተላከ ጊዜ፣ ላለመታዘዝ ከእግዚአብሔር ፊት ሸሸ:: በሐዲስ ኪዳንም በጳውሎስና በባርናባስ መካከል ግጭት ነበር:: ኢየሱስ በተያዘ ጊዜ ጴጥሮስም ሆነ ሌሎች ሐዋርያት ወደ ኋላ ሸሽተዋል:: ነገር ግን በእስልምና ነቢዩ መሐመድ ለሙስሊሞች እውነተኛ ምሳሌ እንደ ሆኑ ይታመናል::

መሐመድ በእስልምና እምነት የመጀመሪያው ሙስሊም ናቸው:: ስለዚህ የእርሳቸው የሕይወት ዘይቤ ለሌሎች ሙስሊሞች ምሳሌ ስለሆነ፣ ሙስሊም ሁሉ ሊከተለው ይገባል:: ይህን ጉዳይ በተመለከተ ቁርአን ስለነቢዩ መሐመድ እንዲህ ይላል:—

> እኔ ጌታዬ ወደ ቀጥተኛው መንገድ ትክክለኛን ሃይማኖት ወደ እውነት አዘንባይ ሲሆን፣ የአብርሃምን መንገድ መራኝ፤ እርሱም ከአጋሪዎቹ አልነበረም በል:: ስግደቴ መገዛቴም ሕይወቴም ሞቴም ለዓለማት ጌታ ለአላህ ነው በል:: ለርሱ ተጋሪ የለውም፤ በዚህም (በማጥራት) ታዘዝሁ፤ እኔም የሙስሊሞች መጀመሪያ ነኝ (በል) (ሱራ 6+161-163 በቅንፍ ያለውን ይጨምራል)::

በተጨማሪም መሐመድ እንዳይሳሳቱ በእግዚአብሔር ይጠበቁ እንደ ነበር ቁርአን በዚህ መልክ ያስተምራል:—

> ነቢያችሁ (መሐመድ) አልተሳሳተም፤ አልጠመመምም:: ከልብ ወለድም አይናገርም:: እርሱ (ንግግሩ) የሚወረድ ራእይ እንጅ ሌላ አይደለም:: ኀይሎቹ ብርቱው (መልአክ) አስተማረው. . .ከዚያም ቀረበ፤ ወረደም:: (ከርሱ) የሁለት ደጋኖች ጫፍ ያህል ወይም (ከዚህ) ይበልጥ የቀረበ ሆነም:: ወደ ባሪያውም (አላህ) ያወረደውን አወረደ:: (ነቢዩም በዐይኑ) ያየውን ልቡ አልዋሸም (ሱራ 53+2-5: 8-11 በቅንፍ ያለውን ይጨምራል)::

እስልምና ከተጀመረ ከሁለት መቶ ዓመታት በኋላ፣ ሙስሊም የነገረ መለኮት መምህራን፣ መሐመድ የአላህን መልእክት ከመቀበል ባለፈ በሚሠሯቸው ሥራዎች በፍጹም አልተሳሳቱም ይሉ ነበር:: የመሐመድ ሕይወት ለሌሎች ሙስሊሞች የሕይወታቸው መመሪያ ነው[6]:: መሐመድ ከኀጢአት ነጻ የሆነ ሕይወት (ኢስማ) ኖረዋል፤ ማንኛውም ሰው እንደ አላህ ፈቃድ እንዲኖር

[6] H. A. R. Gibb, *Mohammedanism* (New York : Oxford University Press, 1969), 92, 98.



የመሐመድ የኑሮ ዘይቤ እውነተኛና ፍጹም ምሳሌ ስለሆነ በዚያ መሠረት መኖር አለበት[7]::

ቀስ በቀስ መሐመድ ምንም ዐይነት ኀጢአት አልሠሩም የሚለው አስተምህሮ በሰፊው መሠራጨት ጀመረ:: ሙስሊሞች፣ ቁርአን ፍጹም ተአምር ከሆነ መልእክቱን የተቀበሉት ነቢይ ኀጢአት የሌለባቸው መሆን አለባቸው ይላሉ[8]:: ይህ አስተምህሮ በካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ማርያም ኀጢአት የለባትም ከሚለው አመለካከት ጋር ይመሳሰላል:: የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን የነገረ መለኮት መምህራን፣ ክርስቶስ ኀጢአት አልባ እስከ ሆነ ድረስ ድንግል ማርያምም ኀጢአት ሊኖርባት በፍጹም አይችልም ሲሉ ይከራከራሉ[9]::

ምንም እንኳ ሙስሊሞች ነቢዩ መሐመድ ኀጢአት ሠርተው አያውቁም የሚል አቋም ቢኖራቸውም፣ ቁርአን ከዚህ አስተሳሰብ ጋር የሚቃረኑ ትምህርቶችን ያስተምራል:: ለምሳሌ ሱራ 80+1-10 ባለው ክፍል፣ የሕይወትን መመሪያ በመፈለግ አንድ ዐይነ ስውር ሰው የእርሳቸውን ዕገዛ በመሻት እርሳቸው ዘንድ በመምጣቱ፣ ፊታቸውን አጨፍግገው ከእርሱ ዞር በማለታቸው እግዚአብሔር እንደ ገሠጻቸው ይናገራል:: ነቢዩ መሐመድ ለሠሩት ኀጢአት ከእግዚአብሔር ዘንድ ምሕረትን እንዲጠይቁ ቁርአን ሲያዛቸው እንመለከታለን (ሱራ 47+19፤ 48+2):: ይሁንና እስልምና መሐመድን ያለ ልክ ከፍ ከፍ አድርጓአቸዋል:: ቁርአን እግዚአብሔር ለመሐመድ "አንተም በታላቅ ጠባይ ላይ ነህ" (ሱራ 68+4) ሲል ተናግሯቸዋል:: በሌላ ስፍራም ቁርአን ስለ ነቢዩ መሐመድ፣ "ለናንተ አላህንና የመጨረሻውን ቀን የሚከጅል ለሆነ ሰው አላህንም በብዙ ለሚያወሳ በአላህ መልእክተኛ መልካም መከተል አላችሁ" (ሱራ 33+21) ይላል:: በተጨማሪም ቁርአን መሐመድን መቀበል አላህን እንደመቀበል ነው ይላል[10]::

> እኛ መስካሪ አብሳሪና አስፈራሪም አድርገን በእርግጥ ላክንህ:: በአላህ ልታምኑ በመልእክተኛውም (ልታምኑ) ልትረዱትም ልታከብሩትም (አላህን) በጧትና

[7] Andrew Rippin, *Muslims: Their Religious Beliefs and Practices* (New York: Rutledge, 2001), 50.

[8] ዝኒ ከማሁ::

[9] በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የሚገኙ አንዳንድ ምሁራን፣ ይህ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያንን ትምህርት ትክክል ነው የሚል አቋም አላቸው::

[10] Abdullah Yusuf Ali, *The Holy Qur'an: Text, Translation and Commentary* (Beirut: Dar Al Arabia, 1958), 1393. note 4877.

ከቀትር በኋላ ሊታወድሱትም (ላክነው):: እነዚያ ቃል ኪዳን የሚጋቡህ ቃል ኪዳን የሚጋቡት አላህን ብቻ ነው፤ የአላህ እጅ (ኀይሉ) ከእጆቻቸው በላይ ነው፤ ያፈረሰም ሰው የሚያፈርሰው በነፍሱ ላይ ብቻ ነው፤ በርሱ ላይ አላህን ቃል ኪዳን የተጋባበትን የሞላም ሰው ታላቅ ምንዳን በእርግጥ ይሰጠዋል (ሱራ 48፥8-10 በቅንፍ ያለውን ይጨምራል)::

ሙስሊሞች የመሐመድን ደረጃ በጣም ከፍ የሚያደርጉት የመሐመድን የኑሮ ዘይቤ ለመከተል ስለሚፈልጉ ነው:: ሱፊ ሙስሊሞች የመሐመድን ደረጃ ከሌሎች ሙስሊሞች ይልቅ ያተልቁታል:: ክርስቲያኖች ለመሲሑ የሚሰጡትን የጌትነት ደረጃ፣ ሱፊ ሙስሊሞች ደግሞ ለነቢዩ መሐመድ ይሰጣሉ:: እንደ ጎርጎሮሳውያኑ የዘመን አቈጣጠር ከ1876 ዓ.ም—1938 ዓ.ም የኖረው መሐመድ ኢቅባል የተባለ ሰው፣ ስለ መሐመድ የጻፈው ውዳሴ በእስልምና ጽሑፎች ውስጥ እንደ ምሳሌ ይጠቀሳል:: መሐመድ ኢቅባል ከጻፋቸው ውዳሴዎች ውስጥ ቀጥሎ ያለው ግጥም አንዱ ነው:—

> በዓለም ውስጥ ያሉ ማሕፀኖች ሁሉ መሐመድን የሚመስል አይፀንሱም፤
> እንደበቴ በመሐመድ የፍቅር ዝማሬ ሞልቶአል::
> መቶ ቃላት ልቤን በኀይል ይደልቃሉ፤
> ኸረ ለመሆኑ፣ ለእርሱ የሚመጥነውን ውዳሴ እንዴት አድርጌ ልገልጽ እችላለሁ?[11]

የሙስሊሙ ማኅበረሰብ የመሐመድን የሕይወት ዘይቤ ለመከተል ካለው ፍላጐት የተነሣ፣ ስለ መሐመድ ማንነት አዎንታዊ የሆነ አመለካከት አዳብሮአል:: ነቢዩ መሐመድ ምን ዐይነት ሰው ነበሩ? ምን ዐይነትስ ተክለ ሰውነት ነበራቸው? ከእርሳቸው በኋላ ያለው ትውልድ ስለነቢዩ መሐመድ የሚነገሩ ታሪኮች ጥቃቅን ዝርዝሮችን በመጨመር እያበራከታቸው መጥቶአል:: የመሐመድ ተከታዮች፣ መሐመድ እጅግ ዐይነ ግቡ የሆነ ተክለ ሰውነት እንደ ነበራቸው ብቻ ሳይሆን፣ ውበታቸውንና ደም ግባታቸውን ለመግለጽ በተደረገው ሙከራ ላይ፣ አስደናቂ የሆኑና "በርግጥ አስፈላጊ ጉዳይ ናቸውን?" ብለን እስክንጠይቅ ድረስ የሚያደርሱ ጥቃቅን ዘገባዎች ቀርበዋል፤ ለምሳሌ:—

[11] Kenneth Cragg, *Muhammad and the Christian* (Maryknoll, N.Y.: Orbis Books, 1984), 75.



> የመሐመድ ጠጕር ቀጭን ወይም አጭር ወይም የሱፍ መልክ አልነበረውም:: ጠጕራቸው ትከሻቸው ላይ የተንዘላፈ ነው:: ጠጕራቸው በአራት ቦታ የተከፈለ ነበር:: ጆሮአቸው በሁለቱ ጉንጉኖች መካከል ደምቀው ይታያሉ:: በጠጕራቸው መካከል ያሉ ሽበቶች ቍጥራቸው ከዐሥራ ሰባት አይበልጥም ነበር:: ዐይናቸው ዛጐላማ እንዲሁም ጥቍር ነበር፤ አፍንጫቸው ሰልካካ፣ ደረታቸውም ሰፊ ነበር[12]::

ሙስሊሞች ሁሉ መሐመድን ያከብራሉ:: ሱፊ ሙስሊሞች ግን ከልክ በላይ የሆነ እንዲሁም ወደ አምልኮ የቀረበ ክበሬታ አላቿው:: ከቀድሞዎቹ የሱፊ ሙስሊሞ ምሁራን ውስጥ ኢብን አል-ዐራቢ የተሰኘው ሰው፣ መሐመድን "ለተከታዮቹ ብርሃን፣ በተፈጥሮው የእግዚአብሔር ፍጹም ምስያ ያለበት፣ መለኮታዊ ዕውቀት የነበረው፣ ፍጥረታት ሁሉ የተፈጠሩበት ቀደምት ብርሃን ነው"[13] ሲል ጽፎአል:: የኢብን አል-ዐረቢ አስተምህሮ፣ መጽሐፍ ቅዱስ ቃል የተባለው ኢየሱስ ሥጋ በመሆን (በምስጢረ ሥጋዌ ወይም ትስብእት በመሆን) ተገለጠ ከሚለው አስተምህሮ ጋር ይቀራረባል:: ኦርቶዶክስ ሙስሊሞች ይህንን አስተምህሮ የሚቃወሙ ቢሆንም፣ የተለያዩ የሱፊ ሙስሊም ቡድኖች ይህንን እምነት በተጠናከረ ሁኔታ ያስተምራሉ::

## ሱና

"ሱና" ማለት የመሐመድ የኑሮ ዘይቤ ማለት ነው:: የመሐመድ የኑሮ ዘይቤ ምን ይመስል እንደ ነበር መማር የምንችለው፣ ከቁርአን ሳይሆን ከሐዲስ ነው:: ሱና ነቢዩ መሐመድ ለተከታዮቻቸው መመሪያ ይሆን ዘንድ ትተውላቸው ያለፉት የሕይወት ዘይቤ ነው::

የነቢዩ የሱና መመሪያ ግራ የሚያጋቡና ትርጕማቸው እምብዛም የማይጨበጥ ትምህርቶችን የያዘ ነው:: ለምሳሌ ከነቢዩ መሐመድ ሚስቶች ውስጥ አይሻ ስለመሐመድ እንዲህ ትናገራለች:— "ማንኛውንም ሥራ ሲሠሩ በቀኝ እጃቸው መጠቀም ይወዱ ነበር፤ ከእነዚህም ውስጥ ጫማቸውን ሲጫሙ፣ ጠጕራቸውን

[12] From Al-Ghazali, *Ihya' 'Ulum al-Din,* Vol. 2 (Cairo: al-Maktabe al-Tijara al-Kubra, 1965), 381, quoted in Kees Wagtendonk, "Images in Islam, Discussion of a Paradox," *in Effigies Dei: Essays on the History of Religion,* edited by Dirk van der Plas (Leiden: E. J. Brill, 1987), 123.
[13] J. S. Trimingham, The Sufi Orders in Islam (Oxford: Clarendon Press, 1971), 161.

ሲያበጥሩ እንዲሁም ከሰላት በፊት በሚካሄደው መተጣጠብ ጊዜ ሁሉ ከቀኝ ይጀምሩ ነበር"[14]:: አብዛኛው ሙስሊም ከዚህ ንግግር የተነሣ በቀኝ ጀምሮ በግራ መጨረስ ይወዷል::

የሙስሊሙ ማኅበረሰብ ባህል፣ በነቢዩ መሐመድ የአኗኗር ዘይቤ የተቃኘ ነው:: ማንኛውም ሙስሊም በአንድም ሆነ በሌላ መንገድ የነቢዩን የኑሮ ዘይቤ ባህሉ አድርጉአል:: ይህ የሆነበት ምክንያት፣ ሙስሊሞች የነቢዩ መሐመድን ፈለግ መከተል የሕይወታቸው ቀዳማይ ዐላማ ስለሆነ ነው (ምዕራፍ 12 ላይ ስለ ሱና በሰፊው እንመለከታለን)::

## ኢየሱስ በእስልምና እምነት

ኢየሱስ በሙስሊሞች ዘንድ የተከበረና የተወደደ ነቢይ ነው:: ከረጅም ዓመት በፊት ሙስሊሞችና ክርስቲያኖች በመስጊድ ተሰብስበን እየተወያየን ሳለን፣ በውይይታችን መኻል የኢየሱስ ክርስቶስ ስም ድንገት ሲነሣ፣ የሙስሊሞቹ መሪ ማልቀስ ጀመረ:: የሰውየው ሁኔታ ውይይታችንን እንድናቋርጥ የግድ ስላለን፣ የግለሰቡን ገጽ በጕጕት መመልከት ጀመርን:: ግለሰቡም አፍንጫውን እያጸዳና ዕንባውን እየጠረገ፣ "የኢየሱስ ክርስቶስ ስም ሲጠራ፣ ከደስታዬና ለእርሱ ካለኝ አክብሮት የተነሣ ዕንባ ቀደመኝ:: ኢየሱስን እጅግ በጣም እወደዋለሁ"፤ በመቀጠልም "ኢየሱስ የእግዚአብሔር መልእክተኛ ነው፤ ነገር ግን የእግዚአብሔር ልጅ አይደለም" አለ::

ታሪፍ ሐሊዲ የተባለ ጸሓፊ፣ "ዘ ሙዝሊም ጂሰስ" (የሙስሊሙ ኢየሱስ) በሚለው መጽሐፉ ከስምንተኛው እስከ ዐሥራ ስምንተኛው ክፍለ ዘመን ባለው ጊዜ ውስጥ ሙስሊሞች ለኢየሱስ ክርስቶስ የነበራቸውን አክብሮትና ፍቅር ለመዳሰስ ሞክሮአል[15]:: ታሪፍ ሐሊዲ ስለ ኢየሱስ የጻፈው ጽሑፍ፣ ቁርአን ስለ ኢየሱስ በሚያስተምረው ትምህርት የተቃኘ ነው:: በእርሱ አገላለጽ ኢየሱስ ሙስሊማዊ ነቢይ ነው::

---

[14] Cragg, *Muhammad and the Christian*, 70

[15] Tarif Khalidi, *The Muslim Jesus* (Cambridge, Mass.: Harvard University Press, 2001).



አንዳንድ የእስልምና ቡድኖች፣ ኢየሱስ በመጨረሻው ዘመን ወደ ምድር ዳግም በመምጣት ሰዎችን ለመጨረሻው ፍርድ ያዘጋጃል ብለው ያምናሉ[16]:: የዚህ አመለካከት ምንጩ፣ በሱራ 43፥61 ላይ የመጨረሻው ዘመን ምልክት የኢየሱስ ዳግም ምጽአት ነው የሚለው የቁርአን አስተምህሮ ነው::

ስለኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ምጽአት ያለው ሌላኛው አመለካከት፣ ኢየሱስ ከሌሎች ነቢያት ጋር በመሆን ለእግዚአብሔር ንጹሕ አምልኮን ለማቅረብ እንዲሁም በጽድቅ ለመኖር ይመጣል የሚል ነው:: ይህ ኢየሱስ ለሙስሊም መናንያን ጠባቂ ቅዱስ ነው[17]:: ኢየሱስ በሱፊ ሙስሊሞች ዘንድ የተከበረና የተመሰገነ ቢሆንም፣ የኢየሱስን የሕይወት ዘይቤ በመከተሉ በኩል ወይም ይህን ጒዳይ ይተገብሩታል የሚለውን ጥያቄ በእርግጠኛነት መመለስ ያስቸግራል:: ኢየሱስን በየበረሃው በሚገኙ ዋሻዎች የሚከተሉት መነኩሳት፣ ከተከተሉት ይበቃል የተባለ ይመስላል::

ምንም እንኳ ሙስሊሞች በየዘመናቱ ኢየሱስን እናከብረዋለን ቢሉም፣ ስለ ኢየሱስ ያላቸው አመለካከት ቤተ ክርስቲያንም ሆነች ወንጌላት ስለ ኢየሱስ የሚያስተምሩት አስተምህሮ ለዘመናት ሳይጣጣሙ ኖረዋል:: ታሪፍ ካሊዲ ስለ ሙስሊሙ ኢየሱስ እንዲህ የሚል አስተያየት ሰጥቶአል:—

> ይህ ኢየሱስ የተራራው ስብከት ወይም ምሳሌያዊ ንግግሮች ወይም ስለ ሕግና ስለመንፈስ ወይም ስለመስቀል አላስተማረም:: በዚህ ፈንታ ኢየሱስ ለእናቱ ታማኝና ታዛዥ ነበር፤ የቀድሞዎቹን ነቢያት ትምህርት በሚያጠናክር መልኩ የአላህን አንድነት ሰብኮአል::. . ትክክለኛው ኢየሱስ ይህ ነው:: ክርስቶስን ከተዛባው የሐዋርያቱ አመለካከት ነጻ አድርገን ስናየው፣ ይህ ኢየሱስ እንደ ነቢይ ለፈጣሪው ታዛዥ እንደ ነበረ እንረዳለን፤ ትክክለኛው ኢየሱስ በዚህ መልኩ ሊቀርብ ይገባዋል እንጂ፣ ክርስቶስ የእግዚአብሔር መገለጥ ነው፤ ሞቶአል እንዲሁም አዳኝ ነው ማለት አግባብ አይደለም[18]::

የቁርአኑ ኢየሱስ፣ "የራሱን ማንነት በተመለከተ እውነታውን ለመግለጽ ባደረገው ሂደት፣ ቁርአናዊ ውጥረቶች እንዲፈጠሩ ምክንያት ሆኖአል"[19]:: ይህ ውጥረት በልደቱ ጊዜ ኢየሱስ በተአምራዊ ሁኔታ በመናገሩ ይጀምራል:: በሱራ

---

[16] ዝኒ ከማሁ፤ 24-26::

[17] ዝኒ ከማሁ፤ 34::

[18] ዝኒ ከማሁ፤ 15::

[19] ዝኒ ከማሁ::

19+30 ላይ ኢየሱስ ስለራሱ እንዲህ ብሏል:— "(ሕፃኑም) አለ:— እኔ የአላህ ባሪያ ነኝ፤ መጽሐፍን ሰጥቶኛል ነቢይም አድርጎኛል"። ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ አወላለድ በእስልምና ኢየሱስና በወንጌላት ውስጥ ባለው ኢየሱስ መካከል ላለው ክርክር ቁርአን አስታራቂ የሆነ "እውነት" እንዳለው ይታመናል።

> ይህ የመርያም ልጅ ኢሳ ነው፤ ያ በርሱ የሚጠራጠሩበት እውነተኛ ቃል ነው። ለአላህ ልጅን መያዝ አይገባውም፤ (ከጉድለት ሁሉ) ጠራ፤ ነገርን በሻ ጊዜ ለርሱ የሚለው ኹን ነው ወዲያውም ይሆናል (ሱራ 19+34-35 በቅንፍ ያለውን ይጨምራል)።

ቁርአን ሐሰተኞች ስለኢየሱስ የሚያስተምሩትን የሐሰት አስተምህሮ ለማጥራት የተላከ መልእክት እንደ ሆነ ይታመናል። ሙስሊሞችም ቁርአን ስለ ኢየሱስ ትክክለኛውን አስተምህሮ ይሰጣል የሚል እምነት አላቸው (ሱራ 3+55)።

ቁርአን ለኢየሱስ የሰጠው ስም በእስልምናና በወንጌል ውስጥ ዐቢይ ልዩነቶች እንዳሉ ፍንጭ የሚሰጥ ነው። በቁርአን ኢየሱስ "ኢሳ" ተብሎ ይጠራል። በመጽሐፍ ቅዱስ በክርስቶስ ልደት ዋዜማ መልአኩ የሕፃኑ ስም "የሹዋ" ተብሎ ይጠራል ሲል ተናግሮ ነበር። ወደ ዐረብኛ ሲተረጐም "ያሱአ" ሲሆን፣ በግሪኩ ደግሞ "ኢየሱስ" ነው። በዕብራይስጥ ቋንቋ "የሹዋ" ማለት "እግዚአብሔር ያድናል" ማለት ነው። በቁርአን በተጻፈው "ኢሳ" በሚለው የኢየሱስ ስም ውስጥ "እግዚአብሔር ያድናል" የሚለው ትርጉም የለም። ኢየሱስ ነቢይ ብቻ ነውና[20]።

አንዳንድ ሙስሊሞች በቁርአን ውስጥ ስለኢየሱስ ክርስቶስ ተአምራዊና ልዩ ማንነት የተዘረዘሩት አስተምህሮዎች እንቈቅልሽ ይሆኑባቸዋል። ከዚህ ቀጥሎ በቁርአን ውስጥ ስለኢሳ/ኢየሱስ ማንነት እንዲሁም ስለሠራቸው ሥራዎች የተጻፉትን ምንባባት ከቁርአን በአጭር በአጭሩ በመጥቀስ ለማቅረብ ልሞክር።

መሲሕ፣ መልካም የምሥራች ነው (ሱራ 3+45)፤ ወንጌልን አብሣሪ ነው (ሱራ 5+49፤ 19+30)፤ ለማርያም በመልአኩ አማካይነት ስለ ልደቱ ተነግሮለታል (ሱራ 19+16-20)፤ ከእግዚአብሔር ዘንድ የሆነ ምልክት ነው (ሱራ 19+20)፤ ከድንግል የተወለደ (ሱራ 19+16-35)፤ የእግዚአብሔር ቃል ነው (ሱራ 4+171)፤ የእግዚአብሔር መንፈስ ነው (ሱራ 4+171)፤ የእግዚአብሔር ልጅ አይደለም (ሱራ 19+34-35፤ 9+30)፤ የእግዚአብሔር ነቢይና መልእክተኛ ብቻ ነው (ሱራ 4+171)፣ ለእግዚአብሔር ታዛዥ (ሱራ 19+30)፣ ተአምር አድራጊ (ገባሬ መንክራት) (ሱራ 3+49)፤ የቀድሞዎቹን ቅዱሳት መጻሕፍት ያጸና (ሱራ 5+49)፤ ለእስራኤል ልጆች ለተወሰነ ጊዜ የተላከ (ሱራ 3+49-50፤ 13+38)፤ በመስቀል ላይ እንዳይሞት እግዚአብሔር ያስመለጠው (ሱራ 4+157)፣ ሳይሞት ወደ ሰማይ ያረገ (ሱራ 3+55-58)፤ በዘመን መጨረሻ ሰዎችን ለመጨረሻው ፍርድ ለማዘጋጀት የሚመጣ (ሱራ 43+61)፤ ስለመሐመድ መምጣት ትንቢት የተናገረ (ሱራ 61+6)፣ ኀጢአት የሌለበት (ሱራ 19+19) ነው።

ከላይ የተመለከትናቸው የቁርአን ጥቅሶች፣ ቁርአን ለኢየሱስ ያለውን ከፍተኛ ግምትና አክብሮት የሚያሳዩ ናቸው። ይሁንና የቁርአኑ ኢየሱስ ለእስራኤል ሕዝብ ለተወሰነ ጊዜ የተላከ እንጂ፣ ለሰው ልጆች ሁሉና ለየትኛውም ዘመን የተላከ አይደለም።

የክርስቶስ ሥነ ምግባር ለሌሎች አርአያ የሚሆን ሲሆን፣ የተወሰኑ የኅብረተሰብ ክፍሎች በዓለም ውስጥ እንዴት መኖር እንዳለባቸው የሚያሳይ ነው። ክርስቶስ አገልግሎቱ ለዓለም ሁሉ አልነበረም። በአንጻሩ መሐመድ ለዓለም ሕዝብ በሙሉ መጥተዋል[21]። መሲሑ ነቢይ እንጂ፣ "የእግዚአብሔር በእኛ መካከል መገኘት" አይደለም። እግዚአብሔር ክርስቶስ በመስቀል ላይ እንዳይሞት አስመልጦታል፤ በእርሱም ፈንታ ሌላ ሰው ተሰቅሎአል። የሙስሊሞች መጽሐፍ በክርስትና ውስጥ ክርስቶስን በተመለከተ የሚታመኑት እምነቶች ለምሳሌ ትሥጉት (ትሰብእት)፣ ሥርየት እንዲሁም ክርስቶስ በአካለ ሥጋ ከሙታን ተነሥቶአል የሚሉትን አስተምህሮዎች ይቃወማል። ኢየሱስ ክርስቶስ በሙስሊሞች ዘንድ የተከበረ ቢሆንም እንኳ፣ ቁርአን ስለ ኢየሱስ የሚያቀርበው ዘገባ ከወንጌላት ትምህርት ጋር በእያሌው የሚለያይ አንዳንዱም የሚቃረን ነው።

ክርስቶስን በተመለከተ የሚነሡ ተቃውሞዎች የሚያጠነጥኑት በክርስትና ውስጥ ስለ ሥላሴ የሚሰጠውን ትምህርት፣ ሙስሊሞች በተሳሳተ መንገድ በመረዳት ክርስቲያኖች ሦስት አማልክት ያመልካሉ ብለው ስለሚያስቡ ነው። ለሙስሊሞች የሥላሴ አስተምህሮ እግዚአብሔርን ለሦስት ቦታ የሚከፍል

[20] Cragg, *Muhammad and the Christian,* 10.

[21] *Ra'd* (Thunder) 13:38. Ali, *The Holy Qur'an,* footnote 1861.

ይመስላቸዋል:: በተጨማሪም ክርስቲያኖች እግዚአብሔር ማርያምን አግብቶ ልጅ ወለደ ብለው ያምናሉ የሚል የተሳሳተ ግንዛቤ አላቸው::

እንዲሁም ክርስቲያኖች መሲሑ እግዚአብሔር ነው የሚል እምነት እንዳላቸው ከሙስሊሞች አስተምህሮ መረዳት ይቻላል:: በመጨረሻዎቹ ምዕራፎች ስለክርስትና እምነት በሙስሊሞች ዘንድ ስላለው የተሳሳተ ግንዛቤ እንመለከታለን::

በእስልምናና በክርስትና እምነት መካከል ያለው መሠረታዊ ልዩነት ምንጩ ስለ እግዚአብሔር ማንነትና ስለሰው አጠቃላይ ሁኔታ ያለው አስተምህሮ ነው:: እስልምና የእግዚአብሔርን ልዕልናና ታላቅነት የሚነካ ማንኛውንም ዐይነት ትምህርት በአጽንኦት ይቃወማል:: በአንጻሩ ደግሞ፣ ሙስሊሞች የክርስቲያኖች ወንጌል የእግዚአብሔርን ልዕልናና ታላቅነት ያሳንሳል የሚል እምነት አላቸው:: እግዚአብሔር በመሲሑ ውስጥ በመስቀል ላይ ሆኖ የጠፋውን ሰው ወደ ራሱ በመጥራት ከራሱ ጋር በማስታረቅ በእርሱ የሚያምኑትን ሰዎች ያድናል ለሚለው ትምህርት ሙስሊሞች ሲመልሱ:— ይህ ዐይነቱ ተግባር ልዑል በሆነው ኀያል አምላክ ላይ እንዴት ሊፈጸም ይችላል? ሲሉ ይጠይቃሉ:: ይህም ሙስሊሞች ግራ እንዲጋቡና ወንጌልንም እንዲቃወሙ አርጉአቸዋል::

## መሐመድና ክርስቲያኖች

ብዙ ጊዜ ሙስሊሞች፣ ክርስቲያኖች ስለመሐመድ ያላቸው አመለካከት ምን እንደሚመስል ለማወቅ ይፈልጋሉ:: ይህ እንደዋዛ መታየት የለበትም:: ቁርአን መሐመድ የመጨረሻው ነቢይ እንደ ሆኑ የማያምን ሰው እግዚአብሔርን የሚወድ ሰው አይደለም ይላል (ሱራ 58+20-22):: ይሁንና ክርስቲያኖች ለሙስሊሞች የቀረቡና ወዳጆች እንደ ሆኑ ቁርአን ያስተምራል (ሱራ 5+81-88)::

በናይሮቢ ከተማ ኢስትሌይ በተባለው ቦታ በአንድ ምግብ ቤት ግብዣ ላይ እንዳለን፣ የሙስሊሞች መሪ፣ መሐመድ የእግዚአብሔር መልእክተኛ ናቸውን? ሲል ጠየቀን:: እኔም፣ "እግዚአብሔር ለአዳምና ሔዋን ከሴቲቱ የሚወለደው ልጅ ሰኩናው በጠላት ይቀጠቀጣል፤ ነገር ግን በመጨረሻ በክፉና በሞት ላይ ድል ይነሣል:: ይህም የተስፋ ቃል ስለ መሲሑ የተነገረ ነው:: ከሁለት ሺህ ዓመት በፊት የተስፋው ቃል ተፈጽሞአል አልሁት"::



ነቢያት ስለዚህ የተስፋ ቃል የተለያየ ገጽታዎች በተደጋጋሚ ሰብከዋል:: መሲሑ ሲመጣ ሰዎችን ከኀጢአታቸው እንደሚያድናቸው አስተምረዋል:: የመሲሑ ተልእኮ የእግዚአብሔር መንግሥት በምድር ሁሉ እንዲሰፋ ነው፤ ለዘላለም ይነግሣል:: መሲሑ ሰላምና እውነት ለሕዝብ ሁሉ ያውጃል:: እርሱ የዓለም ሁሉ መድኀኒት ነው::

ለበርካታ መቶ ዓመታት ነቢያት የተናገሩት የተስፋ ቃል፣ በመሲሑ ሕይወትና አገልግሎት ውስጥ እውን ሆኖአል:: ስለ መሲሑ መጽሐፍ ቅዱስ የሚሰጠው ምስክርነት ግልጽ ነው:: መጽሐፍ ቅዱስ መሲሑ በእግዚአብሔር የተቀባ የዓለም ሁሉ መድኀኒት ነው ይላል::

ነቢዩ መሐመድ ከመሲሑ ሕይወት፣ አገልግሎት አስተምህሮና መጽሐፍ ቅዱስ ስለመሲሑ ከሚሰጠው ምስክርነት ጋር ምን ያህል ይስማማሉ? እኔን ሁል ጊዜ የሚያሳስበኝ ይህ ጥያቄ ነው:: ምንጊዜም ሰዎች መጽሐፍ ቅዱስ ስለ መሲሑ የሚሰጠው ምስክርነት ትክክል ነው ብለን እንድናምን ሲያበረታቱን ውስጤ ሐሴት ያደርጋል::

## ኢየሱስና መሐመድ

ክርስቲያኖች መሐመድና ኢየሱስን ማነጻጸር የለባቸውም፤ ምክንያቱም መሲሑ ከነቢይ ይበልጣልና:: ምንም እንኳ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የምናገኛቸው ነቢያት ትምህርታቸው ከመሐመድ በእጅጉ የተለየ ቢሆንም፣ ነቢዩ መሐመድ መነጻጸር ያለባቸው ሕዝባቸውን ከጣዖት አምልኮ መልሰው በጽድቅ እንዲኖሩ ከሰበኩት ነቢያት ለምሳሌ ከአሞጽና ሆሴዕ ጋር ነው::

እስልምና የነቢይንና የመሲሕን ተግባር ክፉኛ ስለሚያደባልቅ ክርስቲያኖች መሐመድንና ኢየሱስን በሚያነጻጽሩበት ጊዜ ሁሉ በእስልምና አስተምህሮ ግራ ይጋባሉ:: የትኛውም ነቢይ መሲሕ ተብሎ አልተጠራም:: መሲሕ ማለት የተቀባ ማለት ነው:: ይህም ከነቢያት ተግባር ፍጹም የተለየ ነው:: ቀጥሎ ባሉት ተከታታይ ምዕራፎች የመሲሑን የኢየሱስን ተግባራት በጥልቀት እንመለከታለን::

## የኢየሱስ ተግባር ምንድን ነው?

ነቢዩ መሐመድ የመጨረሻ ነቢይ ናቸው ብሎ በሚያምነው በሙስሊም ነገረ መለኮት ውስጥ የመሲሑ ተግባር ምንድን ነው? በእስልምና እምነት አዳም፣ አብርሃምና መሐመድ እንደ ቅደም ተከተላቸው የመጀመሪያ፣ የመካከለኛና የመጨረሻ ነቢያት ናቸው:: አዳም የመጀመሪያ ነቢይ ሲሆን፣ ከእግዚአብሔር

ምሪትን በመቀበል የእስልምናን ሃይማኖት መርሖች በካዕባ ተግባራዊ ያደረገ ሰው ነው:: መካከለኛው ነቢይ አብርሃም ነው:: አብርሃም ከልጁ ከእስማኤል ጋር በመሆን የእስልምናን እምነት በካዕባ መሥርቶአል:: የመጨረሻው ነቢይ ደግሞ መሐመድ ናቸው:: መሐመድም እንደ አዳምና አብርሃም እውነተኛውን የእስልምና ሃይማኖት በካዕባ መሥርተዋል:: ከሙስሊም ነገረ መለኮት ዐላማ አንጻር መሲሑ ወሳኝ ስፍራ የለውም::

መሲሑ በመከራ ውስጥ ጸንተው እግዚአብሔርን እንደ ተከተሉት ነቢያት ለምሳሌ ኖኅ፣ አብርሃም፣ ሙሴና መሐመድ ሁሉ ክብር ይሰጠዋል (ሱራ 42፥13):: ሙስሊሞች የመሲሑን ርኅራኄ ያወድሳሉ:: ይሁን እንጂ በዕለት ተዕለት ኑሮአቸው ውስጥ መሲሑ ኢየሱስ አንዳችም ስፍራ የለውም፤ እንዲያውም ክርስቲያኖች የኢየሱስን ተልእኮ ከፉኛ አዛብተዋል የሚል እምነት አላቸው::

ልብ በሉ፣ አንዳንዶም ክርስቲያኖች እንደ ሙስሊሞች ሁሉ ስለ ኢየሱስ ማንነት ለመረዳት አስቸጋሪ ይሆንባቸዋል:: በዚህ ዐይነት ግራ በተጋባ መልኩም ያቀርቡታል:: የመሲሑ ማንነትና ተልእኮ ሙስሊሞችን ብቻ ሳይሆን፣ ብዙ ክርስቲያኖችንም ግራ የሚያጋባ ጉዳይ ነው:: ስለ ኢየሱስ ማንነት ግራ የሚጋቡት ሙስሊሞች ብቻ ሳይሆኑ፣ በተወሰነ ደረጃም ቢሆን ክርስቲያኖችም ጭምር ናቸው:: የጦርነት ዜና ዓለምን በሚያስጨንቅበት በዚህ ጊዜ ለክርስቲያኖች የክርስቶስ ሚና ምንድን ነው? ከመቼውም ጊዜ በበለጠ የሀብት ክምችት ባለበት ዓለም ውስጥ፣ በየምሽቱ በቢሊዮን የሚቈጠሩ ሰዎች በረሀብ እየተጠበሱ ባሉበት ጊዜ ለክርስቲያኖች ክርስቶስን ማክበር ማለት ምን ማለት ነው? በመቶ ሚሊዮኖች የሚገመቱ የዓለም ሕዝቦች፣ የወንጌልን እውነት ባልሰሙበት ሁኔታ እንደ ክርስቲያን ክርስቶስን መከተል ማለት ትርጕሙ ምንድን ነው?

በእስልምና ነገረ መለኮት አተያይ መሲሑ የነበረውን ተልእኮ ፈጽሞ ዐልፎአል:: መሐመድ ለሰው ዘር በሙሉ እንዲሆን የታቀደውን የመጨረሻ መልእክት ይዘው ተነሥተዋል:: መሲሑ ከእርሱ በኋላ፣ ነቢዩ መሐመድ እንደሚመጡና ዓለም ዐቀፋዊ ተልእኮ እንደሚኖራቸው እንደ ተናገረ ይታሰባል::

## የኢየሱስ እውነታ ሕያውነት

እንደ እውነቱ ከሆነ ግን ኢየሱስ ስፍራውን ለሌላ ነቢይ አላስረከበም:: በጣም በሚያስደንቅና ልታይ ባይነት በሌለበት መንገድ ኢየሱስ ሰዎች እንዲሰሙትና ትኵረት እንዲሰጡት ማድረጉን እንደቀጠለ ነው::



ታሪፍ ካሊዲ የተሰኘው ጸሐፊ ስለመሲሑ እንዲህ ብሎአል:—

"የሆነ ይሁን፤ ኢየሱስ ዛሬም ግዙፍና ጕልሕ ሚና አለው:: በቀላልና ተራ በሆነ መንገድ በእስልምናና በክርስትና ሃይማኖቶች ውስጥ ከፍ ያለ ቦታ አግኝቶአል:: አንደኛው ሃይማኖት ቀዳሚ ሲያደርገው ሌላኛው ተቀብሎታል::. . .ኢየሱስ ከታሪክና ከሃይማኖታዊ ደረጃዎች በላይ የሆነ ባሕርይን አላብሶታል"[22]::

በሳራዬቮ ከብዙ ዓመታት የዘርና የሃይማኖት ጦርነት በኋላ፣ ክርስቲያን ሰርቢያውያንና ቦስኒያውያን ተማሪዎቼን አስከትዬ በፈረሰችው ከተማ ወደሚገኘው "የሙስሊም ተማሪዎች ኅብረት" በመባል ወደሚጠራው ስፍራ ለመጐብኘት ሄደን:: እነዚህ ወጣት ሙስሊም ተማሪዎች ሻይ ጋበዙን:: ከዚያ በኋላ የነበረን ውይይት በጣም ጥሩ ነበር:: ለአራት ሰዓት ያህል ውይይት ካደረግን በኋላ ከተማሪዎቹ መካከል ብዙዎቹ ውይይቱ ሌላም ጊዜ እንዲቀጥል ተስማሙ::

ከተማሪዎቹ ተለይተን ልንሄድ ስንዘጋጅ፣ በውይይቱ ውስጥ ከነበሩት መካከል አንዱ እንዲህ አለ:— "ዛሬ በዚህ ከሰዓት በኋላ በመካከላችን እንግዳ አብሮን አለ፣ ተለይቶን መሄድ የሚወድ አይደለም:: እንግዳው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው:: እርሱም በመካከላችን መገኘት ብቻ ሳይሆን የውይይታችን ማዕከላዊ ስፍራ ይዞ ነበር"::

በሳራዬቮ በዚያች ከሰዓት በኋላ እንደ ነበረው፣ ኢየሱስ ክርስቲያኖችና ሙስሊሞች በሕይወት ዘመናቸው ሁሉ እርሱን እንዲያውቁትና እንዲረዱት ይፈልጋል::

*የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባብ*

ሉቃስ 1፥26-38፤ 4፥14-30

*የቁርአን ምንባብ*

ሱራ 19፥16-36፤ 3321፣ 40፣ 34፥28

---

[22] Khalidi, *The Muslim Jesus*, 45.

## የአስተውሎትና የውይይት ጥያቄዎች

1. ሙስሊሞችና ክርስቲያኖች ኢየሱስ መሲሕ እንደ ሆነ ይስማማሉ:: በሙስሊሞችና በክርስቲያኖች መካከል ስለመሲሑ ማንነት እንዲሁም ሥራ ያለውን ልዩነት ይግለጹ::
2. አንድ ሰው ሙስሊሞች ማንኛውንም ሃይማኖታዊ ተግባር እንዴት እንደሚፈጽሙ መረዳት ይችላል:: ነገር ግን የክርስቲያኖችን መረዳት ያዳግተዋል:: ልዩነቱ ከምን እንደ መጣ ይግለጹ:: (ማቴዎስ 5+48፣ ሱራ 33 +40)::
3. ሙስሊሞች ነቢዩ መሐመድ የመጨረሻ ነቢይ ናቸው ብለው ማመናቸው ምን ዐይነት ትርጒም እንዳለው ይግለጹ (ሱራ 33 +40)?
4. ክርስቲያኖች ኢየሱስ መሲሕ ነው ብለው ማመናቸው ምን ትርጒም ያለው ይመስሎታል (ሉቃስ 4 +14-40)?
5. ኢየሱስ ክርስቶስ በቁርአን ውስጥ ምስጢራዊ ሰው ነው:: ኢየሱስ በሙስሊሙ ማኅበረሰብ (ኡማ) ውስጥ ያለው ስፍራ እጅግ አነስተኛ ነው:: ለብዙ መቶ ዓመታት ቤተ ክርስቲያንም ኢየሱስን አስፈላጊ ወዳልሆነና ከእውነተኛ ሕይወት ተሞክሮ ውጪ በሆነ ሁኔታ ምስጢራዊ ሰው ስታደርገው ቆይታለች:: ስለ ኢየሱስ እውነታ ከመሆኑ ይልቅ ምስጢር ተደርጎ የቀረበበት ምክንያት ምን እንደ ሆነ ይግለጹ::



ምዕራፍ ስድስት

# ቅዱሳት መጻሕፍት

# ቁርአን—መጽሐፍ ቅዱስ

ኢብራሂም መሐመድ፣ "እባክህ መጽሐፍ ቅዱስህን አውሰኝ" ሲል ጠየቀኝ:: እኔም መልካሙ የምሥራች (Good News) የሚባለውንና አረንጓዴ እንዲሁም ጠንካራ ያልሆነ ጥራዝ ያለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ቅጅ አንሥቼ ሰጠሁት:: ኢብራሂምም ሰዎች የመጽሐፉን ማንነት እንዳያውቁ በሚል በቡናማ ወረቀት ለበደው:: መጽሐፉን በአክብሮትና በጥንቃቄ በመያዝ ከቤታችን ሹልክ ብሎ በመውጣት ወደ ቤቱ ሄደ::

በማግሥቱ ማታ ኢብራሂም ያንኑ መጽሐፍ ይዞ ወደ ቤታችን መጣ:: በኢብራሂም ገጽ ላይ ከፍተኛ የሆነ የሐዘን ድባብ በግልጽ ይነበብ ስለነበረ፣ በአያሌው እንዳዘነ ማወቅ አዳጋች አልነበረም:: ቤት በመግባት ወንበር ላይ ከተቀመጠ በኋላ፣ መጽሐፉን ከቦርሳው ውስጥ በማውጣት ጠረጴዛው ላይ አነጠፈው::

"እኔ መቼም መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል መስሎኝ ነበር:: ነገር ግን እንደዚያ ሆኖ አላገኘሁትም:: ሰዎች የክርስቲያኖችን ቅዱሳት መጻሕፍት አበላሽተዋል:: እንዴት ዐይነት አሳዛኝ ጥፋት ነው! መጽሐፍ ቅዱስ የታሪክ መጽሐፍ ከሆነ እንጂ፣ የእግዚአብሔር ቃል ግን አይደለም"::

ኢብራሂም በዚህ ዐይነቱ ታላቅ ሐዘን ውስጥ እያለ፣ ቡናማ መልክ ያለውን ባዶ ቦርሳውን አንከርፍፎ በዚያ ጨለማ ወደ ቤቱ ሂደ:: "ተበላሽቶአል" የተባለው የመጽሐፍ ቅዱስ ቅጅ ምስቅልቅል ባለው ጠረጴዛዬ ላይ ተዘርሮአል::

## ታሪክና መገለጥ

ኢብራሂም ትክክል ነው:: መጽሐፍ ቅዱስ የታሪክ መጽሐፍ ነው:: እስትንፋስ እግዚአብሔር ያለበት እንደ እርሱም ያለ የታሪክ መጽሐፍ የለም:: በእኔ ግምት ኢብራሂም ንባቡን የጀመረው ከዘፍጥረት መጽሐፍ ሲሆን፣ ንባቡን ከጀመረ ከጥቂት አንቀጾች በኋላ ቃየን ወንድሙ አቤልን የገደለበትን በሰው ልጆች ታሪክ ውስጥ የመጀመሪያውን የግድያ ታሪክ አንብቦአል:: ከጥቂት ምዕራፎች በኋላም፣ የኖኅ ልጆች አባታቸው ሰክሮ እንዲሁም ራቁቱን ሆኖ